
የዕውቀት ብልጭታ

ከአቡር ዶ/ር ከበደ ሚካኤል

Scanned with CamScanner

በPDF ያዘጋጀው...



ፎ መጽሐፍ

Bookstore

የቴሌግራም ቻናል

@and_metshaf

Scanned with CamScanner

R 13

የዕውቀት ብልጭታ

ከአበደ ሚካኤል

Scanned with CamScanner

2008 ዓ.ም

አዛዲዞ ኦሊ ባር አጣሊ
የተገዛ

አክፋፋይ ባህሩ መጻሕፍት ቤት
ስታዲየም ይሓ ሲቲ ሴንተር
0911-63-68-15

ሦስተኛ እትም 2007 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም 1999 ዓ.ም
የመጀመሪያ እትም ፲፱፻፺ ዓ.ም

መ ግ ቢ ያ ።

ሴት ፣ ተቀን ፣ አድርጎ ፣ መንፈሱን ፣ ጠንካራ
ሕፃን ፣ ተግቶ ፣ ሲማር ፣ ወዋቂም ፣ ሲሠራ ፣
የዕውቀቱ ፣ ብልጭታ ፣ እየሆነ ፣ ርቆ ፣
ርቆውም ፣ ተስፋፍቶ ፣ በመሆን ፣ ውጋጋን ፣
እንደ ፣ ቀትር ፣ ፀሓይ ፣ የጥበቡ ፣ ብርሃን ፣
ሞቆ ፣ ይደምቅና ፣ ኃይሉ ፣ እየገነነ ፣
ለማለት ፣ ይቻላል ፣ አገር ፣ ሠለጠነ ፣
ዕውቀት ፣ ካልተስፋፋ ፣ ጥበብ ፣ ካልደረጀ ፣
የትምህርቱን ፣ አክሊል ፣ ልጅ ፣ ካልተቀዳጀ ፣
ወዋቂም ፣ ለሥራ ፣ ሕግ ፣ ክላበጀ ፣
የትልቅነትን ደረጃ ፣ ለማግኘት ፣
በሴላ ፣ ዓይነት ፣ መንገድ ፣ መፈለግ ፣ መመኘት
የሕልም ፣ ሩጫ ፣ ነው ፣ በብዙ ፣ መታለል ፣
እመኑኝ ፣ ከንቱ ፣ ነው ፣ ነፋስን ፣ መከተል ።

Scanned with CamScanner

መ ቅ ድ ም ።

ተርበ ፣ ለመጣ ፣ ሰው ፣ በዶ ፣ መሶብ ፣ ቢያቀርቡለት ፣ በውሥጡ ፣ እንጀራና ፣ ወጥ ፣ ካላገኝበት ፣ ሊጠግብ ፣ አይችልም ። እናንተም ፣ በየ ትምህርት ፣ ቤቱ ፣ ያላችሁ ፣ ሕፃናት ፣ እንደዚሁ ፣ መጻሕፍት ፣ ከሌሉ ፣ የትም ህርት ፣ ቤት ፣ ብቻ ፣ ቢከፈትላችሁ ፣ የትምህርቱን ፣ እንጀራ ፣ ልትመ ገቡ ፣ አትችሉም ። ይህንንም ፣ ስላልሁ ፣ በትምህርት ፣ ቤት ፣ ውሥጥ ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ቋንቋ ፣ የተጻፉ ፣ በየዓይነቱ ፣ ትምህርት ፣ የምታገኙ ባቸው ፣ መጻሕፍት ፣ ተሰናድተው ፣ እንደሚቀርቡላችሁ ፣ አውቃለሁ ። ግን ፣ ሕፃን ፣ የባዕድ ፣ ቋንቋ ፣ ተምሮ ፣ በውሥጡ ፣ ያለውን ፣ ምሥ ጢር ፣ ለመረዳት ፣ እስኪችል ፣ ድረስ ፣ ያለበት ፣ ድካም ፣ እኔም ፣ እንደ ፣ እናንተ ፣ ሕፃን ፣ በነበርሁ ፣ ጊዜ ፣ ስለደረሰብኝ ፣ ይህ ፣ ድካም ፣ እንዳታለልላችሁ ፣ ባለኝ ፣ አቅሜ ፣ ስረዳችሁ ፣ በጣም ፣ ደስ ፣ ይለኛል ። በዚህ ፣ መጽሐፍ ፣ ውስጥ ፣ ሁለት ፣ ዋናች ነገሮች ፣ ተከትያለሁ ።

አንደኛው ፣ በተረቲና ፣ በጨዋታ ፣ አነጋገር ፣ ሆኖ ፣ የምታግ ኙት ፣ የሙቀትንና ፣ የብርድን ፣ የመጥፎ ፣ አየርንና ፣ የነፋስን ፣ ባሕርይ ፣ በአጭሩ ፣ የሚያስረዳችሁ ፣ ለጥበብ ፣ (ሲያንስ ፣) ትምህርት ፣ መሰናጃ ፣ የሚሆናችሁ ፣ ንባብ ፣ ነው ። ይህንንም ፣ አብዛኛውን ፣ ያገኘሁት ፣ ቶል ስቶኢ ፣ ከሚባለው ፣ ከትልቁ ፣ የመስከብ ፣ ደራሲ ፣ መጽሐፍ ፣ ውሥጥ ፣ ነው ። እሱም ፣ ትልልቅ ፣ መጻሕፍት ፣ የጻፈ ፣ ዐዋቂ ፣ ሆኖ ፣ ሳለ ፣ ለሕፃናት ፣ የሚጠቅም ፣ ነገር ፣ ላሰናዳ ፣ ብሎ ፣ አስቦ ፣ በመድከሙ ፣ በዓለም ፣ ላይ ፣ ያሉ ፣ በእሱ ፣ መጽሐፍ ፣ የሚማሩ ፣ ብዙ ፣ ሕፃናት ፣ አመሰግነውታልና ፣ እናንተም ፣ አመሰግኑት ። ከእሱ ፣ ያገኘኋቸውን ፣ ሁሉ ፣ እመዘረሻው ፣ ላይ ፣ (ሌ ፣ ቶ ፣) የሚል ፣ ምልክት ፣ አድር ጌባቸዋለሁ ፤ ይህም ፣ ሌዎን ፣ ቶልስቶኢ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ሁለተኛውም ፣ በአለፉት ፣ መጻሕፍቶቼ ፣ የሚያጫውቱና ፣ የሚ ያስቁ ፣ ሆነው ፣ በውሥጣቸው ፣ ትምህርት ፣ ያለው ፣ ምሥጢር ፣ የሚ ገኝባቸው ፣ ተረቶች ፣ በግጥምና ፣ በስድ ፣ ንባብ ፣ እያደረግሁ ፣ አሰናድቼ ላችሁ ፣ ነበር ። በዚህ ፣ በአሁኑ ፣ መጽሐፍ ፣ ውሥጥ ፣ ደግሞ ፣ ከፍ ፣ ከለ ፣ የትምህርት ፣ ደረጃ ፣ ስትደርሱ ፣ በዓለም ፣ ታሪክ ፣ ውሥጥ ፣

ከምታገኙዊቸው ፣ በየዘመኑ ፣ ተፈጥረው ፣ ከነበሩት ፣ ታላላቆች ፣ ሰዎች ፣ ጋር ፣ የሚያስተዋውቋችሁ ፣ ተረቶች ፣ ጽፌላችኋለሁ ። በእነ ዚህም ፣ ተረቶች ፣ ውስጥ ፣ ከምቢገ ፣ ዳምጋን ፣ ጀንጂስካን ፣ የሚባ ሉና ፣ እነሱንም ፣ የመሰሉ ፣ ሰዎች ፣ ታገኛላችሁ ። ወደፊት ፣ በዓለም ፣ ታሪክ ፣ ላይ ፣ እንደምታገኙት ፣ እነዚህ ፣ ሰዎች ፣ በዓለም ፣ ላይ ፣ ትል ልቅ ፣ ሥራ ፣ የሠሩ ፣ ስለሆኑ ፣ ካሁኑ ፣ ጀምሮ ፣ ስማቸውን ፣ ብታው ቋቸውና ፣ ከባሕሪያቸውም ፣ ጥቂት ፣ ነገር ፣ ብታውቁ ፣ ይጠቅማችኋል ።

በጣም ፣ ደግሞ ፣ አደራ ፣ የምላችሁ የውጭ ፣ አገር ፣ ቋንቋ ፣ ከተ ማራችሁ ፣ በኋላ ፣ ስጦታችሁ ፣ በሚያደላበት ፣ ዕውቀት ፣ እየደከማ ችሁበት ፣ በውስጡ ፣ የምታገኙትን ፣ ፍሬ ፣ ነገር ፣ እያጣራችሁ ፣ ወደ ፣ አማርኛ ፣ ቋንቋ ፣ እንድትገለብጡትና ፣ ከናንተ ፣ በኋላ ፣ ለሚ መጡት ፣ ልጆች ፣ አውርሰችሁ ፣ ቋንቋችሁን ፣ እንድታበለጥጉበት ፣ ነው ።

የባዕድ ፣ ቋንቋ ፣ በወንዝ ፣ በምንጭ ፣ ወይም ፣ በጉድጓድ ፣ ውኃ ፣ መመሰሉን ፣ አትርሱ ። ሰው ፣ ውኃ ፣ ወደ ፣ አለበት ፣ ስፍራ ፣ ሲሔድ ፣ በእንሥራ ፣ ወይም ፣ በመቅኝ ፣ አምጥቶ ፣ ለቤተ ፣ ሰቦቹ ፣ ካልሰጠ ፣ ለራሱ ፣ ብቻ ፣ ጠጥቶ ፣ ቢመለስ ፣ ድካሙ ፣ ፍሬ ፣ ሳይ ሰጥ ፣ መካን ፣ ሆኖ ፣ ይቀራል ። የውጭ ፣ አገር ፣ ቋንቋ ፣ ተምሮ ፣ ብዙ ፣ መጻሕፍት ፣ ወደ ፣ አገሩ ፣ ቋንቋ ፣ የሚተረጉም ፣ ሰው ፣ ግን ፣ የወንዙን ፣ ውኃ ፣ በቦይ ፣ መልሶ ፣ ድርቀት ፣ የጎዳ ውን ፣ የአባቱን ፣ ርስት ፣ እያጠጣ ፣ በሚያለማ ፣ ሰው ፣ ይመሰ ላል ። ከሌላው ፣ ቋንቋ ፣ ቀድተው ፣ ያመጡትን ፣ ለአገራቸው ፣ ቋንቋ ፣ ማወልጠኛ ፣ ያደርጉታል ፣ እንጂ ፣ በሰው ፣ ቋንቋ ፣ ብቻ ፣ የሠለጠኑ ፣ ሕዝቦች ፣ አታዟኙም ። የውጭ ፣ አገር ፣ ቋንቋ ፣ ብቻ ውን ፣ ቢስፋፋ ፣ የሚጠቅም ፣ እንዳይመስላችሁ ። ከባዕድ ፣ እየጐረስህ ፣ ወደ ፣ ዘመድህ ፣ ዋጥ ፣ የሚባለውን ፣ ተረት ፣ አስቡ ።

ማ ው ጫ

አርአስት ገጽ
የተማረ ሰው ብልጫ ..... ፲፩
መልካም በቀል ..... ፲፪
የውኃ ታሪክ ..... ፲፪
ሱልጣን ሞሐመድ ..... ፲፫
የውቅያኖስ ባሕር ..... ፲፭
ሁለት ሌቦች ..... ፲፭
ነፋስ ..... ፲፯
አንድ ትርጉጎ ..... ፲፯
ፀሐይና ጨረቃ ..... ፲፰
አንድ ብልህ ዓይነ ስውር ሰው ..... ፲፰
ዲን ሱዊፍት ..... ፳
አንድ ገበሬና አንዲት ዐይጥ ..... ፳፩
ዲዎጋን ..... ፳፪
የዝና ከንቱነት ..... ፳፬
የነፍስ ጠቃሚነት ..... ፳፭
ሶስት መንገደኞች ..... ፳፱
የጦር ሠራዊት ሥርዓት አፈጻጸም ..... ፴
ሙቀትና ቅዝቃዜ ..... ፴፩
አንድ ውለታ ቢስ ድኩላ ..... ፴፪
የአታላይ ሰው ታማኝነት ..... ፴፭
ሻርልከ ..... ፴፰
አንድ ረጅም ሰውና አንድ አጭር ሰው ..... ፴፱
አትክልትና አረም ..... ፵፩
አንድ ጅል ..... ፵፩

Scanned with CamScanner

ሽታና ውሻ ..... ፵፩
ጀንጂስካን ..... ፵፫
የውኃ ጉዞ ..... ፵፬
አቡንና ወንበዴ ..... ፵፮
አንድ ንጉሥና አንድ ሊቅ ..... ፵፯
ጀንጂስካንና ለማዳ አሞራ ..... ፵፰
መጥፎ አየር ..... ፶
አንድ መስፍንና አንድ ፈላስፋ ..... ፶፫
ካምቢዝና ፕሳሜኒት ..... ፶፱
ከሕግ የወጣ ትርፍ ..... ፷፩
ሁሉም የሆነ ነው ..... ፷፪
አባትና ልጅ ..... ፷፬
የቅኝ አገር ወርቅ የሰላም ጠንቅ ..... ፷፭
ትንቢተ ዮናስ ..... ፷፰
ከመጠጥ የሚመጣ ጉዳት ..... ፸፫
የአንድ ሰካራም ታሪክ ..... ፸፯
መታዘዝን ዕወቅ ..... ፯
የካምቢዝ ሞካኔ ..... ፯፪
ብልህ ራሱን ያድናል ..... ፯፮
አንድ አዳኝ ሰውና አንዲት ዋኔ ..... ፯፯
አንድ ሰው አንድ አንበሳና አንድ ጅብ ..... ፯፰
አንድ ዚቀኝ ..... ፰
በግር ጠብታ አገር ተመታ ..... ፰፭
የገንዘብ ፍቅር ..... ፰፰
ዓሣ አጥማጅና ዛጎል ..... ፱፬
ስለ ተግባረ እድ ..... ፱፫
አግኝቶ ያጣ ሰው ..... ፱፱

ጥቁሮችም እንደ ሰው ..... ፻፲
የበረሃ መንገደኛ ..... ፻፲፭
የአዚናራ አስረኛ ..... ፻፲፫
የፀሐይ ባሕሪ ..... ፻፲፯
የልቦና ሥልጣኔ ..... ፻፲፰
የመሬት ሁኔታ ..... ፻፳
የሐር ትል ..... ፻፳፪
ዛሬና ነገ ..... ፻፳፪
ሲ ሲንግ ሺ የምትባለው የቺና አገር ንግሥት ..... ፻፳፬
ሙዚቃ ..... ፻፳፰
የሥራ ጥቅም ..... ፻፳፯
ስለ ጨረቃ ..... ፻፳፰
የሐር ትል በቡክሐራ አገር እንደምን እንደገባ ..... ፻፳፱
ኮከቦች ፕላኔቶችና ጅራታም ኮከቦች ..... ፻፴
ዬ ኪያንግ ..... ፻፴፬
ቡሶል ..... ፻፴፯
ዕብነ አድማስ ..... ፻፴፰
ካሎሪክ ..... ፻፴፰
ቴርሞሜትር ..... ፻፴፱
ሺማ ..... ፻፵
አፄ ቴምድሮስ ..... ፻፵፪
ንጹሕ አካሎችና ቅልቅል አካሎች ..... ፻፵፬
የውኃ ሁኔታ ..... ፻፵፰
የአየር ባሕሪ ..... ፻፵፯
አቶም ..... ፻፵፯
አኒባል ..... ፻፶፬
አስትሮኖሚ ..... ፻፶፬
ያሳብ ጥልቅ አስተያየቶች ..... ፻፷

Scanned with CamScanner

ትምህርት ሳይመገብ ያደገ ሰው ማንኛውም ዓይነት ከፍ ያለ ሙያ ቢኖረው ባለመማሩ ምክንያት ብዙ ጉድለት ይገኝበታል።

❋

የጦር ሠራዊት ዋናው ጉልበቱ ወታደሮቹ ሥርዐት ፈጻሚዎች ሲሆኑ ነው።

❋

ችግርና መከራ ብልሃትንና ድፍረትን ይወልዳሉ።

❋

በሽተኞች ይሞታሉ እንጂ በሽታ አይሞትም፤ ክፋትም ሰውን ሲያጠፋው ይኖራል። ሰዎች ግን ክፋትን ከዓለም ላይ ሊያጠፉት አልቻሉም።

❋

በደስታና በተድላ ላይ በነበረበት ሰዓት ያልመከርኸውን ሰው መከራና ችግር ባገኘው ጊዜ አጽናናው እንጂ ባለፈው ጊዜ በሠራው ስሕተት አትውቀሰው።

❋

አንድ ጊዜ ካመለጠ ዳግም የማይገኘውን ጊዜ የሚባለውን ገንዘብ ሠራተኞች ይሻሙታል፤ ሰነፎች ግን በከንቱ ያባክኑታል።

❋

ልብ ለልብ የተራራቁ ሰዎች በቅን ልቡና ጨዋታ ሲጨዋወቱ አንዱ የተናገረውን አንደኛው በብዙ ዓይነት መጥፎ መንገድ ከመተርጉም ብዛት የሚያቀያይም አሽሙር ያገኝበታል። ቅን መንገድ የሚከተሉ የተግሙኑ ሰዎች ግን የተባረኩ ናቸው።

❋

በደስታ በክብር ይኖር የነበረ አንድ ትልቅ ንጉሥ ከጣቱ የማይለያት አንዲት የምታምር የወርቅ ቀለበት ነበረችው። በቀለበት

Scanned with CamScanner

ዋም ላይ «ሰው ህና አንድ ቀን ትሞታለህ፤ ይህን አትርሳ» የሚል ቃል አጽፎባት ነበር።

*

ልትከለክለው የሚቻልህ ክፉ ሥራ ሲሠራ እየተመለከትህ ዝም ካልህ ዘንድ ከሠሪው ሰው ይልቅ የአንተ አጥፊነት የባሰ መሆኑን ዕወቀው።

*

ቀን ጐድሎብኝ በጠላቶቼ በሮማውያን እጅ የወደቅሁ እንደሆነ ከመማረክ በገዛ እጄ መሞትን እመርጣለሁ ብሎ አኒባል ከጣቱ በማይነጠያት ባንዲት ቀለበት ውስጥ ዕድሜውን ሙሉ መርዝ ይዞ ይኖር ነበር።

*

ጥቂት ሽቱ የፈሰሰበት ቦታ በአፈሩ ላይ እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ መልካም መዓዛ ይገኝበታል። ትልቅ ሙያ ያለው ሰው ሲፈጠርም እንዲሁ እንኳንስ በሕይወቱ ላለ ከሞተም በኋላ ቢሆን የተወለደባትን አገር ሲያስመሰግናትና ሲያስከብራት ይኖራል።

*

አዳኝ አግኝቷት ጠበንጃውን ሲደግንባት ባየች ጊዜ ራስዋን ከአፈር ውስጥ ቀብራ ዓይኖችዋን የምትጨፍን ሰጎን ባንድ አገር አለች። ይህንንም ማድረግዋ አዳኝ የለም፤ ጠበንጃም የለም ብላ ብታስብ ነው ይባላል። ብዙ ሰዎችም እንደዚሁ የማይወዱት እውነተኛ ነገር ሲፈጸም ሲቃረብ አይደረግም እያሉ የአእምሮ ዓይናቸውን ይጨፍናሉ። ይሁን እንጂ ሰጎንዋ ዓይኖችዋን ስለጨፈነች የአዳኙ ጠበንጃ እንዳይተኩስና ጥይቱም እንዳይገድላት ለማድረግ አትችልም። የሚሆነውን ነገር አይደረግም የሚሉ ሰዎችም እነሱ ስለካዱት የመጣው ነገር አይመለስም። ለምሽት መብራት ለመከራ ጊዜ ብልሃት አስቀድመው የሚያሰናዱ ሰዎች ግን ጠቢባን ናቸው።

*

ከንቱ ፡ ሰው ፡ ሊፈጽመው ፡ አደራ ፡ የተቀበለውን ፡ ሥራ ፡ በስንፍናና ፡ በቸልታ ፡ ምክንያት ፡ ሳይሠራው ፡ ቀርቶ ፡ እየተገኘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠው ፡ ጕልበቱና ፡ ዕውቀቱ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ባለመቻሉ ፡ ይቆጨዋል ። በሬት ፡ በእጅህ ፡ ያለውን ፡ አቅምህ ፡ የሚችለውን ፡ ትንሹን ፡ ሥራ ፡ ከፊጸምህ ፡ በኋላ ፡ ከጕልበትህ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ለመሥራት ፡ ብትመኝ ፡ ያም ርብሃል ።

*

ሠራተኛን ፡ ሰው ፡ ሲገምቱት ፡ የአሳቡን ፡ መሠረትና ፡ የውጥኑን ፡ አያያዝ ፡ እየተመለከቱ ፡ ነው ። ምንም ፡ ሥራ ፡ ከአሳባቸው ፡ አመንጭተው ፡ ለማቋቋም ፡ የማይችሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሌላው ፡ ብልህ ፡ ቦሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጥፋትና ፡ ስሕተት ፡ ለማግኘት ፡ ይቸኩላሉ ፡ ይህንኑም ፡ ከትልቅ ፡ ስጦታ ፡ ቆጥረውት ፡ ይመኩበታል ። ትልቁ ፡ ሊቅ ፡ ግን ፡ ሲናገር ፡ የሰው ፡ ፍጹም ፡ አይገኝም ። የማይሳሳት ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ የማይሠራ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስሕተት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ልማድ ፤ ምሕረት ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብልዋል ።

*

ጦርነትን ፡ ኃይል ፤ ማዕበልን ፡ ዘይ ፤ ታጠሎን ፡ ውኃ ፤ በሽታን ፡ መድኃኒት ፡ ይመልሰዋል ። ፡ መሬት ፡ በተናወጠች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ መድኃኒት ፡ የለውም ፡ ስለዚህ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ከድንጋጤ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ዕብድ ፡ ይሆናሉ ።

*

የውቅያኖስ ፡ ጠሊቅነት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከሦስት ፡ ሺ ፡ እምስት ፡ መቶ ፡ ሜትር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሜትር ፡ ነው ፤ ግን ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ሺና ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺም ፡ የሚደር ስበት ፡ ቦታ ፡ አለ ፡ ይላሉ ።

*

ጥንት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ የነበሩ ፡ ታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ቻና ፤ ኢትዮጵያ ፤ ግብጽ ፤ ባቢሎን ፤ አሦር ፤ እስራኤል ፤ ፈንቄ ፤ ፋርስ ፡ ግሪክ ፤ ሮማ ፡ ናቸው ።

Scanned with CamScanner

*

በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ከብዙዎቹ ፡ ሀብቶች ፡ ዋናዎቹ ፡ ወር ቅና ፡ ዉው ፡ ናቸው ። በሺ ፡ ኪሎ ፡ የባሕር ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ጨ ፡ ሚለግራም ፡ ወርቅ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ሊቃውንት ፡ ገምተዋል ።

*

ሙዚቃ ፡ ማለት ፡ ውብ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ በድምጥ ፡ ብቻ ፡ መግለጥ ፡ ማለት ፡ ነው ።

*

የዓመትን ፡ አቈጣጠርና ፡ የሳምንትን ፡ ቀኖች ፡ ቁምረው ፡ የወሰኑ ፡ የርገመትን ፡ መሥፈሪያና ፡ የክብደትን ፡ ሚዛን ፡ መጀመሪያ ፡ የሠሩ ፡ የአሦር ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ ይባላል ።

*

በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ የነበሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ በፀሓይ ፡ በጨረቃ ፡ በነፋስ ፡ በዘፍ ፡ በደንጊያ ፡ በሴላም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ሁሉ ፡ ሲያመልኩ ፡ እስራኤላውያን ፡ ግን ፡ የሚያምኑ ፡ በአንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

*

ቀድሞ ፡ የጥበብ ፡ ዓይነት ፡ ሁሉ ፡ ተዘባርቆና ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ተቀላቅሎ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ በዓይነት ፡ በዓይነቱ ፡ ለይቶ ፡ አቅድ ፡ የሰጠው ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ነው ።

*

ጠላትም ፡ የለኝ ፡ ጠብም ፡ አልወድም ፡ ብሎ ፡ የዕለት ፡ ተግባሩን ፡ በሰላም ፡ እየሠራ ፡ ከቤቱ ፡ አርፎ ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ ሰላምን ፡ የሚያገኝ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበር ። ግን ፡ ክፉቱ ፡ ያለምክንያት ፡ ጠብ ፡ ያለህ ፡ ዳቦ ፡ እያሉ ፡ እቤቱ ፡ ድረስ ፡ መጥታው ፡ ሰውን ፡ የሚበጠብጡ ፡ ሰዎች ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለሞሉ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ጠባዩ ፡ ታጥቆና ፡ ለጠብ ፡ ተሰናድቶ ፡ መቀመጥ ፡ ግዴታ ፡ ሆናበታል ።

*

በጣም ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ የፀሓይ ፡ ብርሃን ፡ ፈጽሞ ፡ አይደርስም ፤ ስለዚህ ፡ እግዜር ፡ በጥበቡ ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩት ፡ ነፍሳቶች ፡ ገላቸው ፡ እያብረቀረቀ ፡ ብርሃን ፡ እንዲሰጣቸው ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮዋቸዋል ።

*

መስማት ፡ ትምህርት ፡ መሰብሰብ ፡ ነው ፡ መለፍለፍ ፡ ግን ፡ ዕውቀት ፡ ማባከን ፡ ነው ።

*

የትምህርት ፡ ጊዜዬ ፡ አልፏል ፡ ብሎ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ሞኝ ፡ ነው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የተፈጠሩትን ፡ የትልልቆች ፡ ሰዎች ፡ የሕይወታቸውን ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከት ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ዕድሚያቸው ፡ ሰባና ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ከሞላው ፡ በኋላ ፡ ተነሥተው ፡ ትምህርት ፡ እየጀመሩ ፡ ለትልቅ ፡ ዕውቀት ፡ ደርሰዋል ።

*

በግልጥ ፡ ከታወቀው ፡ ጠላት ፡ ይልቅ ፡ ወዳጅ ፡ እየመሰለ ፡ የጠላትነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ እንደሚጎዳና ፡ ሳይታወቅበት ፡ እንደሚያጠፋ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሊቅ ፡ ሲናገር ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ በዙሪያዬ ፡ ያሉት ፡ ጠላቶቼ ፡ እንዳያጠፉኝ ፡ ስታግል ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ አደራህን ፡ ከወዳጆቹ ፡ ሰውረኝ ፡ አለ ፡ ይባላል ።

*

በወና ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ምጥማጥና ፡ እሱንም ፡ የመሰሉ ፡ መጥፎ ፡ አውሬዎች ፡ ይሰበሰቡበታል ፤ በሥራ ፡ ፈት ፡ ሰው ፡ መንፈስ ፡ ውስጥም ፡ እንዲሁ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ የክፋትና ፡ የተንኰል ፡ አሳብ ፡ ይሰፍርበታል ።

*

የሰው ፡ ልጅ ፡ ዕድል ፡ በሕፃንነቱ ፡ አብቦ ፡ በጎልማሳነቱ ፡ ያፈራል ። ይህም ፡ ሰው ፡ በልጅነቱ ፡ የዘራውን ፡ ባደገ ፡ ጊዜ ፡ ይሰበስባል ፡ ማለት ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner

*

ተሙርሱንግ ፡ ወይም ፡ ታሜርላን ፡ የሚባለው ፡ ኃይለኛው ፡ የሞንጎል ፡ አገር ፡ ጠረኛ ፡ ሰው ፡ ቢወድቅ ፡ ይነሣል ፤ ቢሸሽ ፡ ተመልሶ ፡ መጥቶ ፡ ይገጥማል ፡ ቢሸነፍም ፡ እንደገና ፡ ጦር ፡ አደራጅቶ ፡ ይዋጋል ፡ ስለዚህ ፡ ከፉ ፡ ነገር ፡ ያገኘናል ፡ ብላችሁ ፡ ምንም ፡ አትሥጉ ፡ አያዟችሁ ፡ ተከተሉኝ ፡ እያለ ፡ ወታደሮቹን ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሜዳ ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

*

ሰው ፡ ለአገሩ ወይም ፡ ለኑሮው ፤ ወይም ፡ ለክብሩ ፣ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ለጠንቱ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ ሊሠራው ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ ሲኖር ፡ በግዴታው ፡ ይፈጽመዋል ፡ እንጂ ፡ ለጠባዩ ፡ የወደደውን ፡ ሠርቶ ፡ ያልወደደውን ፡ ሊተው ፡ አይገባውም ። ጠባይ ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ቀብራራ ፡ ስለሆነ ፡ በግድ ፡ እየቀጡ ፡ ይገሩታል ፡ እንጂ ፡ እያባበሉ ፡ ቢያሞላቅቱት ፡ ግን ተበላሽቶ ፡ ያበላሻል ።

*

ሰውን ፡ የማይጠጉ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ለጥቅማቸው ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ለጉዳታቸው ፡ በጠባያቸው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጉድለት ፡ ቢኖር ፡ ነውራቸውን ፡ ሰው ፡ ሳያውቀው ፡ በመኖራቸው ፡ ይጠቀማሉ ። መልካም ፡ ጠባይ ፡ ቢኖራቸው ፡ ግን ፡ ደግነታቸው ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሳይታወቅ ለምሳሌነትም ፡ ሳይረዳ ፡ በመኖሩ ፡ ይጎዱበታል ።

*

ስንዴ ፡ ከመሬት ፡ ወድቃ ፡ ክልበሰበሰች ፡ አታፈራም ። ብረትም ፡ በእሳት ፡ እየተጠበሰ ፡ በመዶሻ ፡ ክልተቀጠቀጠ ፡ ጥሩ ፡ መሣሪያ ፡ አይወጣውም ። ሰውም ፡ እንደዚሁ ፡ መከራ ፡ ክልቀጠቀጠው ፡ ብልህ ፡ አይሆንም ። የዚህ ፡ ምሥጢር ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ የገባው ፡ የመስክ ብን ፡ አገር ፡ ያሠለጠነ ፡ ንጉሥ ፡ ትልቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚባልው ፡ ነው ። የሱዊዲን ፡ ወታደሮች ፡ ከመስክብ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ እየደጋገሙ ፡ ሲያሸንፉዋቸው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ትልቁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ግዘኑን ፡ ትቶ ፡ መቼ ፡ ጠቀመንና ፡ ነው ፤ ሱዊዲኖች ፡ ገና ፡ ይቀጠቅጡናል ፤ ግን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከተሸነፍን ፡ በኋላ ፡ በመከራ ፡

ብዛት ፡ ዘዴውን ፡ ከእነሱ ፡ ተምረን ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ተራችንን ፡ መልሰን ፡ እስኪያንገፈግፉቸው ፡ ድረስ ፡ እንቀጠቅጣቸዋለን ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ጴጥሮስ ፡ አልተሳሳተም ፡ ልክ ፡ እንደተናገረው ፡ ተፈጸመለት ።

*

ዕድል ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ተመልሶ ፡ እንጀራ ፡ እንዲመጣለት ፡ ምክንያት ፡ ይሆንዋል ። ያልታደለ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንደ ፡ መጥቀም ፡ የገዛ ፡ ሙያው ፡ አጥሬ ፡ ይገዛለታል ። ዕድለ ፡ ቢስ ፡ ሰው ፡ ጧፍ ፡ ልንግድ ፡ ብሎ ፡ ቢነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሴሊቴን ፡ ቀን ፡ ያደርግበታል ፡ የሚል ፡ በወረቡቾ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ተረት ፡ አለ ።

*

ብልሆች ፡ ሲጫወቱ ፡ ፀሐይ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ስትወጣ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ እንዲህ ፡ ትለዋለች ፡ ይላሉ ፤ ሰው ፡ ሆይ ፤ በእኔ ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ ልትቀና ፡ ይገባሃል ፤ ስለምን ፡ እኔ ፡ ማታ ፡ ሲሆን ፡ ጠልቄ ፡ እየጠፋሁ ፡ ጧት ፡ ሲሆን ፡ ተመልሼ ፡ እየመጣሁ ፡ ዘለዓለም ፡ ስመላለስ ፡ እኖራለሁ ። አንተ ፡ ያልታደልህ ፡ ምስኪን ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከጠፋህ ፡ ተመልሰህ ፡ ሁለተኛ ፡ አትመጣም ።

*

የውቅያኖስ ፡ ባሕር ፡ ላዩ ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ሜዳ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። በውስጡ ፡ ግን ፡ አዞና ፡ አልቅትን ፡ ጉማሬና ፡ ዓሣነባሪን ፡ የመሰሉ ፡ ፍጥረቶች ፤ ወይም ፡ አልማዝና ፡ ዕንቊን ፡ የመሰሉ ፡ የሚያምሩና ፡ የከበሩ ፡ ደንጊያዎች ፡ አሉበት ። የሰው ፡ ራስም ፡ እንደዚሁ ፡ ከውጭ ፡ ሲያዩት ፡ ምንም ፡ የሌለው ፡ ባዶ ፡ ቅል ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። በውስጡ ፡ ግን ፡ ተንከሎልንና ፡ ምቀኝነትን ፡ የመሰሉ ፡ የክፋት ፡ ጠባዮች ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ፍቅርና ፡ ታማኝነትን ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀትን ፡ የመሰሉ ፡ ሰውን ፡ የሚያስከብሩ ፡ መልካሞች ፡ ባሕርዮች ፡ ይገኙበታል ።

*

ጣሌስ ፡ የሚባለው ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ጥንታዊ ፡ ነው ፤ መጀመሪያ ፡ የለውምና ፤ ዓለም ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠች ፡ ውብ ፡ ነች ፤ የእግ

Scanned with CamScanner

ዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ነችና ። አሳብ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠች ፡ ረቂቅ ፡ ነች ፤ በቅጽበት ፡ ዓለምን ፡ ትዞራለችና ። ችግር ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ኃይለኛ ፡ ነው ፡ የሚያግደው ፡ ነገር ፡ የለምና ። ጊዜ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ብልሀ ፦ ነው ፤ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ያስረሳልና ።

*

አንድ ፡ የሚያምር ፡ ትልቅ ፡ ሕንፃ ፡ ስናይ ፡ ትልቅነቱንና ፡ ውበቱን ፡ በማስተዋል ፡ በምናውቀው ፡ ነገር ፡ በጭታና ፡ በደንጊያ ፡ የተሠራ ፡ አይመስለንም ። ሊቅም ፡ እንደዚሁ ፡ ሌሎቹ ፡ የጻፉትን ፡ በማንበብና ፡ በመመርመር ፡ ብዛት ፡ የምናውቀውን ፡ ነገር ፡ አገጣጥሞ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፡ ይሁን ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ አንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልነበረውን ፡ ነገር ፡ ሊፈጥር ፡ አይችልም ።

*

ብዙ ፡ የደንቆሮ ፡ ብልሆች ፡ አለማወቃቸውን ፡ ለመደበቅ ፡ በገምተኝነታቸው ፡ ዐዋቂዎች ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ደግሞ ፡ ለሚያገኙት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጥበብና ፡ ትምህርት ፡ የመላበት ፡ ጨዋታ ፡ ባለመታከት ፡ ከማውራት ፡ የተነሣ ፡ ለፍላፊዎች ፡ እያሉ ፡ መጥፎ ፡ ስም ፡ ያወጡላቸዋል ። ሰቅራጥስ ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፋ ፡ በአፉ ፡ እየለፈለፈ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በሕይወቱ ፡ መጽሐፍ ፡ አልጻፈም ። ጥቅም ፡ ያለውን ፡ ጨዋታ ፡ አትናቁ ።

*

ክልፍልፍ ፡ ሰው ፡ በመንቀሻቀሻ ፡ ብዛት ፡ መጀመሪያ ፡ ሰዎች ፡ ንቁና ፡ ትጉህ ፡ እየመሰላቸው ፡ ያቀርቡታል ፡ ያከብሩታልም ፤ በቀን ፡ ብዛት ፡ ግን ፡ ቀሊልነቱ ፡ እየተገለጠበት ፡ ሲሔድ ፡ ይንቁትና ፡ ሁሉም ፡ ይነቅፉታል ፡ የሚያስጠጋው ፡ አያገኝም ። አንዳንድ ፡ ሰው ፡ ያው ፡ ያነሣው ፡ ጠባይ ፡ መልሶ ፡ ይጥለዋል ፡ የሚባለው ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነው ። የረጋ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ዋጋው ፡ የሚታወቀው ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

ሰው ፡ የጤንነትን ፡ ጥቅም ፡ የሚያውቀው ፡ ታሞ ፡ ሲተኛ ፤ የገንዘብን ፡ ጥቅም ፡ የሚያውቀው ፡ አጥቶ ፡ ሲቸገር ፤ የሕይወትን ፡ ጥቅም ፡

የሚያውቀው ፡ ለመሞት ፡ ሲቃረብ ፤ የነፃነትንም ፡ ጥቅም ፡ የሚያውቀው ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ ግፍ ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

*

ጥበብ ፡ የምትገኘው ፡ በትምህርትና ፡ በመጣጣር ፡ ብዛት ፡ ነው ። ግን ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በትምህርት ፡ ሲደክም ፡ የኖረ ፡ የስልሳና ፡ የሰባ ፡ ዓመት ፡ ሽማግሌ ፡ ያላገኘውን ፡ ዕውቀት ፡ የአሥርና ፡ የአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ በዕድልና ፡ በስጦታ ፡ ያገኘዋል። ቶማስ ፡ ቻተርቶን ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመቱ ፡ አስተክክሎ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ ግጥም ፡ ይጽፍ ፡ ነበር ። ፓስካል ፡ ገና ፡ በሕፃንነቱ ፡ የጆሜትሪ ፡ መስመሮች ፡ እያስተካከለ ፡ በክርታስ ፡ ይነድፍ ፡ ነበር ። ሞዛር ፡ በአምስት ፡ ዓመቱ ፡ አሳምሮ ፡ ሙዚቃ ፡ እየተጫወተ ፡ በሰባት ፡ ዓመቱ ፡ ኖታውን ፡ ከሊቃውንት ፡ አብልጦ ፡ ይደረድር ፡ ነበር ።

*

መሮጥ ፡ የሚያበዛ ፡ ሰው ፡ ልቡ ፡ ፈርሶ ፡ ይሞታል ፤ በዝግታ ፡ እያዘገመ ፡ የተጓዘ ፡ ግን ፡ ይዘግይ ፡ እንጂ ፡ ከሰበበት ፡ ቦታ ፡ መድረሱ ፡ አይቀርም ። ችኩል ፡ ሰው ፡ የራሱ ፡ ፍጥነት ፡ አሰናክሎ ፡ ይጥለዋል ። ደመ ፡ በራድ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በመቻልና ፡ በመታገሥ ፡ ብዛት ፡ ሳይታግል ፡ ይጥላል ፤ ሳይሟገት ፡ ይረታል ። በትዕግሥት ፡ መጠበቅን ፡ ማወቅ ፡ ትልቅ ፡ ብልህነት ፡ ነው ።

*

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያቀዱትን ፡ የሥራ ፡ አሳብ ፡ ወስደው ፡ ብልህ ፡ ለመሰላቸው ፡ ሰው ፡ ሲያቀርቡለት ፡ እሱም ፡ ሰንፎ ፡ በማስነፍ ፡ እንደ ፡ ወኃ ፡ የበረደ ፡ አፍራሽ ፡ የሆነ ፡ ምክር ፡ አምጥቶ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ግሎ ፡ ለሥራ ፡ የተነሣሣው ፡ መንፈሳቸውን ፡ ያቀዘቅዘውና ፡ ተስፋ ፡ ያስቆርጣቸዋል ። ብልህ ፡ ሠራተኛ ፡ ግን ፡ እየሠራና ፡ ሳይሆንለትም ፡ ሲቀር ፡ እያፈረሰ ፡ ደጋግሞ ፡ በመድከም ፡ ብዛት ፡ እውነተኛውን ፡ ምክር ፡ በሥራው ፡ ውስጥ ፡ ፈልጎ ፡ ያገኘዋል ፡ እንጂ ፡ ከሰው ፡ ዘንድ ፡ ሔዶ ፡ አይጠይቅም ። የማያሰሳት ፡ መልካሙ ፡ ዘዴ ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃልና ።

Scanned with CamScanner

*

አዉር ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ተጠቅልሎ ፡ የተቀመጠ ፡ ምግምግ ፡ ወርቅ ፡ ይመስላል ። ሞኝ ፡ አዉር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይንቀዋል ፡ ብልህ ፡ ግን ፡ ትርጉሙን ፡ እየተረተረ ፡ ሲዘረጋውና ፡ ሲያስፋፋው ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ ያገኝበታል ።

*

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የቆመችው ፡ በወንጌል ፡ ቃል ፡ እየመራች ፡ ሰዎችን ፡ ከመጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ ለመመለስ ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ የዓለም ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሔዱት ፡ ስለ ፡ ሽርሽር ፡ ያህል ፡ ሆኗል ። የምክርም ፡ ቃል ፡ ጥንት ፡ የተጀመረው ፡ በሰው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ መጥፎ ፡ አመል ፡ እያረቁ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ባሕርይ ፡ ለማቅናት ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ያምራል ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ ሰዓ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ጌጥ ፡ በማድነቅ ፡ ይመለከቱታል ፡ እንጂ ፡ አመላችንን ፡ እናሻሽልበት ፡ ብለው ፡ ማሰብን ፡ ትተውታል ። መፈረሻው ፡ ይህ ፡ መሆኑን ፡ ቢያውቁ ፡ ኖሮ ፡ ብዙዎቹ ፡ ሊታወኑት ፡ የሞራል ፡ መጽሐፍ ፡ በማሰናዳት ፡ በከንቱ ፡ ባልደከሙ ፡ ነበር ።

*

የሰዎች ፡ ጠባይ ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ያደነቀውን ፡ ነገር ፡ አንደኛው ፡ ይነቅፈዋል ፤ ላንዱ ፡ የሚያጓጓው ፡ ነገር ፡ አንደኛውን ፡ ያስቄጣዋል ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ እስኪንሰቀሰቅ ፡ ድረስ ፡ ያስለቀሰው ፡ ነገር ፡ ሌላውን ፡ ልቡ ፡ እስኪ ፈርስ ፡ ድረስ ፡ ያስቀዋል ። እነሆ ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ እያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጠባዩ ፡ ይይዙታል ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ አሳብ ፡ ለማሰር ፡ አይቻልም ።

*

ሳት ፡ ሲበዛ ፡ የኅዘንን ፡ ያህል ፡ እንባ ፡ ያስፈስሳል ፤ መቀመጥም ፡ ሲበዛ ፡ የመሥራትን ፡ ያህል ፡ ያደክማል ፡ ደግነት ፡ ሲበዛም ፡ እንዲሁ ፡ የክፋትን ፡ ያህል ፡ ይጎዳል ፡ እንጂ ፡ አይጠቅምም ። ሁሉን ፡ ነገር ፡ በመጠን ፡ ከያዙት ፡ ግን ፡ እንኳንስ ፡ መልካሙ ፡ ክፉውም ፡ ይጠቅማል ።

አንድ ፡ ባላገር ፡ ሰው ፡ ትምህርት ፡ ስለማይወድ ፡ ልጁ ፡ አስተምረኝ ፡ አባክህ ፡ አባባ ፡ እያለ ፡ ሲለምነው ፡ እምቢ ፡ ብሎት ፡ ይኖር ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ ሁለቱም ፡ ወደ ከተማ ፡ ሔደው ፡ ከገበያ ፡ መከከል ፡ አንድ ፡ ወንጀለኛ ፡ ተሰቅሎ ፡ አዩና ፡ አባትዮው ፡ ምን ፡ አጥፍቶ ፡ ነው ? ብሎ ፡ ሰዎች ፡ ቢጠይቅ ፡ የሰው ፡ ፊርማ ፡ አስመስሎ ፡ ፊርሞ ፡ ትልቅ ፡ ጥፋት ፡ ስላጠፋ ፡ ነው ፡ አሉት ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ ቂሉ ፡ ባላገር ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ይኸውልህ ፡ አትማር ፡ ብዬ ፡ የምከለክልህ ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ አለው ፡ ይባላል ። ለተሰቀለው ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ ባሕሪ ፡ ሞቱ ፡ ቢሆን ፤ ትምህርት ፡ ለብዙዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ ሆና ፡ የሁለቱን ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ የምታስገኝ ፡ ናት ።

*

መሬት ፡ ሁሉን ፡ ዓይነት ፡ ሀብት ፡ ትሰጣለች ፤ በመጻሕፍትም ፡ ውስጥ ፡ እንዲሁ ፡ የጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ዓይነት ፡ ተጽፎ ፡ ተቀምጧል ። ግን ፡ የመሬትም ፡ ሀብት ፡ ሞኑ ፡ ወይም ፡ በመጽሐፍ ፡ ያለ ፡ ጥበብ ፡ ከልደከመበት ፡ አይገኝም ።

የተማረ ፡ ሰው ፡ ብልጣ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የተማረ ፡ ወዋቂ ፡ ሰው ፡ ከአንድ ፡ ወዳጁ ፡ ጋር ፡ ሲጫወት ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ከቀረው ፡ ሰው ፡ የሚበልጡበት ፡ ነገር ፡ በምንድን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ሰውዬው ፡ በጣም ፡ የተማረ ፡ ፈላስፋ ፡ ነበርና ፡ ይህ ፡ የምታየው ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሕገወጥ ፡ የምንለው ፡ ሁሉ ፡ ረግቶ ፡ የሚኖረው ፤ በልጓም ፡ ተይዞ ፡ ነው ። ልጓሙም ፡ ሕግና ፡ አዋጅ ፡ ናቸው ። ሕግና ፡ አዋጅ ፡ በይኖሩ ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይፋጃል ። በእውነት ፡ የተማሩ ፡ ፈላስፎች ፡ ግን ፡ ራሳቸው ፡ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ ስለሆኑ ፡ ያለ ፡ ሕግና ፡ ያለ ፡ አዋጅ ፡ ተስማምተውና ፡ ተከባብረው ፡ በጤና ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ። ይኸውልህ ፡ ወዋቂዎች ፡ ከሌላው ፡ ከማናቸውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ የሚበልጡበት ፡ በዚህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

Scanned with CamScanner

መልካም ፡ በቀል ።

አንድ ፡ ደሀ ፡ ሰው ፡ በመንገድ ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ ሲሄድ ፡ አይቶ ፡ ምጽዋት ፡ ለመነው ። ሀብታሙ ፡ ተቆጥቶ ፡ ሂድ ፡ ተፈቴ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ደሀው ፡ ግን ፡ ያገኝ ፡ መስለሎት ፡ ስለጓጓ ፡ ልመናውን ፡ ቀጠለ ። ሀብታሙ ፡ ተናደደና ፡ ደንጊያ ፡ አንሥቶ ፡ በደሀው ፡ ላይ ፡ ወረወረበት ። ደሀውም ፡ የተወረወረበትን ፡ ደንጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ዛሬስ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ሀብታም ፡ ነህና ፡ ልደፍርህ ፡ አልችልም ፡ ግን ፡ ምናልባት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ትጥረድ ፡ ይሆናል ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ደሞም ፡ በዚህ ፡ ደንጊያ ፡ መልሼ ፡ እመታሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ደንጊያውን ፡ ከኪሱ ፡ ከቶ ፡ ሄደ ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ተከሰሰና ፡ አደባባይ ፡ ወጥቶ ፡ በተከሰሰበት ፡ ኃጢአት ፡ ተረትቶ ፡ ተፈረደበትና ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ተወርሶ ፡ ካገር ፡ እንዲወጣ ፡ ተደረገ ። ታስሮ ፡ በዘበኛ ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡ ሲሄድ ፡ ደሀው ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ቆሞ ፡ ጠበቀውና ፡ ባጠገቡ ፡ ሲያልፍ ፡ ከኪሱ ፡ ደንጊያውን ፡ አወጣና ፡ ሊመረውርበት ፡ እጁን ፡ አነሣ ። በኋላ ፡ ግን ፡ አሰበና ፡ ተወው ። ይህን ፡ ደንጊያ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተሸክሜ ፡ የኖሩሁት ፡ ለካ ፡ በከንቱ ፡ ኖርዋል ። ይህ ፡ ሰው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሀብታም ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እንዳልመታው ፡ ፈራሁት ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ቀን ፡ ቢገ◦ድልበት ፡ አሳዘነኝ ፡ ብሎ ፡ ደንጊያውን ፡ ጥሎ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ።

የወኃ ፡ ታሪክ ።

መጀመሪያ ፡ ወኃ ፡ ከብዙ ፡ ቦታ ፡ እየተንቆረቆረ ፡ መጥቶ ፡ ይገናኝና ፡ ተጠራቅሞ ፡ የምንላው ፡ ወኃ ፡ ይሆናል ። ከየምንጩና ፡ ከየኩሬው ፡ የሚነሣውም ፡ ወኃ ፡ ማረሻ ፡ አንደቀደደው ፡ ሠሬት ፡ የበይ ፡ መንገድ ፡ አውጥቶ ፡ በዚያ ፡ ውስጥ ፡ ይንቆረቆራል ። ከዚያም ፡ እየጨመረ ፡ ይሄድና ፡ ጎርፍ ፡ ይሆናል ። ጎርፉም ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድ ፡ ወንዝና ፡ ጄረት ፡ ይሆናል ። እነዚህም ፡ ወንዞች ፡ ወይም ፡ ጅረቶች ፡ ሄደው ፡ ሄደው ፡ ከባሕር ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላሉ ።

ከየበታውና ፡ ከየአገሩ ፡ እየተነሡ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚገቡት ፡ ወንዞች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ከእነዚህም ፡ ብዙዎቹ ፡ የሚናሩት ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። የቀሩት ፡ ግን ፡ አጀማመራቸው ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንደተነገረው ፡ አኳኋን ፡ ነው ። የወንዞችና ፡ የጅረቶች ፡ ወኃ ፡ የሚገባው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ነው ፡ ትባለ ፡ የባሕሮችስ ፡ ወኃ ፡ የሚሄደው ፡ ወዴት ፡ ይሆን ? እንደ ፡ መጠራቀሙ ፡ ብዛት ፡ ቢሆን ፡ ወኃው ፡ ተርፎ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይፈስ ፡ ነበር ። ግን ፡ ከባሕር ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ እንፋሎት ፡ እየሆነ ፡ ብዙ ፡ ወኃ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይነሣና ፡ ደመና ፡ ይሆናል ። ደመናውም ፡ ነፋስ ፡ እየጠረገው ፡ ወስዶ ፡ በየአገሩ ፡ ይበታትነዋል ፡ ዝናም ፡ እየሆነም ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ይዘንማል ። የዘነመውም ፡ ዝናም ፡ ወኃው ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ምንጭና ፡ ወደ ፡ ወንዞች ፡ ይገባል ። ወንዞችም ፡ ጅረት ፡ ይሆናሉ ፡ የጅረቱም ፡ ወኃ ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተመልሶ ፡ ይገባል ። ከባሕሩም ፡ ላይ ፡ በእንፋሎትነት ፡ ጉም ፡ ወይም ፡ ጭጋግ ፡ እየሆነ ፡ ወኃው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይወጣና ፡ ደመና ፡ ይሆናል ። ደመናውም ፡ ዝናም ፡ ሆኖ ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ይዘንማል ። እነሆ ፡ የወኃ ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሌ ፡ ቶ።

ሱልጣን ፡ ሞሐመድ ።

ሱልጣን ፡ ሞሐመድ ፡ የሚባለው ፡ የእስላሞች ፡ ንጉሥ ፡ ሁል ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ እያነሣ ፡ ሌሎችን ፡ ሕዝቦች ፡ እየወጋ ፡ አገራቸውን ፡ ሲያጠፋና ፡ ሲዘርፍ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። እሱ ፡ የወጋው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ችግርና ፡ መከራ ፡ ወድቆበት ፡ ኖረ ፡ ከእነዚህም ፡ አንዱ ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ የሱልጣን ፡ ሞሐመድ ፡ ጦር ፡ መትቶት ፡ ሕዝቡ ፡ በግማሽ ፡ አልቆ ፡ የሚበልጠውም ፡ አገሩ ፡ ጠፍ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። ከመኳንንቶቹ ፡ አንደኛው ፡ ቢዚር ፡ የወሮችን ፡ ቋንቋ ፡ ተምሬያለሁ ፡ ወሮች ፡ በጮሁ ፡ ጊዜ ፡ የሚናገሩት ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ሳይቀረኝ ፡ ሁሉንም ፡ አሰማለሁ ፡ አያለ ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

Scanned with CamScanner

አንድ ፡ ቀን ፡ ሱልጣን ፡ ሞሐመድ ፡ ከመኳንንቶቹ ፡ ጋር ፡ አደን ፡ ሲያድን ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ በምሽት ፡ ሰዓት ፡ ሲመለስ ፡ ካንድ ፡ አሮጌ ፡ ግንብ ፡ አጠገብ ፡ በቅሎ ፡ ከነበረ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ጉጉቶች ፡ ተቀምጠው ፡ አየ ። ጉጉቶቹ ፡ ሲጮሁ ፡ ሰምቶ ፡ ሱልጣን ፡ ሞሐመድ ፡ የወፍ ፡ ቋንቋ ፡ አውቃለሁ ፡ ያለውን ፡ መኰንን ፡ ጠርቶ ፡ እኒህ ፡ ጉጉቶች ፡ የሚናገሩትን ፡ ነገር ፡ አዳምጠህ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። መኰንኑም ፡ ጉጉቶቹ ፡ ወደተቀመጡበት ፡ ዛፍ ፡ ተጠግቶ ፡ ልብ ፡ አድርጎ ፡ ሲያዳምጣቸው ፡ ቆየ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሱልጣን ፡ ሞሐመድ ፡ ቀርቦ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ የተናገሩትን ፡ ነገር ፡ ሰማሁ ፡ ግን ፡ ልነግርዎት ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ አልደፍርም ፡ አለ ።

ሱልጣኑ ፡ መለሰና ፡ አልገባኝም ፡ የምትል ፡ እንደሆነ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ግን ፡ የተናገሩትን ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ከሰማኸው ፡ አንድ ፡ ታል ፡ ሳይቀር ፡ ሁሉንም ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። እንግዲያውስ ፡ የሰማሁትን ፡ ልንገርዎት ፡ ያድምጡኝ ፡ አለ ። ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ጉጉት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ አንደኛውም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አለችው ። ልጆቻቸውን ፡ ሊያጋቡ ፡ ይስማማሉ ። የሴቲቱ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ለወንዱ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ እንዲህ ፡ አለው ። ጋብቻውን ፡ አልጠላሁም ፡ ወድጀለሁ ፡ ግን ፡ ልጄን ፡ ለልጅህ ፡ ስሰጥ ፡ ጥሎሽ ፡ አምሳ ፡ ከሚሆኑ ፡ የፈረሱና ፡ የጠፉ ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ ልጄ ፡ እያማረጠች ፡ የምትቀመጥበት ፡ ቦታ ፡ እንድታሰናዳላት ፡ እጠይቅሃለሁ ፡ ቢለው ፡ የወንዱ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ መለሰና ፤ ለንጉሡ ፡ ለሱልጣን ፡ ሞሐመድ ፡ እግዜር ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ ይስጥልን ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ ካለ ፡ የፈረሰና ፡ የጠፋ ፡ መንደር ፡ መቼ ፡ ገደደን ። ደግሞ ፡ ለአምሳው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አንተ ፡ የተቸገርከው ፡ እኔስ ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ እያማረጠች ፡ ልጅህ ፡ ከወደደችበት ፡ የምትቀመጥበት ፡ ከአምስት ፡ ሙቶ ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ ስፍራ ፡ አሰናዳላታለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ሱልጣን ፡ ሞሐመድ ፡ ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ልቡ ፡ በኀዘን ፡ በጣም ፡ ስለተነካ ፡ በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ አጥፍቶዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ ብዙ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮች ፡ ተመልሰው ፡ እንደገና ፡ ታድሰው ፡ እንዲሠሩ ፡ አድርጎ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የሕዝቦችን ፡ ኑሮ ፡ ማጥፋቱ ፡ ቀርቶ ፡ ለመጠቅ ፡ ይጣጣር ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

የውቅያኖስ ፡ ባሕር ።

የውቅያኖስ ፡ ባሕር ፡ በጣም ፡ ሰፊና ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፡ መዉረሻ ውም ፡ ለዓይን ፡ አይታይም ። ፀሓይ ፡ ከባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ተነሥታ ፡ ከባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ትጠልቃለች ። ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መዉረሻውን ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ የለም ። ነፋስ ፡ በሌለበት ፡ በጸጥታ ፡ ሰዓት ፡ ባሕር ፡ ረግቶና ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ባሕር ፡ ይናወጥና ፡ አረፋ ፡ ይደፍቃል ። የባሕሩም ፡ ውኃ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እየተውዘገዘገ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይማታል ። ወደ ፡ ላይ ፡ እየተነሣ ፡ እንደዚህ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ እየተጋጨ ፡ ሲማታ ፡ አረፋ ፡ ይደፍቃል ። በዚህ ፡ ባሕሩ ፡ በታወከበትም ፡ ሰዓት ፡ ተራራ ፡ እየመሰለ ፡ የሚነሣው ፡ ማኅ ፡ ታናናሾች ፡ መርከቦች ፡ ሲያገኝ ፡ እየመታ ፡ እንደሰንበሌጥ ፡ ይሰባብራቸዋል ። በመርከቡም ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ አደጋው ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ይጨነቃሉ ፡ ከመዓቱም ፡ እንዲያድናቸው ፡ አጥብቀው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸልያሉ ። የሚበልጠውንም ፡ ጊዜ ፡ የሁከቱ ፡ ሰዓት ፡ በጣም ፡ ይቆያል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ባሕር ፡ ተቈጣ ፤ ማዕበል ፡ ተነሣ ፡ የባሕር ፡ ሞገድ ፡ ሆነ ፡ ይባላል ።

ሴ ፡ ቶ ።

ሁለት ፡ ሴቦች ።

ጓደኞች ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሴቦች ፡ ቢተውና ፡ ጀንበሬ ፡ ከአንድ ፡ ሆቴል ፡ ተገናኙ ። ቢተው ፡ ጀንበሬን ፡ ምነው ፡ አዝነሃል ፡ ? ምን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አገኘህ ፡ ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ምነው ፡ አላዝን ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ሲደርስብኝ ። እወደው ፡ የነበር ፡ ጓደኛዬ ፡ ማንደፍሮት ፡ ተሰቅሎ ፡ መሞቱን ፡ ሳትሰማ ፡ ቀርተህ ፡ ነወይ ፡ ? ሲሆንማ ፡ ለአንተም ፡ ወዳጅህ ፡ ነበር ። ከሞተ ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ሦስተኛ ፡ ቀኑ ፡ አይዶለም ፡ ወይ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ቢተው ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ በጣም ፡ አዘነና ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ምነው ፡ ማንደፍሮትማ ፡ ለእኔስ ፡ ዋና ፡ ወዳጄ ፡ አልነበረምን ፡ አዬ ፡ ሲያበላ ፡ ሲያጠጣ ፡ ሲያፈነጥዝ ፡ ለወዳጆቹ ፡ ቸር ፡ ነበር ። ኧረ ፡ በል ፡ ከሆንስ ፡ ሆነና ፡ ምን ፡ ባጠፋ ፡ ያን ፡ የመሰለ ፡ ውቱ ፡ ጨክነው ፡ ሰቀሉት ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

Scanned with CamScanner

ጀንበሬም ፡ መለሰና ፡ ያጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። አንተ ፡ ወይም ፡ እኔ ፡ በእሱ ፡ ቦታ ፡ ብንሆን ፡ የምንሠራው ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ነው ። አንድ ፡ ልጓም ፡ እመንገድ ፡ ወድቆ ፡ አግኝቶ ፡ ስለወሰደ ፡ ነው ። ቢተው ፡ ደንግጠ ፡ ተውከ ፡ አይደረግም ፡ ልጓም ፡ ወድቆ ፡ አግኝቶ ፡ በነሣ ፡ ሊሰቅሉት ፡ አይመስለኝም ፡ አለው ። ጀንበሬም ፡ ወዲያው ፡ ቀጠለና ፡ ያው ፡ ነው ፡ እባክህ ፡ ምን ፡ ይጠምራል ፡ ብለህ ፡ ብቻ ፡ ከልጓሙ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ፈረስ ፡ ነበር ፡ አለው ።

ነ ፍ ስ ።

ዓሦች ፡ በወኃ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰዎችም ፡ በአየር ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ፡ ወኃም ፡ ከልተነቃነቀ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ ከልተንቀሳቀሱ ፡ ለዓሦች ፡ ወኃ ፡ መኖሩ ፡ አይሰማቸውም ። ለእኛም ፡ ለሰዎች ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ አየሩ ፡ ከልተናወጠና ፡ ከልነፈሰ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እኛ ፡ ራሳችን ፡ ከልተንቀሳቀስን ፡ አየር ፡ መኖሩ ፡ አይታወቀንም ።

ግን ፡ በሮጥን ፡ ጊዜ ፡ ነፋስ ፡ ፊታችንን ፡ ሲገርፈን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በጆሮዋችን ፡ ውስጥ ፡ ሲያፏዋጭ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አየር ፡ መኖሩ ፡ ይሰማናል ። ባንድ ፡ በሞቀ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በሩ ፡ ሲከፈት ፡ አየር ፡ እየነፈሰ ፡ በበሩ ፡ አድርጎ ፡ በታች ፡ በኩል ፡ ከውጭ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ። እንዲሁም ፡ በዘያው ፡ በር ፡ ከላይ ፡ በኩል ፡ ከቤት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጣል ። አንድ ፡ ሰው ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ሲሄድ ፡ ፊጠን ፡ ብሎ ፡ ያለፈ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የለበሰውን ፡ ልብስ ፡ ያራገፈው ፡ እንደሆነ ፡ ነፋስ ፡ ሽው ፡ ሲል ፡ ይሰማናል ፡ የበረ ፡ ሽግ ፡ አለም እንደሆነ ፡ ይጠፋል ። እንዲሁ ፡ ሁሉ ፡ ማራገቢያ ፡ ያወዛወዙ ፡ እንደሆነ ፡ አየሩ ፡ ሲነፍስ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ ይታወቃል ።

በውሃ ፡ ግን ፡ ነፋስ ፡ ሲነፍስ ፡ አመጣጡ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚሆነበት ፡ ምክንያቱ ፡ ካንዱ ፡ የመሬት ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ አየር ፡ በጣም ፡ ሲሞቅ ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ አየር ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ ሲቀዘ

ቅዝ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነፋስ ፡ ይነሣል ። በላይኛው ፡ መስመር ፡ ተናግረነው ፡ እንደነበረውም ፡ ከውጭ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በበር ፡ አድርጎ ፡ እንደሚገባው ፡ አየር ፡ ሆኖ ፡ ከታች ፡ አየሩ ፡ ቀዝቀዘ ፡ ከላይ ፡ ግን ፡ ሞቆ ፡ ይነፍሳል ። ሞቃት ፡ የነበረው ፡ ቦታ ፡ እስኪቀዘቅዝና ፡ በራድ ፡ የነበረው ፡ ስፍራ ፡ እስኪሞቅ ፡ ድረስ ፡ አየሩ ፡ ሲነፍስ ፡ ይቈያል ።

ሌ ፡ ቶ ።

አንድ ፡ ትርንጎ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሊሄድ ፡ ሲነሣ ፡ እዚያ ፡ እሚሄድበት ፡ አገር ፡ ሌባ ፡ ሞልቶአልና ፡ እንዳትታለል ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ አስቀድመው ፡ አስጠንቅቀውት ፡ ኖሮ ፡ እዚያ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ተጠግቶ ፡ እንዳያድር ፡ ፈርቶ ፡ ራቱን ፡ ከሆቴል ፡ በላና ፡ ለቁርሱ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ትርንጎ ፡ ገዝቶ ፡ ትርንጎውን ፡ ከእግሩ ፡ ጋር ፡ በቀሚን ፡ ገመድ ፡ አስሮ ፡ ከአንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ሣር ፡ ጎዝጉዞ ፡ ተኛ ።

ሌሊት ፡ አንቅልፍ ፡ መስዶት ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ሌባ ፡ መጥቶ ፡ ትርንጎውን ፡ ከእግሩ ፡ ላይ ፡ ፈትቶ ፡ ወሰደና ፡ እንዳይበላው ፡ በጣም ፡ ጠግቦ ፡ ስለነበረ ፡ ሌባ ፡ ላመሉ ፡ ዳቦ ፡ ይልሳል ፡ እንደሚባለው ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ሄደና ፡ ትርንጎውን ፡ ከእግሩ ፡ ላይ ፡ አሥሮ ፡ ተኛና ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደው ። በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ በማለዳ ፡ እንግዳው ፡ ሰው ፡ ከእንቅልፉ ፡ አስቀድሞ ፡ ነቅቶ ፡ ቢመለከት ፡ ትርንጎውን ፡ አጣው ። ደንግጠ ፡ ከመኝታው ፡ ተነሣና ፡ በተኛበት ፡ ቦታ ፡ አቅራቢያ ፡ እየዞረ ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ሽይ ፡ ሲቃኝ ፡ ሌባው ፡ ትርንጎውን ፡ ከእግሩ ፡ ላይ ፡ አሥሮ ፡ ከንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተኝቶ ፡ አገኘው ። የነገሩ ፡ አኳኋን ፡ በአሳቡ ፡ ውስጥ ፡ ተሳክሮ ፡ አልገባህ ፡ ስላለው ፡ አንተ ፡ አንተ ፡ ብሎ ፡ ቀስቅሶ ፡ ሌባውን ፡ ከእንቅልፉ ፡ አስነሣውና ፡ ሌባው ፡ ሲነቃ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ አልገባኝም ፡ ኧረ ፡ በል ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እኔን ፡ የሆንኸው ፡ ወይስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አንተን ፡ የሆንሁት ፡ ? ብሎ ፡ ጠየቀው ።

Scanned with CamScanner

ፀሐይና ፡ ጨረቃ ።

በሰማይ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ከምናያቸው ፡ ፍጥረቶች ፡ ሁሉ ፡ ፀሐይ ፡ የበለጠች ፡ ውብ ፡ ሆና ፡ ትታያለች ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢናገር ፡ አንደኛው ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ መለሰና ፡ በውበት ፡ በኩል ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ፀሐይ ፡ ከሁሉም ፡ ትበልጥ ፡ ይሆናል ፤ ግን ፡ በጠቃሚነት ፡ ረገድ ፡ ስንመለከተው ፡ ጨረቃ ፡ ትበልጣለች ። እንደምን ፡ ቢሉ ፡ ? ፀሐይ ፡ በማነኛውም ፡ ሰዓት ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ አብርታ ፡ ትውላለች ፤ ጨረቃ ፡ ግን ፡ ሌሊት ፡ ጨለማ ፡ ሲሆን ፡ በተቸገርንበት ፡ ሰዓት ፡ ብርሃንዋን ፡ ትሰጠናለች ፡ አለው ።

የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ መለሰና ፡ አለው ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ተሳስተሃል ። እንግዲያውስ ፡ የፀሐይ ፡ ጠቃሚነት ፡ የበለጠ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳን ፡ ይኸው ፡ አንተ ፡ አሁን ፡ ያመጣኸው ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ጨረቃ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሌሊት ፡ ብርሃንዋን ፡ ትሰጠናለች ፤ ፀሐይ ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ ቀን ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ታበራልናለች ፡ አለህ ፡ ይህን ፡ ስትል ፡ ቀን ፡ የተገኘው ፡ ፀሐይ ፡ በመኖርዋ ፡ መሆኑን ፡ እያሰብህ ፤ ፀሐይ ፡ ባትኖር ፡ ግን ፡ ቀኑ ፡ ጨለማ ፡ ይሆን ፡ እንደነበረ ፡ ተረድተህ ፡ የፀሐይ ፡ ጠቃሚነት ፡ የበለጠ ፡ መሆኑን ፡ ልታውቀው ፡ ይገባሃል ። ደግሞ ፡ ጥቂት ፡ ዕውቀት ፡ በኖረህ ፡ ኖሮ ፡ ጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ የምትቀበለው ፡ ከፀሐይ ፡ መሆኑን ፡ በወቅቱ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ብልህ ፡ ዓይነ ፡ ስውር ፡ ሰው ።

ዓይነ ፡ ስውር ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ አጠራቅሞ ፤ የሚያስቀምጥበት ፡ ቦታ ፡ ቸገረው ። አደራም ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚያምነው ፡ ሰው ፡ አጣ ። አንድ ፡ ቀን ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ከመኝታው ፡ ተነሥቶ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ከአትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ገባና ፡ ጉድጓድ ፡ ቆፍሮ ፡ ወርቁን ፡ በከረጢት ፡ ቆጥሮ ፡ ቀበረው ። ጎረቤቱ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በር ፡ ሲከፍት ፡ ሰምቶ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ተነሥቶ ፡ ከደጅ ፡ ወጥቶ ፡ ጨረቃ ፡ ስለነበረች ፡ ተመልክቶ ፡ ኖሮ ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ጠብቆ ፡ የቀበረውን ፡ ወርቅ ፡ ወሰደበት ።

ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከዋለ ፡ ካደረ ፡ በኋላ ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ወርቁ ፡ መኖሩና ፡ አለመኖሩን ፡ ለማወቅ ፡ ጂዶ ፡ ከቀበረበት ፡ ቦታ ፡ ቢፈልግ ፡ አጣው ። ነገሩን ፡ በአሰቡ ፡ እየመረመረ ፡ የወሰደበትን ፡ ሰው ፡ ለማወቅ ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ አመዛዝኖ ፡ ካየው ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ የሠራኝ ፡ ይህ ፡ ጎረቤቴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ጠረጠረው ። ከጎረቤቱ ፡ ዘንድ ፡ ሄደና ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አንድ ፡ ምሥጢር ፡ አካፍልሃለሁ ፡ ብዬ ፡ ረስቼው ፡ ሳልነግርህ ፡ ቆየሁ ። መቼም ፡ ያለ ፡ አንተ ፡ ሌላ ፡ ዘመድ ፡ የለኝምና ፡ ልንገርህ ። ጥቂት ፡ ወርቅ ፡ በእጄ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በቀደምለት ፡ የማስቀምጥበት ፡ ቦታ ፡ ቢቸግረኝ ፡ አትክልት ፡ ውስጥ ፡ ወስጄ ፡ ቀበርሁት ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከሰው ፡ ዘንድ ፡ ወርቅ ፡ አስቀምጪ ፡ ሲኖር ፡ ሰውዬው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ ስለተነሣ ፡ ገንዘብህን ፡ ተረክበኝ ፡ ብሎ ፡ ዛሬ ፡ እቤቴ ፡ ድረስ ፡ አምጥቶ ፡ ሰጥቶኝ ፡ ሄደ ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ ከእሱ ፡ የተቀበልሁትን ፡ ወርቅ ፡ ፊት ፡ ቀብሬው ፡ ከነበረው ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ አድርጌ ፡ ልቅበረው ፡ ወይስ ፡ ለብቻው ፡ አድርጌ ፡ ከሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ልቅበረው ፡ የ እንዲት ፡ ማድረግ ፡ ይሻል ፡ ይመስልሃል ? ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ጎረቤቱ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲያስብ ፡ ጥቂት ፡ ቆየና ፡ ለየብቻ ፡ ማድረግ ፡ ይሻል ፡ አይመስለኝም ፡ አንድነት ፡ ብትቀብረው ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል ፡ አለው ። ይህን ፡ ተነጋግረው ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ከቤቱ ፡ ወጥቶ ፡ ሲሄድ ፡ ጎረቤቱ ፡ ብቻውን ፡ ሲሆን ፡ በፊት ፡ የቀበረውን ፡ ወርቅ ፡ ከቦታው ፡ ሲያጣው ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ ሊቀብረው ፡ ያሰበውን ፡ አይቀበርም ፡ ብሎ ፡ አሰበና ፡ ሁሉንም ፡ አንድነት ፡ ለመውሰድ ፡ ሲል ፡ የሰረቀውን ፡ ወርቅ ፡ ከነከረጢቱ ፡ ወስዶ ፡ መልሶ ፡ እዚያው ፡ እንበረበት ፡ ቦታ ፡ አስቀመጠው ።

ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ሰው ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ትልቅ ፡ ክረጢት ፡ ተሸክሞ ፡ ከቤቱ ፡ ወጣና ፡ አትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ቀድሞ ፡ የቀበረበትን ፡ ቦታ ፡ ቆፍሮ ፡ ከቤቱ ፡ ይዘት ፡ የመጣውን ፡ ከጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ቀብሮ ፡ አፈር ፡ አለበሰና ፡ በፊት ፡ የቀበረውን ፡ ግን ፡ አውጥቶ ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ። ጎረቤቱ ፡ ገና ፡ ቀኑ ፡ ሳይጨልም ፡ በጊዜ ፡ ጅምር ፡ አትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ተደብቆ ፡ ይጠብቀው ፡ ኖሮ ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ለእኔ ፡ የነገረኝ ፡ ሁለቱንም ፡ አንድነት ፡ አቀብረዋለሁ ፡ ብሎ ፡

Scanned with CamScanner

ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ የፊተኛውን ፡ አውጥቶ ፡ መውሰዱ ፡ ለምንድነው ፡ እያለ ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ ከነከነው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ አምጥቶ ፡ የቀበረው ፡ ከረጢት ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ ከፊተኛው ፡ ይበልጣል ፡ እያለ ፡ ነገሩን ፡ በልቡ ፡ ሲያወጣና ፡ ሲያወረድ ፡ ቆይቶ ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ እስ ኪገባ ፡ ድረስ ፡ አሳስችልህ ፡ ብሎት ፡ በመጣደፍ ፡ ከጠበቀ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ገብቶ ፡ በሩን ፡ እንደዘጋ ፡ ሄደና ፡ ወርቁ ፡ የተቀበረበትን ፡ ሥፍራ ፡ ቆፍሮ ፡ ከረጢቱን ፡ ጎትቶ ፡ አውጥቶ ፡ በችኮላ ፡ ማሰሪያውን ፡ ፈትቶ ፡ እጁን ፡ አግብቶ ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ዘግኖ ፡ አውጥቶ ፡ በጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ቢመለከተው ፡ ወርቅ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ጠጠር ፡ ደንጊያ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ብልሀ ፡ ዓይነ ፡ ስውር ፡ በብልሃት ፡ ገንዘቡን ፡ አስመለሰ ።

ዲን ፡ ሱዊፍት ።

ዲን ፡ ሱዊፍት ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ደራሲ ፡ አዲስ ፡ አሽከር ፡ በቀጠረ ፡ ቁጥር ፡ እንዲህ ፡ ይለው ፡ ነበር ። እንድትፈጽማቸው ፡ የምለምንህ ፡ ሁለት ፡ ነገሩች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። አንዱ ፡ የምለምንህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ስትተላለፍ ፡ ካንዱ ፡ ክፍል ፡ ወጥተህ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ስትገባ ፡ በሩን ፡ እንድትዘጋ ፡ ነው ። ሁለተኛውም ፡ የምለምንህ ፡ ነገር ፡ እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ካንዱ ፡ ክፍል ፡ ወጥተህ ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ ስትሄድ ፡ የከፈትኸውን ፡ ቤት ፡ ዘግተህ ፡ እንድትሄድ ፡ ነው ።

አንዱ ፡ አሽከሩ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ዘንድ ፡ ቀርቦ ፡ እጎቱ ፡ ልትጸር ፡ ነውና ፡ ለሰርግዋ ፡ እንድሄድ ፡ ጥቀድልኝ ፡ አለው ። ዲን ፡ ሱዊፍት ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ፈቀደለትና ፡ እሱ ፡ ከሚቀመጥባቸው ፡ ፈረሶቹ ፡ አንደኛው ፡ ተጭኖለት ፡ አንድ ፡ ሴላ ፡ አሽከር ፡ ተከትሎት ፡ ሄዶ ፡ ከቤቱ ፡ አድርሶት ፡ እንዲመለስ ፡ አዘዘ ። አሽከሩም ፡ ከደስታ ፡ ብዛት ፡ ጊታው ፡ ያስጠነቀቀውን ትእዛዝ ፡ ዘንግቶ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ሳይዘጋው ፡ ሄደ ። ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ቆይቶ ፡ ዲን ፡ ሴላ ፡ አሽከር ፡ ጠራና ፡ ፈረስ ፡ ሞነህ ፡ ጋልበህ ፡ ድረስባቸውና ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ርቀው ፡ ቢሄዱ ፡ ከደረሱበት ፡ ቦታ ፡ ተመልሰው ፡ በፍጥነት ፡ እንዲመጡ ፡ ንገራቸው ፡ ብሎ ፡ ላከው ።

የተላከው ፡ አሽከር ፡ በፈረስ ፡ ጋልቦ ፡ ግማሽ ፡ መንገድ ፡ እንደሄዱ ፡ ደረሰባቸውና ፡ የጌታውን ፡ ትእዛዝ ፡ ነገራቸው ። ፈቃድ ፡ ተቀብሎ ፡ የነበረው ፡ አሽከር ፡ ምክንያቱ ፡ ምን ፡ ይሆን ? የሰጡኝን ፡ ስንብት ፡ መልሰው ፡ ሊከለክሉኝ ፡ ይሆን ? እያለ ፡ ደንግጦ ፡ ሲሠጋ ፡ ተመልሶ ፡ መጣ ። ከጌታውም ፡ አጠገብ ፡ ቁርቦ ፡ እነሆ ፡ ተመልሼ ፡ መጣሁ ፡ ክቡር ፡ ትእዛዝዎን ፡ ይስጡኝ ፡ አለው ። ዲን ፡ ሱዊፍት ፡ አይ ፡ የጠራሁህ ፡ ለሴላ ፡ ነገር ፡ አይዶለም ። ከፍተህ ፡ ትተኸው ፡ የነበረውን ፡ በር ፡ ዘግተህ ፡ እንድትሄድ ፡ ነው ፡ አለው ።

አንድ ፡ ገበሬና ፡ አንዲት ፡ ዐይጥ ።

ለአንድ ፡ ሀብታም ፡ ገበሬ ፡ ለአህል ፡ ለአርሻው ፡ ጌታ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንዲት ፡ ዐይጥ ፡ ሠርታለት ፡ ውለታ ፡ ገበሬው ፡ በብዙ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከልቡ ፡ ውለታ ፡ ሊመልስ ፡ ቈረጠ ፡ ባሳቡ ። ነይ ፡ እንሂድ ፡ ብሎ ፡ ወሰደና ፡ አቤቱ ፡ ያለውን ፡ አሳያት ፡ በሰፈው ፡ ንብረቱ ። ኋላም ፡ እንዲህ ፡ አላት ፡ ከየሽው ፡ ሁሉ ፡ ዕቃ ፡ አህል ፡ ሆነ ፡ ሥጋ ፡ ዳቦ ፡ ወይም ፡ ጣቃ ፡ የምትፈልጊውን ፡ መርጠሽ ፡ ተናገሪ ፡ ፈቅጀልሻለሁ ፡ ጠይቂኝ ፡ አትፍሪ ። ገበሬ ፡ ለዐይጢቱ ፡ ይህንን ፡ ሲናገር ፡ እሷ ፡ መራት ፡ መሬት ፡ ትመለከት ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ ቀርቶ ፡ ልቡናህ ፡ ከቸረ ፡ ይህንን ፡ ብትሰጠኝ ፡ ይበቃኝ ፡ ነበረ ። ብላ ፡ እያመነታች ፡ ስትፈራ ፡ ስትቸር ፡ አመለከተችው ፡ ስትጠራጠር ። ገበሬ ፡ አልገባው ፡ በፊት ፡ መቼ ፡ ዐወቀ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ሲረዳው ፡ እጅግ ፡ አርጎ ፡ ሳቀ ። እሱስ ፡ አይታ ፡ ናርዋል ፡ ከቀረው ፡ ሁሉ ፡ ዕቃ ፡ አንዲት ፡ የአተር ፡ ፍሬ ፡ እሚዳ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ።

Scanned with CamScanner


በገበሬ ፡ ጓዳ ፡ ተርፎ ፡ ስንት ፡ ነገር ፡
ልመና ፡ አለማወቅ ፡ ወይ ፡ ምኞት ፡ ማሳጠር ።
ዐይጥ ፡ መሆን ፡ ክፉ ፡ አወይ ፡ መበለጥ ፡
ያንን ፡ ይዛ ፡ ሄደች ፡ ስትገላመጥ ።
ልክ ፡ የዚህ ፡ ምሳሌ ፡ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፡
ብዙ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ እየቻለ ፡
ለፍሬ ፡ ቢስ ፡ ጥቅም ፡ ልቡ ፡ እየተቆጨ ፡
ምኞቱና ፡ አሳቡ ፡ በአጭር ፡ የተቀጨ ።

ዲ ዎ ጋ ን ።

ዲዎጋን ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፋ ፡ ከጌታ ፡ ል ደት ፡ በፊት ፡ በ፬፻፲፫ ፡ ዓ ፡ ተወልዶ ፡ በ፫፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ሞተ ። ዲዎ ጋን ፡ የዓለምን ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ የናቀ ፡ ከሕይወት ፡ ተድላ ፡ የራቀ ፡ ፈላስፋ ፡ ነበር ። ቀን ፡ ያለ ፡ ጫማ ፡ ባዶ ፡ እግሩን ፡ ይሄዳል ። ሴሊ ትም ፡ ቀን ፡ ለብሶት ፡ የሚውለውን ፡ ካባ ፡ ደርቦ ፡ በንድ ፡ ቀፎ ፡ ውስጥ ፡ ተኝቶ ፡ ያድር ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቅልና ፡ አንድ ፡ ቀፎ ፡ ነበሩት ፡ የሚከተለውም ፡ አንድ ፡ ውሻ ፡ ነበር ። ቀፎው ፡ ቤቱ ፡ ነው ፡ ውሻው ፡ የማይከዳኝ ፡ ታማኝ ፡ ወዳጄ ፡ ነው ፡ ቅሉም ፡ ውኃ ፡ ቀድቶ ፡ የሚያጠጣኝ ፡ አገልጋዩ ፡ ነው ፡ ይል ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ እምንጭ ፡ ጻር ፡ ሆኖ ፡ በእጁ ፡ ውኃ ፡ እየቀዳ ፡ ሲጠጣ ፡ ዲዎጋን ፡ አይቶት ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሳልረዳው ፡ እኖር ፡ የነበረውን ፡ ዕውቀት ፡ አስተማረኝ ፤ ይህ ፡ ይገርው ፡ የምዠረው ፡ ቅል ፡ ለካ ፡ ትርፍ፡ነገር፡ኖር ዋል ፡ ብሎ ፡ ወረወረውና ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ውኃ ፡ በእጁ ፡ እጁ ፡ እየቀዳ ፡ ሲጠጣ ፡ ኖረ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ በቀትር ፡ ሰዓት ፡ ፋኖስ ፡ አብርቶ ፡ በገ በያ ፡ መከከል ፡ ሲመላለስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ መጥቶ ፡ በእኩለ ፡ ቀን ፡ መብራት ፡ አብርተህ ፡ የምትሄደው ፡ በምን ፡ ምክን ያት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ዲዎጋንም ፡ ሰው ፡ አጥቼ ፡ እፈልጋ ለሁ ፡ አለው ። ይህ ፡ የምታየው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ አይዶለም ፡ ወይ ፡



ሥዕል ፡ ፩ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሰው

Scanned with CamScanner

ብሎ ፡ መልሶ ፡ ሰውዬው ፡ ቢጠይቀው ፤ ይህን ፡ የማየውን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አልልም ። ይህ ፡ የምትመለከተው ፡ ሕዝብ ፡ እውነተኛን ፡ ነገር ፡ ትቶ ፡ ሁሉም ፡ የየራሱን ፡ ጥቅም ፡ የሚሻና ፡ ለግል ፡ ምኞቱ ፡ የሚገዛ ፡ ፍጡር ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ከውጭ ፡ የሰው ፡ አካል ፡ የለበሱ ፡ ውስጣቸው ፡ ግን ፡ እንስሳ ፡ የሆነ ፡ እሳቸዋለሁ ፡ እንጂ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ አልልም ። እውነተኛ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ግን ፡ አእምሮው ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፤ እውነትን ፡ የሚሻ ፡ ፍጡር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ዲዎጋን ፡ መለሰለት ።

ዲዎጋን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፀሓይ ፡ ሲሞቅ ፡ ትልቁ ፡ አስክንድር ፡ መጥቶ ፡ አጠገቡ ፡ ቆመና ፡ የምትፈልገውን ፡ ነገር ፡ ጠይቀኝና ፡ ልስጥህ ፡ አለው ፤ ዲዎጋን ፡ እኔ ፡ የምለምንህ ፡ ፀሓይዋን ፡ እንድሞቅ ፡ ከፊቴ ፡ ዞር ፡ እንድትልልኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። እኔ ፡ እስክንድር ፡ በልሆን ፡ ኖሮ ፡ ዲዎጋንን ፡ ብሆን ፡ በወደድሁ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ አብረውት ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ተናገራቸው ፡ ይባላል ። ዲዎጋን ፡ በእርጅና ፡ ዕድሜው ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንግዲህ ፡ አረጀህ ፤ ሥራ ፡ ትተህ ፡ ዕረፍት ፡ ብታደርግ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ አለው ። ዲዎጋን ፡ ግን ፡ ሰው ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሲያገኝ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አይሸሽም ። እኔም ፡ ከልጅነቴ ፡ ጀምሬ ፡ ሞትን ፡ ስከተለው ፡ ኖርሁ ፡ አሁን ፡ ስደርስበት ፡ እቸኩላለሁ ፡ እንጂ ፡ ስለምን ፡ ዕረፍት ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

የዝና ፡ ከንቱነት ።

ሰው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የሚጣጣረው ፡ እንዳንዱ ፡ ለዝና ፡ እንዳንዱ ፡ ግን ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡ ወደ ፡ ደግነት ፡ ስለሚያደላ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ጥበብ ፡ ለመግለጥ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ሕይወታቸውን ፡ ሙሉ ፡ የሚደክሙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ከእነዚህም ፡ ግማሾቹ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ የሚጠቅም ፡ ፍሬ ፡ ሰጥተው ፡ የሕዝብን ፡ ኑሮ ፡ አሻሽለው ፡ ከነዘን ፡ ወደ ፡ ደስታ ፤ ከችግር ፡ ወደ ፡ ሀብት ፡ ለመመለስ ፡ ሲሉ ፡ ነው ። ብዙዎቹ ፡ ግን ፡ ስማቸው ፡ በዓ

ለም ፡ ላይ ፡ ታውቆ ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ አንደበት ፡ ሲሞገሱና ፡ ሲመሰገኑ ፡ ለመስማት ፡ ይህም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ደግሞ ፡ ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ሳይረሳና ፡ ሳይዘነጋ ፡ ሐውልት ፡ ተሠርቶላቸው ፡ በዕውቀታቸው ፡ ወይም ፡ በጀግንነታቸው ፡ ስማቸው ፡ ዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ሲፈልጉ ፡ ነው ።

የፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የነበረው ፡ ቀዳማዊ ፡ ናፖሌዎን ፡ የኢጣሊያንን ፡ አገር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ሲመለስ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የኢጣሊያ ፡ አገሮች ፡ ወሰን ፡ ከሆኑት ፡ ከአልፕ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ከጦር ፡ ሹማምንቶቹ ፡ እንደኛው ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ አንሥቶ ፡ ሲያጫውተው ፡ አሁን ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ በፊትም ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ በተዋጋናቸው ፡ ጦርነቶች ፡ ላይ ፡ ያገኘናቸው ፡ ብዙዎቹ ፡ ድሎች ፡ እስከ ፡ መቼም ፡ ድረስ ፡ ቢሆን ፡ የሚረሱ ፡ አይደሉም ። የአንተም ፡ ስም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከተፈጠሩት ፡ ከትልልቆቹ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ጋር ፡ የሚተካከል ፡ የከበር ፡ ደረጃ ፡ አግኝቷል ። ታሪክህም ፡ በሰፊው ፡ ይጻፋል ፡ እያለ ፡ የማጋነን ፡ ቃል ፡ ቢናገረው ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ሲሠራ ፡ ደሙ ፡ በትዕቢት ፡ ይፈላና ፡ ራሱን ፡ ትልቅ ፡ አድርጎ ፡ ያያል ። ይህም ፡ ሥጋ ፡ ለባሾች ፡ በሆነው ፡ በእኛ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ነው ። ግን ፡ በእውነተኛው ፡ መንገድ ፡ ስንመለከተው ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ስሙ ፡ በታሪክ ፡ የተከበረና ፡ የማይረሳ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይምሰልህ ። እንኳንስ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የሠራነው ፡ ትንሹ ፡ ሥራ ፡ ይቅርና ፡ ወደፊትም ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ብዙ ፡ ሴላ ፡ ትልልቅ ፡ ሥራ ፡ ብንጨምርበት ፡ ከሞትን ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ይቅርና ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ቆይቶ ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሲጻፍ ፡ አምስት ፡ መስመር ፡ አይወጣውም ፡ ብሎ ፡ ናፖሌዎን ፡ መለሰለት ።

ይህ ፡ ነገር ፡ ትልቁ ፡ ናፖሌዎን ፡ ወደፊት ፡ በሕይወቱ ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እንደሚችል ፡ በራሱ ፡ በጣም ፡ ይተማመን ፡ የነበር ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ከታሪክ ፡ ጋር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አድርጎ ፡ እያስተያየ ፡ ሲያመዛዝነው ፡ ራሱን ፡ በትንሹ ፡ እንጂ ፡ በትልቁ ።

Scanned with CamScanner

ይገምተው ፡ እንዳልነበር ፡ ያስረዳል ። በእውነቱ ፡ ታላላቅ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ትልቅ ፡ ትሕትና ፡ ይገኛል ። ናፖሌዎን ፡ ይህን ፡ ማለቱ ፡ ታሪክ ፡ ማንበብ ፡ በጣም ፡ ስለሚወድ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ጣጣ ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቅ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ።

እንኳንስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ይቅርና ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ስማቸው ፡ ያልታወቀ ፡ አንዳንዶች ፡ ሰዎች ፡ ትንሽ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ የራሳቸውን ፡ ክብር ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱታል ።

ይህን ፡ የመሰለ ፡ የከንቱነት ፡ ምኞት ፡ በልቡ ፡ ያደረበት ፡ ፖምፒኛን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ጽንዲታወቅለት ፡ ሲጣጣር ፡ ትልቁ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ቮልቴር ፡ የሚባለው ፡ ታዝቦት ፡ ኖሮ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ስምን ፡ ለማስጠራትና ፡እንዳይረሳ ፡ አድርጎ ፡ ለማኖር ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ አስቸጋሪ ፡ መሆኑን ፡ እያሳሰበ ፡ እንኳንስ ፡ የአንዳንድ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ይቅርና ፡ ብዙ ፡ መንግሥታት ፡ ብዙ ፡ የጥበብ ፡ሥራ ፡ ሠርተውና ፡ ከከፍተኛ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ደርሰው ፡ የተነሣ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተመልሶ ፡ መውደቁ ፡ አይቀርምና ፡ መንግሥታቸው ፡ እየተፈታ ፡ ሕዝባቸው ፡ እየተበተነ ፡ ከተማቸው ፡ እየፈረሰ ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ ታሪካቸው ፡ ጠፍቷል ።

በብዙ ፡ አገሮች ፡ ገበሬ ፡ መሬት ፡ ሲያርስ ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ላንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ መሬት ፡ ሲቆፍር ፡ ድንገት ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ የሥራ ፡ መሣሪያ ፡ ወይም ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሰዓ ፡ የሆነ ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ከአፈር ፡ ጋር ፡ ተፈንቅሎ ፡ ይወጣል ። ያም ፡ ስፍራ ፡ ተቆፍሮ ፡ ሲመረመር ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ጥንት ፡ ተሠርቶበት ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ የሚያስረዳ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይገኝበታል ። ግን ፡ ከዚያ ፡ ሥፍራ ፡ የነበረው ፡ ከተማ ፡ የማን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሚናገር ፡ ሊቅ ፡ አይገኝም ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ከታሪክ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ዘመን ፡ ብለው ፡ ይጠሩታል ። ቮልቴር ፡ በታትኛው ፡ መስመር ፡ እንደምናገኘው ፡ የእስክንድርና ፡ የቄሣር ፡ ስም ፡ ተረስቷል ፡ ማለቱ ፡ ከእነሱ ፡ በፈት ፡ እኛ ፡ ከምናውቀው ፡ ታሪክ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበሩ ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ንጉሥታቸውና ፡ ጀግኖ

ታቸው ፡ ሊታወጉቱታቸውም ፡ ሁሉም ፡ አንድነት ፡ ተረስተው ፡ ቀር ተዋልና ፡ እስክንድርና ፡ ቄሣርም ፡ እንዲሁ ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ ይረሳሉ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ መረሳት ፡ ጀምረዋል ፡ ታሪካቸውን ፡ በሙሉ ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ፈልገው ፡ አቅቷቸዋል ። የሰው ፡ ትልቅነቱ ፡ በሕይወቱ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ነው ። ፖምፒኛን ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ከንቱ ፡ ምኞት ፡ ከመንፈሱ ፡ እንዲያስወግድ ፡ ሲል ፡ ቮልቴር ፡ በግጥም ፡ የጻፈውን ፡ ታል ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ አስመስለን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ስንተረጉመው ፡ የሚለው ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

በአለፉት ፡ ዘመናት ፡ ጥንት ፡ በጊዜያቸው ፡
ወሰን ፡ ያልነበረው ፡ ኃይልና ፡ ክብራቸው ።
አፈር ፡ ሆነው ፡ ዛሬ ፡ ትቢያ ፡ እየለበሱ ፡
ስንቶቹ ፡ ንጉሦች ፡ ቀሩ ፡ እየተረሱ ።
ባቢሎን ፡ ከተማው ፡ የት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡
ቢፈለግ ፡ ሳይገኝ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ቀረ ።
ትልቁ ፡ እስክንድርም ፡ መቃብሩ ፡ ፈርሶ ፡
ከከተማው ፡ ጋራ ፡ ጠፍቷል ፡ ተደምስሶ ።
ዋናው ፡ መታሰቢያው ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡
የተቀበረበት ፡ መቃብሩ ፡ ጠፍቶ ፡
ቄሣርም ፡ ተረስቷል ፡ ስንት ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ።
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ሳያስብ ፡ አስተውሎ ፡
ስሜን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ አስጠራለሁ ፡ ብሎ ።
ወዳጄ ፡ ፖምፒኛን ፡ በመንጠራወዙ ፡
እጅግ ፡ አርጎ ፡ በጣም ፡ አሳቀኝ ፡ በብዙ ።

የነፍስ ፡ ጠቃሚነት ።

ልጆች ፡ ሁለት ፡ ቀጭን ፡ የዕንጨት ፡ ዘንጎች ፡ ወይም ፡ ሰንበሌጥ ፡ አጣምረው ፡ ያጣብቋቸውና ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ወረቀት ፡ ዘርግተው ፡ በሙጫ ፡ አጣብቀው ፡ ይወጥሩታል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ረጅም ፡ የወረቀት ፡ ጅራት ፡ ያበጁለትና ፡ አንደ

Scanned with CamScanner

ኖው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ክር ፡ አስረው ፡ ክሩን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ሲሮጡ ፡ ይህ ፡ መጨዋቻቸው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይነሣል ፡ የሚያነሣውም ፡ ነፋስ ፡ ነው ። ነፋስ ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ አይነሣም ፡ ነበር ።

እንዲሁም ፡ በነፋስ ፡ ኃይል ፡ እየዘረ ፡ እህል ፡ የሚፈጭ ፡ ወፍጮ ፡ አለ ፡ ነፋስ ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ ወፍጮው ፡ አይዘርም ፡ ነበር ። በነፋስ ፡ ኃይል ፡ እየተገፋ ፡ የሚገሠግሥ ፡ የሸራ ፡ መርከብ ፡ አለ ፡ ነፋስ ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ የሸራ ፡ መርከብ ፡ ለመንቀሳቀስ ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ ተሰብስቦ ፡ ከሚኖርበት ፡ ቦታ ፡ የሚገኘው ፡ አየር ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ይበላሻል ፡ ግን ፡ ነፋስ ፡ እየመጣ ፡ ይህን ፡ መጥፎ ፡ አየር ፡ ጠራርጎ ፡ ይወስደውና ፡ በጫካና ፡ በገጠር ፡ የሚገኘውን ፡ ንጹሕ ፡ አየር ፡ አምጥቶ ፡ በእሱ ፡ ቦታ ፡ ይተክል ። ነፋስ ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ ሰዎች ፡ መጥፎውን ፡ አየር ፡ አጥፍተው ፡ ለጤንነታቸው ፡ የሚበጃቸውን ፡ መልካም ፡ አየር ፡ ለማግኘት ፡ አይችሉም ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ አየር ፡ የተበላሸበትን ፡ ቦታ ፡ ትተው ፡ መልካም ፡ አየር ፡ የሚገኝበትን ፡ ሥፍራ ፡ ለመፈለግ ፡ ሲሉ ፡ መሰደድ ፡ ግዴታ ፡ ይሆንባቸው ፡ ነበር ።

የዱር ፡ አውሬዎች ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ዱር ፡ ሰዱር ፡ ሲሄዱ ፡ ፊታቸውን ፡ ለነፋስ ፡ ሰጥተው ፡ ነው ። ጆሮዎቻቸውንም ፡ አቁመው ፡ ያዳምጣሉ ፡ ወደፊታቸው ፡ ያለውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያሸታሉ ። ነፋስ ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ ሽታና ፡ ድምጥን ፡ እያመጣላቸው ፡ መሪ ፡ የሚሆን ፡ ረዳት ፡ አያገኙም ፡ ነበር ። ሙቀት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከውኃ ፡ ላይ ፡ ላቦት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ ይወጣል ። ይህም ፡ ላቦት ፡ ወይም ፡ እንፋሎት ፡ ተሰብስቦ ፡ ይከማችና ፡ ከሰማይ ፡ ወጥቶ ፡ ከላይ ፡ ሲደርስ ፡ ቀዝቅዘ ፡ ይረጋና ፡ እየተንጠባጠበ ፡ ዝናም ፡ ሆኖ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ያወርዳል ፡ ይህም ፡ ሲሆን ፡ ዝናም ፡ ዘነመ ፡ ይባላል ።

ጻሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ላቦት ፡ የሚነሣው ፡ ውኃ ፡ ከለበት ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ግለት ፡ ከምንጭ ፡ ከኩሬ ፡ ከሐይቅ ፡ ከወንዝ ፡ ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ ከባሕር ፡ ላይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነፋስ ፡ ባይኖር ፡ እንፋሎቱ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ለመነሣት ፡ ስለማይችል ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ እየሆነ ፡ እዚያው ፡ አለበት ፡ ቦታ ፡ ተከማችቶ ፡ ይቀርና ፡ ተመልሶ ፡ እዚያው ፡ ይወ

ድቅ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ዝናሙ ፡ እዚያው ፡ አምንጩ ፡ አኩሬው ፡ ከሐይቁ ፡ እወንዙና ፡ አባሕሩ ፡ ላይ ፡ ተመልሶ ፡ ይዘንም ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ጫካው ፡ ገጠሩና ፡ አርሻው ፡ የቀረውም ፡ መሬት ፡ ሁሉ ፡ ዝናም ፡ አያገኝም ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ነፋስ ፡ ሲነፍስ ፡ ግን ፡ ደመናውን ፡ ይበታትነውና ፡ ዝናሙ ፡ በሁሉ ፡ ቦታ ፡ አንዲደርስ ፡ ያደርገዋል ። ነፋስ ፡ ባይኖር ፡ ዝናም ፡ ተመልሶ ፡ ውኃ ፡ ከለበት ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ይዘንማል ፡ የቀረውም ፡ መሬት ፡ ውኃ ፡ በማጣት ፡ ምክንያት ፡ ደረቅ ፡ ሆኖ ፡ ይቀር ፡ ነበር ። ነፋስ ፡ የሚሰጠን ፡ ጥቅም ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ሌ ፡ ቶ ።

ሦስት ፡ መንገደኞች ።

ሦስት ፡ መንገደኞች ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ አንድነት ፡ ሲሄዱ ፡ መሸ ፡ ቸውና ፡ አመንገድ ፡ አደሩ ። ስንቃቸውን ፡ ፈትተው ፡ ራታቸውን ፡ ከበሉ ፡ በኋላ ፡ እንግዲህ ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ሁሳችንም ፡ ብንተኛ ፡ አይበጅምና ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሲተኙ ፡ በተራ ፡ በተራ ፡ አንዱ ፡ ነቅቶ ፡ ቢጠብቅ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተመካክረው ፡ በዚህ ፡ ተስማሙ ። ከሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ተንኰለኛ ፡ አንደኛው ፡ ደግሞ ፡ መላጣ ፡ ነበሩ ። መጀመሪያ ፡ ጓደኛቸውን ፡ ሰው ፡ ጠብቅ ፡ ብለውት ፡ ተንኰለኛውና ፡ መላጣው ፡ ተኙ ። ተራውን ፡ ከጠበቁ ፡ በኋላ ፡ ነቅቶ ፡ የነበረው ፡ ጓደኛቸው ፡ ተንኰለኛውን ፡ ቀስቅሶ ፡ አስነሣውና ፡ እሱ ፡ ተራውን ፡ ተኛ ። ተንኰለኛ ፡ ሰው ፡ መቼም ፡ አያርፍምና ፡ ጥቂት ፡ ተቀምጦ ፡ እንደ ፡ ጠበቀ ፡ አንድ ፡ የተንኰል ፡ አሳብ ፡ በመንፈሱ ፡ ውስጥ ፡ መጣበት ።

ቀስ ፡ ብሎ ፡ መጀመሪያ ፡ ጠብቆ ፡ ወደነበረው ፡ ሰው ፡ ተጠግቶ ፡ ራሱን ፡ ብድግ ፡ አደረገና ፡ ከኪሱ ፡ የሰላ ፡ ምላጭ ፡ አውጥቶ ፡ ጠጉሩን ፡ ላጨው ። ላጭቶም ፡ ከሠረሰ ፡ በኋላ ፡ ቀሰቀሰውና ፡ እንግዲህ ፡ ተራህን ፡ ጠብቅ ፡ እኛ ፡ ሁለታችን ፡ ተራችንን ፡ ጠብቀን ፡ ጨርሰናል ፡ አለው ። ሰውዬው ፡ እያዛጋና ፡ እየተንጠራራ ፡ ተነሥቶ ፡ መጀመሪያ ፡ የጠበቅሁ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ እንዴ ፡ ? በምን ፡ ምክንያት ፡

Scanned with CamScanner

ነው ፣ አሁን ፣ ደግሞ ፣ መጠበቂ ፣ ? አለና ፣ ወዲያው ፣ ቅዝቃዜ ፣ ተሰ
ምቶት ፣ ኖሮ ፣ ራሱን ፣ በሁለት ፣ እጆቹ ፣ አሻሸና ፣ ለክ ፣ ያስነሣኸው ፣
መላጣውን ፣ ሰው ፣ ነው ፣ እኔስ ፣ እኔን ፣ መስሎኝ ፣ ተናድጄ ፣ ነበር ፣
ብሎ ፣ ተቀምጦ ፣ ይጠብቅ ፣ ጀመር ። ተንኰለኛው ፣ ሰው ፣ ቂስ ፣ ብሎ ፣
ሠስጥ ፣ ውስጡን ፣ በሆዱ ፣ እየሳቀ ፣ ተመልሶ ፣ ቸኛ ።

የጦር ፣ ሠራዊት ፣ ሥርዐት ፣ አፈጻጸም ።

የጀርመን ፣ አገር ፣ ንጉሥ ፣ ትልቁ ፣ ፍሬዴሪክ ፣ የሚባለው ፣
የጀርመንን ፣ መንግሥት ፣ አስተዳደር ፣ አሻሽሎ ፣ በመልክም ፣ መሠ
ረት ፣ ላይ ፣ የመሠረተ ፣ ጦረኛና ፣ ፖሊቲክ ፣ ወዋቂ ፣ ብልህ ፣ ንጉሥ ፣
ነበር ። ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ወደ ፣ ጦርነት ፣ ዘምቶ ፣ ሳለ ፣ ሚስ ፣
ሲመሽ ፣ ከንድ ፣ ቦታ ፣ ከሦር ፣ ሠራዊቱ ፣ ጋር ፣ ሰፈረ ። የሰፈረበት
ንም ፣ ቦታ ፣ ጠላት ፣ እንዳያውቀው ፣ መጠንቀቅ ፣ አስፈላጊ ፣ ስለሆ
ነበት ፣ ምንም ፣ መብራት ፣ እንዳይበራና ፣ እሳትም ፣ እንዳይነድ ፣ ከል
ክሎ ፣ ይህን ፣ ትእዛዝ ፣ ጥሶ ፣ የተገኘ ፣ ሰው ፣ ግን ፣ በሞት ፣ ይቀ
ጣል ፣ ብሎ ፣ ለጦር ፣ ሹማምንቶቹ ፣ አስታወቃቸውና ፣ እነሱም ፣
ደግሞ ፣ በየክፍላቸው ፣ ለወታደሮቻቸው ፣ ትእዛዙን ፣ እንዲያስተላ
ለፉ ፣ አስጠንቅቆ ፣ ነገራቸው ።

ሴሊት ፣ ሲሆን ፣ ፍሬዴሪክ ፣ እሱው ፣ ራሱ ፣ ተኝሥቶ ፣ የሸጠው ፣
ትእዛዝ ፣ መፈጸምና ፣ አለመፈጸሙን ፣ እየዘረ ፣ ሲመለከት ፣ ባንድ ፣
ድንኳን ፣ ውስጥ ፣ የብርሃን ፣ ምልክት ፣ በሩቅ ፣ አየ ። አቅጣጫውን ፣
ተከትሎ ፣ በቀጥታ ፣ ሄደና ፣ መብራቱ ፣ ከበራበት ፣ ቦታ ፣ ደረሰ ።
ድንኳኑን ፣ ገለጠና ፣ ቢገባ ፣ አንድ ፣ የጦር ፣ ሹም ፣ ሽማ ፣ አብሮቶ ፣
ደብዳቤ ፣ ሲጽፍ ፣ አገኘው ። ይህ ፣ የጦር ፣ ሹም ፣ ለንጉሡ ፣ አብሮ ፣
አደጉ ፣ ነበር ። የተሰጠውን ፣ ትእዛዝ ፣ ሰምተህ ፣ ይህን ፣ ሥራ ፣ መሥ
ራትህ ፣ ለምንድነው ፣ ? ብሎ ፣ ጠየቀው ። ሹሙም ፣ የንጉሡ ፣ ወዳጅ ፣
በመሆኑ ፣ ከርቶ ፣ እየሳቀ ፣ ነገ ፣ ጧት ፣ ጦርነት ፣ መግጠማችን ፣ ስለ
ሆነ ፣ ምናልባት ፣ እሞት ፣ ይሆናል ፣ ብዬ ፣ ይህንኑ ፣ ሚስቴ ፣ እንድታ
ውቀው ፣ ወረቀት ፣ መጻፌ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ መለሰለት ።

ፍሬዴሪክም ፣ በእርጋታ ፣ መልሶ ፣ ከቤታችን ፣ ስንወጣ ፣ ለጦር
ነትና ፣ ለሞት ፣ መሄዳችንን ፣ ዘመዶቻችን ፣ ሳያውቁት ፣ የቀሩ ፣ አይ
መስልኝም ። አሁን ፣ ግን ፣ ሕግ ፣ ጥሰህ ፣ ትእዛዝ ፣ አፍርሰህ ፣ መብ
ራት ፣ ስታበራ ፣ ጠላት ፣ ብርሃኑን ፣ አይቶ ፣ መጥቶ ፣ አደጋ ፣ ቢጥል
ብን ፣ በአንተ ፣ ጦስ ፣ የተነሣ ፣ ብዙ ፣ ሰው ፣ ያልታል ። ስለዚህ ፣ ሥር
ዐት ፣ ለማፍረስ ፣ ከደፈርህ ፣ ቅጣቱን ፣ ደግሞ ፣ ለመቀበል ፣ ትፈራ ፣
እይመስለኝም ። በል ኣበዚሁ ፣ ወረቀት ፣ ላይ ፣ ይህንኑ ፣ ያጠፋኸውን ፣
ጥፋት ፣ ተናግረህ ፣ በዚሁ ፣ ምክንያት ፣ ተፈርዶብህ ፣ መገደልህን ፣
ለሚስትህ ፣ ጻፍላት ፣ አለውና ፣ ጽፎ ፣ ከወረሰ ፣ በኋላ ፣ እንግዲህ ፣
ወዳጄ ፣ ደኅና ፣ ሰንብት ፣ ና ፣ ሰመኝ ፣ ብሎ ፣ ስሞ ፣ ተሰነባበቱና ፣
ይማግሥቱ ፣ ጧት ፣ በማለዳ ፣ የወታደሩ ፣ ሹም ፣ ተገደለ ።

ሙቀትና ፣ ቅዝቃዜ ።

በባቡር ፣ ወይም ፣ በሴላ ፣ መኪና ፣ ውስጥ ፣ ብዙ ፣ ብረቶች ፣
እርስ ፣ በርሳቸው ፣ እንዳይነካኩ ፣ ተደርገው ፣ ጥቂት ፣ እየተራራቁ ፣
ይሠራሉ ። ምክንያቱም ፣ በክረምት ፣ ጊዜ ፣ ከብርዱ ፣ ጽናት ፣ የቱ
ነማ ፣ እየተጠበጡ ፣ በበጋም ፣ ጊዜ ፣ በሙቀት ፣ ምክንያት ፣ ስለሚዘ
ረጉ ፣ ታስበ ፣ ነው ። ሰዎች ፣ ሲሠርዋቸው ፣ ባለማሰብ ፣ አጠጋግ
ተው ፣ በጣም ፣ ያቀራረቡዋቸው ፣ እንደሆነ ፣ በሙቀት ፣ ጊዜ ፣ ሲዘረ
ጋጉ ፣ እርስ ፣ በእርሳቸው ፣ ተነካክተው ፣ ይማቱና ፣ ይሰበራሉ ።

ሙቀት ፣ ሁሉን ፣ ነገር ፣ እያፍታታ ፣ ይዘረጋዋል ። ብርድ ፣ ግን ፣
ሁሉን ፣ ነገር ፣ እየወበጠ ፣ ያክራምተዋል ። ብርዋቆ ፣ የሞቀ ፣ ውኃ ፣
ሲጨምሩበት ፣ የሚሰበርበት ፣ ምክንያት ፣ የሞቀው ፣ ውኃ ፣ በውስጡ ፣
ሲፈስ ፣ ብርዋቆው ፣ ከታች ፣ ይሞቅና ፣ ይዘረጋል ፣ የሞቀው ፣ ውኃ ፣
ያልደረሰው ፣ የላይኛው ፣ ወገን ፣ ግን ፣ ቀድሞ ፣ እንደነበረ ፣ ሆኖ ፣
ይቀራል ። ስለዚህ ፣ የታችኛው ፣ ልስፋ ፣ ሲል ፣ የላይኛው ፣ ወገን ፣
ግን ፣ እምቢ ፣ ሲል ፣ በመካከሉ ፣ ብርዋቆው ፣ ይሰነጠቅና ፣ ይሰ
በራል ።

የበረዶ ፣ ፍሬ ፣ ከመሬት ፣ ላይ ፣ ሲቀመጥ ፣ ሳይመ·ዋመ·ዋ ፣ ብዙ ፣
ጊዜ ፣ ይቆያል ። አንሥታችሁ ፣ ከእጃችሁ ፣ ውስጥ ፣ ብታስቀምጡት ፣
ግን ፣ ቶሎ ፣ ይመ·ዋመ·ዋል ፤ የሚያመ·ዋመ·ዋውም ፣ በእጃችሁ ፣

Scanned with CamScanner

ውስጥ ፡ ያለው ፡ የሰውነታችሁ ፡ መቅኔት ፡ ነው ። የበረዶው ፡ ቅዝ
ቃዜ ፡ ደግሞ ፡ ለእጃችሁ ፡ ይሰማዋል ። እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ዝናም ፡
በሚዘንምበት ፡ ሰዓት ፡ ብዙ ፡ የቤት ፡ በር ፡ አልዘጋም ፡ እያለ ፡ ያስ
ቸግራል ፡ ምክንያቱም ፡ የዝናሙ ፡ ውኃ ፡ ላቦት ፡ እየሆነ ፡ ተንሥዶ ፡ በዕን
ጠቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገባና ፡ በሩን ፡ ስለሚያወፍረው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡
በክረምት ፡ ወራት ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ይቸገራል ። በበጋ ፡
ወራት ፡ ግን ፡ በበሩ ፡ ዕንጨት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የነበረው ፡ ውኃ ፡
ይደርቅና ፡ በሩ ፡ ተመልሶ ፡ ትክክል ፡ ይሻሻላል ።

ሴ ፡ ቶ ።

አንድ ፡ ውሉታ ፡ ቢስ ፡ ድኩላ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ድኩላ ፡ ሲሄድ ፡ በሸለቆ ፡
አንድ ፡ አዳኝ ፡ አገኘው ፡ መሣሪያውን ፡ ታጥቆ ።
ደመኛው ፡ መሆኑን ፡ ጠርጥሮ ፡ ድኩላ ፡
ሊያጠፋው ፡ ማሰቡን ፡ ወመቀ ፡ በመላ ።
ስለዚህ ፡ መንገዱን ፡ አሳብሮ ፡ እየሮጠ ፡
አንዲት ፡ ቁጥቋጦ ፡ ሥር ፡ ተኝቶ ፡ አደፈጠ ።
አዳኙም ፡ በፍጥነት ፡ ተከተለውና ፡
በሄደበት ፡ በኩል ፡ መንገዱን ፡ አቀና ።
ሥፍራውም ፡ የሚታይ ፡ ነበረ ፡ ገላጣ ፡
በዚያም ፡ በዚህ ፡ ቢሻው ፡ ድኩላውን ፡ አጣ ።
ኋላም ፡ ቢታከተው ፡ እያጉረመረመ ፡
ሴላ ፡ አውሬ ፡ ሊፈልግ ፡ ሄደ ፡ እያዘገመ ።
አዳኝ ፡ ወደ ፡ ሴላ ፡ ሲሄድ ፡ ተመልክቶ ፡
እዚያው ፡ ቁጥቋጦ ፡ ሥር ፡ እንዳለ ፡ ተኝቶ ፡
ሳይቸግረው ፡ ደርሶ ፡ ቀበጡ ፡ ድኩላ ፡
አንድ ፡ ጉርሻ ፡ እሚሆን ፡ ከቅጠሉ ፡ በላ ።
አዳኝ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ሲሰማ ፡ ከሽታ ፡
ተመልሶ ፡ አየና ፡ ያለበትን ፡ በታ ፡
ወዲያው ፡ አነጣጥሮ ፡ ቢተኩስ ፡ በዱባይ ፡
ድኩላውን ፡ መታው ፡ ቧጥይት ፡ ሽንጡ ፡ ላይ ።

መመታቱን ፡ ሲያውቀው ፡ አዳኙ ፡ ቢገድለኝ ፡
ተረድቼዋለሁ ፡ ያጠፋሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
እሱን ፡ ተጠግታ ፡ በዳነች ፡ ሕይወቴ ፡
እስኪ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ቅጠሉን ፡ መብላቴ ።
ደግ ፡ ለዋለልኝ ፡ መለስኩለት ፡ ክፉ ፡
ውሉታ ፡ የማያውቅ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ትርፉ ።
ብሎ ፡ በጥፋቱ ፡ እየተፀፀተ ፡
ድኩላው ፡ ተንጋሎ ፡ እያጓራ ፡ ሞተ ።
ሁልጊዜ ፡ ለክፉት ፡ አሳቡ ፡ እያደላ ፡
ተንኰልን ፡ የሚወድ ፡ ፍቅርን ፡ የሚጠላ ፡
ደግ ፡ ለዋለለት ፡ ክፉ ፡ የመለሰ ፡
ይሙት ፡ በሕሊናው ፡ እየተወቀሰ ።

የአታላይ ፡ ሰው ፡ ታማኝነት ።

በኪሱ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ድሀ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ የአንድ ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ወድቆ ፡ አግ
ኝቶ ፡ ቀለበቱን ፡ ይዞ ፡ ከሀብታሙ ፡ ዘንድ ፡ ሄደና ፡ እንዲህ ፡ አለው ።
ይህ ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ወድቆ ፡ አገኘሁት ፤ ከላዩ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ
ውን ፡ ፊደል ፡ ባንበው ፡ የእርስዎን ፡ ስም ፡ እንደሚጠራ ፡ ተመለከ
ትሁ ። ይህን ፡ ከማየቴ ፡ በፊት ፡ ለመሸጥ ፡ አስቤ ፡ ዋጋውን ፡ እባ
ክህ ፡ ገምትልኝ ፡ ብዬ ፡ ለአንድ ፡ ወርቅ ፡ ሠራተኛ ፡ በሳየው ፡ ከቀ
ለበቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ አልማዝ ፡ ፈልቅቀህ ፡ ብትሸጠው ፡ ዐሥር ፡
ሺ ፡ ብር ፡ ያወጣልሃል ፡ አለኝ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ወድቆ ፡ ያገኘሁት ፡
ቢሆን ፡ ከስቀረሁት ፡ ያው ፡ እንደመስረቅ ፡ ያህል ፡ መሆኑን ፡ ልቡ
ናዬ ፡ ስለሚያውቀውና ፡ ሕሊናዬም ፡ ስለማይፈቅድልኝ ፡ ቀለበትዎን ፡
ልመልስልዎት ፡ መጣሁ ፡ አለው ።

ሀብታሙ ፡ ሰውዬ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ተደንቆ ፡ ከመገረም ፡
ብዛት ፡ ናላው ፡ ዞረ ። እስኪ ፡ በሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትክክለኛ ፡
ሰው ፡ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ አይታችሁና ፡ ሰምታችሁ ፡ ታውቃላችሁን ? ጠፍ
ቶብኝ ፡ የነበረው ፡ ይህ ፡ ቀለበት ፡ አልማዙ ፡ ብቻ ፡ ቢሸጥ ፡ እሙ
ነት ፡ ነው ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ያወጣል ። ይህን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡
ገንዘብ ፡ እንደሚያወጣ ፡ እያወቀ ፡ አምጥቶ ፡ ለእኔ ፡ ለባለቤቱ ፡ መልሶ ፡

Scanned with CamScanner

መስጠቱ ፡ በእውነት ፡ ወዋ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እው
ትስ ፡ ምንም ፡ የተረፈኝ ፡ ሀብታም ፡ ብሆን ፡ ስለ ፡ ሽልማት ፡ ብዙ
እንኳንስ ፡ ከፀሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ ያቅርና ፡ የዚህን ፡ ግማሽ
ወይም ፡ ኩርማን ፡ እንደማልሰጠው ፡ አጥቶት ፡ አይደለም ። ገንዘብ
የሚያታልለው ፡ ሰው ፡ ቢሆንስ ፡ ኖሮ ፡ ያስቀረዋል ፡ እንጂ ፡ ቀለበ
ቱን ፡ ይዘ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ አይመጣም ፡ ነበር ። እንግዲህ
ይህ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይገበዋል ፡ ትላላችሁ ? የማበላቸው ፡ና ፡ የማጠጣ
ቸው ፡ የማለብሳቸውም ፡ አብረውኝ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የኖሩ ፡ እንደ ፡
ልጆቼ ፡ የምመለከታቸው ፡ ታማኞቼ ፡ የምላቸው ፡ የልጡኝ ፡ እሽ
ሮቼ ፡ ከገበታ ፡ ላይ ፡ ረስቼ ፡ ትቼው ፡ የሄድኩት ፡ እንድ ፡ መሐለቅ ፡
ሲያገኙ ፡ ይሰርቁኛል ። ከእኔ ፡ እጅ ፡ እንድ ፡ ሳንቲም ፡ ተቀብሎ ፡
የማያውቅ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የታማኝነት ፡ ሥራ ፡
ሠራልኝ ። ይኸውላችሁ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ለመንፈሳችን ፡ እንግዳ ፡
የሆነ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ጠባይ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ፡ እያለ ፡
ሀብታሙ ፡ ሰው ፡ ላገኛቸው ፡ ወዳጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ሲያጫውታቸው ፡ ሰነበተ ።

ለጊዜው ፡ ጉርሻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠውና ፡
ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ጠርቶ ፡ ዋና ፡ የግምጃ ፡ ቤት ፡
ሹም ፡ ብሎ ፡ ለገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ አደረገው ። ሀሥር ፡ ዓመት ፡
ሙሉ ፡ በፍጹም ፡ ታማኝነት ፡ ሲያገለግለው ፡ ኖረ ። አንድ ፡ ቀን ፡
ከግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ሥስት ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይዘ ፡ ይህ ፡ ታማኝ ፡
የነበረ ፡ ሰው ፡ ጠፋ ፡ ለጊታውም ፡ አንድ ፡ ወረቀት ፡ ጽሮ ፡ ትቶለት ፡
ሄደ ። በወረቀቱም ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ታል ፡ አንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ።

« ከልጅነቱ ፡ ጀምሬ ፡ የምመኘው ፡ ለሕይወቱ ፡ ሙሉ ፡ የሚ
« በቃኝ ፡ ብሎ ፡ ገንዘብ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በእጁ ፡ እንዲገባልኝ ፡ ነበር ።
« ቀለበትህን ፡ ወድቆ ፡ ያገኘሁት ፡ ዕለት ፡ ብሸጠው ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡
« እንደሚያወጣልኝ ፡ አላጣሁትም ። ግን ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ ለማግ
« ኘት ፡ ስል ፡ ነገሩን ፡ አመዛዝኜ ፡ ከንድ ፡ የእምነት ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡
« ታውለኛለህ ፡ ስል ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ አምጥቼ ፡ ሰጠሁህ ። እንዳ
« ሰብኩትም ፡ ሆነልኝ ። ይህን ፡ ገንዘብ ፡ ለመስረቅ ፡ የተመቸ ፡ ጊዜ ፡
« ስጠብቅ ፡ ሀሥር ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ታገሥሁ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ቀን ፡
« ሞላልኝ ። እኔን ፡ እይዛለሁ ፡ ብለህ ፡ በከንቱ ፡ አትድከም ፡ የሄድ
« ኩት ፡ ወደግልገኝበት ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ነው ።

እውነትም ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ መንገዱን ፡ አሰናድቶ ፡ ኖሮ ፡ እን
ዳመለጠ ፡ ቀረ ፡ ይባላል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በህብታሙ ፡ ሰው ፡ መን
ፈስ ፡ ውስጥ ፡ የሆነውን ፡ የአሳብ ፡ መበጥበጥና ፡ የአእምሮ ፡ መና
ወጥ ፡ በአሳብ ፡ መንገድ ፡ ስትከተሉት ፡ ትደርሱበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ጸሐፊስ ፡ በብርዕ ፡ ዘርዝሮ ፡ ሊያስረዳ ፡ አይችልም።

* ሽ ር ል ክ ።

ዘለዓለም ፡ ሙሉ ፡ ስሜም ፡ አይረሳ ፡
ከትልቅነቱ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡
በሰፈው ፡ መንግሥቱ ፡ ፀሓይ ፡ አትጠልቅም ፡
መንግሥቱ ፡ ሽኑ ፡ ነው ፡ አይነቃነቅም ።
እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይመጣም ፡
የወረሰኩት ፡ መንግሥት ፡ ያከራኛል ፡ በጣም ።
ይኖራል ፡ ታሪኬ ፡ በብዙ ፡ ተከብሮ ፡
የዘውዴ ፡ ብዛቱ ፡ አያልቅም ፡ ተቈጥሮ ።
አውሮፓ ፡ ሲጠበው ፡ ዕረፍት ፡ የማይወድ ፡
ከባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ የአኔ ፡ ጦር ፡ ሲሄድ ፡
የቱርክን ፡ ሠራዊት ፡ የሚያርበደብድ ።
የማይደክመው ፡ መድፌ ፡ ሴት ፡ ተቀን ፡ ሲያገሣ ፡
ለጎረቤቶቼ ፡ እንቅልፍ ፡ የሚነሣ ።
በዕውቀት ፡ በጉልበቱ ፡ እጅግ ፡ የምከራ ፡
ጠረኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ ማንንም ፡ አልፈራ ።
እንደዚህ ፡ እያለ ፡ በጎልማሳነቱ ፡
ሽርልክ ፡ የሚሉት ፡ ቀደሞ ፡ በሰዓቱ ፡
የተመካ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ፡ በጉልበቱ ።
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኖሮ ፡ መንግሥቱ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡
የቁርጥማት ፡ ሕመም ፡ አደረበትና ፡
ከባለሟሎቹ ፡ በጣም ፡ የሚደፍረው ፡
ሊያነክስ ፡ አየና ፡ እንዲህ ፡ ተናገረው ፡
እንግዲህ ፡ እግርህ ፡ ማንከስ ፡ ከጀመረ ፡
መንግሥቱም ፡ አንድነት ፡ መድከሙም ፡ አልቀረ ።

* ሽርልክ ፣ ሽርል ፣ ጅና ፣ የሚባለው ፣ የአበጻንያና ፣ የጀርመን ፣ አገሮች ፣ ንጉሥ ፣ ነው ።

Scanned with CamScanner

የማይሸነፈው ፡ ዲፕሎማት ፡ ንጉሥ ፡
እንዲህ ፡ ተናገረ ፡ ለዚህ ፡ ሲመልስ ፡
ሕመምተኛ ፡ ሆኖ ፡ እግሬ ፡ ቢያንክስ ፡
መንግሥቴ ፡ እንዳይመስልህ ፡ አብሮ ፡ የደከመ ፡
የጥበብን ፡ ያህል ፡ ጉልበት ፡ መች ፡ ጠቀመ ።
የተበጠበጠው ፡ በዘዴ ፡ ይጠናል ፡
ጦር ፡ ያጠፋውንም ፡ ፖሊቲክ ፡ ያቀናል ፡
ኃይል ፡ የማይበግረው ፡ በዕውቀት ፡ ይታዘዛል ፡
ሰው ፡ በናሳው ፡ እንጂ ፡ በእግሩ ፡ መች ፡ ይገዛል ።

ሻርልክ ፡ በጊዜው ፡ በጣም ፡ የተፈራ ፡
ኃያል ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ፡ ስሙ ፡ የተጠራ ።
ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሙሉ ፡ እያነሣ ፡ ጦር ፡
ዓለምን ፡ ሊገዛ ፡ ይደክም ፡ ነበር ።
ኋላ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አሳብ ፡ ከቶ ፡ የማይዘልቀው ፡
መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ መሸነፉን ፡ ሲያውቀው ፡
ግማሹን ፡ መንግሥቱን ፡ ላንዱ ፡ ልጁ ፡ አውርሶ ፡
በተረፈውም ፡ ላይ ፡ ወንድሙን ፡ አንግሦ ፡
አየሁት ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ለምንም ፡ አይረባ ፡
ከንቱ ፡ ነው ፡ አሉና ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ገባ ።
እዚያ ፡ ለነፍሱ ፡ አድሮ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ።
እየተወዛ ፡ ባለፈው ፡ ኃጢአቱ ፡
ንስሓና ፡ ጸሎት ፡ ጾም ፡ እያዙተረ ፡
በመንፈሳዊነት ፡ ተወስኖ ፡ ኖረ ።
በገዳምም ፡ ሳለ ፡ ይነሣና ፡ ቤጢት ፡
እዚያ ፡ እሚኖሩትን ፡ ብዙ ፡ መነኮሳት ፡
ተነሡ ፡ ጸልዩ ፡ ይበቃል ፡ መኝታ ፡
እያለ ፡ ቀስቅሶ ፡ ሁሉንም ፡ በተርታ ፡
ያስነሣቸው ፡ ነበር ፡ ቤሩን ፡ እየመታ ።
አንደኛው ፡ መነኩሴ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ደክሞት ፡
የቡን ፡ በር ፡ ሲመታ ፡ ዛሬ ፡ መነሣት ፡
አልችልም ፡ ደክሞኛል ፡ ብሎ ፡ ቢናገር ፡



ሻ ር ል ክ

Scanned with CamScanner

እሱ ፡ አልሰማ ፡ ብሎ ፡ ይማታ ፡ ጀመር ።
መነኩሴው ፡ ተነሥቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተቈጣ ፡
ቢታክተን ፡ ሸሽተን ፡ የዓለምን ፡ ጣጣ ፡
ከሰው ፡ ተለይተን ፡ ወደዚህ ፡ ብንመጣ ፡
ለዓለም ፡ ጤና ፡ ነሥተህ ፡ ሳይቸግርህ ፡ ደርሰ ፡
ፍጥረትን ፡ ስታምስ ፡ የኖርኸው ፡ ጊዜ ፡ አንሶ ፡
ደግሞ ፡ እዚህ ፡ መጣህ ፡ ወይ ፡ ልታሳይ ፡ አበሳ ፡
ወመል ፡ አልተው ፡ ብሎህ ፡ እንቅልፍ ፡ ልተኛሳ ?
እንግዲህ ፡ የት ፡ ይሆን ፡ የሚገኝ ፡ ዕረፍቱ ?
ለሰላም ፡ ነበረ ፡ ሰው ፡ ገዳም ፡ መግባቱ ።
ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ንጉሥ ፡ ትቶት ፡ ሄደ ፡ ስቆ ፡
መነኩሴው ፡ ክንጅቱ ፡ መመረሩን ፡ ዐውቆ ።

አንድ ፡ ረጅም ፡ ሰውና ፡ አንድ ፡ አጭር ፡ ሰው ።

አንድ ፡ ረጅም ፡ ጎበዝ ፡ ሰውና ፡ አንድ ፡ ድንክዩ ፡ ሰው ፡ ወዳ
ጆች ፡ ሆነው ፡ እየተረዳዱ ፡ አብረው ፡ ሊኖሩ ፡ ተስማሙ ። ምንም ፡
ነገር ፡ ቢመጣ ፡ ሳይለያዩ ፡ ደስታውንና ፡ መከራውን ፡ እኩል ፡ ሊ
ፈሉ ፡ ተዋዋሉ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አብረው ፡ እየተጓ
ዙ ፡ ሲሄዱ ፡ ሁለት ፡ ወንበዴዎች ፡ አገኙ ። ድንክዬው ፡ በጣም ፡
ኃይለኛና ፡ ደፋር ፡ ስለነበር ፡ አስቀድሞ ፡ እንደኛውን ፡ ወንበዴ ፡
መታው ፤ የተመታውም ፡ ወንበዴ ፡ ወዲያው ፡ ታጥቆት ፡ የነበ
ረውን ፡ ጎራዴ ፡ መዝዘ ፡ ድንክዬውን ፡ መታና ፡ ክንዱን ፡ ቈርጦ ፡
ጣለው ። ሁለተኛ ፡ ሊደግመው ፡ ሲሰነዝር ፡ ረጅሙ ፡ ሰው ፡ ደረሰና ፡
ሁኔቱንም ፡ ወንበዴዎች ፡ መትቶ ፡ ወዲያው ፡ ጣላቸው ። ድንክዬ
ውም ፡ ደሙን ፡ እያዘራ ፡ ቁሁለቱንም ፡ ወንበዴዎች ፡ ጭንቅላት ፡
ቈርጦ ፡ ጣለ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በማያውቁት ፡
አገር ፡ ሲሄዱ ፡ ሦስት ፡ ሻራቆች ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ይዘው ፡ ሲሄዱ ፡
አገኙ ። ድንክዬው ፡ ጠብ ፡ ሲነሣ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ አልደፈረም ፡
ግን ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሲፈሩ ፡ ሲቸር ፡ አዙንም ፡ ኡስቀድሞ ፡ እንደ

ኛውን ፡ ቁራቅ ፡ መታው ። ቁራቁም ፡ መለስ ፡ አለና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
በጡጫ ፡ ቢመታው ፡ አንድ ፡ ዐይኑን ፡ አፈረጠው ። ጓደኛው ፡ ሮጦ ፡
መጣና ፡ ሲደርስለት ፡ ቁራቆቹ ፡ አቋቋሙን ፡ አይተው ፡ ጉልበቱን ፡
ስለገመቱት ፡ ይዘውት ፡ የነበረውን ፡ ልጅ ፡ ጥለው ፡ ሸሹና ፡ አመለጡ ።
እሱም ፡ ባያመልጡኝ ፡ ሦስቱንም ፡ እገድላቸው ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ እየ
ፎከረ ፡ ሄደ ። ከቁራቆቹ ፡ እጅ ፡ የዳነውም ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ አመሰገ
ነው ፡ ድንክዬውን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳያመሰግነው ፡ ቀረ ። አሁንም ፡
ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሲሄዱ ፡ በአንድ ፡
ጉድባ ፡ ውስጥ ፡ ሲያልፉ ፡ ሽፍቶች ፡ ገጠሙዋቸው ። እነዚያም ፡ ከእነርሱ ፡
ጋር ፡ ሲደባደቡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቈዩ ። ግን ፡ ረጅሙ ፡ ሰው ፡ ኃይ
ለኛ ፡ በመሆኑ ፡ ሽፍቶቹ ፡ ተሸንፈው ፡ ሸሹ ። ድንክዬው ፡ በጣም ፡
ተደብድቦ ፡ ስለተጎዳ ፡ ሰውነቱ ፡ ሁሉ ፡ ዛለ ፡ እግሩም ፡ ተሰብሮ ፡ ያን
ክስ ፡ ጀመር ።

ረጅሙ ፡ ጎበዝ ፡ ከአንድ ፡ ቦታ ፡ ሳይ ፡ እንኳን ፡ ሰይቈስል ፡ ድን
ክዬው ፡ አንድ ፡ እጁ ፡ ተቈርጦ ፤ አንድ ፡ ዓይኑ ፡ ጠፍቶ ፡ አንድ ፡
እግሩ ፡ ተሰብሮ ፡ አካለ ፡ ጎደሎ ፡ ሆነ ። ረጅሙ ፡ ጎበዝ ፡ ድንክዬውን ፡
ጓዴ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠላት ፡ ገጥሞን ፡ የተደበደብን ፡
እንደሆነ ፡ ስማችን ፡ የሚመሰገንበትን ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ ገንዘብም ፡
እናገኛለን ፡ አለው ። ድንክዬው ፡ ግን ፡ መለሰና ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡
አንተ ፡ ምን ፡ ታደርግ ፡ ምስጋናውን ፡ አገኘህ ፡ እንጂ ፡ ጉዳቱ ፡
አልደረሰህም ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አካለ ፡ ጎደሎ ፡ የሆንሁት ፡ ጉዳቱ ፡ በጣም ፡
ተሰምቶኛል ። በተደበደብን ፡ ቍጥር ፡ ዋናው ፡ በትር ፡ ያረፈው ፡ በእኔ ፡
ላይ ፡ ነው ። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ያለው ፡ ክብርና ፡ ገንዘብ ፡ በአፍ
ንጫዬ ፡ ይውጣ ። የተረፈውን ፡ ገላዬን ፡ ይገር ፡ አቤቱ ፡ ብገባ ፡ ይሻል
ኛል ፡ ብሎት ፡ ተለያዩ ።

አትክልትና ፡ አረም ።

እንድ ፡ ሰው ፡ ከቤቱ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ የአትክልት ፡
ቦታ ፡ አሰናድቶ ፡ መሬቱን ፡ ቆፍሮ ፡ አፈሩን ፡ ካለሰለሰ ፡ በኋላ ፡ በየ
ዓይነቱ ፡ ዘር ፡ ፈልጎ ፡ የሚበላ ፡ አትክልት ፡ ደግሞ ፡ የሚያምር ፡ መል
ክና ፡ የሚጣፍጥ ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አበባ ፡ ዘራበት ። ጧት ፡

Scanned with CamScanner

ማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ ማታም ፡ ዐሐይ ፡ ሳትጠልቅ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ውኃ ፡ እየቀዳ ፡ አትክልቱን ፡ ያጠጣል ። አበባው ፡ አብቦ ፡ የሚበላውም ፡ ለምልሞ ፡ ለመንፊሱ ፡ ደስታ ፡ ለሥጋውም ፡ ጥቅም ፡ የሚያገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ድካሙን ፡ ለመርሳት ፡ ሰውዬው ፡ በጣም ፡ ይጓጓ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የዘራው ፡ መልካም ፡ ዘር ፡ ገና ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ሣርና ፡ ቅጠል ፡ በመካከሉ ፡ ጉፍ ፡ ብሎ ፡ እየበቀለ ፡ አትክልቱ ፡ በመልካም ፡ አበታቀል ፡ እንዳይወጣ ፡ ከለ ከለው ።

ሰውዬው ፡ ግን ፡ ከአትክልቱ ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ የወጣውን ፡ መጥፎ ፡ አረም ፡ ለማጥፋት ፡ ሲል ፡ ከጧት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ይሠራል ። በቀን ፡ ብዛት ፡ አረሙ ፡ መጥፋቱ ፡ ቀርቶ ፡ እያደር ፡ እየበረከተ ፡ ይሄድ ፡ ጀመር ። አውንም ፡ ተስፋ ፡ ሳይቈርጥ ፡ በብዙ ፡ ሲታገል ፡ ቈየ ፡ በመጨረሻው ፡ የአትክልቱን ፡ ቦታ ፡ አረሙ ፡ በሙሉ ፡ አለበሰው ። ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ሰውዬው ፡ እንደተሸነፈ ፡ ስለተረዳው ፡ ለካ ፡ የደከመውት ፡ በከንቱ ፡ ኖርዋል ። እግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ ካልባረከለት ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ቢለፋ ፡ ጥሬ ፡ እያገኝበትም ። ጎዘኔና ፡ ፀፀቱ ፡ እጅግ ፡ የበረታ ፡ ሆኖ ፡ ለልቤ ፡ በጣም ፡ ተሰማው ። ደስታዬ ፡ ከእኔ ፡ አልር ፡ ለወዳጆቼ ፡ ይተርፋል ፡ ብዬ ፡ ለተስፋዬ ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም ። አውን ፡ ግን ፡ የድካሜ ፡ ዋጋ ፡ ለዓይን ፡ ደስ ፡ የማያሰኝና ፡ ለምንም ፡ የማይጠቅም ፡ መጥፎ ፡ አረም ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ፡ ብሎ ፡ እንባውን ፡ አፍስሶ ፡ ቀረ ።

ልጆች ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ተረት ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል የዚህ ፡ ሰው ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በልጆቻቸው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ የጥበብ ፡ የሩቅርና ፡ የበጎ ፡ ጠባይ ፡ እርእያ ፡ አድሮበት ፡ በባሕርያቸው ፡ ራሳቸውን ፡ እስከ ብረው ፡ ዘመዶቻቸውንም ፡ ያስመሰግናሉ ፡ ብለው ፡ በማስብ ፡ ለፍተውና ፡ ተጠንቅቀው ፡ በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ እንዲያድጉላቸው ፡ ሲጣጣሩ ፡ ልጆቻቸው ፡ ግን ፡ አሳባቸው ፡ ሁሉ ፡ ከፋትና ፡ ብልግና ፡ ሆኖ ፡ ጠባያቸውም ፡ ተበላሽቶ ፡ ሲያገኙት ፡ ተስፋቸው ፡ እየተቈረጠ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ መረር ፡ ጎዘን ፡ የሚያሳየን ፡ መልካም ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

አ ን ድ ፡ ጅል ።

ክንድ ፡ ልብስ ፡ ሰፊ ፡ መደብር ፡ ገባና ፡
አንድ ፡ እውነተኛ ፡ ጅል ፡ ከመድረሱ ፡ ገና ፡
በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከልቡ ፡ እየሳቀ ፡
ልብስ ፡ ሰፊው ፡ የት ፡ ነው ? አለና ፡ ጠየቀ ።
ወዲያው ፡ ቀረበና ፡ ወደ ፡ ልብስ ፡ ሰፊ ፡
ሦስት ፡ የክት ፡ ቀሚስ ፡ አለኝ ፡ ያማረ ፡ ሰፋፊ ።
አስቤያለሁና ፡ ሳይጠብም ፡ ሳያጥር ፡
ክት ፡ እንድትሰፋልኝ ፡ ስፈቱ ፡ የሚያምር ።
ዋጋው ፡ እንዳይጎዳኝ ፡ ብረዳህ ፡ ይበጃል ፡
ቀሚስ ፡ እኔ ፡ ስሰጥህ ፡ ሌላው ፡ ምን ፡ ይፈጃል ?

ሽ ታ ና ፡ ውሽ ።

ሰው ፡ በዓይኖቹ ፡ ያያል ፡ በጆሮው ፡ ይሰማል ፤ በአፍንጫው ፡ ያሽታል ፤ በመላሱ ፡ ያጣጥማል ፡ በእጆቹ ፡ ይዳብሳል ። አንዳንድ ፡ ሰው ፡ ዓይኖቹ ፡ ደኅና ፡ ያዩለታል ። አንዳንድ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ዓይኖቹ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ አያዩለትም ። አንዳንድ ፡ ሰው ፡ ጆሮው ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማለታል ፤ አንዳንዱ ፡ ግን ፡ በመልካም ፡ አይሰማለትም ። አንዳንዱ ፡ ሰው ፡ አፍንጫው ፡ ሩቅ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ያሽታል ፤ አንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አፍንጫውን ፡ ከበሰበሰ ፡ ዕንቊላል ፡ ላይ ፡ ቢያደርገው ፡ እንኳ ፡ አይገማውም ። አንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ዓይኖቹን ፡ ጨፍኖ ፡ በእጁ ፡ በመዳሰስ ፡ ብቻ ፡ የነከው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉንም ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ይችላል ። አንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ዕንጨትን ፡ ከወረቀት ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ አይችልም ። አንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ የሚበላው ፡ ምግብ ፡ በጣም ፡ የጣፈጠ ፡ ቢሆን ፡ የጣዕሙን ፡ ጥሩነትና ፡ መጥፎነት ፡ በቶሎ ፡ ይለየዋል ። አንዳንዱ ፡ ግን ፡ ጣዕሙን ፡ ሳይለይ ፡ ይውጠዋል ።

በእንስሶች ፡ መካከልም ፡ እንደዚሁ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የሕዋሳት ፡ ልዩነት ፡ አለ ። ግን ፡ ጠረን ፡ አሽትተው ፡ በመለየት ፡ እንስሶች ፡ ከሰው ፡ በጣም ፡ ይበልጣሉ ። ሰው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በገኘ ፡ ጊዜ ፡

Scanned with CamScanner

ዓይነቱን ፣ ለመለየት ፣ ሲፈልግ ፣ በዓይኑ ፣ ይመለከተዋል ፣ ድምጥ ፣ ያለውም ፣ ነገር ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ በጆሮው ፣ ያዳምጣል ፤ በእፍንጫው ፣ የሚያሸተውና ፣ በመላሱ ፣ የሚቀምሰው ፣ ግን ፣ ከስንት ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ነው ። እንስሶች ፣ ግን ፣ ማንኛውንም ፣ ነገር ፣ ለይተው ፣ ለማወቅ ፣ ሲፈልጉ ፣ በእፍንጫቸው ፣ ነው ፣ የሚያሸቱት ። ፈረስ ፣ ልቡ ፣ በፈረ ፣ ጊዜ ፣ ፋር ፣ ይላል ። ይህንንም ፣ የሚያደርገው ፣ ደኅና ፣ እድርጎ ፣ እንዲያሸትለት ፣ አፍንጫውን ፣ ሲጠርግ ፣ ነው ። ከሸተተ ፣ በኋላ ፣ ግን ፣ ፈርቶት ፣ የነበረው ፣ ነገር ፣ ምን ፣ እንደሆነ ፣ ቶሎ ፣ ይለየዋል ።

ውሻም ፣ እንደዚሁ ፣ ጌታው ፣ ጠፍቶበት ፣ ሲሸ ፣ ዱካውን ፣ እያ ሸተተ ፣ ይፈልጋል ። የሄደበትንም ፣ ቦታ ፣ ሲያገኘው ፣ እያሸተተ ፣ ይከ ተላል ። በደረሰበት ፣ ጊዜ ፣ በዓይኑ ፣ ሲያየው ፣ ይደነግጣል ። ለይ ቶም ፣ ስለማያውቀው ፣ እንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ይጮኻል ፣ ወዲያው ፣ ደግሞ ፣ ያሸትና ፣ ያውቀዋል ። ካላሸተተ ፣ ግን ፣ በዓይኑ ፣ ብቻ ፣ አይቶ ፣ ጌታ ውን ፣ ለይቶ ፣ አያውቅም ።

በሬዎች ፣ እፈታቸው ፣ ሴቶች ፣ በሬዎች ፣ ሲታረዱ ፣ በዓይናቸው ፣ እያዩና ፣ ሲያኝሩም ፣ እየሰሙዋቸው ፣ ነገሩ ፣ አይገባቸውም ። ግን ፣ አንድ ፣ በሬ ፣ የታረደበትን ፣ ቦታ ፣ ሲረግጡ ፣ ያሸቱና ፣ እዚያ ፣ ቦታ ፣ በሬ ፣ መሞቱ ፣ ይገባቸዋል ። ስለዚህ ፣ ያንን ፣ ሥፍራ ፣ በአግራቸው ፣ እየቴፈሩ ፣ ከዚያ ፣ ቦታ ፣ እሺ ፣ ብለው ፣ አይሄዱም ።

ባልና ፣ ሚስት ፣ አንዲት ፣ ጥገት ፣ ላም ፣ ነበረቻቸው ፣ ሁል ጊዜ ፣ የምታልባት ፣ ሴቲቱ ፣ ነበረች ። አንድ ፣ ቀን ፣ ሚስቲቱ ፣ ታመመችና ፣ ባልዮው ፣ ሊያልባት ፣ ሥሠውን ፣ ይዘ ፣ ወደ ፣ ላሚቱ ፣ ዘንድ ፣ ሄደ ። ላምዋ ፣ ግን ፣ ሴቲቱ ፣ አለመሆንዋን ፣ ዐውታ ፣ ውቲን ፣ አልሰጥም ፣ ብላ ፣ ከለከለች ። ላምዋን ፣ ስታልባት ፣ ለብርድ ፣ ከላይ ፣ ትደርበው ፣ የነበረውን ፣ ልብስ ፣ ሲቲቱ ፣ ለባልዋ ፣ ሰጠችው ። ወንዱ ፣ ያንን ፣ ለብሶ ፣ ቢቀርባት ፣ ላምዋ ፣ አሸተተችውና ፣ ወተ ትዋን ፣ እንደልማድዋ ፣ ሰጠችው ። ይባላል ።

አዳኞች ፣ ውሾች ፣ ጠረኑን ፣ እያሸተቱ ፣ አውሬ ፣ የሄደበትን ፣ መንገድ ፣ ሲከተሉ ፣ ራቅ ፣ ብለው ፣ በጉን ፣ ይከተላሉ ፣ እንጂ ፣ ልከ ፣ አውሬው ፣ በረገጠው ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ አይሄዱም ። የአደን ፣ ልማድ ፣ የሌለው ፣ ሰው ፣ አውሬው ፣ በረገጠው ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ ው

ሻው ፣ አፍንጫውን ፣ ተክሎ ፣ እያሸተተ ፣ እንዲከተል ፣ ያስገደደው ፣ እንደሆነ ፣ ውሻው ፣ እምቢ ፣ ብሎ ፣ ይዘልና፡ ወደጉን ፣ ይሄዳል። ምክንያቱም፡ ሽታው ፣ በጣም፡ አድርጎ ፣ ለአፍንጫው፡ ስለሚስማው ፣ ጠረኑ ፣ ይበረታበትና፡ አውሬው ፣ የሄደበትን ፣ አግጣጫ ፣ ለማግኘት፡ ስለሚቸግረው፡ ነው። ከዳር ፣ የሆነ ፣ እንደሆነ ፣ ግን ፣ የአውሬው ፣ ጠረን፡ እየበረታ፡ የሚሄድበትን ፣ ወገን ፣ ስለሚለየው ፣ ለመከታተል፡ ይመቸዋል። እነሱም ፣ ራሳቸው ፣ ውሾች ፣ እርስ ፣ በርሳቸው ፣ የሚ ተዋወቁትና፡ አንዱን ፣ ካንደኛው ፣ የሚለዩት ፣ በጠረኑ ፣ ነው።

ትሉች፡ ደግሞ ፣ ለማሽተት ፣ የበለጠ ፣ ስጦታ፡ አላቸው። ንብ ፣ ወዲያና፡ ወዲህ ፣ ሳትል ፣ ወደምትፈልገው ፣ አበባ ፣ ዘንድ ፣ በቀ ጥታ ፣ ትሄዳለች። ምክንያቱም ፣ ከሩት ፣ ሽትዋት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በዓይንዋ ፣ አይታው ፣ አይደለም። ቁንጫ ፣ ትኂን፣ ትንኝ፣ እነዚህ ንም ፣ የመሰሉት ፣ ሁሉ፡ የሰው ፣ ጠረን፡ በጣም ፣ ከሩት ፣ ይሸታ ቸዋል። ማንኛውም ፣ ነገር ፣ ቢሆን ፣ ከሩት ፣ ሲሸተን ፣ ከአፍንጫ ችን ፣ የሚደርሰው ፣ የጠረኑ ፣ ብናኝ፡ በጣም ፣ ትንሽ ፣ ነው። ግን ደግሞ ፣ ትሉቹ ፣ ከሩት ፣ ሲሸታቸው ፣ ከአፍንጫቸው ፣ የደረሰው ፣ የሽታ ፣ ብናኝ፡ ምን ፣ ያህል ፣ ትንሽና፡ ሬቂት ፣ ይሆን ፣ ?

ሌ ፣ ቶ ።

ጀ ን ጂ ስ ካ ን ።

መጀመሪያ ፣ የሞጎልን ፣ መንግሥት ፣ የመሠረተ፡ ጀንጂስካን ፣ የሚባለው ፣ ንጉሥ ፣ ጦርነት ፣ በጣም ፣ ይወድ ፣ ነበር፤ ርኅራኄ ፣ አልነበረውም ። ማነኛውም፡ ልጅ ፣ ቢሆን ፣ በሕፃንነቱ፡ ወራት ፣ ባደ ግሁ ፣ ጊዜ ይህን ፣ እሠራለሁ ፣ እያለ፡ መመኘት ፣ በሁሉ ፣ ሰው ፣ የሚ ደርስ፡ ልማድ ፣ ስለሆነ ፣ አንድ፡ ቀን ፣ ጀንጂስካን ፣ ከጓደኞቹ፡ ጋር ተቀምጦ ፣ ሲጫወት ፣ ከመካከላቸው ፣ አንዱ ፣ ልጅ፡ እኔ፡ ትልቅ ፣ በሆ ንክ ፣ ጊዜ፡ ጥሩ፡ ፈረስ፡ ጭኜ፡ ጥሩ፡ ጦር፡ ይገር፡ በፈረሴ፡ ላይ፡ ተቀ ምጪ፡ በጫካ፡ ውስጥ፡ እየጋለብሁ፡ አውራ፡ አድናለሁ። ከሁሉም፡ነገር፡ አብልጪ፡ የምወደውና፡ የምመኝው፡ ይህን፡ ብቻ፡ ነው፡ ብሎ፡ ተናገረ።

ጀንጂስካንም፡ ተቀበለና፡ ይህ ፣ የአንተ፡ ምኞት፣ የሴት፡ ምኞት ፣ ነው፡ እኔስ ፣ ባደግሁ ፣ ጊዜ ፣ ብዙ ፣ ወታደሮች ፣ ሰብስቤ ፣ ጦርነት ፣ እየገጠምሁ፡ ጠላቶቼን ፣ ማሸነፍ፡ እኔ ፣ ስከተላቸው ፣ እነሱ ፣ ሲሸሹ፡

Scanned with CamScanner

ማየት ፤ ገንዘባቸውን ፡ መዝረፍ ፡ ዘመዶቻቸውም ፡ ተጨንቀው ፡ የሚ
ደርሱበት ፡ ቦታ ፡ እያጡ ፡ ሲላቀሱ ፡ መመልከት ፤ ፈረሶቻቸውን ፡
እየነጠቁ ፡ መቀመጥ ፤ ልጆቻቸውንና ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ማርኬ ፡
ባሮቼ ፡ ግድረግ ፤ የእኔ ፡ ወገኖች ፡ የእነሱን ፡ ወገኖች ፡ ሲያጠቋቸው ፡
እያየሁ ፡ መሰቅ ፡ የእኔ ፡ ምኞት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለንደኞቹ ፡
አሳወቃቸው ፡ ይባላል ። ትልቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጀንጂስካን ፡ ይህ ፡
ሁሉ ፡ ምኞቱ ፡ ተፈጽሞለታል ።

የውኃ ፡ ጉዞ ።

ክንፉሲውስ ፡ የሚባለው ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ትልቁ ፡
የቺና ፡ አገር ፡ ፈላስፋ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከወንዝ ፡ ዳር ፡
ተቀምጠ ፡ ውኃውን ፡ እየተመለከተ ፡ ሲተክዝ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ደረሱና ፡
መምህር ፡ ሆይ ፡ የሚፈሰውን ፡ ይህን ፡ የወንዝ ፡ ውኃ ፡ የምትመለ
ከተው ፡ ስለምንድነው ? ፡ ምን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አገኘህበት ? የወንዝ ፡
ውኃ ፡ ዋንትም ፡ እንዲህ ፡ ነበር ፡ ዛሬም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ወደፊትም ፡
ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ፡ አይለወጥም ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ክንፉሲውስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

አሁን ፡ የተናገራችሁት ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ ነው ። የወንዝ ፡ ውኃ ፡
ዋንትም ፡ ዛሬም ፡ ወደፊትም ፡ እንደዚሁ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ፡ አይለ
ወጥም ። ይህንንም ፡ የሚስተው ፡ ሰው ፡ የለም ። ግን ፡ በፈሳሽነት ፡
የሚንዘው ፡ የወንዝ ፡ ውኃና ፡ እውነትን ፡ የምታስረዳ ፡ የፍልስፍና ፡
ትምህርት ፡ የሚመሳሰሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቀው ፡
አይመስለኝም ። የወንዞች ፡ ውኃ ፡ ሁሉ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ሁልጊዜ ፡
ወደፊቱ ፡ ይገሠግሣል ። ግሥገሣውም ፡ ሴሊትም ፡ ሆነ ፡ ቀንም ፡
ሆነ ፡ አያቋርጥም።በመጨረሻም፡ከሰፊው፡የውቅያኖስ፡በሕር፡ውስጥ፡ገብቶ፡
ይቀላቀልና ፡ ይጠፋል ። እውነትን ፡ የምታስረዳ ፡ ትምህርትም ፡ እንዲ
ዚሁ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ስትወርድ ፡ ስትዋረድ ፡ ከትው
ልድ ፡ ጋር ፡ ተያይዛ ፡ መጥታ ፡ እስከኛ ፡ ደረሰች ። እኛም ፡ ደግሞ ፡
ለሚከተሉት ፡ ልጆቻችን ፡ ለማስተማርና ፡ ለማስረዳት ፡ ብለን ፡ ይኸው ፡ እን
ደከማለን ። ልጆቻችን ፡ ደግሞ ፡ በተራቸው ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ ለሚመጣው ፡

ትውልድ ፡ አስተምረው ፡ ያወርሳሉ ፤ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡
ትውልድ ፡ እስከ ፡ ተፈጸመ ፡ ድረስ ፡ ይህች ፡ እውነትን ፡ ለሰው ፡
ልጆች ፡ የምታስረዳ ፡ ትምህርት ፡ ክትተላለፍ ፡ ትናራለች ።

አቡንና ፡ ወንበዴ ።

ተፈርዶበት ፡ ብአስር ፡ ቤት ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ወንበዴ ፡
ከወህኒ ፡ አምልጠ ፡ ወጣና ፡ ተደብቆ ፡ ሰንብቶ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አለ
ባበሱንና ፡ አካሄዱን ፡ የሚጠራበትንም ፡ ስሙን ፡ ለውጠ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡
ወጣ ። ፖሊሶች ፡ ሲፈልጉት ፡ ሰንብተው ፡ ነበርና ፡ ዐውቀውት ፡ ተክ
ታተሉት ። እሱም ፡ መንገድ ፡ እየለዋወጠ ፡ ሲቅበዘበዝ ፡ ከአንድ ፡
አቡን ፡ ግቢ ፡ ደረሰ ። ጊዜው ፡ መሽቶ ፡ ግን ፡ የአቡኑ ፡ ግቢ ፡ በሮች ፡
እንደልማዳቸው ፡ ገና ፡ አልተዘጉም ፡ ነበርና ፡ ወንበዴው ፡ ደኅና ፡
ሰው ፡ መስሎ ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ ገባ ። አገልጋይ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ መነ
ኩሴ ፡ አይቶት ፡ ማነህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ወንበዴው ፡ መጀመሪያ ፡
የሚመልሰው ፡ አጥቶ ፡ ደነገጠና ፡ ተቸገረ ፤ ወዲያው ፡ አፉ ፡ እን
ዳመጣለት ፡ ከአቡኑ ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ እፈልጋለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ከእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ቤት ፡ አርፎ ፡ አቡኑ ፡ ወዲያው ፡ ተቀበሉ
ትና ፡ የመጣህበት ፡ ጉዳይ ፡ ምንድነው ፡ ? ብለው ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡
መለሰ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፤

እኔ ፡ ወንበዴ ፡ ነኝ ፡ ከወህኒ ፡ አምልጬ ፡ ፖሊሶች ፡ ሊይዙኝ ፡
ተከታትለውኛል ። ደብቀህ ፡ እድነኝ ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ እገድልሃለሁ ።

አቡኑም ፡ መልሰው ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ አርጅቻለሁ ፡ ከእንግ
ዲህ ፡ ወዲያ ፡ ሞትን ፡ አልፈራም ። ግን ፡ ብመለከትህ ፡ ፊትህ ፡ ከሲታ ፤
ልብስህ ፡ ደባደቦ ፤ ሰውነትህም ፡ የተጎሳቆለ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ልቤ ፡
በጣም ፡ አዘነልህ ። በል ፡ አሁንም ፡ እዚያ ፡ ጓዳ ፡ ገብተህ ፡ ጥቂት ፡
ዕረፍት ፡ አድርግ ፡ የምትበላውንም ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብለው ፡ አስተናገዱት ።

ፖሊሶቹ ፡ ወንበዴው ፡ ከአቡኑ ፡ ግቢ ፡ ሲገባ ፡ ክሩቅ ፡ አይተ
ውት ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አቡኑን ፡ በማክበር ፡ ገብተው ፡ ግቢውን ፡ ሲፈ
ትሹ ፡ ሰላልደፈሩ ፡ ተመልሰው ፡ ሄዱ ። ወንበዴው ፡ ፊቱን ፡ በልቶ ፡
ካረፈ ፡ በኋላ ፡ አቡኑ ፡ ሄደው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መከሩት ። "ልጄ ፡

Scanned with CamScanner

ሆይ ፡ አንተን ፡ በየሁህ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዘንኩልህ ። ብርዱ ፡ ከአን
ጀትህ ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ወባ ፡ ያንቀጠቅጥሃል ። በአንድ ፡ በኩል ፡
ደግሞ ፡ ረኃቡ ፡ አንጀትህን ፡ ይበረቡረዋል ። እየተከታተሉ ፡ እንደ ፡
ተኵላ ፡ ያሳድዱሃል ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ የባሰ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ እኔን ፡
የሚያሳዝነኝ ፡ በኃጢአትህ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ዕድሜህን ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡
ከፈጀህ ፡ በኋላ ፡ በላይኛው ፡ መንግሥት ፡ ደግሞ ፡ ተፈርዶብህ ፡ ነፍ
ስህ ፡ በመኰንኗ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አባክህ ፡ ለወደፊቱ ፡ ይቅርብህ ፡ ከፉ ፡
ሥራ ፡ አትሥራ ። ላለፈው ፡ ኃጢአትህም ፡ ንስሓ ፡ ግባ ።

ወንበዴውም ፡ ለአቡኑ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፤ "ይህን ፡
ለማድረግ ፡ አልችልም ፤ ክፉ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ልማድ ፡ ሆኖብኛ
ልና ፡ ልተውህ ፡ ብለው ፡ እሺ ፡ አይለኝም ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
ወንበዴ ፡ ሆኜ ፡ ኖሬያለሁ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያም ፡ ደግሞ ፡ ሳልለ
ወጥ ፡ ወንበዴ ፡ እንደሆንሁ ፡ እሞታለሁ ።"

አቡኑ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ በመስማታቸው ፡ ፈታቸውን ፡
አማተቡና ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ አዘኑ ። እንደልማዳቸው ፡ የቤታቸ
ውን ፡ በሮች ፡ ሁሉ ፡ ከፋፈቱና ፡ ሳይዘጉ ፡ ለወንበዴው ፡ የሚተኛበት ፡
ቦታ ፡ ሰጥተው ፡ ከመኝታ ፡ ቤታቸው ፡ ገብተው ፡ ተኙ ።

እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ወንበዴው ፡ ተነሥቶ ፡ በየቤቱ ፡ ክፍ
ሎች ፡ እየገባ ፡ ዕቃ ፡ ሲያማርጥ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፤ በብር ፡ የተሠራ ፡
ባለ ፡ ጌጥ ፡ የሆነ ፡ ትልቅ ፡ የሸማ ፡ ማስቀመጫ ፡ አግኝቶ ፡ እሱን ፡
አንሥቶ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ እያዳመጠ ፡ ከሰለለ ፡ በኋላ ፡ አቡኑን ፡ ብገድ
ላቸው ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ አላገኝበትም ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ብሸጠው ፡
ገንዘብ ፡ ያወጣልኛል ፡ ብሎ ፡ ተደብቆ ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ።

ፖሊሶቹ ፡ ከበር ፡ ይመለሱ ፡ እንጂ ፡ ሄደውም ፡ አልሄዱ ፤ ከአ
ቡኑ ፡ ግቢ ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡ አድፍጠው ፡ ይጠባበቁት ፡ ኖሮ ፡ ሲወጣ ፡
አይተውት ፡ ደረሱበትና ፡ ያዙት ። ሲፈትሹት ፡ ያ ፡ የሰረቀው ፡ በን
ጹሕ ፡ ብር ፡ የተሠራው ፡ የሸማ ፡ ማስቀመጫ ፡ ከለበሰው ፡ ደበደቦ ፡
ውስጥ ፡ ተጠቅልሎ ፡ ተገኘ ። እሱ ፡ ግን ፡ አልሰረቅሁም ፡ ብሎ ፡ ከደ ።
ፖሊሶቹ ፡ እየደበደቡ ፡ ወደ ፡ አቡኑ ፡ ዘንድ ፡ ይዘውት ፡ ሄዱ ። ወን
በዴው ፡ ክእቡኑ ፡ ፊት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የሚያገኘውን ፡ ውርደት ፡
አስቦ ፡ ከድንጋጤ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ፈገዘ ፡ በድኑን ፡ እየተንተ

ሄደ ። ከአቡኑ ፡ ዘንድ ፡ ሲደርሱ ፡ ይህ ፡ የሸማ ፡ ማስቀመጫ ፡ የእር
ስዎ ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ ? ብለው ፡ ፖሊሶቹ ፡ ጠየቋቸው ። አቡኑም ፡
አዎን ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱ ። እንግዲያውስ ፡ ተሰርቆ ፡ ከሌባ ፡
እጅ ፡ አገኘነው ፡ ሌባውም ፡ ይኸውና ፡ ብለው ፡ እየገፈተሩ ፡ እፊታ
ቸው ፡ አቁረቡት ። ሌባው ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍስ ፡ አን
ገቱን ፡ አቀርቅሮ ፡ ቆመ ። አቡኑ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እየሮጡ ፡ ወደ ፡
ቤታቸው ፡ ገብተው ፡ የተሰረቀውን ፡ የሚመስል ፡ በብር ፡ የተሠራ ፡
ሌላ ፡ የሸማ ፡ ማስቀመጫ ፡ ይዘው ፡ ወጡና ፡ ወዳጇ ፡ ሆይ ፡ ምነው ፡
አንዱን ፡ ብቻ ፡ ይዘህ ፡ ሄድህ ፡ እኔ ፡ የሰጠሁህ ፡ ሁሉንም ፡ ነበር ፡
እክ ፡ ብለው ፡ ለሌባው ፡ ሰጡት ።

ሌባው ፡ ይህ ፡ በአሳቡ ፡ በፍጹም ፡ ያልነበረ ፡ ነገር ፡ ሲደረግ ፡
በየ ፡ ጊዜ ፡ ስቅ ፡ ስቅ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰና ፡ እንባውን ፡ እያጎረፈ ፡ ይዛ
ችሁኝ ፡ ሂዱ ፡ እኔ ፡ ሌባ ፡ ነኝ ፡ ይህንንም ፡ ዕቃ ፡ ሰርቄዋለሁ ።
እኒህ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በእውነት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያደሩ ፡ ብፁዕ ፡ ሰው ፡
ናቸው ፡ ብሎ ፡ ለፖሊሶቹ ፡ ተናገረ ። ፖሊሶቹም ፡ እያዳፉ ፡ ሲወስ
ዱት ፡ ወደ ፡ አቡኑ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ አየና ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ብለው ፡
ይቅርታ ፡ ያድርጉልኝ ፡ በጸሎትዎም ፡ አይርሱኝ ፡ አማልደው ፡ ከፈ
ጣሪ ፡ ያስታርቁኝ ፡ ብሎዋቸው ፡ ሄደ ።

ልጆች ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ከቅጣት ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡
የደግነት ፡ ሥራ ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ከክፋት ፡ ወደ ፡ በጎነት ፡ እንደ
ሚመልሰው ፡ ያስረዳናል ።

አንድ ፡ ንጉሥና ፡ አንድ ፡ ሊቅ ።

ስሙ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ደራሲ ፡ እጅ ፡ ሊነሣ ፡
ወደ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። ንጉሡ ፡ በደስታ ፡ ተቀበለውና ፡
የምሳ ፡ ሰዓት ፡ ሲደርስ ፡ ሊቁን ፡ ሰው ፡ አጠገቡ ፡ አስቀምጦ ፡ ከእሱ ፡
ጋር ፡ በአንድ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ምሳውን ፡ አበላው ። መኳንንቶቹና ፡
ባለሙዋሎቹ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ተቀምጦ ፡ ሲበላ ፡ አይ
ተው ፡ በጣም ፡ ደኃቸው ። በሕልማችን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በውናችን ?

Scanned with CamScanner

እያሉ ፡ ዓይናቸው ፡ ያየውን ፡ ለማመን ፡ ቸገራቸው ። ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ክብር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለማንኛውም ፡ ትልቅ ፡ መኰንን ፡ ሲሰጠው ፡ አላየንም ። በምን ፡ ምክንያት ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ተሰጠው ፡ ብሎ ፡ አንዱ ፡ ባለሟል ፡ ንጉሡን ፡ ጠየቀው ። ንጉሡም ፡ መለሰና ፡ መኳንንቶቼንና ፡ ባለሟሎቼን ፡ የፈጠርኋቸው ፡ እኔ ፡ ነኝ ። ፈጠርኋቸው ፡ ማለቴም ፡ ማንኛውንም ፡ ድሀ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ከወደድሁትና ፡ ካቀረብሁት ፡ ከድህነቱ ፡ አንሥቼ ፡ መኰንንና ፡ ሀብታም ፡ ላደርገው ፡ እችላለሁ ፡ ስል ፡ ነው ። ይህን ፡ የምታዩትን ፡ ሊቅ ፡ ሰው ፡ ለመፍጠር ፡ የሚችል ፡ ግን ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ የእርሱ ፡ ክብር ፡ የበለጠ ፡ መሆኑ ፡ ብሎ ፡ አጠገቡ ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ተናገረ ፡ ይባላል ።

ጂንጂስካንና ፡ ለማዳ ፡ አሞራ ።

ትልቁ ፡ ጂንጂስካን ፡ የሞንጎል ፡ ንጉሥ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ዘምቶ ፡ ሲመለስ ፡ ከወታደሮቹ ፡ ብዙዎች ፡ አስከትሎ ፡ ከጫካ ፡ ገባና ፡ አውሬ ፡ ሲያድን ፡ ውሎ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ሲሆን ፡ ለመንቸራቸር ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ሲሄድም ፡ ያለ ፡ አሽከር ፡ ብቻውን ፡ ነበር ። ከበስተኋላው ፡ ግን ፡ ለአደን ፡ የሚረዳ ፡ ተከትሎት ፡ ነበር ፡ የአሞራ ፡ ለማዳ ። አፋፍ ፡ ለአፋፍ ፡ ሲሄድ ፡ ተራራ ፡ እየዘረ ፡ ውኃ ፡ ጠማውና ፡ በጣም ፡ ተቸገረ ። ምንጭ ፡ ያለበት ፡ ቦታ ፡ አይቶ ፡ ነበረና ፡ ወደዚያ ፡ ለመሄድ ፡ መንገዱን ፡ አቀና ። ምንጩን ፡ ግን ፡ አገኘው ፡ ደርቆ ፡ በቀስታ ፡ ውኃው ፡ ሲንቧረቧር ፡ ባንዳንድ ፡ ጠብታ ። ጂንጂስካን ፡ በናጥነት ፡ ወርዶ ፡ ከፈረሱ ፡ አጎንበሰና ፡ ገና ፡ ከመድረሱ ፡ ትንሽ ፡ የብር ፡ ዋንጫ ፡ አውጥቶ ፡ ክኪሱ ፡

ደቅኖ ፡ ሲጠብቅ ፡ ጓጒቶ ፡ በችኮላ ፡ ጥቂት ፡ አንደቀረው ፡ ዋንጫውን ፡ ሊሞላ ፡ ሳያስበው ፡ ድንገት ፡ ከላይ ፡ በኩል ፡ መጥቶ ፡ በክንፉ ፡ ቢመታው ፡ አሞራው ፡ ተነሥቶ ፡ ዋንጫው ፡ ወደቀና ፡ ውኃውም ፡ ፈሰሰ ። ንጉሡ ፡ ተናዶ ፡ ደሙ ፡ ደፈረሰ ። ውኃ ፡ በጣም ፡ አርጎ ፡ ጠምቶት ፡ ነበርና ፡ ራሱን ፡ ነቅንቆ ፡ መልሶ ፡ እንደገና ፡ በቶሎ ፡ አነሣና ፡ ዋንጫውን ፡ ደቀነ ፡ ተጠራቀመና ፡ ግማሽ ፡ እንደሆነ ። ደገመና ፡ አሁንም ፡ ቢመታው ፡ በክንፉ ፡ ተደፍቶ ፡ ወደቀ ፡ የብር ፡ ዋንጫው ፡ በፋ ። ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ስለተሳቀቀ ፡ ነገሩ ፡ ቸግሮት ፡ በጣም ፡ ተጨነቀ ። በእጁ ፡ ያሳደግሁት ፡ ይህ ፡ ለማዳ ፡ አሞራ ፡ ስለምን ፡ ይሠራል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ? ያጫወተኝ ፡ መስለት ፡ ወይም ፡ የማልማት ፡ ሊገድለኝ ፡ ነውነ ፡ በውኃ ፡ ጥማት ! ብሎ ፡ ተከዘና ፡ አሁንም ፡ መልሶ ፡ ሦስተኛ ፡ ሞከረ ፡ ሊቀዳ ፡ አጎንብሶ ። ደገመና ፡ አሞራው ፡ ሦስተኛ ፡ አፈሰሰ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ንጉሡ ፡ ቀጣው ፡ በጣም ፡ ባሰ ። በንዴት ፡ አኳኋን ፡ ሰይፉን ፡ ወዲያው ፡ መዘዘ ፡ በግራ ፡ ዋንጫውን ፡ በቀኝ ፡ ሰይፉን ፡ ይዞ ፡ ውኃውን ፡ ሊቀዳ ፡ አሁንም ፡ አሞራ ፡ የሰይፍ ፡ ስለት ፡ አይቶ ፡ ለነፍሱ ፡ ሳይፈራ ፡ እራተኛ ፡ ጊዜ ፡ ለማፍሰስ ፡ ቢመጣ ፡ ንጉሡ ፡ ተሳድቦ ፡ በንዴት ፡ በቀጣ ፡ በኃይል ፡ አሞራውን ፡ መታና ፡ ገደለው ። የውኃውም ፡ ጥማት ፡ በጣም ፡ ቢያቃጥለው ፡ መጠበቅ ፡ ተስኖት ፡ እንዳንዱን ፡ ጠብታ ፡ በቶሎ ፡ ለመቅዳት ፡ ያን ፡ የምንጩን ፡ ቦታ ፡

Scanned with CamScanner

በእጆቹ ፡ ፈንቅሎ ፡ ድንጋዩን ፡ ቢያነሣ ፡
ተጠቅሎ ፡ አገኘ ፡ የአንድ ፡ እባብ ፡ እሬሣ ።
በድንጋጤ ፡ ብዛት ፡ ጠፉና ፡ ጥማቱ ፡
በጣም ፡ ተፀዕኖ ፡ በዚህ ፡ በስሕተቱ ፡
አሞራውን ፡ ይዘ ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ።
በጎዘንም ፡ ብዛት ፡ ተከዘና ፡ ገብቶ ፡
ለወታደሮቹ ፡ ሬሣውን ፡ ሰጥቶ ፡
እዩት ፡ ተቈጥቼ ፡ ብሰሃዘር ፡ እጄን ፡
ከሞት ፡ ያዳነኝን ፡ ገደልሁት ፡ ወዳጀን ።
በነደደው ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ምክርመራ ፡
ቸኩሎ ፡ በቀጣ ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡
ጥፋትና ፡ ጉዳት ፡ ፀፀት ፡ እንዲያፈራ ፡
ዛሬ ፡ ደኅና ፡ አድርጌ ፡ ተረዳሁ ፡ ብሎዋቸው ፡
ያሞራውን ፡ ታሪክ ፡ አዝኖ ፡ አጫወታቸው ።
ካለፈ ፡ በኋላ ፡ እንዳትናደዱ ፡
ቁጣ ፡ ሲያገኛችሁ ፡ ትዕግሥትን ፡ ውደዱ ።

መጥፎ ፡ አየር ።

በመስኩብ ፡ አገር ፡ ኒክልስክዩ ፡ በሚባል ፡ ገጠር ፡ አንዲት ፡
ልጅ ፡ አገረድ ፡ ከጒድጓድ ፡ ውኃ ፡ ስትቀዳ ፡ መቅጃው ፡ ገመዱ ፡
ተበጥሶ ፡ ከጒድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ ። ልጅቱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
ለመነችና ፡ እሱ ፡ በብልሃት ፡ አድርጎ ፡ የገመድ ፡ መያያዣ ፡ አበጀላትና ፡
እሱን ፡ ጨብጣ ፡ መቅጃውን ፡ ልታወጣ ፡ ከጒድጓዱ ፡ ውስጥ ፡
ወረደች ። ሰውዬው ፡ የጨበጠችውን ፡ ገመድ ፡ ከውሃ ፡ ሆኖ ፡ ቀስ ፡
በቀስ ፡ ወደታች ፡ እየለቀቀላት ፡ ከውኃው ፡ አጠገብ ፡ ስትደርስ ፡ የሱ ፡
ንጠለጠለችበት ፡ ገመድ ፡ ለሰውዬው ፡ በጣም ፡ ስለቀለለው ፡ ጎንበስ ፡
ብሎ ፡ ወደ ፡ ጒድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ቢመለከት ፡ ልጅቱ ፡ ከገመዱ ፡
ላይ ፡ ወድታ ፡ ከውኃው ፡ ውስጥ ፡ ተደፍታ ፡ ተመለከተ ፡ ደነገጠና ፡
እየመላለሰ ፡ ቢጠራት ፡ ምንም ፡ ቃል ፡ ሳትመልስለት ፡ ቀረች ። ቀኑም ፡
በዓል ፡ ኖሮ ፡ የመንደሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ስለሄዱ ፡ ቢጣራ ፡ የሚደርስለት ፡ ሰው ፡ አጣ ። በኋላ ፡ ፈረስ ፡ ልጓሚ ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እቤት ፡ ቀርቶ ፡ ኖሮ ፡ ሰማና ፡ መጣለት ።
ፈረስ ፡ ለጓሚው ፡ ገመዱን ፡ ከውሃ ፡ ሆኖ ፡ ያዘለትና ፡ ሰውዬው ፡
እንደ ፡ ልጅቱ ፡ በገመዱ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ከጒድጓዱ ፡ ውስጥ ፡
ወረደ ። እሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ከውኃው ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ ገመዱን ፡
ለቆ ፡ ተወረወረና ፡ እልጅቱ ፡ አጠገብ ፡ በአፍንጫው ፡ ተደፍቶ ፡
ወደቀ ። ይህን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ፈረስ ፡ ለጓሚው ፡ ደንግጦ ፡ እየሮጠ ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄዶ ፡ ቀዳሴ ፡ ይሰሙ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡
ጠራቸው ። እነሱም ፡ ቀዳሴ ፡ አልቆ ፡ መውጣታቸው ፡ ስለነበረ ፡
ሮጠው ፡ ሁሉም ፡ ከጒድጓዱ ፡ አጠገብ ፡ ተሰበሰቡ ። ልጅቱና ፡ ሰውዬው ፡ ከጒድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ሲገቡ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ እግኝቷቸው ፡ እንደ
ወደቁ ፡ ለማወቅ ፡ ቸገራቸው ። ከመካከላቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከጒ
ድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ እገባለሁ ፡ ብሎ ፡ ገመዱን ፡ ከወገቡ ፡ ቁቦቶ ፡
ጋር ፡ አጥብቆ ፡ አስሮ ፡ ገመዱን ፡ ከውጭ ፡ ሰዎች ፡ ይዘው ፡ ቀስ ፡
በቀስ ፡ እየለቀቁለት ፡ ወረደ ። እዚያ ፡ የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
የሚሠሃኑን ፡ ነገር ፡ ለማየት ፡ የጒድጓዱን ፡ ዙሪያ ፡ ከብበው ፡ ቀኑል
ቀኑል ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ።
እሱም ፡ ከውኃው ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ ተገልብጦ ፡ በአፍንጫው ፡
ወደቀ ። ግን ፡ ገመዱ ፡ ከወገቡ ፡ ላይ ፡ ታስሮ ፡ ስለነበር ፡ መገልበጡን ፡
ሲያዩ ፡ ገመዱን ፡ የያዙት ፡ ሰዎች ፡ ቶሎ ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ጎትተው ፡ አወጡት ። ሲጎትቱትም ፡ ሰውነቱ ፡ እንደ ፡ ሬሣ ፡ ሆኖ ፡
ራሱ ፡ ቀኑልቀኑል ፡ ተዘቅዝቆ ፡ እየተወዛወዘ ፡ ከጒድጓዱ ፡ ግድግዳ ፡
ጋር ፡ ሲጋጭ ፡ ተሰብስበው ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በመሰቀቅ ፡ ይመለከ
ቱት ፡ ነበር ። ሲወጣ ፡ ገመዱን ፡ ከወገቡ ፡ ላይ ፡ ፈትተውለት ፡ እሚዳ ፡
ላይ ፡ ዘርረው ፡ አስተኙት ። ሁሉም ፡ የሞተ ፡ መስሎዋቸው ፡ ተስፋ ፡
ቆርጠው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ቆይቶ ፡ ተነፈሰና ፡ ትንሽ ፡ ካሳለው ፡ በኋላ ፡
ነፍስ ፡ ዘርቶ ፡ ዓይኑን ፡ ከፈተ ።
ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እዚህ ፡ ጒድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡
ነገር ፡ ገብተን ፡ እናያለን ፡ ብለው ፡ ተነሡ ። ግን ፡ ተሰብስበው ፡ ከነበ
ሩት ፡ ሰዎች ፡ መከከል ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ እዚህ ፡ ጒድጓድ ፡ ውስጥ ፡
የተመረዘ ፡ አየር ፡ አለ ፡ አይሆንም ፡ አትግቡ ፡ ብሎ ፡ ከለከላቸው ።

Scanned with CamScanner

ትልልቅ ፡ የብረት ፡ መንጠቆ ፡ ያለው ፡ መማሪያ ፡ አምጥተው ፡ በገ
መድ ፡ አስረው ፡ ልብሳቸውን ፡ እየጠለፉ ፡ ጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ የወደ
ቀችውን ፡ ልጅ ፡ አገረድና ፡ አሲን ፡ ሊያወጣ ፡ ገብቶ ፡ የቀረውን ፡
ሰው ፡ አወጧቸው ። ሁለቱም ፡ ጨርሰው ፡ ሞተው ፡ ኖሮ ፡ ማነኛው
ንም ፡ መድኃኒት ፡ ቢያደርጉላቸው ፡ ሊያድኗቸው ፡ ሳይችሉ ፡ ቀሩ ።
በኋላ ፡ ሊቃውንት ፡ ሄደው ፡ ቢመረምሩት ፡ እዚያ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡
ያለው ፡ አየር ፡ የተመረዘ ፡ መጥፎ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ።

የተመረዘ ፡ መጥፎ ፡ አየር ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፡
ሊኖርበት ፡ የማይችል ፡ ከባድ ፡ አየር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህን ፡ የመሰለ ፡ የተመረዘ ፡ መጥፎ ፡ አየር ፡ ካንዳንድ ፡ ቦታ ፡
በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ተከማችቶ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ ማዕድን ፡ ከሚወ
ጣባቸው ፡ አጎዶዎች ፡ ውስጥ ፡ ሠራተኞች ፡ ሳይገቡ ፡ አስቀድሞ ፡
ለመመርመሪያ ፡ የሚሆን ፡ ልዩ ፡ ፋኖስ ፡ ተሠርቷል ። ፋኖሱ ፡ በገ
መድ ፡ ታስሮ ፡ ከማዕድኑ ፡ ጉድጓድ ፡ (አጎዶ ፡) ውስጥ ፡ ይገባል ።
መብራቱ ፡ የጠፋ ፡ እንደሆነ ፡ አዚያ ፡ ቦታ ፡ ሠራተኞች ፡ አይገቡም ።
አስቀድመው ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡ ያስገቡበትና ፡ ፋኖሱን ፡ አብርተው ፡
መልሰው ፡ ይሞክሩታል ፤ ትክክል ፡ ሲበራ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ሠራተ
ኞች ፡ እንዲገቡ ፡ ይደረጋል ።

እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ መጥፎ ፡ አየር ፡ የሚገኝባቸው ፡ ብዙ ፡
ዋሻዎች ፡ አሉ ፤ ሰው ፡ ወይም ፡ እንስሶች ፡ እውስጣቸው ፡ ቢገቡ ፡
ይሞታሉ ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ መጥፎ ፡ አየር ፡ የተበለው ፡ የሚመጣው ፡ ክወ
ዴት ፡ ይሆን ? አመጣጡ ፡ እኛ ፡ የምንተነፍሰው ፡ ጥሩው ፡ አየር ፡
ተመልሶ ፡ መጥፎ ፡ አየሆነ ፡ ነው ። መስከቶቹና ፡ በሮቹ ፡ በተዘጉበት ፡
ቤት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ቢቀመጡ ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡
ከውጭ ፡ እየመጣ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባበት ፡ መንገድ ፡ ስለ
ማያገኝ ፡ በላይኛዎች ፡ መስመሮች ፡ በተነገረው ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡
ያለውን ፡ የመሰለ ፡ መጥፎ ፡ አየር ፡ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ይከማቻል ።
ስዚህም ፡ የተነሣ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሊሞት ፡ ይችላል ።

ጥንት ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ወታደሮች ፡
ተማረኩና ፡ ከዋሻ ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ ዘጉባቸው ። በማግሥቱ ፡
ጧት ፡ ያዩ፫ቱ ፡ ሙተው ፡ ተገኙ ። የተረፉትም ፡ ታመውና ፡ በጣም ፡
ደክመው ፡ ተገኙ ፡ ይባላል ። መጀመሪያ ፡ በዋሻው ፡ ውስጥ ፡ የነበ
ረው ፡ አየር ፡ ጥሩ ፡ ይሆናል ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ጥሩው ፡ አየር ፡ ከውጭ ፡
ስለማይገባበትና ፡ በውስጡም ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ስለሆኑ ፡
በዚያ ፡ በውኃ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ዓይነት ፡ መጥፎ ፡
አየር ፡ በዋሻው ፡ ውስጥ ፡ ተጠራቅሞ ፡ እስረኞቹን ፡ እየመረዘ ፡ ገደላ
ቸው ። ሰው ፡ በተነፈሰ ፡ ጊዜ ፡ ወዲ ፡ አፍ ፡ የሚገባው ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡
ሲወጣ ፡ መርዝ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ። ስለዚህ ፡ ሁልጊዜ ፡ አዲስ ፡
የሆነ ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡ ከልተኮከበት ፡ የገዘ ፡ ራሱ ፡ ትንፋሽ ፡ መርዝ ፡
ሆኖ ፡ ይገለዋል ። ይህንንም ፡ ለመረዳት ፡ ብትፈልጉ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡
ባደረበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጧት ፡ ስትገቡ ፡ መጥፎ ፡ ጠረን ፡ ታገኙበ
ታላችሁ ።

ሌ ፡ ቶ ።


አንድ ፡ መስፍንና ፡ አንድ ፡ ፈላስፋ ።

ክብሩ ፡ ጌጣጌጡ ፡ ገንዘቡ ፡ የበዛ ፡
አንድ ፡ መስፍን ፡ ነበር ፡ አገር ፡ የሚገዛ ።
ከእሱ ፡ የማይስይ ፡ ክጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡
ባለሟልነቱ ፡ እጅግ ፡ የዘረ ፡
ባማካሪነቱ ፡ ተከብሮ ፡ የኖረ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።
አንድ ፡ ሊቅ ፡ ፋላስፋ ፡ ብልህ ፡ ቀርቦ ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ለምሳ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡
ምግብ ፡ ሲጀምሩ ፡ እጆቹን ፡ ሰብስቦ ፡
አንገቱን ፡ ከምድር ፡ እንዳቀረቀረ ፡
በትካዜ ፡ ብዛት ፡ አሳብ ፡ ውጦት ፡ ቀረ ።
ወዲያውም ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ እያለ ፡
የልቡን ፡ ትካዜ ፡ ሊያስታምም ፡ ቀጠለ ።
መስፍኑም ፡ አየና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ፡
እንደዚህ ፡ ስታዝን ፡ ታይተሀ ፡ የማታውቀው ፡

Scanned with CamScanner

በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ የምታዝነው ?
የተጨነቅህበት ፡ ነገሩ ፡ ምንድነው ?
ፈላስፋው ፡ ጎዘኑን ፡ ወዲያው ፡ እያደሰ ፡
አዬ ፡ ጉድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሌላም ፡ አልመለሰ ።
አሁንም ፡ መስፍኑ ፡ መልሶ ፡ ጠየቀው ፡
በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ የምትጨነቀው ?
ይህን ፡ ያህል ፡ ዛሬ ፡ አጥብቀህ ፡ በብርቱ ፡
የምትተክዝበት ፡ ምንድነው ፡ ብልሃቱ ?
ፈላስፋው ፡ መለሰ ፡ ዋ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ጣጣ ፡
ታየኝ ፡ ለወደፊት ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ ሲመጣ ።
ይህንን ፡ ተናግሮ ፡ ጎዘኑን ፡ ቀጠለ ፡
አዬ ፡ ጉድ ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ እያለ ።
መላ ፡ ሰውነቱ ፡ በሽብር ፡ ደፍርሶ ፡
በመጨነቅ ፡ ብዛት ፡ ከፈላስፋው ፡ ብሶ ፡
እባክህ ፡ ነገሩን ፡ በሙሉ ፡ ግለጠው ፡ ·
ለምንድነው ፡ ልቤን ፡ የምታናውጠው ?
እባክህ ፡ መንፈሴ ፡ በሳብ ፡ ባሕር ፡ ዋኝ ፡
እንዲህ ፡ የሚያሠጋ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ተገኝ ?
እያለ ፡ መስፍኑ ፡ በጣም ፡ ወተወተው ።
ፈላስፋው ፡ መለሰ ፡ ለተመለከተው ፡
የሚያንቀጠቅጥ ፡ ነው ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡
ወየው ፡ ባገራችን ፡ የመጣው ፡ መቅሰፍ ፡
ጥቂት ፡ ጊዚ ፡ ኖረን ፡ ክፉ ፡ ዘመን ፡ አለ ።
ሁለት ፡ ዓመት ፡ መጥፎ ፡ ዝናም ፡ እየጣለ ፡
የዚያን ፡ ዘመን ፡ ሠነ ፡ ሲጠጣ ፡ እንዳመሉ ፡
ሠርቁን ፡ ጥለው ፡ ያብዳል ፡ ያገሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ።
ይህን ፡ መጥፎ ፡ ትንቢት ፡ መስፍኑ ፡ ሲሰማ ፡
አሁን ፡ እዚኪ ፡ ታዲያ ፡ ለዚህ ፡ የሚስማማ ፡
ምን ፡ ምክር ፡ ይገኛል ፡ አለና ፡ ጠየቀው ፡
ፈጣፋው ፡ መልሶ ፡ እኔማ ፡ የማውቀው ፡
የዚህ ፡ የመዓቱ ፡ ዘመኑ ፡ ሳይደርስ ፡
ካሁኑ ፡ ሳይበክን ፡ በከንቱ ፡ ሳይፈስ ፡

አንድ ፡ መስፍንና ፡ አንድ ፡ ፈላስፋ ።



Scanned with CamScanner

በመልካሙ ፡ ጊዜ ፡ ውኃ ፡ ተጠራቅሞ ፡
ሰዉ ፡ በየደጁ ፡ ያኑር ፡ አስቀድሞ ፡
ይህኑም ፡ በአዋጅ ፡ ማስታወቅ ፡ ነው ፡ ቶሎ ፡
የምሰጠው ፡ ምክር ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
ፈላስፋው ፡ በዚሁ ፡ ነገሩን ፡ አቆመ ።
መስፍኑም ፡ በቶሎ ፡ እየደጋገመ ፡
አዋጁን ፡ ለሕዝቡ ፡ ወዲያው ፡ አስነገረ ።
ሕዝብ ፡ ግን ፡ ሲሰማ ፡ እያንገራገረ ፡
ዛሬስ ፡ ብለው ፡ ብለው ፡ የሚሠሩት ፡ ቢያጡ ፡
ከፈጣሪ ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረው ፡ መጡ ።
እስኪ ፡ በማን ፡ አገር ፡ ውኃ ፡ ያሳብዳል ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ለሰሚው ፡ ይከብዳል ።
የማይመስል ፡ ወሬ ፡ ቢያወሩም ፡ አይበጅ ፡
ዛሬስ ፡ ቀለዱብን ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ።
እኛስ ፡ ለኑሮአችን ፡ አለብን ፡ ብዙ ፡ ዕዳ ፡
የሁለት ፡ ዓመት ፡ ስንቅ ፡ ውኃም ፡ አንቀዳ ።
ሥራ ፡ ሞልቶብናል ፡ እንደክምም ፡ ከንቱ ፡
እየተባባለ ፡ ሄደ ፡ በየቤቱ ።
መልካም ፡ ዘመን ፡ አልፎ ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ ደረሰ ፡
መጥፎ ፡ ዝናም ፡ ዘንሞ ፡ ውኃውም ፡ ፈሰሰ ።
ያን ፡ የጠጣ ፡ ሁሉ ፡ እውነትም ፡ አበደ ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲናገር ፡ እየዘላበደ ።
ይቀባጥር ፡ ጀመር ፡ የባጡን ፡ የቆጡን ፡
በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ጨርሶ ፡ አጣ ፡ ቅጡን ።
አብዶ ፡ ዘሎ ፡ ከንፎ ፡ ጨፍሮ ፡ ሲያበቃ ፡
እንደ ፡ ባነነ ፡ ሰው ፡ ከእንቅልፉ ፡ እንደ ፡ ነቃ ፡
ኧረ ፡ ይህን ፡ ሰሞን ፡ ምንድነው ፡ ብልሃቱ ?
የመስፍናችን ፡ ድምጥ ፡ አለመሰማቱ ?
ብቻውን ፡ መኖሩ ፡ ከኛ ፡ ተለይቶ ፡
ግበዱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ከቶ ።
ተነሡ ፡ እንፈልገው ፡ ወዲት ፡ ገባ ፡ ብለው ፡
ወደ ፡ መስፍኑ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ፡ ተከታትለው ።

በመስፍኑ ፡ ግቢ ፡ ጉድጓዱ ፡ ተወርቶ ፡
በመልካሙ ፡ ዘመን ፡ ውኃውም ፡ ተቀድቶ ፡
ተጠራቅሞ ፡ ኖሮ ፡ እሱን ፡ እየጠጡ ፡
በመልካም ፡ አእምሮ ፡ ደኅና ፡ ሲቀመጡ ።
ከሰገነቱ ፡ ላይ ፡ መስከት ፡ ተደግፎ ፡
እያጉረመረመ ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰልፎ ፡
አየና ፡ አመጣጡ ፡ መሆኑን ፡ ለመጥፎ ፡
መስፍኑ ፡ ደንግጦ ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ሠጋ ፡
ሠራዊቱን ፡ አዝዘ ፡ ሳንቃውን ፡ አዘጋ ።
የሚያደርገው ፡ አጥቶ ፡ ስለተጨነቀ ፡
ፈጥኖ ፡ ፈላስፋውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀ ።
ሕዝብ ፡ በብዛቱ ፡ መጣ ፡ መስሎ ፡ ጉንዳን ፡
ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ፡ ከዚህ ፡ ጉድ ፡ ለመዳን ?
ፈላስፋው ፡ መለሰ ፡ እኔማ ፡ አስቀድሞ ፡
ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሳይሆን ፡ ውኃው ፡ ተጠራቅሞ ፡
ሰዉ ፡ በየደጁ ፡ ያኑር ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡
ግን ፡ አልሰማ ፡ ብሎ ፡ አዋጁ ፡ ሲነገር ፡
ፍጥረት ፡ ተበላሸ ፡ እንዳልሁት ፡ አበደ ።
አሁንም ፡ ብልሃቱ ፡ ነፍሱን ፡ የወደደ ፡
የዘመኑን ፡ ውኃ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ጠጥቶ ፡
አብሮ ፡ ካላበደ ፡ መዳን ፡ የለም ፡ ከቶ ፡
አንተ ፡ ግን ፡ ጠጥተህ ፡ አልልም ፡ እበድ ፡
ግን ፡ የሕዝቡን ፡ ሞገድ ፡ እንድታስወግድ ፡
አብረህ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ መስለህ ፡ ያበደ ፡ ሰው ፡
ካልጨፈርህ ፡ በቀር ፡ ሕዝቡን ፡ ልትመልሰው ፡
አትችልም ፡ ከቶ ፡ አለና ፡ መከረው ።
መስፍኑም ፡ ፈላስፋው ፡ ልክ ፡ እንደነገረው ፡
ያበደ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ አንጐሉ ፡ የዘረ ፡
በሚናገረውም ፡ እየቀበጠረ ፡
በሩን ፡ ክፈት ፡ ብሎ ፡ ይጮኽ ፡ ጀመረ ።
ተንደረደረና ፡ በሩን ፡ አስከፍቶ ፡
ከተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መኻል ፡ ገብቶ ፡

Scanned with CamScanner

አብሮ ፡ ያብድ ፡ ጀመር ፡ ከጥፍረቱ ፡ ጋራ ።።
ግማሹ ፡ ሲዘፍን ፡ ግማሹ እያቅራራ ፡
ሁሉም ፡ በደስታ ፡ እየተራወጠ ፡
እልል ፡ በል ፡ ተበሉ ፡ እልልታው ቀለጠ ።።
ከሩቅ ፡ የነበረው ፡ እየፈነደቀ ፡
ነገሩ ፡ ምንድነው ፡ አሰና ፡ ጠየቀ ።።
የመጣውን ፡ ፍጥረት ፡ ቶሎ ፡ እያሰለፈ ፡
በመካከላቸው ፡ ሰንጥቆ ፡ እያለፈ ፡
ድምጡን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ ለፈፈ ።።
በጣም ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ መስፍናችን ፡ ዳነ ፡
በፊት ፡ አብዶ ፡ ነበር ፡ ዛሬ ፡ ደንና ፡ ሆነ ።።
ያልሰማው ፡ ሲሰማ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ገና ፡
ድምጡን ፡ የበለጠ ፡ ከፍ ፡ አደረገና
ጭራሽ ፡ ወሰን ፡ ያጣ ፡ ሆነና ፡ ደስታ ፡
ያስተጋባ ፡ ጀመር ፡ በታላቅ ፡ አልልታ ።።
ሰሚዬው ፡ የሚበጅ ፡ ብልሃት ፡ አስፈልጎ ፡
ከሕዝቦቹ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ እየከነፈ ፡
ያንን ፡ መጥፎ ፡ ዘመን ፡ በሰላም ፡ አለፈ ።።
በብዙ ፡ አብድ ፡ መኻል ፡ አንድ ፡ ደንና ፡ ሲገኝ ፡
ምንም ፡ በእውነተኛው ፡ መንገድ ፡ መሥራት ፡ ቢመኝ፡
የሕይወቱን ፡ ሰላም ፡ ልቡ ፡ ከወደደ፡
ለመኖር ፡ አይችልም ፡ አብሮ ፡ ካላበደ ።።
መስማማት ፡ ሲያቅተው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከብዙ ፡
የሚያገኘው ፡ አሳር ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ መዘዙ ።።
የብዙዎቹን ፡ አሳብ ፡ እየተከተለ ፡
ጠባዩ ፡ ከእነሱ ፡ ካልተመሳሰለ ፡
ምንም ፡ የሱ ፡ አሳብ ፡ ቢሆን ፡ እውነተኛ ፡
ከሱ ፡ የበለጠ ፡ ማነው ፡ ጥፋተኛ ፡ ?
ስለዚህ ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ስንመለከተው ፡
የሱሎቹን ፡ ጥፋት ፡ በምክር ፡ ለማስተው ፡
እየተጣጣረ ፡ በፍጹም ፡ ሲያቅተው ፡

ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ ያደርጋል ፡ ምንም ፡ ቢቆረቆር ፡
ከዘመኑ ፡ ሰዎች ፡ ተስማምቶ ፡ ለመኖር ።።
በግድ ፡ ይኑር ፡ እንጂ ፡ እንደጊዜው ፡ መስሎ ፡
እንደምን ፡ ይዘልቃል ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ታግሎ ።።
ሲተጋገዝ ፡ እንጂ ፡ ጥጡር ፡ የሚድነው ፡
ምንም ፡ ብርቱ ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ነው ።።
ዓይን ፡ ላልከፈተ ፡ ላልደረሰ ፡ ገና ፡
ናላው ፡ ላልበሰለ ፡ ዕውቀቱ ፡ ላልጠና ።።
አዲስ ፡ ሕግ ፡ ሰጥቶ ፡ ቶሎ ፡ በማስገደድ ፡
ልማድ ፡ ያረገውን ፡ ስሕተት ፡ ለማስወገድ ።።
ኑሮውን ፡ ማሻሻል ፡ እችላለሁ ፡ ብሎ ፡
ይህን ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ቀላል ፡ አስመስሎ ።።
ቸኩሎ ፡ በፍጥነት ፡ ደፍሮ ፡ ለሚነሣ ፡
ወዮለት ፡ በብዙ ፡ አለበት ፡ አበሳ ።።
አስኪ ፡ ቀስ ፡ በሉ ፡ አለ ፡ ብዙ ፡ ጣጣ ፡
ዘዴ ፡ ከልጨመሩ ፡ ኽቅም ፡ አያዋጣ ።።
ይህን ፡ ያመጣነው ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
አብራችሁ ፡ አበዱ ፡ ለማለት ፡ አይዶለም ።።
ለምነው ፡ ብቻዬን ፡ በከንቱ ፡ እምለፋ ፡
ብሎ ፡ መልከመ ፡ ሰው ፡ እንዳይቄርጥ ፡ ተስፋ ፡
የሚያበረታታው ፡ እንዲያገኝ ፡ ደገፋ ፡
ብዙ ፡ ልበ ፡ ቅን ፡ ሰው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ አይጥፋ ።።

ከምቢዝና ፡ ፕሳሜኒት ።።

የፋርስ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ከምቢዝ ፡ የግብፅን ፡ አገር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ ፕሳሜኒት ፡ የሚባለው ፡ የግብፅ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ምርኮኛ ፡ ሆኖ ፡ በእጁ ፡ ወደቀ ።። ከምቢዝ ፡ የግብፅን ፡ ንጉሥ ፡ ፕሳሚኒትን ፡ ከሌሎች ፡ የግብፅ ፡ ተወላጆች ፡ ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ከደባባይ ፡ እንዲያወጡትና ፡ የፕሳሚኒትንም ፡ ልጅ ፡ ከሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ እንዲያመጧት ፡ አዘዘ ።። የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ደበደቦ ፡ ጨርቅ ፡ ለብሳ ፡ ከቀሩት ፡ ከግብፅ ፡ መኳንንቶች ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ከጉድጓድ ፡ ውኃ ፡ እየቀዳች ፡ ተሸክማ ፡ እንድታልፍ ፡ አዘዘ ።።

Scanned with CamScanner

መኳንንቶቹ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ የውርደት ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ውኃ ፡ ተሸክመው ፡ እያለቀሱ ፡ በጠገባቸው ፡ ሲያልፉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸው ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመር ፡ ፕሳሜኒት ፡ ብቻ ፡ ልጁን ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ አንገቱን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ አላለቀሰም ።

ሴቶቹ ፡ ልጆች ፡ ከለፋ ፡ በኋላ ፡ የፕሳሜኒት ፡ ወንድ ፡ ልጁ ፡ ከሌሎቹ ፡ የግብፅ ፡ ታላላቆች ፡ ሰዎች ፡ ከሆኑት ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እንዲወጣ ፡ ካምቢዝ ፡ አዘዘ ። ልጆቹም ፡ በአንገታቸው ፡ ገመድ ፡ አጥልቀው ፡ በአፋቸውም ፡ ልጓም ፡ አግብተውባቸው ፡ ነበር ። የሚሄዱትም ፡ ሊገደሉ ፡ ነበር ። መኳንንቶቹ ፡ ልጆቻቸው ፡ እንደዚህ ፡ ሆነው ፡ ሲያልፉ ፡ አይተው ፡ አለቀሱ ፤ ፕሳሜኒት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ቦታ ፡ መሄዱን ፡ ቢያውቅ ፡ አሁንም ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ አላለቀሰም ።

ቀጥሎ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ጓደኛው ፡ ሆኖት ፡ ይኖር ፡ የነበር ፡ አንድ ፡ ዘመዱ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ደህይቶ ፡ ከወታደሮች ፡ ላይ ፡ ምፅዋት ፡ ሊለምን ፡ አየው ።

ፕሳሜኒት ፡ ወዲያው ፡ እንዳየው ፡ ጓደኛውን ፡ በስሙ ፡ ጠራውና ፡ ራሱን ፡ በእጁ ፡ እየመታ ፡ ጮኸ ፡ አለቀሰ ። ካምቢዝ ፡ እንደዚህ ፡ ሲያደርግ ፡ ፕሳሜኒትን ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ አሱ ፡ ልከ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ።

ፕሳሜኒት ፡ ሆይ ፡ ጌታህ ፡ ካምቢዝ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይጠይቅሃል ፡ ሴቷ ፡ ልጅህ ፡ ተዋርዳ ፡ ወንዱ ፡ ልጅህም ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ቦታ ፡ ሲሄድ ፡ እያየህ ፡ ሳታለቅስላቸው ፡ ቀርተህ ፡ ከደምህ ፡ ላልተወለደ ፡ ላንድ ፡ ችግረኛ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ያዘንህለት ፡ በምን ፡ የተነሣ ፡ ነው ? ፕሳሜኒትም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፡ ጎዘኔ ፡ እጅግ ፡ የበረታ ፡ ስለሆነ ፡ ስለልጆቹ ፡ ላለቅስ ፡ ዘንድ ፡ አልተቻለኝም ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ጓደኛዬ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ በሽምግልና ፡ ጊዜው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ አግኝቶ ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አዘንኩለት ።

ምርኮኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ አንደኛው ፡ ንጉሥ ፡ ከሬሱስ ፡ የሚባለውም ፡ እዚያው ፡ ከካምቢዝ ፡ ጋር ፡ ነበርና ፡ ፕሳሜኒት ፡ ይህን ፡ ታል ፡ ሲናገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የደረሰበትን ፡ መጥፎ ፡

ዕድል ፡ ስላሰበው ፡ ክፉኛ ፡ እያለቀሰ ፡ እንባውን ፡ ይረጭ ፡ ጀመር ፡ እዝያም ፡ የነበሩት ፡ የሩርስ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ አለቀሱ ።

ይህን ፡ ነገር ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ጨካኙ ፡ ካምቢዝ ፡ ልቡ ፡ በርኅራኄ ፡ ተነክቶ ፡ ፕሳሜኒትን ፡ አስጠርቶ ፡ ወንድ ፡ ልጁን ፡ ደግሞ ፡ እንዲያመጡለት ፡ አዘዘ ። ነገር ፡ ግን ፡ የፕሳሜኒት ፡ ልጅ ፡ በሕይወት ፡ ሳይገኝ ፡ ቀረ ፡ የሞቱ ፡ ፍርድ ፡ ተፈጽሞበት ፡ ነበርና ፡ ካምቢዝም ፡ ፕሳሜኒትን ፡ ከፊቱ ፡ በቀረቡለት ፡ ጊዜ ፡ ምሕረት ፡ አደረገለት ።

ከሕግ ፡ የወጣ ፡ ትርፍ ።

በንድ ፡ አገር ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ነግሦ ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ሞተና ፡ ሴላ ፡ ንጉሥ ፡ በሱ ፡ ቦታ ፡ ተተካ ። አዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ አስገዳጅ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ቢገጥመው ፡ አዲስ ፡ ግንዘብ ፡ አሠራና ፡ የቀድሞው ፡ ግንዘብ ፡ እንዲቀር ፡ አወጀ ። ግንዘብ ፡ በጣም ፡ የሚወድ ፡ ሕግ ፡ የከለከለውን ፡ ትርፍ ፡ መፈለግ ፡ የለመደ ፡ አንድ ፡ ተንኰለኛ ፡ ነጋዴ ፡ አሮጌውን ፡ ግንዘብ ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ እየገዛ ፡ ሰብስቦ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ ጠበቀና ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ አቤት ፡ አለ ። ንጉሡም ፡ ቆሞ ፡ አቤት ፡ ያለበትን ፡ ምክንያት ፡ ጠየቀው ። ነጋዴውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎት ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ግንዘብ ፡ ተበደረና ፡ ሳይከፍል ፡ ሞተ ፤ አበዳሪው ፡ ግንዘቡን ፡ ከማን ፡ ሊከፈል ፡ ይችላል ? አለ ። ንጉሡም ፡ ከወራሹ ፡ ነዋ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ነጋዴው ፡ መለሰና ፡ ወራሹ ፡ እምቢ ፡ ያለስ ፡ እንደሆነ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ፤ ንጉሡም ፡ መልሶ ፡ በሕግ ፡ ያስገድደዋል ፡ አለው ። ነጋዴው ፡ አሁንም ፡ መልሶ ፡ በሕግም ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነስ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ሕግ ፡ አስፈጻሚዎች ፡ እምቢ ፡ ሲሉት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ መጥቶ ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ፡ አለው ።

ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እንግዲያውስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎት ፡ በቀድሞው ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ ለፍቼ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ግንዘብ ፡ ሰብስቤ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ይህ ፡ ግንዘብ ፡ ባዋጅ ፡ እንዳይሠራበት ፡ ተከለከለ ።

Scanned with CamScanner

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ የቀድሞውን ፡ ንጉሥ ፡ ዕዳ ፡ አልጋ ፡ የወረሱት
እርስዎ ፡ ክልከፈሉኝ ፡ ማን ፡ ይከፍለኛል ፡ ብሎ ፡ ነጋዴው ፡ አመለ
ከተ ። ንጉሡም ፡ መልክም ፡ ነው ፡ ገንዘቡን ፡ ይዘህ ፡ ከቤተ ፡ መን
ግሥቴ ፡ እንድትመጣ ፡ ብሎ ፡ ቀጠሮ ፡ ሰጠው ።

ንጉሡ ፡ ይህ ፡ ነጋዴ ፡ ጠባዩ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ቢያስጠይቅ ፡
ከሕግ ፡ የወጣ ፡ ትርፍ ፡ የለመደ ፡ ተንኰለኛ ፡ መሆኑና ፡ ይህም ፡
ገንዘብ ፡ የደከመበት ፡ ሳይሆን ፡ በርካሽ ፡ ገዝቶ ፡ እንደ ፡ ሰበሰበው ፡
ሰማ ፤ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ነጋዴው ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሲመጣ ፡
የያዘውን ፡ አሮጌ ፡ ገንዘብ ፡ ቁጥረው ፡ ተቀብለው ፡ በዚያ ፡ ልክ ፡
አዲስ ፡ ገዘንብ ፡ አዲሰጡት ፡ አዘዘና ፡ ነጋዴው ፡ ገንዘቡን ፡ ከተረ
ከበ ፡ በኋላ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ አዋጅ ፡ ፈቅዶ ፡ ሲቀበል ፡ አቤ
ቱታ ፡ ያቀረብህ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ገንዘብህን ፡
አልከለከልኩህም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የማዝዝህ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡
አለ ፤ ይኸውም ፡ ከሙታን ፡ አገር ፡ ሄደህ ፡ ለቀድሞው ፡ ንጉሥ ፡
ባንተ ፡ ላይ ፡ የነበረኝን ፡ ዕዳ ፡ ተከፍያለሁ ፡ ብለህ ፡ ራስህ ፡ መስክረህ ፡
እንድትነግረው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ ነጋዴውን ፡ አስገደለው ፡ ይባላል ።

ሁሉም ፡ የሆነ ፡ ነው ።

ዑልጊዜ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ምነው ፡ መወይዱ ፡
ሁሉም ፡ እያረጀ ፡ አይቀርም ፡ መሄዱ ።
ሰሎሞን ፡ ብሎናል ፡ ደጉ ፡ ተመልከች ፡
አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ።
ጀንጂስካን ፡ ቲሙርሌንግ ፡ አቲላ ፡ ቄሣር ፡
ሻርልከ ፡ ናፖሊዮን ፤ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡
አልፎ ፡ አልፎ ፡ በተራ ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡
ዓለምን ፡ በሙሉ ፡ ይዘው ፡ ለመጠቅለል ፡
በሰይፍ ፡ በጎራዴ ፡ ፍጥረት ፡ እያመሱ ፡
በብዙ ፡ ቁስኔ ፡ ደም ፡ እያፈሰሱ ፡
ይመስላቸው ፡ ነበር ፡ ሠርተው ፡ የፈጸሙ ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ አልሆነም ፡ በክንቱ ፡ ደክመ ፡

ዓለም ፡ ሳትለወጥ ፡ በህልዋን ፡ ሳትረሳ ፡
እስር ፡ ትገባለች ፡ ወዲያው ፡ ተመልሳ ።
የታሪክን ፡ ጉዞ ፡ ያልተገነዘበ ፡
ሁሉንም ፡ ያደንቃል ፡ እያጨበጨበ ።
ለመጪው ፡ ሳያስብ ፡ ላላፊው ፡ ሳያዝን ፡
በልማድ ፡ ይኖራል ፡ ጅል ፡ ሳያመዛዝን ።
ብልህ ፡ ግን ፡ ያስተውላል ፡ አይደናበርም ።
መሪድ ፡ መመለሱን ፡ አይጠራጠርም ።
ጊዜ ፡ እየለወጠው ፡ የልማድን ፡ አዋጅ ፡
ጠላት ፡ የነበሩት ፡ ይሆናሉ ፡ ወዳጅ ።
እንዲሁም ፡ ቢመስለን ፡ ግራ ፡ መስሎ ፡ ለኛ ፡
ፍየል ፡ ከነብር ፡ ጋር ፡ ይሆናል ፡ ጓደኛ ።
ልዘ ፡ ተላላ ፡ ሰው ፡ ዘላለም ፡ ይሞኛል ፡
እስኪ ፡ ረግቶ ፡ ያለ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ይገኛል ?
የተማመኑበት ፡ እየሆነ ፡ ፈራሽ ፡
ሲፈጸም ፡ ይገኛል ፡ ያልታሰበው ፡ ቁራሽ ።
ደካማ ፡ ይጠናል ፡ ኃይለኛ ፡ ሲዋረድ ፡
ቡቃያ ፡ ይለማል ፡ ያፈራው ፡ ሲታጨድ ።
ሰፈው ፡ ይቀነሣል ፡ ጠባቡ ፡ ሲሰፋ ፡
ጨረቃ ፡ ታምራለች ፡ ዐሓይ ፡ ስትጠፋ ።
ሀብታመ ፡ ሲደኸይ ፡ ደሀ ፡ ሰው ፡ ይከብራል ፡
አንዱ ፡ ሲደፈርስ ፡ አንደኛው ፡ ይጠራል ።
ከእንቅልፉ ፡ ሲነቃ ፡ ቀድሞ ፡ የፈዘዘ ፡
የሞቀው ፡ ይሄዳል ፡ እየቀዘቀዘ ።
ትንሹም ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ ትልቁም ፡ ትንሽ ፡
መጥፎውም ፡ መልክም ፡ ነው ፡ መልከመ·ም ፡ ብላሽ ።
እንደ ፡ ሕልም ፡ ታይቶ ፡ ያልፋል ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ የለው ፡ መላ ።
ሁሉም ፡ ያለ ፡ ጊዜው ፡ ነውና ፡ አስቀያሚ ፡
ዕውቀትም ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ኃይልም ፡ አጋጣሚ ።
ትልቅ ፡ ሰው ፡ ሲቀበር ፡ ሕፃን ፡ ይወለዳል ፡
አንዱ ፡ ሲመሠረት ፡ አንደኛው ፡ ይናዳል ።

Scanned with CamScanner

ሳይተጓጐሉ ፡ እንበለ ፡ ፍጻሜ ፡
ይፈራረቃሉ ፡ ጠፍና ፡ ልምላሜ ።
እንዲህ ፡ ከሆነማ ፡ የፍጥረት ፡ ልማዱ ፡
ሰዎች ፡ ተቀበሉት ፡ ብትወዱም ፡ ቢትወዱ ፤
ጥንትም ፡ ወደፊትም ፡ ዛሬም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ሁሉም ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ።

አባትና ፡ ልጅ ።

መልክም ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ላባቱ ፡
አባት ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከንጀቱ ፡
አለና ፡ መረቀው ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ውለድ ፡
ልጁም ፡ መለሰና ፡ ምርቃት ፡ ሳይገድ ፡
እግዚአብሔር ፡ አይንሳህ ፡ ገንዘብና ፡ ሀብት ፡
የሰው ፡ መውደድ ፡ ይስጥህ ፡ ብሎ ፡ እንደማለት ።
ልጅ ፡ ምን ፡ ይጠቅመኛል ፡ ብሎ ፡ ቢናገረው ፡
ልጁ ፡ አድምጠኝ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መከረው ።
ለሰው ፡ ከተሰጠው ፡ ከመልካሙ ፡ ዋጋ ፡
ከልጅ ፡ የበለጠ ፡ የት ፡ ይገኛል ፡ ጸጋ ።
ሩቅም ፡ ሳንሄድ ፡ ላስረዳህ ፡ በጭር ፡
እኔ ፡ አንተን ፡ ባልወልድህ ፡ የት ፡ ትገኝ ፡ ነበር ?
ልጁ ፡ መለሰለት ፡ በትወልደኝ ፡ አባቴ ፡
እርግጥ ፡ ነው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ አለመገኘቴ ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ መወለድ ፡ ብቻ ፡ የት ፡ ይበቃል ፡
ሰው ፡ በመፈጠሩ ፡ ሙት ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ያውቃል ።
እኔ ፡ መፈጠሬን ፡ ጠልቼው ፡ ስመረር ፡
አልመኝም ፡ ከቶ ፡ ልጅ ፡ የሚሉ ፡ ነገር ።
ይህንን ፡ ሲሰማ ፡ ተከዘ ፡ በብርቱ ፡
አንጉቱን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አቀርቅሮ ፡ አባቱ ፡
በጣም ፡ አሳዝኖት ፡ የልጁ ፡ ንግግር ፡
እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ያጉረመርም ፡ ጀመር ፡

እኛ ፡ በልጅነት ፡ ቀድሞ ፡ በጊዜያችን ፡
የልጅ ፡ ፍቅር ፡ ነበር ፡ ዋና ፡ ምኞታችን ።
አሁን ፡ የኛ ፡ ልጆች ፡ በስምንተኛው ፡ ሺ ፤
መጥፎ ፡ አሳብ ፡ መከተል ፡ መልካሙን ፡ መሸሺ ።
ዕውቀት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ አዲስ ፡ ፍልስፍና ፤
ሲሄዱ ፡ አየናቸው ፡ ወደ ፡ ድንቁርና ፡
ከዚህ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ይገኛል ፡ ወይ ፡ ሌላ ፤
ልጄ ፡ እኔን ፡ መውደዱ ፡ መፈጠር ፡ ሲጠላ ።

የቅኝ ፡ አገር ፡ ወርቅ ፤
የሰላም ፡ ጠንቅ ።

ጸጥንት ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ መንግሥታት ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ እንደ
ነበሩዋቸው ፡ በታሪክ ፡ ተጽፎአል ። እነዚሁም ፡ በለቅኝ ፡ አገሮች ፡
የነበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ፈንቂ ፤ ከርታጐ ፡ ግሪክና ፡ ሮማ ፡ ነበሩ ።
በጥንት ፡ ዘመን ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ የሚያገለግሉት ፡ ለንግድ ፤
ለጦርና ፡ ለፖሊቲካ ፡ ጐዳዮች ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ ፈንቂ ፡ የፖሊ
ቲካ ፡ ሁከት ፡ በአገርዋ ፡ ውስጥ ፡ በተነሣ ፡ ቊጥር ፡ ካገር ፡ የሚወ
ጡት ፡ የፖሊቲካ ፡ ስደተኞች ፡ ወደ ፡ ቅኝ ፡ አገሮችዋ ፡ እየሄዱ ፡
ይኖሩ ፡ ነበር ። ቅኝ ፡ አገሮችዋም ፡ የሚገኙት ፡ በሜዴቴራኔ ፡ ባሕር ፡
ላይ ፡ በሉት ፡ ደሴቶች ፡ ነበር ። እንደ ፡ ሽፕር ፤ ሮድ ፤ ክሬት ፤ ደግ
ሞም ፡ በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ ክፍሎች ፡ እንደ ፡ ከርታጐ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ።
ቀጥሎ ፡ ከርታጐ ፡ ሲሲል ፤ ሳርዴኝ ፤ ኮርስ ፡ የሚባሉትን ፡
ደሴቶች ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ አድርጋ ፡ ያዘቻቸው ። ስለ ፡ ቅኝ ፡ አገ
ሮች ፡ ጐዳይ ፡ ከርታጐዎች ፡ አሳባቸው ፡ ከሁኑ ፡ ዘመን ፡ ያውሮፓው
ያን ፡ አሳብ ፡ ጋራ ፡ ይቀራረባል ። የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ለመፈለግ ፡ ሲሉ ፡
በጦርከበቧቸው ፡ በውቃያኖስ ፡ ላይ ፡ ይመላለሱ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡
ይልቁንም ፡ በማዕድን ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ የምትሰጣቸው ፡ የቅኝ ፡
አገር ፡ እስፓኛ ፡ ነበረች ።
ታሪክ ፡ መጻፍ ፡ ከጀመረበት ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ ግሪኮችም ፡
በመቄዶንያ ፡ ጠረፍ ፡ በትራክያና ፡ በቢዛንስዮም ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡

Scanned with CamScanner


ነበሩዋቸው ። በትንሹ ፡ እስያ ፡ ክፍልም ፡ እንደዚሁ ፡ የቅኝ ፡ ሳ
ሮች ፡ መሥርተው ፡ ነበር ። በኋላም ፡ የሲሲልን ፡ ደሴትና ፡ ደቡ
ዊዉን ፡ የኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ያዙ ። ከዚያም ፡ እስከ ፡ ሊቢያ ፡ ከሂዱ ፡
በኋላ ፡ በትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ጊዜ ፡ ግብፅን ፡ ይዘው ፡ ተመልሰው ፡
ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ አመሩ ።

ሮማውያንም ፡ እንደዚሁ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ነበሩዋቸው ።
ሮማ ፡ ግዛቷን ፡ እያስፋፋች ፡ በሄደችበት ፡ መጠን ፡ ድል ፡ አድርጋ ፡
በያዘቻቸው ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ አገር ፡ አቅኚዎች ፡ የሆኑ ፡
ሰዎች ፡ ከሕዝቦቿ ፡ አየከፈለች ፡ ከላከች ፡ በኋላ ፡ የቅኝውን ፡ አገር ፡
መፌት ፡ አከፋፍላ ፡ ለእነዚሁ ፡ አገር ፡ አቅኚዎች ፡ ተሰጣቸው ፡ ነበር ።
ስለ ፡ አገሩ ፡ አገዛዝና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ አስተዳደር ፡ የሚሠሩት ፡
ሕግጋት ፡ ግን ፡ እየተወሰኑ ፡ ለቅኝ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚላኩት ፡
ከሮማ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡
ባዲሱ ፡ ዘመን ፡ ያለው ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ሁኔታ ፡ ደግሞ ፡ ቀጥሎ ፡
እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ነው ።

ካውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ መከከል ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ መያዝ ፡ የጀ
መሩ ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ናቸው ። በመጀመሪያ ፡ የያዟቸው ፡ አገሮች ፡
በአፍሪከ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ማዴር ፡ አሶር ፡ የከፕ ፡ ቬርት ፡ ደሴ
ቶች ፤ ሲየራ ፡ ሴዎኔ ፡ እና ፡ ኩንጐ ፡ የሚባሉትን ፡ ነው ። ከዚ
ያም ፡ በ፲፱፻፸፮ ፡ ዓ. ም. ባርቲሌሚ ፡ ዲያዝ ፡ የሚባል ፡ የፖርቱጋል ፡
ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ መርከበኛ ፡ የመልከም ፡ ተስፋ ፡ ጠረፍ ፡ (ከፕ) ፡
ከተባለው ፡ አገር ፡ ለመድረስ ፡ ቻለ ። ቀጥሎ ፡ ቫስኮ ፡ ደ. ጋማ ፡
የሚባለው የበለጠ ፡ ወደፊት ፡ ገፍቶ ፡ በመርከብ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡
የሕንድ ፡ አገር ፡ መንገድ ፡ ለፖርቱጋሎች ፡ ተከፈተላቸው ። በሕንድ ፡
አገር ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ማላባር ፡ የሚባለውን ፡ አገር ፡ በኢንዱስታን ፡
ክፍል ፡ የሚገኘውን ፡ መጀመሪያ ፡ ያዙ ። ቀጥሎ ፡ በአፍሪከ ፡ ውስጥ ፡
ሞዛምቢክ ፡ ሶፋላ ፡ ሜሊንዳ ፡ የሚባሉትን ፡ አገሮች ፡ አርመተገ ፡
ሴላን ፡ ማላክ ፡ ሞሉክ ፡ ቲምር ፡ ቱርናት ፡ የሚባሉትን ፡ ይግሞ ፡ በእ
ስያ ፡ ክፍል ፡ እጅ ፡ አደረጉ ። በእነዚህ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ከሰፈሩ ፡
በኋላ ፡ ወደ ፡ አስያ ፡ ሣፍ ፡ እየዘለቁ ፡ ገቦቫ ፡ ሱማትራ ፡ ሴሌብ ፡

ቦርኔዎ ፡ ሺና ፡ ጃፓን ፡ ከሚባሉት ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ በንግድ ፡ ተገና
ኝተው ፡ ይገበያዩ ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ እነሱ ፡ በከፈቱት ፡ መን



በቅኝ ፡ አገር ፡ ምክንያት ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ደደረፃ ፡ የንበር ፡ የመርከብ ፡ ውጊያ

ገድ ፡ የአስፓኛ ፡ ሰዎች ፡ ተመርተው ፡ ስለተከታተሏቸው ፡ በሁለቱ ፡
ሕዝቦች ፡ መከከል ፡ ወዳያው ፡ በዚሁ ፡ በቅኝ ፡ አገር ፡ ጦዳይ ፡ ጠብ ፡

Scanned with CamScanner

ተወለደ ። እንግዲህ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥ
ታት ፡ ሁሉ ፡ አሳባቸውና ፡ ጥረታቸው ፡ ወደ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ጉዳይ ፡
ስለተሳበ ፡ በየጊዜው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የሚዋጉት ፡ ጦርነት ፡
ሁሉ ፡ የሚነሣው ፡ በቅኝ ፡ አገሮች ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

ሆኖም ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ከያዟቸው ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ብዙዎቹን ፡
ሌሎቹ ፡ ነጮቀቸው ፡ የተረፉዋቸውን ፡ አንዳንድ ፡ አገሮች ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይዘው ፡ ይኖራሉ ። የፖርቱጋሎች ፡ ኃይል ፡ እየደከመ ፡
ሲሄድ ፡ የእስፓኛ ፡ ኃይል ፡ እየበረታ ፡ በመሄዱ ፡ የእስፓኛ ፡ መንግ
ሥት ፡ በክሪስቶፍ ፡ ኮሎምብ ፡ አነሣሽነት ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡
ተመርቶ ፡ ሂስፓኒዎላ ፡ የተባለችውን ፡ የሃይቲ ፡ አገር ፤ ቀጥሎም ፡
ኩባ ፡ ፓርቶሪኮ ፡ ጃማይክ ፡ ሜክሲክ ፡ ፔሩ ፡ ቺሊ ፡ ኪቶ ፡ የሚባሉ
ትን ፡ አገሮች ፡ ያዘ ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ እስፓኛ ፡ ሀብት ፡ አግኝታ ፡ ከቀሩት ፡
ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ለመሆን ፡ በቃች ። ነገር ፡
ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከቅኝ ፡ አገር ፡ የሚፈለገው ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡
የወርቅና ፡ የብር ፡ ማዕድን ፡ ለማግኘት ፡ ነበር ። በቅኝ ፡ አገሮቹም ፡
ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ለማከማቻ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማዕ
ድኑ ፡ በሚወጣበት ፡ ቦታ ፡ አቅራቢያ ፡ ከተማዎች ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ።
አካፑልኮ ፤ ፓናማ ፡ ሊማ ፡ በየዘር ፡ የሚባሉ ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡
የሚገኙት ፡ ከተማዎች ፡ የተከተሙት ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቀጥሎ ፡ ፈረንሳዮችና ፡ እንግሊዞች ፡ ስለ ፡ ተነሡ ፡ እስፓኛ ፡
ደግሞ ፡ ተራዋን ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ የቅኝ ፡ አገሮቿን ፡ ተነጠቀች ። የታ
ሪኩን ፡ ተራ ፡ እንከተልና ፡ ከእስፓኛ ፡ ቀጥሎ ፡ ሆላንድ ፡ ተነሣች ።
ሆላንዶች ፡ ፖርቱጋሎች ፡ የከፈቱትን ፡ የባሕር ፡ መንገድ ፡ ተከትለው ፡
በመርከብ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ ገብተው ፡ ወጭቸውና ፡
ይዘዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ነጠቋቸው ። እኔም ፡ በሕ
ንድ ፡ አገር ፡ ገቢ ፡ አምቢን ፡ ቱርናት ፡ ሴላን ፡ ማክሳር ፤ ከሚባሉት ፡
አገሮች ፡ ገቡ ። ኃይላቸው ፡ የፈቀደላቸውን ፡ አገሮች ፡ ተገገርዎቻቸው ፡
ሲያደርጉ ፡ በኃይል ፡ ለማስገበር ፡ ያልቻሉትን ፡ አገር ፤ አገረ ፡ ገገርዎች ፡
ከሆኑት ፡ ካገሩ ፡ ተወላጆች ፡ መሳፍንቶች ፡ ጋራ ፡ እየተስማሙ ፡ የን
ግድ ፡ ውል ፡ ተፈራረሙ ። ቀጥሎ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡

ብሬዚል ፤ ታባጐ ፤ ኩራሳዎ ፤ ጉያን ፡ የሚባሉትን ፡ አገሮች ፡ ያዙ ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሁለቱ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ ንግዳቸውን ፡ እያስፋፉ ፡
ሄዱ ። የሆላንድ ፡ ኃይል ፡ ይልቁንም ፡ በንግድ ፡ በኩል ፡ እያደገ ፡ ሲሄድ ፡
የእስፓኛ ፡ ኃይልና ፡ ጥቅም ፡ እየደከመ ፤ እየወደቀ ፡ ሄደ ። ከዚህም ፡
የተነሣ ፡ እስፓኛ ፡ በንዴት ፡ ምክንያት ፡ ሆላንድን ፡ የባሕር ፡ ሽረሪት ፡
ብላ ፡ ሠየመቻት ። ምክንያቱም ፡ መርከቦቿ ፡ በሁሉም ፡ ውቅያኖሶች ፡
ላይ ፡ ከመዘዋወራቸው ፡ የተነሣ ፡ የመንገዶቻቸው ፡ መሥመሮች ፡ እንደ ፡
ሸረሪት ፡ ድር ፡ ተስፋፍተውና ፡ ተጠላልፈው ፡ የተዘረጉ ፡ በመሆናቸው ፡
ነው ።


ቀጥሎ ፡ በለው ፡ ዘመን ፡ ሆላንዶች ፡ አዲሷ ፡ ዜላንድ ፡ የተባለ
ችውንና ፡ ሌሎችም ፡ አዲሶች ፡ አገሮች ፡ አግኝተው ፡ ያዙ ።

በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ የአ
ንግሊዝ ፡ ኃይል ፡ ስለ ፡ ገነነ ፡ ሆላንድ ፡ ደግሞ ፡ ተራዋን ፡ ቅስሟ ፡ መሰ
በር ፡ ጀመረ ። በመጀመሪያ ፡ የፑርስሮን ፡ ደሴት ፡ የምትባለውን ፡ አገር ፡
እንግሊዝ ፡ ቀማቻት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሆላንዶች ፡ የተቀሙትን ፡ ተቀ
ምተው ፡ የተረፉዋቸውን ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ይኖራሉ ።

እንግሊዞች ፡ በንግሥት ፡ ኤልዛቤጥ ፡ ዘመን ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡
መያዝ ፡ ጀመሩ ። ይኸውም ፡ ከኒዩፀፖር ፡ እስከ ፡ ፲፭፻፫ ፡ (1533—1603 ፡)
ዓ. ም. መሆኑ ፡ ነው ። እንግሊዞች ፡ መጀመሪያ ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡
አንቲይ ፡ የሚባሉትን ፡ አገሮች ፡ ያዙ ። ከዚያም ፡ የሕንድን ፡ አገር ፡
ያዙ ። ቀደም ፡ ብለው ፡ ደግሞ ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ሲየራ ፡ ሌዮኔ ፡
የሚባለውን ፡ አገር ፡ ከፖርቱጋል ፡ ቀምተው ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡
ይዘው ፡ ነበር ። በቅኝ ፡ አገር ፡ በኩል ፡ እንግሊዝ ፡ ያገኙትው ፡ መስ
ፋፋት ፡ ከሷ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ባለቅኝ ፡ አገሮች ፡ ከሆኑት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ሆነ ። ይህንኑም ፡ ለመረዳት ፡ የተ
ባበሩትን ፡ የአሜሪካ ፡ አገሮችና ፡ አስትራሊ ፡ የሚባለውንም ፡ አገር ፡
መመልከት ፡ ይበቃል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንግሊዝ ፡ በአሜሪካ ፤ በአ
ፍሪካ ፡ በእስያ ፤ በአሴያኒ ፡ በየጊዜው ፡ የያዘቻቸውን ፡ የቅኝ ፡ አገ
ሮች ፡ ለመዘርዘር ፡ ሰፊ ፡ ቦታ ፡ ስለሚፈልግ ፡ የዓለምን ፡ ክርታ ፡ መመ
ልከት ፡ ይበቃል ።

Scanned with CamScanner

የዕውቀት ፡ ብልጭታ ።



በ ሥርዝ ፡ ድልድይ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የጠበጠ ፡ ውጊያ ።

ለምሳሌ ፤ ፍራንሲስ ፡ ድሬክ ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ መርከበኛ ፡ በወንበዴነት ፡ በውቅያኖስ ፡ ባሕሮች ፡ ላይ ፡ እየተዘዋወረ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሲመላለሱ ፡ የሚያገኟቸውን ፡ የእስፓኛ ፡ መርከቦች ፡ እየወጋ ፡ ከቅኝ ፡ አገሮቻቸው ፡ ወደ ፡ እስፓኛ ፡ ሊወስዱ ፡ የጫኑትን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ይቀማቸው ፡ ነበር ።

እንደዚሁም ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ክፍል ፡ በያዟቸው ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ በየወደቦቹ ፡ ቆመው ፡ በሚገኙት ፡ መርከቦቻቸው ፡ ላይ ፡ በድንገት ፡ አደጋ ፡ እየጣለ ፡ ያቃጥልባቸው ፡ ነበር ።

ከቅኝ ፡ አገሮቻቸውም ፡ ብዙዎቹን ፡ ቀምቷቸዋል ። ቢሞሩ ፡ ፍራንሲስ ፡ ድሬክ ፡ የእስፓኛ ፡ ኃይል ፡ እየተሰበረና ፡ የእንግሊዝ ፡ ጉልበት ፡ እየገነነ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ በሰፈው ፡ የረዳ ፡ ሰው ፡ ነው ።

በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ወደፊት ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ ታሪክ ፡ ለብቻው ፡ በሰፈው ፡ እንጽፈዋለን ።

ለፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ አገልግሎት ፡ በመሥራቱና ፡ በሁሉም ፡ ረገድ ፡ ክብርዋ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ ታላላቅ ፡ ነገሮች ፡ በመፈጸሙ ፡ በታሪክ ፡ ስመ ፡ ጥሩነትን ፡ ያገኘ ፡ ሪሸሊየ ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ የፈረንሳይ ፡ ፖሊቲክ ፡ ወደ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ጉዳይ ፡ እንዲመራ ፡ ማድረግ ፡ ስለ ፡ ጀመረ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ፈረንሳይም ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠራናቸውን ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ትልም ፡ ተከትላ ፡ በየዓለሙ ፡ ክፍል ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ስትይዝ ፡ ኖረች ። በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ፈረንሳይ ፡ የሰሜን ፡ አሜሪካን ፡ አገር ፡ በሙሉ ፡ ስለያዘች ፡ ግዛቷ ፡ በካሊፎርኒና ፡ በሜክሲክ ፡ በኩል ፡ ከባሕር ፡ ጋራ ፡ ይገጥም ፡ ነበር ። ከካናዳም ፡ እንደዚሁ ፡ ትልቅ ፡ ያገር ፡ ክፍል ፡ ይዛ ፡ ነበር ። ቀጥሎ ፡ በአፍሪካና ፡ በእስያ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ በየዘመኑ ፡ ብዙ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ያዘች ። ነገር ፡ ግን ፡ በአሜሪካና ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ የነበሩዋትን ፡ ብዙዎቹን ፡ አገሮች ፡ እንግሊዝ ፡ ስትቀማት ፡ የተረፈው ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዛሬ ፡ በለቅኝ ፡ አገሮች ፡ ከሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ቀጥላ ፡ ብዙ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ያላት ፡ ፈረንሳይ ፡ ነች ።

የቅኝ ፡ አገር ፡ ማለት ፡ ትርጕሙ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንመልከት ።

Scanned with CamScanner

አንድ ፡ መንግሥት ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ ያ
ረገውን ፡ ደከማ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ ፡ ከቀንበር ፡ አግብቶ ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ
የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ ለራሱ ፡ እያደረገ ፡ ሕዝቡንም ፡ በወደደው
ወይነት ፡ የጭቆና ፡ ሕግ ፡ ያስተዳድረዋል ። ይህንንም ፡ አሳብ ፡ ለ
ፈጸም ፡ እንዲመቸው ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ አገር ፡ አቅኒዎች ፡ የሆኑ
ሰዎች ፡ ከወገኖቹ ፡ መካከል ፡ በብዙ ፡ እየላከ ፡ በቅኝው ፡ አገር ፡ ውስጥ
ተቀምጠው ፡ እንዲሠሩና ፡ እንዲበላጽጉ ፡ ያደርጋል ። እነሱም ፡ የ
ፖለቲካቸውን ፡ ያህል ፡ ከቀኚው ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ሀብቱንና ፡ መ
ቱን ፡ ርስቱንም ፡ እየገፈፉ ፡ የራሳቸውን ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ማ
ሚያ ፡ ያደርጉታል ።

አውሮፓውያን መጀመሪያ በአሜሪካ አገር ቅኝ አገሮች በያዙ
ጊዜ አገሩን የሚያለሙት በባሮች ጉልበትና ድካም ነበር። ወደ
ሦስት መቶ ዓመት በሚጠጋ ዘመን ውስጥ የቅኝ አገሮቻቸውን
በባርያ ጉልበት ሲያለሙ ከቆዩ በኋላ የፋብሪካ ጥበብ ተገኝቶ ትልቅ
አርምጃ በማድረጉ የኤኮኖሚን ጉዳይ ለዋወጠው።

ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ በፋብሪካ ፡ ምክንያት ፡ ሀብታቸው ፡
አለመጠን ፡ እየጨመረና ፡ እየተስፋፋ ፡ በመሄዱ ፡ ከ፲፰፻፲፭ ፡ (1815) ፡
ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ለቅኝ ፡ አገር ፡ ጉዳይ ፡ አዲስ ፡ አስተያየት ፡ ሰጡት ።
ይኸውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ፋብሪከቻቸው ፡ ለሚሠሩዋቸው ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ ነገሮች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እንደ ፡ ብረታ ፡ ብረት ፡ ጥሮ ፡ ሌላም ፡
ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ከመሬት ፡ የሚወጣ ፡ ሀብት ፡ በብዙ ፡ የሚያገ
ኙበትና ፡ ፋብሪከቻቸው ፡ ሠርተው ፡ የሚያቀርቡትንም ፡ የሸቀጥ ፡ ዕቃ ፡
እየወሰዱ ፡ የሚሸጡበት ፡ አገሮች ፡ ማግኘት ፡ ትልቅ ፡ ጥቅም ፡ የሚ
ሰጣ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ለእነዚህ ፡ ለሁለቱ ፡ ነገሮች ፡
የሚያገለግሉ ፡ በመሆናቸው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሀብታም ፡ የሆነ ፡ መሬት ፡
የያዙትን ፡ ጉልበት ፡ የሌላቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ እየወጉ ፡ የተገዢነትን ፡
ቀንበር ፡ ይጭኑባቸው ፡ ጀመር ።

ከዚህም ፡ ኖተንሣ ፡ አውሮፓ ፡ በፋብሪካ ፤ በዕውቀት ፤ በኃይል ፡
በሀብት ፤ በጠቅላላው ፡ በሥልጣኔ ፡ ሊታመን ፡ በማይቻል ፡ አኳኋን ፡
ሰፊ ፡ አርምጃ ፡ በደረገችበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የሚያስፈልጓትን ፡
ከመሬት ፡ የሚገኙ ፡ ሀብቶች ፡ በገርዋ ፡ ውስጥ ፡ ስለማታገኝ ፡ የቅኝ ፡
አገሮች ፡ በይኖሩ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ ይበጃት ፡ ነበር ? በለምለምነትም ፡
ሆነ ፡ ወይም ፡ በማዕድን ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ሀብት ፡ ያላቸው ፡ አገሮች ፡
ሕዝቦቻቸው ፡ ዕውቀት ፡ ስለሌላቸው ፡ ሳይጠቀሙበት ፡ ይኖራሉ ።
ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህንኑ ፡ አስቦ ፡ እነዚህን ፡ አገሮች ፡ ለኛ ፡
መጠባበቂያ ፡ አድርጎ ፡ አኖረልን ። በዕውቀት ፡ ስትገለምስ ፡ በመሬት ፡
ሀብት ፡ አርያታ ፡ የነበረችውም ፡ አውሮፓ ፡ በቅኝ ፡ አገሮች ፡ ርዳታ ፡
ለመታደስ ፡ ቻለች ፡ እያሉ ፡ ያውሮፓ ፡ ሰዎች ፡ አሰቡ ፤ ተናገሩም ።
ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእነሱ ፡ መጠቀሚያ ፡ አድርጎ ፡ መፍ
ጠሩ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። እግዚአብሔርስ ፡ ባዥር ፡ ቃል ፡
"የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ አትመኝ ፡" ሲል ፡ ክልክሏል ። እውነተኛውስ ፡
ነገር ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡ ቢያድርባቸው ፡ ምንም ፡ ጥበብን ፡
ቢመረምሩ ፡ ምንም ፡ ቢሠለጥኑ ፡ የራሳቸውን ፡ ንብረት ፡ ለማልማት ፡
ሲሉ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ከማፍረስ ፤ የራሳቸውን ፤ ኑሮ ፡
ለማሻሻል ፡ ሲሉ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ መሥዋዕት ፡ ከማ
ድረግ ፡ በለመታገዳቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ከሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ይገ
ኛል ፡ ተብሎ ፡ ከቶ ፡ የማይታሰብ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ መታየቱ ፡ ነው ።

አውሮፓ ፡ የፋብሪካን ፡ ጥበብ ፡ ከማስፋፋቷ ፡ አስቀድሞ ፡ ለም
ሳሴ ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ በያዙ ፡
ጊዜ ፡ የቅኝ ፡ አገሩ ፡ ጠቃሚነት ፡ የሚታወቀው ፡ በውስጡ ፡ ያሉት፤
ያገሩ ፡ ተወላጆች ፡ በግብርናም ፡ ሆነ ፡ አትክልት ፡ በመትከል ፤ ወይም ፡
ከብት ፡ በማርባት ፡ በኩል ፡ በሚሰጡት ፡ አገልግሎት ፡ መጠን ፡
ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፤ ሲስፋፋ ፤ መሬቱን ፡ በእ
ርሻ ፡ መኪና ፡ ለማረስና ፡ በጠቅላላው ፡ ሰው ፡ ይሠራው ፡ የነበረ

Scanned with CamScanner


ውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በመኪና ፡ ለመሥራት ፡ በመቻሉ ፡ የቅኝውን ፡ አገር ፡ ለማልማት ፡ ያገሩ ፡ ተወላጆች ፡ የማያስፈልጉ ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ።

ስለዚህ ፡ አገር ፡ አቅኚዎች ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ መሬቲን ፡ ያለ ድክም ፡ በመኪና ፡ እያለሙ ፡ የራሳቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ዘር ፡ እንዲበዛ ፡ ብቻ ፡ ስላሰቡ ፡ የቅኝ ፡ አገሩን ፡ ተወላጅ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ነገርና ፡ እንደ ፡ ሸክም ፡ አድርገው ፡ ተፅእኖለከቱት ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ውለሙ ፡ አድሮ ፡ መብቱን ፡ ጠያቂ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚነሣ ፡ ከማሰባቸው ፡ የተነሣ ፡ አገሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕዝቡ ፡ ምንም ፡ አይጠቅመንም ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ አመጡ ። ይኸውም ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በያዘችበት ፡ ባጭሩ ፡ ጊዜ ፡ ተከትላው ፡ የነበረው ፡ ፖሊቲክ ፡ መሆኑን ፡ የሚዘነጋው ፡ ሰው ፡ የለም ። እንግዲህ ፡ አሁን ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ጉዳይ ፡ በዓለም ፡ ፖሊቲክ ፡ ውስጥ ፡ እንዲወለድ ፡ ያደረገውን ፡ መዘዝ ፡ እናስተውል ።

በግፍ ፡ የሚገኝ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጠብና ፡ ሁከት ፡ ማስከተሉ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በአውሮፓውያን ፡ ሠንፈስ ፡ ውስጥ ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ ጉዳይ ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ከመዋጋትና ፡ ከመበጣጠጥ ፡ አላቋረጡም ። ከቅኝ ፡ አገሮች ፡ በተገኘው ፡ ሀብት ፡ ኃይላቸውና ፡ ክብራቸው ፡ እየገነነ ፡ በሄደበት ፡ መጠን ፡ መሠዙም ፡ ያንኑ ፡ ያህል ፡ የሚያሠጋቸው ፡ ሆኖል ። የመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ የተነሣበት ፡ አንዱ ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ በቅኝ ፡ አገር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ማስረጃ ፡ የጀርመን ፡ ንጉሥ ፡ ዳግማዊ ፡ ጊዮም ፡ በደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ ምክንያት ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋር ፡ ቂምን ፡ አበቀለ ፡ በኋላም ፡ በግሮክ ፡ ምክንያት ፡ ያነሣው ፡ ትልቅ ፡ ሁከት ፡ እየተፋፋመ ፡ ሄደ ። ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ የበረደ ፡ ከመሰለ ፡ በኋላ ፡ ተምልሶ ፡ በባልካን ፡ ውስጥ ፡ በመንደዱ ፡ ያለም ፡ ጦርነት ፡ እንዲፈነዳ ፡ አደረገ ።

አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ደግሞ ፡ ሂትለር ፡ በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጀርመን ፡ ድል ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ የተቀማችው ፡ የቅኝ ፡

አገሮች ሊመልሰላት ፡ ይገባል፡ ብሎ ፡ ያደረገው ፡ ጥያቄ ፡ በተሩት ፡ መንግሥታት፡ ዘንድ፡ ተሰሚነት፡ ባለማግኘቱ ፡ የሁለተኛው ፡ የዓለም



ከውጊያ፡ በኋላ አሸናፊዎቹ፡ ከጠላት፡ መርከብ፡ ላይ፡ የዘረፉትን፡ ወርቅና፡ ብር፡ ሲከፋፈሉ

ጦርነት፡ ፊንዳ። ኢጣሊያ፡ በመጀመሪያው ፡ የዓለም፡ ጦርነት፡ ከዳር ሆና ፡ የድል ፡ አድራጊነቱ ፡ ሚዛን ፡ ወደ ፡ ማን ፡ ወገን ፡ እንደሚ

Scanned with CamScanner

ያደላ ፡ ስትመለከት ፡ ከቄየች ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ አገማሚያውን ፡ አይታ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ጓደኞቿ ፡ ዘረች ።

ጦርነቱ ፡ ሲያልቅ ፡ የጀርመን ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ ዕጣ ፡ በሰላም ፡ ዕርቅ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ቀርቦ ፡ አብዛኛውን ፡ ድርሻ ፡ እንግሊዝ ፡ ስት ወስድ ፡ ኢጣሊያ ፡ የደረሳት ፡ ግን ፡ ለወላዋይ ፡ ሰው ፡ በሚገባው ፡ መጠን ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ስለሆነ ፡ ምስኪን ፡ የሆነው ፡ ብልጣቂ ፡ የተመኘችውን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ሳይሰጥ ፡ በመቅረቱ ፡ አፍሯ ፡ ቀረች ።

በኋላ ፡ ግን ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ኃይላቸውን ፡ አድቅቆትና ፡ ሀብታቸውን ፡ ጨርሶት ፡ በማለፉ ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ጥቂት ፡ ማገም ፡ ሲጀምሩ ፡ ኢጣሊያ ፡ ከቅኝ ፡ አገር ፡ የደረሰኝ ፡ ድርሻ ፡ ጥቂት ፡ በመሆኑ ፡ ተጎድቻለሁ ፡ እያለች ፡ ስትናገር ፡ ከቄየች ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ በመውረሯ ፡ ምክንያት ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ ሰለተበጠበጠ ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደተናገርነው ፡ ሂትለር ፡ የጀርመንን ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ ድል ፡ አድራጊዎች ፡ ከነበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ለማስመለስ ፡ የሚሞክርበት ፡ ሰዓት ፡ የደረሰ ፡ መስሎ ፡ ታየው ። አውሮፓውያን ፡ የቅኝ ፡ አገሮችን ፡ ጨቁነው ፡ የሚገዟቸው ፡ የግል ፡ ሀብታቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያደረጉ ፡ ለመሄድ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚ ጊዜው ፡ በቅኝ ፡ አገር ፡ ምክንያት ፡ የሚነሣው ፡ ጦርነት ፡ አውሮፓን ፡ እያማቀቀ ፡ በማለፉ ፡ ይህ ፡ ተመላላሽ ፡ የሆነው ፡ ጦርነት ፡ በመጨረሻ ፡ ጨርሶ ፡ ለመነሣት ፡ እንደማትችል ፡ አድርጎ ፡ የሚያስቀራት ፡ መሆኑን ፡ ዛሬ ፡ ማነኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በትክክል ፡ ሊገምተው ፡ ችሏል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ቀንበር ፡ የወደቀባቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ኃይል ፡ አግኝተው ፡ ግዛዎቻቸውን ፡ ባይጎዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀብታቸውን ፡ በግፍ ፡ ላይ ፡ ያቋቋሙ ፡ ኃያላን ፡ በዚያው ፡ በግፍ ፡ ሀብታቸው ፡ ምክንያት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተዋጉ ፡ በመድከማቸው ፡ ረግጠው ፡ የሚገዟቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ነፃነታቸውን ፡ የሚያገኙበትን ፡ መንገድ ፡ ራሳቸው ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ አደረገ ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ የሚያስተውል ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጠቢባን ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ጠቢብ ፡ ከኃያላን ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ኃያል ፡ በመሆኑ ፡ መጠን ፡ ሥራውን ፡ እንደሚሠራ ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል ።

ሕንድ ፡ ፣ ግብፅ ፡ ፣ ሶርያ ፡ ፣ ኢንዶኔዚ ፡ ነፃነታቸውን ፡ ለማግኘት ፡ የቻሉት ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ነው ። ብዙ ፡ አገሮች ፡ እንደዚሁ ፡ ወደፊት ፡ ነፃ ፡ እንደሚወጡ ፡ አይጠረጠርም ። እነዚሁ ፡ ተገዢዎች ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በተነሣ ፡ ቁጥር ፡ ግፈኞችን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ በሆነው ፡ ውጊያ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ከገገርዎቻቸው ፡ ጋር ፡ ጉን ፡ ለጉን ፡ ተሰልፈው ፡ እየተዋጉ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ነፃነትና ፡ ስለ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ደማቸውን ፡ በማፍሰሳቸው ፡ የራሳቸውን ፡ ነፃነት ፡ መጠየቅና ፡ ማግኘት ፡ እንደሚገባቸው ፡ የዓለም ፡ ሕሊና ፡ ተረድቶታል ።

በግፍና ፡ በጭካኔ ፡ ቀንበር ፡ ተጨቁነው ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ ነፃነታቸውን ፡ በኛ ፡ ዘመን ፡ ሲያገኙ ፡ ማየታችንና ፡ ይህን ፡ የመሰለውም ፡ የግፍ ፡ አገዛዝ ፡ እንዲቀር ፡ እንዲደረግ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሲያስቡ ፡ መመልከታችን ፡ ዕድለኞች ፡ ነን ። በርያ ፡ መሸጥና ፡ መግዛት ፡ ከዓለም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተወገደ ፡ ሁሉ ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ አገዛዝም ፡ እንደዚሁ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጨርሶ ፡ እንደሚደመሰስ ፡ አይጠረጠርም ።

የግፍ ፡ አገዛዝ ፡ ከዓለም ፡ ላይ ፡ ከልጠፋ ፡ በቀር ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሰላምን ፡ ለማግኘት ፡ እንደማይችሉ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ነፃ ፡ እንዲወጡ ፡ ማድረግና ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ የሚባለውን ፡ አገዛዝ ፡ ጨርሶ ፡ ማስወገድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ራሳቸው ፡ በለቅኝ ፡ አገሮች ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ተረድተውታል ።

Scanned with CamScanner

ትንቢተ ፡ ዮናስ ።

በሕዝብዋ ፡ መከከል ፡ ዓመፅ ፡ ስለ ፡ ጸና ፤
በጣም ፡ ተቈጥቼ ፡ አዝኛለሁና ፡
ይህን ፡ ለነነዌ ፡ ንገራት ፡ በአዋጅ ፡
አለና ፡ ለዮናስ ፡ ለአሚታይ ፡ ልጅ ፡
እግዚአብሔር ፡ አዘዘው ፡ እንዲሄድ ፡ ቢዮሎ ፡
ዮናስ ፡ እምቢተኛው ፡ አሰበ ፡ ክብልሎ ፡
ከአምላክ ፡ ተደብቆ ፡ አምልጦ ፡ ሊጠፋ ፡
ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ሊጓዝ ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ያፋ ።
ዋጋ ፡ ከፈለና ፡ በመርከብ ፡ ተሳፍሮ ፤
እያጉረመረመ ፡ ባሕሩን ፡ ተሻግሮ ፡
ዮናስ ፡ ተደብቆ ፡ ሲሄድ ፡ በግሥጋሣ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ተልከ ፡ ማዕበል ፡ ተነሣ ፡
ታላቅ ፡ ሞገድ ፡ ሆኖ ፡ ባሕሩ ፡ ተቈጣ ፡
መርከበኞች ፤ ፈሩ ፤ ትልቅ ፡ ሽብር ፡ መጣ ፡
መርከቡ ፡ እንዲቀልለው ፡ እናድርግ ፡ አያሉ ፡
አንሥተው ፡ ብዙ ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉ ።
ባሕሩም ፡ ባሰበት ፡ በጣም ፡ ተናወጠ ፡
መርከቡ ፡ መሰለ ፡ የተገለበጠ ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተነሣ ፡ ጸሎት ፡ ለማድረስ ፡
ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ተኝቷል ፡ ዮናስ ።
ወደ ፡ ዮናስ ፡ ሄዶ ፡ የመርከቡ ፡ አለቃ ፡
ቀሰቀሰውና ፡ ከእንቅልፉ ፡ ሲነቃ ፡
እግዜር ፡ እንዲያድነን ፡ ከዚህ ፡ ክፉ ፡ ጥፋት ፡
ተነሥ ፡ ጸልይ ፡ አለው ፡ ይብቃህ ፡ ማንቀላፋት ።
በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡
ተመካከሩና ፡ በነገሩ ፡ አሰቡ ፡
አለ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቶ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ የመጣ ፡
ለይተን ፡ ለማወቅ ፡ እንጣጣል ፡ ዕጣ ።

አለዚያ ፡ አንድንም ፡ ስለተባባሉ ፡
ተሰበሰቡና ፡ ፅጣ ፡ ቢጣጣሉ ።
እውነትም ፡ እንዳሉት ፡ አጥፊው ፡ ሰው ፡ ታወቀ ፡
በእምቢተኛው ፡ ነቢይ ፡ በዮናስ ፡ ወደቀ ።
ዮናስ ፡ ተረዳና ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡
ያጠፋውን ፡ ጥፋት ፡ ገልጦ ፡ ተናዘዘ ፡
ምነው ፡ በትመጣ ፡ ተጣልተህ ፡ ከጌታ ።
እየው ፡ መርከባችን ፡ እንደሚንገላታ ፡
ቀጣው ፡ እንዲታገስ ፡ ለማግኘት ፡ ጸጥታ ፡
በል ፡ አንተው ፡ ፍረደኝ ፡ ምን ፡ ይበጃል ፡ ቢሉ ፡
ዮናስ ፡ መለሰና ፡ እዚህ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡
ስለምን ፡ ይጠፋል ፡ በኔ ፡ የተነሣ ፡
ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉኝ ፡ አለበኝ ፡ አበሳ ።
ተመልከቱ ፡ እነሆ ፡ ሥራውን ፡ ዐወቀ ፡
ጥፋቱን ፡ ገለጠ ፡ ይኸው ፡ መኾ ፡ ደበቀ ፡
እሱው ፡ ከፈረደ ፡ መልሶ ፡ በራሱ ፡
ምን ፡ እናድርግ ፡ ብለው ፡ ሊጥሉት ፡ ተነሡ ።
ከደሙ ፡ እንፃን ፡ ሲሉ ፡ ለእግዜር ፡ አመልክተው ፡
ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉት ፡ ዮናስን ፡ አውጥተው ።
በዮናስ ፡ ላይ ፡ ኖሮ ፡ የመጣው ፡ ይህ ፡ መዓት ፡
ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ አለ ፡ ልክ ፡ በዘያው ፡ ሰዓት ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ዮናስን ፡ እንዲውጥ ፡ ሕይወቱን ፡ ሳይጎዳ ፡
አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዓሣ ፡ እግዜር ፡ አሰናዳ ።
ዮናስም ፡ ተውጦ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡
ሦስት ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ሲያድር ፡ ባሣ ፡ ሆድ ፡



ተቀይመህ ፡ ኖሮ ፡ ከላይ ፡ ብትቈጣ ፡
ይህን ፡ ያህል ፡ መዓት ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ መጣ ።
የበሕሩ ፡ ሞገድ ፡ እኔን ፡ አዋከበኝ ፡
ውኃና ፡ ጨለማ ፡ ሲአልም ፡ ከበበኝ ፡
እያለ ፡ ባሣ ፡ ሆድ ፡ ዮናስ ፡ ሲቀመጥ ፡
አምላኩን ፡ ለመነው ፡ በመለማመጥ ፡
የታዛዥነትም ፡ ጠባይ ፡ እያሳየ ፡
አዝኖ ፡ ተጸጽቶ ፡ ከልቡ ፡ ጸለየ ።
ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢቈጣ ፡ ነውና ፡ መሓሪ ፡
ፊቱን ፡ መልሶለት ፡ ታረቀው ፡ ፈጣሪ ፡
ዓሣውም ፡ ዮናስን ፡ ውጦ ፡ ሳያስቀረው ፡
ከባሕር ፡ ተፋና ፡ መሬት ፡ ወረወረው ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ይህንን ፡ የእኔን ፡ ቃል ፡ ስማና ፡ በቶሎ ፡
ሄደህ ፡ ለነነዌ ፡ እንድትነግራት ፡ ብሎ ፡
ደገመና ፡ እግዚአብሔር ፡ ዮናስን ፡ አዘዘ ፡
ነነዌ ፡ ሊገባ ፡ ዮናስም ፡ ተጓዘ ።
ድምጡን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ነቢዩ ፡ ዮናስ ፡
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
ነነዌ ፡ ጠፊ ፡ ነች ፡ ከሥር ፡ ተገልብጣ ፡
አለና ፡ ለፈፈ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቍጣ ።
ሳያንገራግሩ ፡ ሁሉም ፡ ስላመኑ ፡
የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ ተጨንቀው ፡ አዘኑ ።
ከትልቅ ፡ ጀምሮ ፡ ሕፃኑ ፡ ድረስ ፡
ሕይወቱ ፡ የቆመች ፡ በሥጋ ፡ በነፍስ ፡
ሰውም ፡ ሆነ ፡ እንስሳ ፡ ይቀበል ፡ ንስሓ ፡
ፍጡር ፡ ሁሉ ፡ ይጹም ፡ ይለይ ፡ ከእህል ፡ ውኃ ።
ሁሉም ፡ ክልብ ፡ አዝኖ ፡ ማቅ ፡ እየለበሰ ፡
ከክፉ ፡ ወደ ፡ ደግ ፡ እየተመለሰ ።
መቼም ፡ ወሰን ፡ የለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሕረቱ ፡
ይጸልይ ፡ አለና ፡ ይለምን ፡ በብርቱ ፡

Scanned with CamScanner

ንገሡ ፡ አሳወጀ ፡ ከነመኳንንቱ ።።
የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ በውነት ፡ ከልቡና፡
መጸጸታቸውን ፡ እግዚአብሔር ፡ አየና ።።
ፍጡር ፡ ቢለምነው ፡ እንባ ፡ እያፈሰሰ፡
ምሕረቱን ፡ አውርዶ ፡ መዓቱን ፡ መለሰ ።።

ምዕራፍ፡ ፬ ።።

የተናገረው ፡ ቃል ፡ ስላልተፈጸመ ፡
ዮናስ ፡ ተቆጥቶ ፡ እያጉረመረመ ፡
እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ጸለየ ፡ ወደ ፡ አምላክ ፡
እኔን ፡ መጀመሪያ ፡ ነነዌ ፡ ለመላክ ።።
አስበህ ፡ ብታዘዝኝ ፡ ይህንኑ ፡ ዐውቂ ፡
ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ልሄድ ፡ ጠፋሁ ፡ ተደብቄ ፡
ምሕረትህ ፡ የበዛ ፡ መሐሪና ፡ ታጋሽ ፡
በደል ፡ የምትረሳ ፡ ክቱጣ ፡ ተመላሽ ፡
የቁጣህን ፡ ያህል ፡ ምሕረትህ ፡ የጠና ፡
መሆንህን ፡ ጥንቱንም ፡ እነ ፡ ዐውቃለሁና ።።
እኔን ፡ ግን ፡ ግደለኝ ፡ ልሙት ፡ ልቀበር ፡
ሐሰት ፡ ተናግሬ ፡ የማይሆን ፡ ነገር፡
አልፈልግምና ፡ ቆሜ ፡ ለመኖር ።።
ከከተማ ፡ ወጥቶ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡
ከወደ ፡ ዳር ፡ ኖኖ ፡ ነነዌን ፡ ሊያስተውል ፡
ምን ፡ እንደሚያገኝት ፡ ለማየት ፡ ዮናስ ፡
ሠርቶ ፡ ተቀመጠ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ዳስ ።።
እግዜር ፡ በጥበቡ ፡ አንድ ፡ ቅል አብቅሎ ፡
ቅሉም ፡ አደገና ፡ ከፍ ፡ ከፍ፡ ብሎ፡
የዮናስ ፡ ራሱ ፡ እንዲያገኝ ፡ ጥላ ፡
ለፀሓዩ ፡ ንዳድ ፡ ሆነለት ፡ ከለላ ።።
በዚህ ፡ በቅል ፡ ነገር ፡ ዮናስን ፡ ደስ ፡ አለው ።።
እንዲህ ፡ ቶሎ ፡ ደርሶ ፡ ስላገለገለው ፡
እግዜር ፡ በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ በማለዳ፡
ቅል ፡ የሚበላ ፡ ትል ፡ ፈጠረ ፡ አሰናዳ ።።

ትሉ ፡ ቅሉን ፡ በልቶ ፡ በፍጥነት ፡ ደረቀ ፡
ፀሓይ ፡ ወጣችና ፡ ጊዜው ፡ በጣም ፡ ሞቀ ።።
እዜር ፡ አዘዘና ፡ ትኩስ ፡ ነፋስ፡ መጣ ፡
የሚከለልበት ፡ መጠጊያ ፡ ስላጣ ፡
ቅሉ ፡ ደረቀና ፡ ንዳድ ፡ ቢያቃጥለው ፡
ዮናስ ፡ ተበሳጭቶ ፡ ለአምላክ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡
እንደዚህስ ፡ ሆኜ ፡ ቆሜ ፡ ከመኖር ፡
እባክህ ፡ ግደለኝ ፡ ልሙት ልቀበር ።።
ደረቀብኝ ፡ ብለህ ፡ ይህን ፡ ቅል ፡ በማጣት ፡
እውን ፡ ይገባል ፡ ወይ ፡ የአንተ ፡ አሁን ፡ መቆጣት ?
ብሎ ፡ እግዜር ፡ ቢጠይቅ ፡ መለሰ ፡ ዮናስ ፡
በንዴት ፡ ብዛት ፡ አስከሞት ፡ ድረስ ፡
አዎን ፡ ይገባኛል ፡ መናደድ ፡ መጨሰ ።።
እግዜርም ፡ መለሰ ፡ ለምን ፡ ጠፋ ፡ ስትል ፡
ይህ ፡ ያልለፋህበት ፡ ያልደከምህበት ፡ ቅል ፡
አንተ ፡ ስትናደድ ፡ ፈጥፈያት ፡ እኔማ ፡
ሳጠፋት ፡ ሳፈርሳት ፡ ነነዌን ፡ ከተማ ፡
መቶ ፡ ሃያ ፡ ሺ ፡ ነው ፡ የሕዝበዋም ፡ ብዛት ፡
ለምን ፡ ትቆጣለህ ፡ እኔ ፡ ባገሬንላት ፡
ብሎ ፡ በምሳሌ ፡ ሲያስተምር ፡ ይቀርታ ፡
ለዮናስ ፡ ነገረው ፡ የምሕረቱ ፡ ጌታ ።።
ለእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ምስጋና ፡ ይድረስ ፡
በዚህ ፡ ተፈጸመ ፡ ትንቢተ ፡ ዮናስ ።።

ከመጠጥ፡ የሚመጣ፡ ጉዳት።።

የሚያሰክር ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነት ፡ መጠጥ ፡ በመጠጣት ፡ ኣል
ኮሊስም ፡" የሚባል ፡ አልኮል ፡ የሚመጣ ፡ ልዩ፡ ልዩ ፡ በሽታ።
በሰውነት ፡ ውስጥ ፡ ይፈጠራል ።። ከአልኮል ፡ የሚመጣ ፡ በሽታ ፡ ዓይ
ነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ።። የመጀመሪያው ፡ ስካር ፡ የሚባል ፡ አጭር ፡ በሽታ ፡
ነው ።። መጠጥ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ጤንነት ፡ የማይስማማ ፣ መሆኑን ፡ የሚ

Scanned with CamScanner

ያስረዱን ፡ ቡብዙ ፡ ዓይነት ፡ ምርመራ ፡ የደረሱበት ፡ በአሁኑ ፡ በ
ልጣኔው ፡ ዘመን ፡ ያሉ ፡ ትልልቆቹ ፡ የሕክምና ፡ መምህራን ፡ ግ
አይደሉም ። የጥቡብ ፡ ምንጭ ፡ የሆነውን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ እስከ
ገልጠን ፡ እናንብብ ።

ኖኅ ፡ ሥራው ፡ ግብርና ፡ ስለነበረ ፡ መሬት ፡ እያረሰ ፡ ሲኖር ፡
የወይን ፡ አትክልት ፡ ተክሎ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አሰናዳና ፡ ጠጥቶ ፡
ፅከረ ። ከአእምሮውም ፡ ስለወጣ ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ልብ
ሱን ፡ ጥሎ ፡ ራቁቱን ፡ ታየ ። ከልጆቹ ፡ አንዱ ፡ ክፉ ፡ የሚባለው ፡
ነውሩን ፡ ሳይሸሽግለት ፡ ሲቀር ፡ ሴምና ፡ ያፌት ፡ ግን ፡ ፊታቸውን ፡
ወደኋላቸው ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወደ ፡ ኖኅ ፡ ቀረቡና ፡
ልብስ ፡ አለበሱት ። ኖኅም ፡ ከስካር ፡ እንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ አእምሮውን ፡
ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ካምን ፡ ረግሞ ፡ ሴምና ፡ ያፌትን ፡ ባረካቸው ። አሪት ፡
ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፱ ፡ ቁጥር ፡ ከ፳ ፡ እስከ ፡ ፳፯ ፡ ተመልከት ።

የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ዕሲምሰን ፡ እናት ፡ ተገለጠላት ፡ አላ
ትም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ፀንሰሽ ፡ ትወልጃለሽ ፡ የወይን ፡ ጠጅና ፡ ሌላም ፡
ማነኛውንም ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ እንዳትጠጪ ፡ ተጠንቀቂ ። ልጁ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ ነውና ፡ ከናቱ ፡ ሆድ ፡ ጀምሮ ፡ እሱም ፡
ከፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ እስራኤልን ፡ ማዳን ፡ ይጀምራል ። መጽ
ሐፈ ፡ መሳፍንት ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡ ቁጥር ፡ ከ፫ ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ተመልከት ፡

ለክህኑ ፡ ለዘካርያስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ተገለጠ ፡ የዮ
ሐንስ ፡ መጥምቁን ፡ መወለድ ፡ ሲነግረው ፡ ሚስትህ ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ልጅ ፡
ትወልዳለች ፡ ስሙንም ፡ ዮሐንስ ፡ ትለዋለህ ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በመ
ወለዱ ፡ ደስ ፡ ይሳቸዋል ። በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ታላቅ ፡ ይሆናልና ።
የወይን ፡ ጠጅ ፡ አይጠጣም ፤ እንዲሁም ፡ የሚያሰክር ፡ ማነኛውንም ፡
መጠጥ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመላበታል ፡ ከናቱ ፡ ሆድ ፡ ጀምሮ ።
የሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ከ፲፫ ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ተመ
ልከት ።

እንግዲህ ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ሁሉ ፡ ለጠጭውና ፡ ከእሱም ፡
ለሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ የሚጎዳ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳናል ። መጠጥ ፡ የሚ
ወድ ፡ ሰው ፡ በሰከረ ፡ ቁጥር ፡ ከሚደርስበት ፡ ውርደትና ፡ ጉዳት ፡
በላይ ፡ ደሙንና ፡ ውስጣዊ ፡ አካላቱን ፡ ይመርዘዋል ። በመጠጥ ፡

ምክንያት ፡ የ"አልኮሊስም" በሽታ ፡ የሚመጣው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከመ
ጠን ፡ ያለፈ ፡ በመጠጣት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂቱ ፡ ሆኖ ፡
ሳያቋርጡ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ በመጠጣት ፡ ምክንያት ፡ ነው ። መጠጥ ፡
ሊበል ፡ ከጠላ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አረቂ ፡ ድረስ ፡ ማነኛውም ፡ የሚ
ያስከር ፡ መጠጥ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

መጠጥ ፡ የሚያበዛ ፡ ሰው ፡ በሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡ አልኮል ፡ ይጠ
ራቀማል ፤ በጎላም ፡ በደም ፡ መመላለሻ ፡ ሥሮቹ ፡ ውስጥ ፡ እየገባ ፡
ሲዘጋው ፡ ሰውዬው ፡ በድንገት ፡ ይሞታል ። ወይም ፡ ሥሮቹን ፡ እያደ
ረቀ ፡ ሲያበላሻቸው ፡ ይበጠሳሉ ። ሥር ፡ በተበጠሰ ፡ ጊዜም ፡ ለሞት ፡
ይሰጣል ፤ ወይም ፡ ደሙ ፡ በሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡ ይፈስና ፡ ይህ ፡ ደሙ ፡
የፈሰሰበት ፡ አካል ፡ በድን ፡ ይሆናል ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ አል
ኮል ፡ ጨጓራና ፡ አንጀትን ፡ እያቃጠለ ፡ ያቁስላቸዋል ። አንዳንድ ፡
ጊዜም ፡ ወደ ፡ አንጐል ፡ እየወጣ ፡ ክፉ ፡ በሽታ ፡ ይሠራል ። በዚ
ህም ፡ ምክንያት ፡ ቀሺቃንጐ ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ ዕብድ ፡ ያደርጋል ።
ይህም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታ ፡ በሰው ፡
ልጅ ፡ ከሚመጡ ፡ ከሚያስፈሩት ፡ ክፉ ፡ ደዌዎች ፡ ጋር ፡ የሚቆ
ጠር ፡ ቍጥራቸው ፡ አያሌ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የፈጀ ፡ ነው ። ሁል
ጊዜም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መጠጥ ፡ የሚያበዙ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
አስጊዚያቸው ፡ ይቀሠፋሉ ። አሟሟታቸውም ፡ ድንገተኛ ፡ ነው ።
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ በሽታ ፡ ገደ
ለው ፡ ይበላል ፡ እንጂ ፡ በሽታው ፡ የመጣው ፡ ከአልኮል ፡ መሆኑን ፡
የሚያስበው ፡ ሰው ፡ የለም ።

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ከመሸታ ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ መጠጥ ፡
ሲጠጡ ፡ ተለይተው ፡ መቅረት ፡ ነውር ፡ እየመሰላቸው ፡ አብረው ፡
ገብተው ፡ እየጠጡ ፡ ያልነበረባቸውን ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ ይማራሉ ።
ግን ፡ ወዳኛ ፡ በቅብጠቱ ፡ ወደ ፡ አሳት ፡ ወይም ፡ ወዶ ፡ ገደል ፡
ሲገባ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ የሚቻለው ፡ ቢሆን ፡ ይከለክለዋል ፡ እንጂ ፡
ዓይኑ ፡ ሲያይ ፡ ተከትሎት ፡ አብሮ ፡ የሚገባ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጅል ፡
ሰው ፡ ነው ። ትንንሾች ፡ ልጆች ፡ ሳይቀሩ ፡ ከእነሱ ፡ በዕድሜ ፡ ከፍ ፡
ካሉት ፡ ከመጥፎ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ወይም ፡ ከማይረቡ ፡ ዘመዶቻቸው ፡
ጋር ፡ አብረው ፡ በመዋል ፡ እነሱን ፡ ተከትለው ፡ ከመሸታ ፡ ቤት ፡
እየገቡ ፡ መጠጥ ፡ ይለምዳና ፡ ይበላሻሉ ። ይህም ፡ በጣም ፡ የሚያ

Scanned with CamScanner

ሳገዝን ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ነው ። በመጠጥ ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣውን ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለውን ፡ ጉዳት ፡ ለመመልከትና ፡ የሕዝባቸውን ፡ ሀብትና ፡ ጤንነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲሉ ፡ አሜሪካኖች ፡ በአገራቸው ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ እንዳይሠራና ፡ እንዳይሸጥ ፡ ከውጪም ፡ አገር ፡ እየተላከ ፡ እንዳይገባ ፡ በጥብቅ ፡ አሰ ከልክለው ፡ ይኖራሉ ። ይህም ፡ በጣም ፡ የሚያስመሰግናቸው ፡ ነው ። በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንደ ፡ አሜሪካኖች ፡ ባዋጅ ፡ ባይከለከል ፡ በመጠጥ ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣውን ፡ ጉዳት ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ለመከላከል ፡ መድከማቸው ፡ አልቀረም ። ከሁሉም ፡ የባሰ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ የሚያስቱና ፡ የሚያሳዝኑ ፡ ብርድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሁልጊዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ሙቀት ፡ ይሰጠናል ፡ እያሉ ፡ አረቄ ፡ መጠጣትን ፡ ልማድ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። እስኪ ፡ አረቄ ፡ በጉንጫችሁ ፡ ይዛችሁ ፡ ጥቂት ፡ አቈይታችሁ ፡ ሞክሩት ፡ ሥጋችሁን ፡ እንደፈላ ፡ ውኃ ፡ ቀቅሎ ፡ ያገኘትረዋል ። ወደ ፡ ሆዳችሁ ፡ ውስጥ ፡ ያገባ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ልቦና ፡ ካላችሁ ፡ በዚህ ፡ ልትገምቱት ፡ ትችላላችሁ ። ጨጓራና ፡ አንጀትን ፡ እያቃጠለ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ሲጠብሳቸው ፡ ሙቀት ፡ መስጠቱ ፡ አይጠረጠርም ። ግን ፡ አረቄ ፡ በመጠጣት ፡ የሚገኘው ፡ ይህ ፡ ሙቀት ፡ የበሽታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የጤንነት ፡ ሙቀት ፡ አይ ምሰላችሁ ።

ሰው ፡ ሲበርደው ፡ ቡና ፡ ወይም ፡ ቻይ ፡ አፍልቶ ፡ ቢጠጣ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በእግሩ ፡ ቢሄድ ፡ ይሞቀዋል ፤ ይህም ፡ ሙቀት ፡ የጤንነት ፡ ሙቀት ፡ ነው ። ግን ፡ ሰው ፡ ብርድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወዘ ፡ ኖራበት ፡ ብትቀሰቀስ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ በሽታ ፡ ቢይዘው ፡ ትኩሳቱ ፡ ሲነሣ ፡ ይሞቀዋል ፡ ይህም ፡ ሙቀት ፡ አረቄ ፡ በመጠጣት ፡ ከሚገኘው ፡ ሙቀት ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል ። ከምሳ ፡ ወይም ፡ ከራት ፡ በኋላ ፡ አረቄ ፡ መጠጣት ፡ የብሉትን ፡ ምግብ ፡ እንዲንሸራሸር ፡ ያደርገዋል ፡ ይላሉ ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ አስቀድመው ፡ ሲጠጡት ፡ እህል ፡ ያባላል ፡ ይላሉ ። ሰው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታሞ ፡ ሲድን ፡ በገመምተኛነቱ ፡ ወራት ፡ እህል ፡ ያምረዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ሁልጊዜ ፡ መታመም ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደማሰብ ፡ ያህል ፡ ነው ። አረቄ ፡ እያቃጠለ ፡

የእሳትነቱን ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ያስርባል ፡ ወይም ፡ በልተው ፡ እንዳል በሉ ፡ ያደርጋል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የሚሠራው ፡ የመድኃኒትነት ፡ ሥራ ፡ የለውም ። ምክንያቱም ፡ በውስጡ ፡ ሰውነት ፡ ለመመገብ ፡ ወይም ፡ ለማበርታት ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ነው ። ምግብ ፡ ስንበላ ፡ ከሰውነታችን ፡ ጋር ፡ እየተዋሐደ ፡ ተስማምቶ ፡ ደምና ፡ ሥጋ ፡ ይሆናል ። አረቄ ፡ ግን ፡ በውስጡ ፡ ከመርዝ ፡ በቀር ፡ የምግብነት ፡ ባሕርይ ፡ በፍጹም ፡ ስለሌለ ፡ ለጤንነታችን ፡ ሊጠቅመን ፡ አይችልም ።

ይልቅስ ፡ የሚያሳዝነው ፡ በገንዘብ ፡ እየተገዛ ፡ ወደ ፡ ሰውነት ፡ የሚገባ ፡ እንደ ፡ መድኃኒት ፡ የሚታየው ፡ መጠጥ ፡ የሳንባ ፡ የደም ፤ የሥር ፤ የአንጀት ፤ የአንጐል ፡ በሽታ ፡ እያመጣ ፡ መርዝ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ነቀዝ ፡ ሰውነትን ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ በልቶ ፡ ይጨርሰዋል ። በመጠጥ ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣ ፡ በሽታም ፡ ሕመሙ ፡ የሚገለጠው ፡ የሰውዬው ፡ ጤንነት ፡ ጨርሶ ፡ ተበላሽቶ ፡ ለማዳን ፡ የሚቻልበት ፡ ብልሃት ፡ ከሌለው ፡ በኋላ ፡ ነው ። ሳልና ፡ የሳንባ ፡ ነቀርሳ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚመጣው ፡ ከመጠጥ ፡ ነው ። የመጠጥ ፡ ጉዳት ፡ ከባለቤቱ ፡ አልፎ ፡ ተርፎ ፡ ወደልጆቹ ፡ ይተላለፋል ። የሰካራም ፡ ልጆች ፡ ሰውነት ፡ የሚያንቀጠቅጥና ፡ የባርያ ፡ የሚጥል ፡ በሽታ ፡ ያድርባቸዋል ። የሚበልጡትም ፡ የሚሞቱት ፡ ገና ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ነው ። የሚያድጉትም ፡ ቀኝጃጉችና ፡ ዓመፅ ፡ ለመሥራት ፡ የሚደፍሩ ፡ ይሆናሉ ። የሰካራም ፡ ልጅ ፡ በሥጋዊ ፡ ሰውነቱ ፡ ወይም ፡ በአእምሮ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጉድለት ፡ ሳይኖረው ፡ አይፈጠርም ። መጠጥ ፡ ጉዳቱ ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ገና ፡ ያልታወቀ ፡ ትልቅ ፡ መቅሠፍት ፡ ነው ።

የአንድ ፡ ሰካራም ፡ ታሪክ ።

የመጠጥ ፡ ልማድ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ሊሰጠት ፡ የበታ ፡ አይዶለም ፤ አደራ ፡ ሊሉትም ፡ አይገባ ፤ ሰካራም ፡ የሰው ፡ ጐደሎ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ሰካራሞችን ፡ ሰዎች ፡ የማያስቀርብ ፡ አንድ ፡ ብልሀ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ሰካራሞችን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መንቀፍ ፡ አይገባም ፤ ለልማዱ ፡ መጠጥ ፡ እየጠጣ ፡ ይልቁ

ንም ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ቢሰክር ፡ አእምሮው ፡ ሲመለስለት ፡ ጧት ፡ ደኅና ፡ መሆኑ ፡ አይቀርም ፤ ስለዚህ ፡ ቀን ፡ ማንኛውንም ፡ ያላፊነት ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ይችላል ። በሰካራሞች ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ነፃ ፈታ ፡ ማድረግ ፡ የሚገባ ፡ አይመስለንም ፡ ብለው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አሰቡን ፡ ስለተቃወሙበት ፡ የስካር ፡ ልማድ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ለንጊዜውም ፡ ቢሆን ፡ እንደማይበጅ ፡ ምሳሌ ፡ እሰጣችኋለሁና ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ተመልከቱ ። ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ የከተማውን ፡ ሹም ፡ አለ ፡ ጠርቶ ፡ ሁልጊዜ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ የሚሰክር ፡ ሰው ፡ ከከተማ ፡ ውስጥ ፡ ፈልገህ ፡ አሳየኝ ፡ አለው ።

ማታ ፡ ሲሆን ፡ ንጉሡ ፡ ከከተማው ፡ ጩኸ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገብቶ ፡ ከንድ ፡ ሱቅ ፡ አጠገብ ፡ ደረሰ ። ከሱቁም ፡ ደረኛ ፡ ላይ ፡ በሚያስጠይፍ ፡ ቆሻሻ ፡ ቦና ፡ ተጠቅሎ ፡ የተኛ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አየ ፡ ይህም ፡ ሰው ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እየተሸከመና ፡ ማንኛውንም ፡ የሚያ ደክም ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ እየዋለ ፡ የሚያገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ቤት ፡ ልከራይበት ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ ልግዛበት ፡ ሳይል ፡ መጠጥ ፡ ይጠጣ በትና ፡ እየሰከረ ፡ ሲመሽ ፡ ሄዶ ፡ ከየሱቁ ፡ ደረኛ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ያድራል ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ሲኖር ፡ ብዙ ፡ ጊዜው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የከተማው ፡ ሹም ፡ ሰንገሡ ፡ ነገረው ።

ንጉሡ ፡ አገልጋዮቹን ፡ ጠርቶ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ከደረኛው ፡ አነሥተው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መንግሥቱ ፡ ወስደው ፡ ልብሱን ፡ ሰውጠው ፡ ለት ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ እንዲያለብሱትና ፡ ዘጥሩ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ እን ዲያስተኙት ፡ አዘዘው ። እነሱም ፡ ንጉሡ ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረጉ ፡ በማለዳ ፡ መጥተው ፡ ከእንቅልፉ ፡ እስኪነቃ ፡ ድረስ ፡ ጠብቀው ፡ ሲነሣ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ቀረቡ ። ሰውዬውም ፡ ጨንቆት ፡ ያለበትን ፡ ቤት ፡ እየተገላመጠና ፡ እያንገበገበ ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ ምንድነው ፡ እኔንስ ፡ ከዚህ ፡ ማን ፡ አመጣኝ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ ንጉሡ ፡ ከዛሬ ፡ ጅምሮ ፡ በዚህ ፡ በቤተ መንግሥታቸው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠህ ፡ በጌትነት ፡ ኑሮ ፡ እየተቀባ ጠልህ ፡ እንድትኖር ፡ እኛም ፡ መስፍን ፡ እያልን ፡ በክብር ፡ ስም ፡ እየጠራን ፡ እንድናገለግልህ ፡ አዘውናልና ፡ የምትፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጠይቀን ፡ እንድናደርግልህ ፡ አሉት ።

ሰውዬው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ተደንቆና ፡ ዶሀ ፡ ብሎት ፡ ተነሣና ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ ፊቱን ፡ ከታጠበና ፡ መልካም ፡ ቁርስ ፡ ከደረገ ፡ በኋላ ፡ በአበባ ፡ አትክልት ፡ መከከል ፡ እየተመላለሰ ፡ ሲና ፈስ ፡ አረፈደ ። ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ የጣፊጠ ፡ ምግብና ፡ መልኩ ፡ ለይቶ ፡ አበባ ፡ የመሰለ ፡ ጠጅ ፡ ቀርቦለት ፡ ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፤ አገልጋዮቹም ፡ መስኖን ፡ ሆይ ፡ እያሉ ፡ ሲያቀማጥሉት ፡ ቂይቶ ፡ ከምሳው ፡ በኋላ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የጠየቀውን ፡ ጌጥና ፡ ልብስ ፡ እየሰጡት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታ ፡ እያጫወቱት ፡ እመሹ ። መዝም ፡ የደስታ ፡ ሰዓት ፡ ሁልጊዜ ፡ አጭር ፡ ነውና ፡ ሳይታወቀው ፡ መሸቶ ፡ ራት ፡ ቀረበለት ። ራቱም ፡ ምግቡ ፡ እንደ ፡ ምሳው ፡ የጣፈጠ ፡ ነበር ። ከመጠጥ ፡ ግን ፡ የቀረበለት ፡ ጠጅ ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ለዓይኑ ፡ የአማረውንና ፡ ልቡም ፡ የወደደውን ፡ እንዲጠጣ ፡ ተብሎ ፡ ከገበታው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ መጠጥ ፡ ተደርድሮለት ፡ ነበር ። እሱም ፡ ከምግቡ ፡ ጥቂት ፡ ቀማምሶ ፡ መጠጡን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ከያይነቱ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ጠጥቶ ፡ ሰክረና ፡ ተቀምጠ በት ፡ ከነበረው ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተገልብጠ ፡ ወደቀ ። አገልጋዮቹም ፡ ከወደቀበት ፡ ሥፍራ ፡ አንሥተው ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ አስተኙት ። እንቅልፍ ፡ ከወሰደው ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ መጥቶ ፡ በሱ ፡ ያንን ፡ የራሱን ፡ ቆሻሻውን ፡ ልብስ ፡ አልብሰችሁ ፡ ውሰዱና ፡ እዚያው ፡ ትላንት ፡ ከነገበት ፡ ከሱቁ ፡ ደረኛ ፡ ላይ ፡ መልሳችሁ ፡ አስተኙት ፡ አላቸው ። አገልጋዮቹም ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚያን ፡ ስካር ፡ በጣም ፡ የሚያስነቅፍ ፡ ነገር ፡ አይዶለም ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ በሉ ፡ ካ ፡ በጥዋት ፡ ሄዳችሁ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ትላንት ፡ የዋልኸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ጠይቁትና ፡ የሚሰጣችሁን ፡ መልስ ፡ መጥታችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ታል ፡ ሄደው ፡ ጥዋት ፡ ሲነሣ ፡ ቢጠይቁት ፡ ትላንት ፡ ስሸከምና ፡ ሥሠራ ፡ ነው ፡ የዋልሁት ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ሴሊት ፡ በሕልሜ ፡ ከንጉሡ ፡ ግቢ ፡ ገብቼ ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ እየበላሁ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ እየለበስሁ ፡ ከጥሩ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ እየተኛሁ ፡ በተድላና ፡ በምኞት ፡ ስንፈላለስ ፡ አደርሁ ፡ ብሎ ፡ አጣወታቸው ። ሰምቹም ፡ ይህን ፡ ማስረጃ ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ ተመልካችነት ፡ በጣም ፡ አድርገው ፡ አደነቁ ። ሰከራሞችንም ፡ መጥላቱን ፡ ወደዱለት ።

Scanned with CamScanner

ልጆች፡ ሆይ፡ ከፍ ፡ያለ፡ ዕውቀት፡ አግኝታችሁ፡ መጠጥ ፡ ሚያመጣውን፡ ጉዳት ፡ በሙሉ ፡ እስክትረዱት ፡ድረስ ፡ ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጸናከላችሁ፡ የሚበቃ፡ መስሎ፡ ይታየኛል። ይህን ፡ ሁሉ ፡ አያስታወሳችሁ፡ ከመጠጥ ራቁ።

መታዘዝን ዕወቅ።

አንድ፡ ትልቅ፡ ንጉሥ ፡ ማለዳ፡ ተነሥቶ ፡
ሁለት፡ ሠራተኞች፡ ከውጭ፡ አስጠርቶ፡
ከጉድጓዱ፡ አጠገብ ቅርጫት ፡ አስመጥቶ፡
ውኃ እየቀዳችሁ ከዚህ ጉድጓድ አውጡ፡
ከዚያም፡ በዚህ ፡ ቅርጫት፡ እንድትገለብጡ፡
እኔም፡ ወደ ፡ ማታ፡ መጥቼ ፡ እናንተ፡ ጋ ፡
ለሠራችሁበት ፡ እሰጣለሁ ፡ ዋጋ።
አለና፡ ትእዛዙን ፡ ለጠና፡ ሲሄድ ፡
ሁለቱ፡ እየቀዱ ፡ ውኃ ፡ ከጉድጓድ ፡
ጥቂት ፡ እንደሠሩ ፡ ተወና ፡ አጉረምርሞ፡
አንዱ፡ ሠራተኛ፡ ሥራውን ፡ አቁሞ ፡
አይገባኝም፡ አለ፡ ይህ ፡ ነገር፡ ፊጽሞ፡
እንዲያው ፡ መታከት፡ ነው፡ በከንቱ መልፋት ፡
ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ፡ በመድከም ፡ ብዛት፡
አይጠራቀምም ፡ ውኃ ፡ በቅርጫት።
ደስ ፡ ደስ ፡ እያለኝ ፡ ከልሠራሁ ፡ በተሰፋ፡
ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ በከንቱ ፡ ብሰፋ ።
ደኅና ፡ ሁን ፡ አለና፡ ተነሥቶ ፡ ሲሄድ ፡
ጓደኛው ፡ መለስ ፡ ውኃ ፡ ከጉድጓድ ፡
ቀድታችሁ ፡ በቅርጫት ፡ ጨምሩ፡ ማለቱ፡
የዚህ ፡ አጉል ፡ ሥራ ፡ ጥቅሙ ፡ ምክንያቱ ፡
ከቶ ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ ያውቃል ፡ ባለቤቱ ።
የቅርጫት ፡ እንሥራ፡ ውኃ ፡ እንደማይቋጥር፡
ያውቃል፡ አላጣውም ፡ ይህን ፡ አትጠርጥር ።

ግን ፡ ዋጋ ፡ እስጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ከነገረን፡
እኛ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ አከራከረን።
ባልቸገረን፡ ጉዳይ ፡ ከማድርግ ፡ ምርመራ ፡
ይሻል ፡ ይመስለኛል ፡ አርፈን ፡ ብንሠራ ።
ብሎ ፡ ከጓደኛው ፡ ተሰይቶ ፡ ቀርቶ ፡
ሊደክም ፡ ቀጠለ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ።
ሊቀዳ ፡ ዋለና፡ ሊመሽ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡
በጉድጓዱ ፡ሳይቀር ፡ አንድ ፡ እናኳን ፡ ጠብታ ፡
በመጨረሻው ፡ ላይ ፡ ውኃውን ፡ አሟጠ ፡
በቅርጫት ፡ ሲጨምር ፡ ከመቅጃው ፡ ገልብጦ ፡
ውኃው ፡ መራት ፡ ሲፈስ ፡ ቅርጫቱ ፡ ላይ ፡ ቀርቶ ፡
የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ አገኘና ፡ አንሥቶ ፡
ወደያው ፡ ቀለበቱን ፡ ከቅርጫት ፡ ሲያወጣ ፡
ንጉሡ ፡ ሥራውን ፡ ሲመለከት ፡ መጣ ።
ነገሩን ፡ ሲረዳው ፡ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡
በሥራው ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ሲሠራ ፡ የዋለ ፡
አይቀርም ማግኘቱ ፡ የድከሙን ፡ ፍሬ ፡
እኔም ፡ ልፈትን ፡ ነው ፡ ይህን ፡ መናገራ።
መሥዋዕት ፡ አድርግና፡ ልጅህን ፡ አረደው ፡
ሊሰው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይሰሐቅን ፡ ቢወደው ፡
የእኔ ፡ ልጅ ፡ ቢታረድ ፡ ላምላክ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትእዛዝ ፡ በጣም ፡ ያሰገርማል ፡
ብሎ ፡ ከማሰገባት ፡ በልቡ ፡ ቅሬታ ፡
አልተከራከረም ፡ አብርሃም ፡ ከጌታ ።
ባልቸገረው፡ ነገር ፡ እየተቸገረ ፡
ያለሥራው ፡ ገብቶ ፡ የተከራከረ፡
ግብ ፡ የሌለው ፡ መንገድ ፡ መከተል ፡ ነውና ፡
አሳቡም ፡ መካን ፡ ነው ፡ ክርክሩም ፡ መና።
አንተ ፡ ግን ፡ ብልህ ፡ ነህ ፡ አሳብህ ፡ የጸና፡
ለሞላህበትም ፡ ውኃ ፡ በቅርጫት ፡
ቀለበቱን ፡ ውስድ ፡ ስለ ፡ ሽልማት ።
ዋጋህን ፡ ተቀበል ፡ ያንተ ፡ ባልንጀራ ፡

Scanned with CamScanner

ሲሄድ ፡ ተለይተህ ፡ ለሠራኸው ፡ ሥራ ።
ዋጋህን ፡ ስላልሁም ፡ ይህ ፡ ብቻም ፡ አይዶለ ፡
አስተዋይ ፡ የሆነ ፡ በእውነት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
የሚታመኑበት ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡
የሰጡትን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚገኝ ፡
ብልህ ፡ ሰው ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ ስለምመኝ ፡
እንድታገለግል ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡
አስቤልሃለሁ ፡ ማዕርግ ፡ ያለው ፡ ቦታ ።
አለና ፡ ንጉሡ ፡ በጠባዩ ፡ ፈርዶ ፡
ወዲያው ፡ አስጠራና ፡ ይህንን ፡ ሰው ፡ ወስዶ ፡
ከችግር ፡ አውጥቶ ፡ ከዚያ ፡ ድህነቱ ፡
ሹመት ፡ ሰጠው ፡ አሉ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ።
የሰጡትን ፡ ሥራ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡
ሊፈጽም ፡ አስቦ ፡ ሰውም ፡ በጉልበቱ ፡
የተቀበለውን ፡ ታላቁን ፡ አደራ ፡
እምነት ፡ ባለማጉደል ፡ ጠንክሮ ፡ ከሠራ ፡
እሱም ፡ ተመስግኖ ፡ አገሩም ፡ ተከብራ ፡
መሰብሰቡ ፡ አይቀርም ፡ መልካሙን ፡ አገመራ ።

የካምቢዝ ፡ ጭካኔ ።

ካምቢዝ፡ የሚባለው ፡ የፋርስ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ጦረኛና ፡ ጅግና ፡ ሆኖ፡ ግን ፡ የሚሠራው ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ተሰምቶ ፡ የማይታወቅና ፡ ለጆሮ ፡ የሚ ቀፍ ፡ ነበር ። በባለሟሎቹ ፡ መካከል ፡ የቀድሞ ፡ ሽማግሌ ፡ የሆነ ፡ ከአባቱ ፡ ከቂሮስ ፡ ጋር ፡ የኖረ ፡ አንድ ፡ መኰንን ፡ ነበር ። እሱም ፡ የካምቢዝ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ ሲኖር ፡ በመልካም ፡ ምክሩ ፡ ሊረዳው ፡ ይጣጣር ፡ ነበርና ፡ካምቢዝ ፡የወይን ፡ ጠጅ ፡ በጣም ፡ መውደዱንና ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ መጠጡን ፡ ተመልክቶ ፡ መጠጥ ፡ አታብዛ ፡ ክብርህን ፡ ለመጠበቅ ፡ ስትል ፡ ይህን ፡ ከመሰለው ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መወሰን ፡ ያስ ፈልግሃል ፡ ብሎ ፡ መከረው ። መጠጥ ፡ ባበዛ ፡ ምን ፡ ያደርገኝ ፡ ይመ ስልሃል ? ብሎ ፡ ካምቢዝ ፡ ቢጠይቀው ፡ መኰንኑ ፡ መጠጥ ፡ ልቡና ፡ ይነሣል ፡ አእምሮ ፡ ያጠፋል ፡ ሰውነትንም ፡ ይጎዳል ፡ ብሎ ፡ መለ ሰለት ። ካምቢዝ ፡ መለሰና ፡ ሰው ፡ ስንት ፡ ብርጭቆ ፡ ቢጠጣ ፡ አእም

ሮውን ፡ ያጣል ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። መኰንኑም ፡ በመጠን ፡ ቢጠ ጡት ፡ ለጤንነት ፡ ይበጃል ፡ እንጂ ፡ አይጎዳም ፤ ሜን ፡ ከሁለትና ፡ ከሦስት ፡ ብርጭቆ ፡ በላይ ፡ ሲጠጡ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ይሆንና ፡ ሰውነትን ፡ እንደሚጎዳው ፡ አይጠረጠርም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ይህን ፡ ጊዜ ፡ ክምቢዝ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ቤፍጥነት ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘና ፡ አስመጥቶ ፡ እንዲህ ፡ ተመልክት ፡ አንተ ፡ ከሦስት ፡ ብርጭቆ ፡ በላይ ፡ መጠጣት ፡ ለውነትን ፡ ይጎዳዋል ፡ ልቡናም ፡ ይነ ሣል ፡ ብለሃል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ከልኽው ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ አብልጨ ፡ ልጠጣለሁ ፡ ብሎ ፡ እዘያው ፡ አመኰንኑ ፡ ፊት ፡ አየቈ ጠረ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ብርጭቆ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣ ። ከዚያም ፡ ይህ ፡ መኰንን ፡ የወለደው ፡ ቤሳም ፡ የማወደው ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ነበረው ፡ አሱን ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ክምቢዝ ፡ አስይዘ ፡ አስመጥቶ ፡ ራቅ ፡ አድርጎ ፡ ከግንድ ፡ ላይ ፡ አሰሰረው ። አባቱንም ፡ አስተውል ፡ አለው ፡ ልጅህን ፡ በዚህ ፡ በያዝሁት ፡ ቀስት ፡ ሳልደግም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ወርውሬ ፡ ልክ ፡ ልቡን ፡ ወግቼ ፡ አገድለዋለሁ ፡ ከሉሳ ፡ ዘንድ ፡ የወጋሁት ፡ እንደሆን ፡ እውነትም ፡ እንተ ፡ እንዳልሽው ፡ መጠጥ ፡ ልቤን ፡ ነሥቶኛል ፤ ግን ፡ በትክክል ፡ ልቡ ፡ ላይ ፡ የወጋ ሁት ፡ እንደሆነ ፡ አንተ ፡ የተናገርኸው ፡ ሐሰት ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፡ በማ ታውቀው ፡ ነገር ፡ ገብተህ ፡ ምክር ፡ እንዳትሰጥ ፡ ለወደፊቱ ፡ ትምህርት ፡ ይሆንሃል ፡ ብሎ ፡ ቀስቱን ፡ ወጥሮ ፡ በልጁ ፡ ላይ ፡ አነጣጠረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በአባትየው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ መሠነቅ ፡ ልት ረዳት ፡ ትችላላችሁ ። ቀስቱም ፡ ተወረወረና ፡ ሄዶ ፡ ከልጁ ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ተተከለ ። የልጁን ፡ ደረት ፡ ሰንጥቃችሁ ፡ ቀስቱ ፡ የወጋበትን ፡ ቦታ ፡ ለአባትየው ፡ አሳዩት ፡ ብሎ ፡ ካምቢዝ ፡ አዘዘ ። የታዘዙትም ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ቃል ፡ አድርገው ፡ ለመኰንኑ ፡ አሳዩት ። መኰንኑም ፡ ያችን ፡ ምክር ፡የሰጠበትን ፡ ሰዓት ፡ በልቡ ፡ እየረገመና ፡ ፊቱን ፡ በእንባው ፡ እያጠበ ፡ ቢመለከት ፡ ልጁ ፡ የተወጋው ፡ ልክ ፡ አልቡ ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ በዓይኖቹ ፡ አይቶ ፡ ተረዳ ። ይህ ፡ ታሪክ ፡ መጠጥ ፡ ሲበዛ ፡ ወደ ፡ ዕብደት ፡ ያደርሳል ፡ የሚባለው ፡ ነገር ፡ እው ነት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳናል ። አንድም ፡ ደግሞ ፡ የአረመኔዎች ፡ ጭካኔ ፡ እስከ ፡ ምን ፡ ድረስ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥልናል ።

Scanned with CamScanner

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲሁ ፡ ከምቢዝ ፡ እጎቴን ፡ ባገባ ፡ ምን ፡ ክፋት ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ አማካሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ፈርተው ፡ ክፋት ፡ የለበትም ፡ ሲሉ ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ብቻ ፡ አይገባም ፡ ሲል ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ተቃወመ ። ከምቢዝም ፡ አሳቡን ፡ የተቃወመውን ፡ ይህን ፡ ዳኛ ፡ እንዲያርዱትና ፡ ቆዳውን ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ እንዲገፉት ፡ አዘ ፡ በቆዳው ፡ አንድ ፡ ወንበር ፡ አሠራበት ። የዳኛውን ፡ ልጅ ፡ አስጠርቶ ፡ የአባትህን ፡ ሹመት ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ በዚህ ፡ በአባትህ ፡ ቆዳ ፡ በተሠራው ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ እየተቀመጥህ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራህን ፡ እንድትሠራ ፡ አዝዠሃለሁ ፤ ምክንያቱም ፡ ምናልባት ፡ ጥፋት ፡ ቢገኝብህ ፡ የሚመጣብህ ፡ ቅጣት ፡ ከባድ ፡ መሆኑን ፡ እንዳትረሳው ፡ ማሳሰቢያ ፡ እንዲሆንህ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለው ።

ከምቢዝ ፡ ከመኳንንቶቹና ፡ ከባለሟሎቹ ፡ ጋር ፡ ተቀምጦ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲጫወት ፡ ከኔና ፡ ከአባቴ ፡ ማን ፡ ይበልጣል ? ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ሁሉም ፡ ሳያመነቱ ፡ በንድ ፡ ቃል ፡ በሁሉም ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ ትበልጣለህ ፡ ብለው ፡ ሲናገሩ ፡ ክፈሱስ ፡ የሚባለው ፡ የሊድያ ፡ ንጉሥ ፡ ምርኮኛ ፡ ሆኖ ፡ በከሚቢዝ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ከአንተ ፡ አባትህ ፡ ይበልጣል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። እሱ ፡ በተናገረ ፡ የቀሩት ፡ አዘ ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ከምቢዝ ፡ አንኳንስ ፡ አስቀይመውት ፡ አመስግነውትም ፡ አይሆን ፡ በማለት ፡ ደንግጠው ፡ ተንቀጠቀጡ ። ከምቢዝ ፡ እውነትም ፡ ተቈጥቶ ፡ ወዲያው ፡ ፊቱ ፡ እንደ ፡ ጥቀርሻ ፡ ጠቆረና ፡ እንደምን ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ክፈሱስ ፡ ሳይደነግጥ ፡ በሌላው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አንተ ፡ ትበልጣለህ ፤ ግን ፡ አባትህ ፡ ቂሮስ ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡ ብልሀና ፡ ጀግና ፡ ልጅ ፡ ወልዷል ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡ ልጅ ፡ እስከ ትተካ ፡ ድረስ ፡ አባትህ ፡ ይበልጥሃል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ከምቢዝ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ከቀጣጣው ፡ በርዶ ፡ ይህ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንዲያውም ፡ በዚህ ፡ ምላሽ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ሳቀ ፡ ይባላል ።

ብልህ ፡ ራሱን ፡ ያድናል ።

አንድ ፡ መንገደኛ ፡ ሲሄድ ፡ በግሥጋሣ ፤ ድንገት ፡ ደረሰበት ፡ የተራበ ፡ አንበሳ ። ደንግጦ ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ሸሸ ፡

ከንድ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ሮጠና ፡ ወጥቶ ፡ ከንበሳው ፡ ማምለጡን ፡ ሲረዳው ፡ መንፈሱ ፡ ከድንጋጤ ፡ ሽብር ፡ ተመለሰች ፡ ነፍሱ ። ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያስተውል ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንጋጦ ፡ አንድ ፡ ነብር ፡ አየ ፡ ዛፉ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ። ሊሸሽ ፡ አሰበና ፡ ቢያስተውል ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አንበሳው ፡ ተኝቷል ፡ መጥቶ ፡ ከዛፉ ፡ ሥር ። ከበላዩ ፡ ነብር ፡ ከበታቹ ፡ አንበሳ ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ አሳር ፡ አግኝኝ ፡ አበሳ ። አሁን ፡ ወዴት ፡ ልድረስ ፡ ብሎ ፡ በፍርሃት ፡ ተነራምቶ ፡ ቄየ ፡ በጭንቁ ፡ ብዛት ። ቀና ፡ ብሎ ፡ ነብሩን ፡ ቢያስተውለው ፡ በኋላ ፡ አሱም ፡ ተጨብጦ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቡችላ ፡ ለራሱ ፡ ደንግጧል ፡ እንኳንስ ፡ ሊጣላ ። ልብ ፡ ብሎ ፡ ቢያየው ፡ ጥግሮቹ ፡ ነገሩ ፡ አንበሳ ፡ እንዳያየው ፡ ይሸሻል ፡ ነብሩ ። ምሥጢሩን ፡ ሲረዳው ፡ ቂይቶ ፡ መንፈሱ ፡ የተሳለ ፡ ሰንጠ ፡ አውጥቶ ፡ ከኪሱ ። ነብሩ ፡ ያለበትን ፡ ያን ፡ የዛፉን ፡ ክንፍ ፡ እንደ ፡ ማቅናት ፡ አርጎ ፡ እንደ ፡ መደገፍ ፡ በሰንጠው ፡ ከግንዱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ብሎ ፡ ቆረጠና ፡ ጣለው ፡ ከሥሩ ፡ አሰልስሎ ። አመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ነብር ፡ ሲዘረጋ ፡ ምን ፡ መጣብኝ ፡ ብሎ ፡ ያልታሰበ ፡ አደጋ ። ተርበትብቶ ፡ ፉስ ፡ ዘለለና ፡ አንበሳ ፡ ከተኛበት ፡ በታ ፡ ደንግጮ ፡ ተነሣ ። ወዲያው ፡ ተያይዘው ፡ በመተናነቅ ፡ አንደኛው ፡ ሲነሣ ፡ አንደኛው ፡ ሲወድቅ ፡ ሲባሉ ፡ ቂይተው ፡ አንበሳ ፡ አሸነፈ ፡ አሱም ፡ ገላው ፡ ቂስሎ ፡ ምንም ፡ አልተረፈ ፡ ግን ፡ ነብሩን ፡ ጥሎ ፡ በላና ፡ ጨረሰ ። ጥፍሩ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ደሙን ፡ እየላሰ ፡

Scanned with CamScanner

ከዚያ ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ሄደ ፡ እያነከሰ ።
ይመለከቱታል ፡ ውሻ ፡ ጥርሱን ፡ ባጥንት ፡
ይፀል ፡ የነበረው ፡ ደረሰብኝ ፡ ተረት ።
እንዲህ ፡ የተበሉ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡
አማኑኤሎች ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ በጥርሳቸው ፡
ምን ፡ እተርፍ ፡ ነበር ፡ አምላኬ ፡ ተመስገን ፡
ጥበብና ፡ ምሕረት ፡ ሞልቷል ፡ ባንተ ፡ ወገን ፡
እያለ ፡ ሰውዬው ፡ ተርፋለት ፡ ሕይወቱ ፡
ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወርዶ ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ።
እንዲጋጩ ፡ አድርጎ ፡ ብርቱና ፡ ኃይለኛ ፡
ራሱን ፡ ያዳነ ፡ ይጠላል ፡ ዘዴኛ ።

አንድ ፡ አዳኝ ፡ ሰውና ፡ አንዲት ፡ ዋኔ ።

ክፅለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ አዳኝ ፡ አንዲት ፡ ዋኔ ፡ በወጥ መድ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄድ ፡ ወዪት ፡ ነው ፡ የምትወስደኝ? ብላ ፡ ዋኔይቱ ፡ ጠየቀችው ። አዳኙም ፡ ምን ፡ ትጠይቂኛለሽ ፡ አርጂ ፡ ልበላሽ ፡ ነዋ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ። " እንዲት ፡ ያለኸው ፡ ሞኝ ፡ ነህ ፡ እኔ ፡ የሚያሳዝንኝ ፡ በክንቱ ፡ መድከምህ ፡ ነው ። አሁን ፡ እኔን ፡ በል ተህ ፡ ልትጠግብ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ልትመሩር ? አስኪ ፡ አስተውለህ ፡ ተመልከተኝ ። ሰውነቴ ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ጥጥረት ፡ ነኝ ። የቀረው ፡ ቅርቶ ፡ ከጉርርህ ፡ አልወርድም ። እኔን ፡ በልተህ ፡ እውነትስ ፡ ልት ጠቅም ፡ አይደለም ፡ ይልቅስ ፡ እንስማማ ፡ እኔ ፡ ለዕድሜህ ፡ ሙሉ ፡ የሚጠቅሙህ ፡ ሦስት ፡ ምክሮች ፡ አሰጥሃለሁ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ምሕ ረት ፡ ታደርግልኛለህ ። አንዱን ፡ ምክር ፡ እዚሁ ፡ በጅህ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለሁ ፡ አነግርሃለሁ ፡ ሁለተኛውን ፡ ግን ፡ ስትለቂኝ ፡ አጠገባችን ፡ ካለው ፡ ከዚህ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ ሦስተኛውን ፡ ደግሞ ፡ አዘ፡ ግዶ ፡ ከለው ፡ ዳንት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ተቀምጬ ፡ እነግርሃለሁ " አለችው ።

አዳኙ ፡ ሰው ፡ " የመጀመሪያውን ፡ ሰምቼ ፡ ምክርሽ ፡ የሚጠ ቅመኝ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ መልከም ፡ ነው ፡ እለቀሻለሁ ። አላት ። በዚህ ፡ ከተስማሙ ፡ በኋላ ፡ " ባለፈ ፡ ነገር ፡ አትጸጸት ፡ ያመለጠህም ፡ ነገር ፡ አይቆጭህ የመጀመሪያው ፡ ምክሬ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለችው ። ሰው

ዬው ፡ ከዚህ ፡ ምክር ፡ ጋር ፡ የሚገናኝ ፡ ቀድሞውኑ ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ኖሮ ፡ እሱን ፡ ስለቀሰቀሰበት ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ተናገ ርሽ ፡ ምሬሽለሁ ፡ ሂጂ ፡ ብሎ ፡ ለቅቃት ። አሷም ፡ በረረችና ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ አርፋ " አንተ ፡ ቂል ፤ አንተ ፡ ሞኝ ፤ አንተ ፡ ያልታደልህ ፡ ተላላ ፡ ዛሬ ፡ በሠራኸው ፡ ስሕተት ፡ ዕድሜህን ፡ ሙሉ ፡ ስትጸጸት ፡ ትኖራለህ ። አርደህ ፡ ብትበላኝ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ትንሽ ፡ ኑኛኛ ፡ አል ጠቅምህም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሆዴ ፡ ውስጥ ፡ ሐያ ፡ ውሷት ፡ የሚመዝን ፡ ዋጋው ፡ በጣም ፡ የከበረ ፡ ጥሩ ፡ ዓይነት ፡ አልማዝ ፡ አለ ፡ ብታርደኝ ፡ ኖሮ ፡ እሱን ፡ ታገኝ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ሁለ ተኛውን ፡ ምክር ፡ ልንገርህ ፡ "የማይሆነውን ፡ ነገር ፡ ይሆናል ፡ ብለህ ፡ በሞኝነት ፡ አትመን ፡ ። እንግዲህ ፡ ጀጎና ፡ ሁን ፡ ከነሀብቱ ፡ ልሂድ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ብላው ፡ በረረችና ፡ ከፋፉ ፡ ላይ ፡ ወረፈች ።

ሰውዬው ፡ ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ወይ ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ ጉድ ፡ ወራ ችኝ ፡ ብሎ ፡ እየተናደደ ፤ ከንፈሩን ፡ እየነከሰ ፤ እያጨበጨበ ፤ ተከ ተላትና ፡ ከፋፉ ፡ አጠገብ ፡ ደረሰ ። በአንድ ፡ ወገን ፡ በሩጫ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በንዴት ፡ ደክሞ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ እየተነፈሰ ፡ ምሕረት ፡ ባደ ረግሁልሽ ፡ ፈንታ ፡ እንዲህ ፡ የሚያናድድ ፡ ነገር ፡ ባትነግሪኝ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ ቸገረሽ ፡ ነበር ። የውለታዬ ፡ ዋጋ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እየወቀሳት ፡ ዓይናቹን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ተክሎ ፡ ደንጊያ ፡ እንሥቶ ፡ ሊወረውርባትም ፡ ታጣው ። እሷም ፡ ሁኔታውን ፡ አይታ ፡ ከከለላ ፡ ተጠ ግታ ፡ ተመቻቸች ። ምንም ፡ ለማድረግ ፡ የማይቻል ፡ ብልሃት ፡ የሌ ለው ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ "የአልማዙን ፡ ነገር ፡ ይቅር ፡ አታ ንሺው ፡ ይልቅስ ፡ እንደ ፡ ተነጋገርነው ፡ ውል ፡ ሦስተኛውን ፡ ምክር ፡ ንገሪኝና ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ልሂድ ፡ " አላት ። ሁለቱን ፡ ምክሮቹን ፡ ሳትሠ ራቡት ፡ ሦስተኛውን ፡ ብጠምርልህ ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል ? አለ ችው ። እንደምን ? ቢላት ፡ " በመጀመሪያው ፡ -ብለፈ ፡ ነገር ፡ አትጸ ጸት ፤ ያመለጠህም ፡ ነገር ፡ አይቆጭህ ፡ አልሁህ ። ቀጥዬም ፡ ሁለተኛ ፡ የማይሆነውን ፡ ነገር ፡ ይሆናል ፡ ብለህ ፡ በሞኝነት ፡ አትመን ፡ ። አል ሁህ ፤ ይህን ፡ ሁለቱን ፡ ነግሬሃለሁ ፡ ወይስ ፡ አልነገርሁህም ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ። ነግረሽኛል ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ። -እንግዲያው ፡ ይህንን ፡ ከሰማህ ፡ በኋላ ፡ በሆዴ ፡ ውስጥ ፡ አልማዝ ፡ አለ ፡ ስላልሁህ ፡ አን ተም ፡ ለቀኽኝ ፡ እኔም ፡ በርሬ ፡ ዳግመኛ ፡ ልትይዘኝ ፡ አለመቻልህ

Scanned with CamScanner

ንና ፣ ያለፈ ፣ ነገር ፣ መሆኑንም ፣ ስታውቀው ፣ ለምን ፣ ትጸጸታለህ ፣ ለምንስ ፣ ይቆጭሃል ? ሁለተኛ ፣ ደግሞ ፣ እነሆ ፣ እኔ ፣ እንደምትመለ ከትኝ ፣ ሥጋዬንና ፣ አጥንቴን ፣ ከነፍሴና ፣ ከላባዬ ፣ ሞምር ፣ ብትመ ዝነኝ ፣ ሐያ ፣ ወቄት ፣ ልሆን ፣ አልችልም ። እንግዲህ ፣ እንዴት ፣ እድ ርጌ ፣ ሐያ ፣ ወቄት ፣ የሚመዝን ፣ አልግዝ ፣ በሆዴ ፣ ውስጥ ፣ የተሸ ክሙሁ ፣ መስሎህ ፣ ነው ፣ በንዴት ፣ እንዲህ ፣ የምትጠፈው ። የማይሆ ነውን ፣ ነገር ፣ ይሆናል ፣ ብለህ ፣ በሞኝነት ፣ አትመን ፣ ብዬ ፣ ነግሬህ ፣ የነበረውን ፣ ሁለተኛውን ፣ ምክሬን ፣ ተገንዝበኸው ፣ ቢሆን ፣ በከንቱ ፣ እንደዚህ ፣ ባልተናደድህ ፣ ነበር ። " የያዝኸውን ፣ ሳትሠራበት ፣ ሴላ ፣ ጨምሩልኝ ፣ አትበል ፣ ,, ሦስተኛው ፣ ምክሬ ፣ ይህ ፣ ነው ። በሁለቱ ፣ ሳትሠራባቸው ፣ ሦስተኛውን ፣ ልጨምርልህ ፣ አይገቧኝም ፣ ነበር ፣ ግን ፣ አንተ ፣ ይቅር ፣ እንኚ ፣ ከእኔ ፣ አይጐደል ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ እንግዲህ ፣ ደኅና ፣ ሰንብት ፣ ብላው ፣ በረረች ።

ይህች ፣ ዋኔ ፣ በጥበብ ፣ ትመሰላለች ፤ ሰውዬው ፣ ግን ፣ አሳቡን ፣ ሁሉ ፣ እያባከነ ፣ በተስፋና ፣ በምኞት ፣ ብቻ ፣ በሚኖር ፣ ሰው ፣ ይመ ሰላል ። በምኞት ፣ ብቻ ፣ የሚኖር ፣ ሰው ፣ የማይወጥነውና ፣ የማያቅ ደው ፣ ነገር ፣ የለም ፤ ግን ፣ የጀመረውን ፣ እያዝረከረከ ፣ በላይ ፣ በላዩ ፣ አዲስ ፣ አሳብ ፣ ሲሰበስብ ፣ ይኖራል ። በዚህ ፣ አኳኋን ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ ከኖረ ፣ በኋላ ፣ አስተውለው ፣ ቢመለከቱት ፣ በእጁ ፣ ውስጥ ፣ የተፈ ጸመ ፣ አንድ ፣ ሥራ ፣ እንኳን ፣ አይገኝም ፣ ውጥን ፣ ግን ፣ ተርፎታል ። ሥራ ፣ ለመጀመር ፣ አይታክተውም ። እሱንም ፣ ስናስተያየው ፣ እርሶ ፣ ዘርቶ ፤ አጭዶ ፣ ወቅቶ ፣ ሲጠርስ ፣ አንድ ፣ ፍሬ ፣ እንኳን ፣ ሳያመ ርት ፣ ገለባ ፣ ብቻ ፣ ሰብስቦ ፣ ከሚቀረው ፣ ከልታደለው ፣ ገበሬ ፣ ጋር ፣ በጣም ፣ ይመሳሰላል ። ብልህ ፡ ሰው ፣ ግን ፣ ምኞት ፣ አያበዛም ፡ የጀ መረውንም ፣ ሳይጠርስ ፣ አዲስ ፣ ሥራ ፣ አይወጥንም ።

ብልሁ ፡ ተግሪ ፣ እስኪ ፣ በል ፣ ገምተው ፡
ይህንን ፡ ምሳሌ ፡ ስትመለክተው ፡
ይጠቅማል ፣ አይጠቅምም ፣ የምንጫወተው ?

አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ አንበሳና ፡ አንድ ፡ ድብ ።

አንድ ፡ አንበሳ ፡ ተርቦ ፡ ሲቅበዘበዝ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘና ፡ ሲያባርረው ፡ ሰውዬውም ፡ ሲሸሽ ፡ ሁለቱም ፡ ተከታትለው ፡ አንድ ፡

ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ወደቁ ። ከእነሱ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ድብ ፡ እን ዲሁ ፡ ወድቆ ፡ ኖሮ ፡ ሦስቱም ፡ እዚያው ፡ ተገናኙ ። አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከመቼ ፡ ጀምረህ ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ የገባኸው ? ብሎ ፡ አንበሳ ፡ ድብን ፡ ጠየቀው ። ውዬ ፡ አድራለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። አንበሳው ፡ ደገመና ፡ እኔ ፡ ጠጣም ፡ ተርቤ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ አግኝቼ ፡ እበላለሁ ፡ ብዬ ፡ ሳሰድደው ፡ ይኸው ፡ እንዳየኸው ፡ በድንገት ፡ ሁለታችንም ፡ እዚህ ፡ ወደቅን ። አሁንም ፡ በጣም ፡ ርበኛል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፤ ድብም ፡ መለሰና ፡ እኔም ፡ ይኸው ፡ እዚህ ፡ ከወደቅሁ ፡ ሁለት ፡ ቀኔ ፡ ነው ፡ ረኃብ ፡ ይዘኝ ፡ ያንገላታኛል ፡ ብሎ ፡ አዋየው ። እንግዲያውስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ተከፍለን ፡ እንብላ ፡ ብሎ ፡ አንበሳ ፡ ቢናገር ፡ ድብ ፡ መለሰና ፡ ብንበላው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ረኃባችንን ፡ ያስታግሥልናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ እንሆናለን ፡ መቼም ፡ ከዚህ ፡ እንወጣለን ፡ ብለን ፡ አንጓጓ ፤ እኔ ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ ሞክሬ ፡ አቅቶኝ ፡ ነው ፡ የተውኩት ። ይልቅስ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ አሳብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ከጥቅም ፡ ጥቅም ፡ ይበልጣልና ፡ ለሆዳችን ፡ ብለን ፡ እዚሁ ፡ ሞተን ፡ ከምንቀር ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ምሕረት ፡ አድርገንለት ፡ እንደምንም ፡ ብለን ፡ ተራዳ ድተን ፡ ከዚህ ፡ ብናወጣው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ በማነኛውም ፡ ነገር ፡ ከእንስሳ ፡ ሰው ፡ ይበልጣልና ፡ ራሱን ፡ አድኖ ፡ እኛንም ፡ ያድነናል ፡ ብሎ ፡ መልካም ፡ ምክር ፡ አመጣ ።

አንበሳም ፡ የድብን ፡ አሳብ ፡ አመዛዝኖ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ እንዲ ያውም ፡ ከዚህ ፡ ከመቦረ ፡ በታ ፡ የጣለኝ ፡ ይኸው ፡ ሆዴ ፡ አይደ ለምን ? አሁንም ፡ ወደ ፡ ባሰ ፡ መከራ ፡ የሚገፋፋኝ ፡ እሱው ፡ ነው ። አንተ ፡ እንዳልኸው ፡ ከጥቅም ፡ ጥቅም ፡ ይበልጣና ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ብናወጣው ፡ ሰው ፡ ብልሀና ፡ ቁም ፡ ነገራም ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ ከመከራ ፡ እንደሚያወጣን ፡ አውቃለሁ ። አንተ ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ አላምንህም ፡ ነበር ፤ አንተም ፡ እኔን ፡ አታምነኝም ። ሰው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አውሬ ፡ ግን ፡ ዘሮ ፡ ዘሮ ፡ አውሬ ፡ ነው ። ብሎት ፡ አንበሳውና ፡ ድቡ ፡ ተስማምተው ፡ ሰውዬውን ፡ ዶጋፈው ፡ አወጡት ። ሰውዬውም ፡ በእነሱ ፡ እርዳታና ፡ ወራሱም ፡ ጉልበት ፡ ተፍገርግሮ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱንም ፡ አውሬዎች ፡ እንዲወጡ ፡ አደረጋቸው ። አንበሳውም ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ብበላህ ፡ ምን ፡ ዋስ ፡ የሚሆ ንህ ፡ ነገር ፡ አለህና ፡ ነው ፡ ያወጣኸኝ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ሰው

Scanned with CamScanner

ዬው ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ ሲያሳድጉኝ ፡ የተዋዋልኸውን ፡ ቃል ፡ ለመ
ፈጸም ፡ የሚያስፈልግ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ለሕይወትህ ፡ አትሰሳ ፡ ብለው ፡
አስተምረውኛል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ይኸውልህ ፡ የአንተና ፡ የእኔ ፡
ዘመዶች ፡ ሲያሳድጉን ፡ እንዲህ ፡ አላስተማሩንም ። ሰው ፡ ምንም ፡
ቢሆን ፡ ከእንስሳ ፡ ይበልጣል ፡ ያልህህ ፡ ስዚህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አን
በሳ ፡ ለድቡ ፡ ነገረው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሦስቱም ፡ በሰላም ፡ ተለያዩ ።
መልክም ፡ ጠባይ ፡ በጠላትም ፡ ዘንድ ፡ ቢሆን ፡ ዋጋ ፡ አለው ።
ከንቱ ፡ ፍጥረት ፡ ግን ፡ መክራ ፡ በገንው ፡ ቁጥር ፡ መልሶ ፡ ራሱን ፡
በገዛ ፡ አንደበቱ ፡ ያዋርዳል ። ሕሊናው ፡ የማይወቅሰው ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡
ቢጠፋ ፡ እንኳን ፡ በንጽሕናው ፡ እየኮራ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ዚቀኛ ።

ዚቀኛ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሐሩን ፡ አራሽድ ፡ ከሚባለው ፡
ከበግዳድ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ አቅርቡኝ ፡ ብሎ ፡ ስለ፡ሰመነ ፡ ተፈቀደለ
ትና ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ገብቶ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሴላ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ ሊሠራው ፡ የማይችለው ፡ ትንግርት ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡
አሳይዎታለሁና ፡ ይፍቀዱልኝ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ንጉሡም ፡ አሳየኝ ፡
ብሎ ፡ ፈቀደለት ። ሰውዬው ፡ ከኪሱ ፡ ውጅሞ ፡ መሰይ ፡ ጎትቶ ፡
አውጥቶ ፡ በውስጡ ፡ ብዙ ፡ መርፌ ፡ ክተተ ። ቀጥሎ ፡ እልፍ ፡
አደረገና ፡ አንዷን ፡ መርፌ ፡ በማፍዋ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ አፅ
ግት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ቆመና ፡ ከውጅሞው ፡ ውስጥ ፡
ያሱትን ፡ መርፌዎች ፡ አንድ ፡ በንድ ፡ አውጥቶ ፡ እየወረወረ ፡ መሬት ፡
ላይ ፡ በተከላት ፡ መርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ እያሰለፈ ፡ ሁሉንም ፡ ጨረ
ሳቸው ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ አልተሰሳተም ።

ሐሩን ፡ አራሽድ ፡ ስዚህ ፡ ሰው ፡ መቶ ፡ ወርቅ ፡ ሰጥተውት ፡
መቶ ፡ ጅራፍ ፡ እንዲገርፉት ፡ አዘዘ ። እዚያ ፡ የነበሩ ፡ መኳንንትና ፡
ባለሟሎቹ ፡ ቅጣትና ፡ ሽልማት ፡ ማዘዝህ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡
ነው ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። ይህን ፡ ያህል ፡ የመሰጠነ ፡ እጅ ፡
እያለው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ሞያ ፡ እንዳይማርበት ፡ ድክመንና ፡
ጊዜውን ፡ በማይረባና ፡ ለአገር ፡ በማይጠቅም ፡ ጨዋታ ፡ ላይ ፡ በማ
ዋሉ ፡ ተናድጀ ፡ እንዳቀጣ ፡ አዘዝሁ ። የሽለምሁበትም ፡ ምክንያት ፡

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ የሚያስደንቅ ፡ መሆኑ ፡ የማ
ይክድ ፡ ስለሆነ ፡ ዋጋውን ፡ እንዳልነሳው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ሐሩን ፡
አራሽድ ፡ መለሰሳቸው ።

በግር ፡ ጠብታ ፡ አገር ፡ ትውታ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንግቶ ፡ ጠበንጃ ፡
አንድ ፡ አዳኝ ፡ ወረደ ፡ የቤቱን ፡ ደረጃ ።
ከትከሻውም ፡ ላይ ፡ ነበረ ፡ ስልቻ ፡
የተነሣ ፡ መስሎ ፡ ለመሄድ ፡ ዘመቻ ፡
ላደን ፡ የሚረዳው ፡ አስክትለ ፡ ውሻ ፡
ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ ሲሻ ፡
አዚያም ፡ አገኘና ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ዋሻ ፡
ገብቶ ፡ ሲመለከት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ዞሮ ፡
ከጐድጓዳ ፡ ሥፍራ ፡ ንብ ፡ ሰፍሮበት ፡ ኖሮ ፡
የተከማቸ ፡ ማር ፡ አገኘ ፡ በብዙ ።
በጣም ፡ ስለረዳው ፡ ስልቻ ፡ መያዙ ፡
ማሩን ፡ እየዛቀ ። በስልቻው ፡ ሞልቶ ፡
ሲሸጥ ፡ አስበና ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ገብቶ ፡
ከማር ፡ ነጋዴ ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ ሲነጋገር ፡
ነጋዴም ፡ ዋጋውን ፡ ፈት ፡ ሳልከራከር ፡
ልወቀው ፡ አሰና ፡ የማሩን ፡ ዓይነት ፡
ስልቻውን ፡ ፊታ ፡ ቀምሶ ፡ ስማየት ።
ይህን ፡ ጊዜ ፡ ማሩ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ አለ ፡
መልስ ፡ አሰረና ፡ ሊገዛው ፡ ቸኮለ ።
ነጋዴና ፡ አዳኙ ፡ እዚያው ፡ እንጂ ፡ ቆሙ ፡
በዛ ፡ አነሰ ፡ እያሉ ፡ በዋጋ ፡ ሲስማሙ ፡
መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የማሩን ፡ ጠብታ ፡
ትበላው ፡ ጀመረች ፡ አንድ ፡ ዎፍ ፡ ተጠግታ ።
ዎፍዋን ፡ አየችና ፡ የነጋዴው ፡ ድመት ፡
ዘላ ፡ በጥፍሮችዋ ፡ ያዘቻት ፡ ቧድንት ።
ውሻም ፡ ዘለለና ፡ እንደ ፡ ገሠገሠ ፡
ድመትና ፡ ዎፍን ፡ አንድነት ፡ ጎረሰ ።
ነጋዴው ፡ ጮኸና ፡ ድመቱ ፡ አሳስታው ፡

Scanned with CamScanner

ውሸው ፡ ድብን ፡ አለ ፡ በበትር ፡ ቢመታው ።
ለውሸው ፡ ተናዶ ፡ ሳያስብ ፡ በርጋታ ፡
ደገነና ፡ ቢስብ ፡ የጠበንጃ ፡ ቃታ ፡
አዳኝ ፡ ነጋዴውን ፡ ገደለው ፡ በንድ ፡ አፍታ ፡
ከዚያም ፡ በመንደሩ ፡ ቀለጠ ፡ ኡኡታ ።
አዳኙም ፡ ሸሽና ፡ ወጣ ፡ ከመንደሩ ፡
ለካ ፡ የመጣበት ፡ ሌላ ፡ ኖሮ ፡ አገሩ ፡
ወገናቸው ፡ ኖሮ ፡ ሁለት ፡ ልዩ ፡ ገ።ሣ ፡
ጠቡ ፡ ከረረና ፡ በዚህ ፡ የተነሣ ፡
የሚቹ ፡ ወገኖች ፡ ደም ፡ አናውጣ ፡ ብለው ፡
ታጥቀው ፡ ለመዋጋት ፡ ወጡ ፡ ተሰብስበው ።
የገዳይ ፡ ወገኖች ፡ ነገሩን ፡ ሳያውቁ ፡
ወር ፡ መምጣቱን ፡ አይተው ፡ እነሱም ፡ ታጠቁ ።
ከዚያም ፡ ተጋጩና ፡ እየተናነቁ ፡
አንዱ ፡ በንደኛው ፡ ላይ ፡ እየተራኩት ፡
ትልቅ ፡ ውጊያ ፡ ሆኖ ፡ አያሌ ፡ ሰው ፡ ሞት ።
ይህን ፡ በመሰለ ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡
ሕዝብ ፡ እየተዋጋ ፡ የተጎዳው ፡ አገር ፡
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ቢቈጠር ፡
አያሌ ፡ ነውና ፡ ምንጩን ፡ ሳታስተውሉ ፡
ያለ ፡ መመራመር ፡ ለጠብ ፡ አትቸኩሉ ።

የገንዘብ ፡ ፍቅር ።

የሃይማኖት ፡ ቀኖስ ፡ የፍቅር ፡ ነቁርሳ ፡
ገንዘብ ፡ ሆነ ፡ ምንጩ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ አበሳ ።
ገንዘብ ፡ ነው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ከሁሉ ፡ እሚበልጥ ፡
ገንዘብ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ክብርን ፡ የሚሰጥ ፤
ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ እየተናነቀ ፡
ሰው ፡ ወዳጁን ፡ ጠላ ፡ ከዘመዱ ፡ ራቀ ።
ሰው ፡ ተስገበገበ ፡ ክብሩንም ፡ ረሳ ፡
ተረት ፡ ላማው፡ታችሁ ፡ በዚህ ፡ የተነሣ ፡
እጅግ ፡ አርጎ ፡ በጣም ፡ ገንዘብ ፡ የወደደ ፡

ሁሉን ፡ በያይነቱ ፡ ዕቃ ፡ እየነገደ ፡
ሱቅ ፡ ከፍቶ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤
አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ በጣም ፡ የከበረ ፡
ከሱቁ ፡ ገባና ፡ ጪት ፡ በማለዳ ፡
አንሥቶ ፡ አገላብጦ ፡ አንድ ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡
ዋጋው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ? አለና ፡ ጠየቀው ፡
ነጋዴው ፡ ተናግሮ ፡ ዋጋውን ፡ ሳያውቀው ።
ወዲያው ፡ ቀጠለና ፡ መልኩ ፡ የተስማማ ፡
የተዋበ ፡ ሆኖ ፡ ለምን ፡ አንዲህ ፡ ገማ ?
እገዘህ ፡ ነበረ ፡ በጠየቅኸው ፡ ዋጋ ፡
ግን ፡ ሽታው ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ ሰውም ፡ አያስጠጋ ።
በደኅና ፡ አልተሠራም ፡ አለና ፡ መለሰው ።
ነጋዴውም ፡ አለ ፡ ውስጡን ፡ አለስልሰው ፡
ደክመው ፡ የሠሩት ፡ ነው ፡ በደኅና ፡ እየፋቁ ፡
በዚህ ፡ በከተማ ፡ ዘረው ፡ በየሱቁ ፡
ቢሹም ፡ አያገኙ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡
ይመኑኝ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ ይመልከቱ ፡ አያለ ፡
ቢናገር ፡ ሀብታሙ ፡ ቢያምር ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፡
ጠረኑ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ ሲቀርቡት ፡ ይገማል ።
አለና ፡ ሳይገዛ ፡ ቢሄድበት ፡ ትቶ ፡
ሳይሸጥ ፡ በመቅረቱ ፡ በጣም ፡ ተቆጭቶ ፡
የመለሰው ፡ መስሎት ፡ በቶለሞ ፡ አስረድቶ ፡
ምስኪኑ ፡ ነጋዴ ፡ ቸኩሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤
ለእርስዎ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ለሴላም ፡ አይዶለ ።
ይህን ፡ መሳይ ፡ ቆዳ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ የለም ፡
እዩት ፡ እንዴት ፡ ያምራል ፡ የጠጕሩ ፡ ቀለም ፡
ግጥም ፡ ከኔ ፡ ነው ፡ ከቆዳው ፡ አይዶለም ።
ቀባጥሮም ፡ ቀምቶ ፡ ዐሐሰት ፡ ነግዶ ፡
ከክብሩ ፡ አብልጦ ፡ ገንዘብ ፡ በጣም ፡ ወዶ ፡
ብዙ ፡ ሰው ፡ ይኖራል ፡ ራሱን ፡ እዋርያ ።

Scanned with CamScanner

ዓሣ ፡ አጥማጅና ፡ ዛጎል ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጅ ፡ ሰው ፡ መረቡን ፡ ይዘ ፡ በጀልባ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ ሆኖ ፡ ዓሣ ፡ ሲያጠምድ ፡ ከባሕሩ ፡ ሥር ፡ አንዲት ፡ ዛጎል ፡ ስታብለጨልጭ ፡ አይቶ ፡ ዋጋዋ ፡ የቈበረ ፡ አልማዝ ፡ ስለመሰለችው ፡ እንደ ፡ ምጥ ፡ በራ ፡ የምታመል ጠው ፡ መስሎት ፡ ይሆን ? ወይስ ፡ ደግሞ ፡ አልማዝ ፡ ከገኘሁ ፡ የቀረው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ ይሆን ? ወይስ ፡ ከደስታ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ነገረ ፡ ዓለሙን ፡ ረስቶት ፡ ይሆን ? በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደሆነ ፡ እንጃ ፡ ከባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ይጎትተው ፡ የነበረውን ፡ ዓሣ ፡ የመላበትን ፡ መረቡን ፡ ከባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ወር ውሮ ፡ ገሥግሦ ፡ ሄዶ ፡ ቢያነሣት ፡ ያች ፡ የምታብለጨልጪው ፡ ነገር ፡ ቅርፊትዋ ፡ የሚያምር ፡ ውስጥዋ ፡ ግን ፡ ባዶ ፡ የሆነ ፡ ዛጎል ፡ ነች ፡ እንጂ ፡ አልማዝ ፡ አልነበረችም ። እንዲህ ፡ አርጎ ፡ ምስኪኑ ፡ ሰውዬ ፡ የዕለት ፡ እንጀራውን ፡ የሚያገኝበትን ፡ መረቡን ፡ አጥቶ ፡ አልማዝ ፡ በመሰለችውም ፡ ነገር ፡ ተሳቆ ፡ ከሁለቱም ፡ ሳይሆን ፡ እያዘነ ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ።

የዚያን ፡ ዕለት ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ምጭትና ፡ ተስፋ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ እያታለሉ ፡ እንደምን ፡ እንደሚቀልዱበትና ፡ እንደሚጫወቱ በት ፡ እያሰበ ፡ ሲተክዝ ፡ ዋለ ። ደስታም ፡ ሆነ ፡ ኀዘንም ፡ ሆነ ፡ ማለፉ ፡ አይቀርምና ፡ በማግሥቱ ፡ ሴላ ፡ መረብ ፡ ፈልጎ ፡ ዓሣ ፡ ሊያጠምድ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ሄደ ። ጸጸቱን ፡ እንዳይቀሰቅስበት ፡ ቀድሞ ፡ ያጠ ምድበት ፡ የነበረውን ፡ መረቡን ፡ የወረወረበትን ፡ ቦታ ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሴላ ፡ ሥፍራ ፡ ሄዶ ፡ መረቡን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጥሎ ፡ ይጠባበቅ ፡ ያመር ። ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ጎንበስ ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ከውኃው ፡ ሥር ፡ እንደ ፡ ጨለማ ፡ ከከብ ፡ ሆና ፡ የምታብረቀርቅ ፡ እንዲት ፡ ነገር ፡ አየ ። ትላንትና ፡ የተሞንሁት ፡ ይበቃኛል ፡ ዛሬስ ፡ አልታለልም ፡ ብሎ ፡ መረቡን ፡ ጎተተና ፡ የተያዙለትን ፡ ጥቂት ፡ ዓሦች ፡ ይዘ ፡ ያቺን ፡ የምታበራ ፡ ነገር ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። እንዲሁ ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ ዓሣ ፡ ሊያጠምድ ፡ ሄዶ ፡ የነበረ ፡ ጓደኛው ፡ ያቺን ፡ የምታብረቀርቀውን ፡ ነገር ፡ አይቶ ፡ ቢያነሣት ፡ ዋጋዋ ፡ የከበረ ፡ የምታምር ፡ አልማዝ ፡ ሆና ፡ አገኛትና ፡ አለመጠን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከኋላው ፡ አየረረጠ ፡ መጥቶ ፡ ደረሰበትና ፡ ደስታውን ፡ አካፈለው ። የመ

ጀመሪያውም ፡ ሰው ፡ ይህችኔ ፡ አልማዝ ፡ በፊት ፡ ያየኋት ፡ እኔ ፡ ነበርኩ ፡ ግን ፡ ትላንትና ፡ እንደዚሁ ፡ የምታብለጨልጭ ፡ ነገር ፡ አይቼ ፡ ዛጎል ፡ ሆና ፡ አገኘኋት ። አልማዝ ፡ መስላኝ ፡ መረቤን ፡ ከሰሳው ፡ ወርውሬ ፡ ስለነበረ ፡ ሄጄ ፡ ያነሣኋት ፡ በዚህ ፡ ተጸጽቼ ፡ ሳለሁ ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ይህችን ፡ ከይ ፡ እንደ ፡ ትላንትናው ፡ የምሳቅቅ ፡ መስሎኝ ፡ አልፈያት ፡ መጣሁ ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ለምን ፡ ሳላነሣት ፡ ቀረሁ ፡ ብዬ ፡ አይቆጨኝም ። ትላንትና ፡ ለእሷ ፡ ብዬ ፡ ገንዘቤን ፡ አጥፍሁና ፡ ምናልባት ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ በሕይወቴ ፡ ሳትቀጣኝ ፡ አትቀርም ፡ ነበር ፡ ስለምን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሀን ፡ ዕድል ፡ ለእኔ ፡ አላለውም ፡ ብሎ ፡ ለጓደኛው ፡ አጫወተው ።

ሰው ፡ ዕድሉ ፡ ያልሰጠውን ፡ ነገር ፡ አመለጠኝ ፡ ብሎ ፡ መጸጸቱን ፡ ትቶ ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፡ በዚያው ፡ በተሰጠው ፡ ዕድል ፡ ደስ ፡ እያለውና ፡ ፈጣሪውን ፡ እያመሰገነ ፡ መኖር ፡ ይገባዋል ።

ስለ ፡ ተግባረ ፡ እድ ።

የጡቴን ፡ ማር ፡ ወተት ፡ እናንት ፡ የጠቧችሁ ፡ በግሕፅኑ ፡ አገሬ ፡ የተሸከምኋችሁ ፡ በኢትዮጵያዊነት ፡ የተወለዳችሁ ፡ ምሥጢሬን ፡ ከልቤ ፡ ዛሬ ፡ ላካፍላችሁ ። ሞልቶ ፡ ሲገነፍል ፡ ሰው ፡ ችግሩ ፡ በገዛ ፡ ከልጅ ፡ የቀረበ ፡ ምን ፡ ዘመድ ፡ ተገኝቶ ። ለግለጠው ፡ ኀዘኔን ፡ የመረረውን ፡ ሆድ ፡ ሆዴን ፡ ሲበላኝ ፡ የሚኖረውን ። ተመልከቱት ፡ እያልሁ ፡ የናንተን ፡ መቸገር ፡ የኔንም ፡ ጉዳቴን ፡ ገልጬ ፡ ልናገር ። የዚገቴንም ፡ ጽናት ፡ እስኪ ፡ ላነሣሣ ፡ እድምጡኝ ፡ ልጆቼ ፡ እንክችሁ ፡ ወቀሳ ፡ በመርከብ ፡ ሲጓዙ ፡ በጣም ፡ እያማረኝ ፡ ባይሮፕላን ፡ ሲበሩ ፡ በጣም ፡ እያማረኝ ፡ የማግኘቱ ፡ ነገር ፡ ብልሃቱ ፡ ቸገረኝ ። ሞርታችሁ ፡ ልይና ፡ እናንተ ፡ ልጆቼ ፡ እኔም ፡ ወግ ፡ ይድረሰኝ ፡ እንደ ፡ ጓደኞቼ ።

Scanned with CamScanner

በሉ ፡ ተረዳዱ ፡ ስንፍና ፡ ተሻረ ፡
በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥራ ፡ ተከበረ ።
ይህ ፡ የልቤ ፡ ምኞት ፡ በውነት ፡ ተፈጽሞ ፡
የፋብሪካ ፡ ሥራ ፡ እዚህ ፡ ተቋቁሞ ፡
የጦር ፡ መሣሪያና ፡ አኤሮፕላን ፡ ተሠርቶ ፡
የጅ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ በኔም ፡ አገር ፡ ገብቶ ፡
በእናንተ ፡ ልጆቼ ፡ እጅ ፡ ተከናውኖ ፡
ሕዝቤ ፡ በዕውቀት ፡ መንገድ ፡ በቶሎ ፡ ወልጥና
እንደ ፡ ቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉን ፡ በቤታችሁ ፡
ለመሥራት ፡ ለማፍራት ፡ ለመፍጠር ፡ ችላችሁ ፡
የማይበት ፡ ጊዜው ፡ እኩል ፡ ስትሆኑ ፡
ምነው ፡ ዘገየብኝ ፡ ናፈቀኝ ፡ ዘመኑ ።
እንደዚህ ፡ ስንን ፡ ተሳቅቄ ፡ እንዳልቀር ፡
ማን ፡ አደራ ፡ እላለሁ ፡ ከእናንተ ፡ በተቀር ።
የአምስት ፡ ዓመት ፡ ሥታይ ፡ ክለፈ ፡ በኋላ ፡
የቀመሳችሁት ፡ የውርደት ፡ አተላ ፡
ማንገፍገፉ ፡ ቀርቶ ፡ መች ፡ ያሰኛል ፡ ችላ ።
ሥሩልኝ ፡ ልጆቼ ፡ እናንት ፡ ወጣቶቼ ፡
እየተሰለቁ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ሲተቹ ፡
መቼም ፡ አያልፍልሽ ፡ አይበሉኝ ፡ ሴሎቹ ።
በሉ ፡ ተረዳዱ ፡ ስንፍና ፡ ተሻረ ፡
በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥራ ፡ ተከበረ ።
የቀረውን ፡ ሁሉ ፡ ሀብት ከላጣችሁ ፡
በዚሁ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተበለጣችሁ ።
ልባችሁ ፡ ዘላለም ፡ ስንፍናን ፡ አይውደድ ፡
ይጠብጥ ፡ እጃችሁ ፡ መዶሻና ፡ ሞረድ ።
ስንፍናው ፡ ከሙያ ፡ እየተቈጠረ ፡
ባለእጅ ፡ ጠይብ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ የነበረ ፡
የሞኝነት ፡ ዘመን ፡ ጊዜው ፡ አልፍልና ፡
ዘንድሮ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እዩት ፡ ይኸውና
በሥራ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚገኝ ፡ ብዙርና ።

መሐንዲስነቱን ፡ የግንብ ፡ የግብርና ፡
የኤሌክትሪክ ፡ ሥራ ፡ የሰዓት ፡ የሞተር ፡
የመቀጥቀጥና ፡ ብረትን ፡ የማንጠር ፡
የእጅ ፡ ሥራ ፡ ሲባል ፡ አንደኛውም ፡ ሳይቀር ፡
ፈጥናችሁ ፡ ሁሉንም ፡ ተግታችሁ ፡ ተማሩ ፡
ታግሉ ፡ ድከሙ ፡ በጣም ፡ ተጣጣሩ ።
በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በይናግው ፡ መሪነት ፡
በትጋቱ ፡ ብርታት ፡ በልቡ ፡ ቅንነት ፡
ታሉን ፡ በመከተል ፡ መሥራት ፡ ክልቻላችሁ ፡
ከዚህ ፡ የተመቸ ፡ ሰዓትም ፡ የላችሁ ።
በሉ ፡ ተረዳዱ ፡ ስንፍና ፡ ተሻረ ፡
በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥራ ፡ ተከበረ ።
ያለም ፡ መንግሥታቶች ፡ የተበሉት ፡ ሁሉ ፡
ልጅና ፡ ሴት ፡ ሳይቀር ፡ ሕዝባቸው ፡ በሙሉ ፡
ከደንጊያ ፡ ከከሰል ፡ ከእንጨት ፡ ከብረቱ ፡
ታግለውና ፡ ደክመው ፡ እየተንገላቱ ፡
ግረውና ፡ ጥረው ፡ በሚያድሩበት ፡ ዘመን ፡
በመግዛት ፡ በመዋስ ፡ ወይም ፡ በመለመን ፡
መናር ፡ አትችሉም ፡ ይህንን ፡ ዕወቁ ፡
እመቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ የምትሰቀቁ ?
ብልጽግና ፡ ተርፎዋል ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡
ላዩም ፡ እጅግ ፡ ለም ፡ ነው ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ።
የእንጨቱ ፡ ሀብትና ፡ የማዕድኑ ፡ ቅርስ ፡
ከሁሉም ፡ ይበልጣል ፡ ከማንም ፡ አያንስ ።
የሚያስፈልጋችሁ ፡ ዕቃው ፡ በያይነቱ ፡
ምነው ፡ በእናንተ ፡ እጅ ፡ አለመሠራቱ ?
ይህን ፡ ለመፈጸም ፡ በርትታችሁ ፡ ትጉ ፡
የባዕድ ፡ ነጋዴ ፡ ምነው ፡ መበልጸጉ ?
በሉ ፡ ተረዳዱ ፡ ስንፍና ፡ ተሻረ ፡
በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥራ ፡ ተከበረ ።

Scanned with CamScanner

ከስሮ ፡ ከማስመጣት ፡ ከሮፕ ፡ ካሜሪካ ፡
ይቋቋም ፡ እዚሁ ፡ የሁሉም ፡ ፋብሪካ ።
የሚከሰርበት ፡ ስሚ ፡ እየታደሰ ፡
መስሎ ፡ ስለታየኝ ፡ ጊዜው ፡ የደረሰ ፡
ይህ ፡ የሴሊት ፡ ሕልሜ የቀኑ ፡ ምጭቱ ፡
ሲፈጸም ፡ ልይና ፡ ይታደስ ፡ ሕይወቱ ።
ሁልጊዜ ፡ መበለጥ ፡ ሰልችቶናል ፡ በሱ ፡
በቶሎ ፡ ለመድረስ ፡ ዛሬ ፡ ተማማሉ ።
መበለጥ ፡ መሸነፍ ፡ መቅረት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡
እንዲወገድልን ፡ ያስፈልጋል ፡ ማለ ።
የዝናቡን ፡ መጠን ፡ መዝኜና ፡ አስቤ ፡
ወደ ፡ ትልቅነት ፡ ተነሣሥቷል ፡ ልቤ ፡
ትልቅ ፡ ለመሆንም ፡ ልቤ ፡ ከተነሣ ፡
ማንም ፡ አያግደው ፡ ያሰቤን ፡ ግሥግሣ ።
ወደ ፡ ትልቅነት ፡ አሳብ ፡ እየሮጠ ፡
በምኞት ፡ ተቅጥሎ ፡ መንፈስ ፡ ከተናጠ ፡
ቅዱስ ፡ ትዕቢት ፡ የለም ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ።
ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ትዕቢት ፡ በልቤ ፡ ማደሩ ፡
ግድ ፡ ሆኖብኝ ፡ ነው ፡ ቢጠንቀኝ ፡ ነገሩ ።

በሉ ፡ ተረዳዱ ፡ ስንፍና ፡ ተሻረ ፡
በጎይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥራ ፡ ተከበረ ።

ይህ ፡ የምሰጣችሁ ፡ ያሁኑ ፡ ምክር ፡
ከሆነም ፡ ሆነልን ፡ ካልሆነም ፡ ይቅር ፡
የሚባል ፡ አይዶለም ፡ ልብችሁ ፡ አይርሳ ፡
ሳልዘገይ ፡ በፍጥነት ፡ ያሻል ፡ እንድነሣ ።
በዚህ ፡ በመልቲ ፡ ዓለም ፡ በሞላበት ፡ ተዡላ ፡
አልኖርም ፡ ወደፊት ፡ በግ ፡ ሆኜ ፡ ስበላ ።
መቼ ፡ ተጠቀመ ፡ ተጎዳ ፡ እንጂ ፡ አገሬ ፡
ሞኝና ፡ ልበ ፡ ገር ፡ ሆኜ ፡ በመኖሬ ።
ዛሬ ፡ ግን ፡ ለሥራ ፡ ሕዝቤ ፡ ቶሎ ፡ ንቃ ፡
ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ሰው ፡ እንዳይጠቃ ፡
ከሥራ ፡ የሚበልጥ ፡ የለውም ፡ ጠበታ ።

ተነሡ ፡ ታጠቁ ፡ የዕውቀት ፡ ብርሃን ፡ ወጣ ፡
የመወዳደሪያ ፡ የሥራ ፡ ቁን ፡ መጣ ።
ታጠቁ ፡ ለጥበብ ፡ ታጠቁ ፡ ለሥራ ፡
እናንተም ፡ ከብራችሁ ፡ እኔም ፡ እንድክራ ፡
ይህ ፡ ነው ፡ ላዲስ ፡ ዘመን ፡ የተሰጠ ፡ አደራ ።
በሉ ፡ ተረዳዱ ፡ ስንፍና ፡ ተሻረ ፡
በጎይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥራ ፡ ተከበረ ።

አግኝቶ ፡ ያጣ ፡ ሰው ።

ደስታና ፡ ሲሳይ ፡ በኑሮው ፡ የሞላ ፡
የተቀማጠለ ፡ በምኞት ፡ በተድላ ፡
ገና ፡ ከልጅነት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡
በወርቅና ፡ በብር ፡ አለመጠን ፡ ከብሮ ፡
አርባ ፡ ዓመት ፡ በሙሉ ፡ በሲሳይ ፡ የኖረ ፡
የትልቅ ፡ ሀብታም ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።
ሦስትና ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ እየጠራ ፡
ይጋብዝ ፡ ነበረ ፡ ፍጥረቱን ፡ በተራ ።
ውሾችም ፤ ነበሩት ፡ በተድላ ፡ እሚኖሩ ፡
ባልጋ ፡ የሚተኙ ፡ የተንቀባረሩ ።
የሚሠራላቸው ፡ ምግብ ፡ በያይነቱ ፡
ሕመም ፡ ሲያገኛቸው ፡ ከየሐኪም ፡ ቤቱ ፡
ይመጣል ፡ ተመርጠ ፡ የሐኪም ፡ ወዋቂ ፡
ደግሞም ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጠያቂ ።
ደስ ፡ ብሎት ፡ የሚኖር ፡ በዚህ ፡ መልካም ፡ ዕጣ ፡
እንዲህ ፡ ጌታ ፡ ነበር ፡ የሚሠራው ፡ ያጣ ።
እመት ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ አመለ ፡ ቅብራራ ፡
እጅግ ፡ ያስገርማል ፡ የወረቷ ፡ ሥራ ።
መላው ፡ አይታወቅ ፡ ጠባይዋ ፡ ፈሊጧ ፡
ድንገት ፡ ትሄዳለች ፡ በዚያው ፡ ባመጣው ።
እንዲት ፡ እንደምትሄድ ፡ እንዲት ፡ እንድትመጣ ፡
አይመረመርም ፡ የሚሥጠርዋ ፡ ጣጣ ።

Scanned with CamScanner

በዚህ ፡ የተነሣ ፡ ይህ ፡ ባለጸጋ ፡ ሰው ፡
ሴላው ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡ አጣ ፡ የሚቀምሰው ።
ድንገት ፡ በአርባ ፡ ዓመቱ ፡ ሀብቱን ፡ ሁሉ ፡ ከስሮ ፡
ተረስቶ ፡ ተንቆ ፡ በጣም ፡ ተቸግሮ ፡
በዚህ ፡ ላይ ፡ በሽታ ፡ በሰውነቱ ፡ አድሮ ፡
ሥቃዩን ፡ ሲቀበል ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖሮ ፡
ተንገላቶ ፡ ሞተ ፡ ልክ ፡ በሰባ ፡ ዓመቱ ፡
በጣም ፡ ሲያጣድፈው ፡ ይዘ ፡ ጣረ ፡ ሞቱ ፡
ታግሎ ፡ ቀና ፡ አለና ፡ ተነሥቶ ፡ ካንገቱ ፡
ገንዘብ ፡ ስለሌለው ፡ ዕቃ ፡ መይም ፡ ዐታ ፡
እንዲህ ፡ ተናገረ ፡ በኑዛዜ ፡ ፈንታ ፡
« ስሄድ ፡ እያያችሁ ፡ እንዲህ ፡ ተጎድቼ ፡
« እዘኑልኝ ፡ በጣም ፡ አወይ ፡ ወዳጆቼ !
« አልቅሱልኝ ፡ በጣም ፡ አፍስሱልኝ ፡ እንባ ፡
« በርባ ፡ ዓመቴ ፡ ሞቼ ፡ ስቀበር ፡ በሰባ ።

ጥቂሮችም ፡ እንደ ፡ ሰው ።

በግራዚያኒ ፡ አደጋ ፡ ሰበብ ፡ የተነሣ ፡
ቁጥራቸው ፡ የሚሆን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡
የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ተይዘው ፡ በአፈሳ ፡
ባራዳ ፡ ቀበሌ ፡ በጥብቅ ፡ የታሰሩ ፡
ሦስት ፡ ቀን ፡ ተርበው ፡ ተጠምተው ፡ አደሩ ።
አቤት ፡ አቤት ፡ ብለው ፡ ቢያበዙበት ፡ እንባ ፡
አለቃው ፡ ፈቀደ ፡ ምግብ ፡ እንዲገባ ።
ሲገድልና ፡ ሲፈጅ ፡ ሕሊና ፡ እንዳይወቅሰው ፡
ፋሺስቶች ፡ ሲልኩት ፡ ጥቁር ፡ ልብስ ፡ አልብሰው ፡
ልዩ ፡ ፍጥረት ፡ እንጂ ፡ ጥቁር ፡ አይዶለም ፡ ሰው ።
ብለው ፡ የሰበኩት ፡ ካገሩ ፡ ሲወጣ ፡
ይህን ፡ በልቡ ፡ አርጎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣ ።
ፎፈትም ፡ ንባብም ፡ ምንም ፡ ያልተማረ ፡
በበመፀኖቱ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ የኖረ ፡

ሳ ፡ ወንበዴ ፡ ፊቱ ፡ የሚያስፈራ ፡
ዘይም ፡ አፍሳሽነት ፡ ጥቂት ፡ የማይራራ ።
እውነተኛ ፡ ደደብ ፡ አንጐሉ ፡ አማይሠራ ፡
ትእዛዝ ፡ ፈጻሚያቸው ፡ ለመግደል ፡ ለማሰር ፡
የጣሊያን ፡ ተወላጅ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ነበር ።
አሉም ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ዓይኖቹን ፡ አፍጦ ፡
እጅግ ፡ አለመጠን ፡ በብዙ ፡ ደንግጦ ።
ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ አስረኞቹን ፡ አይቶ ፡
በመደነቅ ፡ ብዛት ፡ በጣም ፡ ተመልክቶ ፡
እንደተነገረመ ፡ እንደ፡ደነገጠ ፡
ወደ፡ጓደኞቹ ፡ ሄደና ፡ እየሮጠ ።
እውቄ ፡ በር ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ አገኛቸው ። ።
ትንግርተኛ ፡ ነገር ፡ አየሁኝ ፡ አላቸው ፡
ለካ ፡ እኔ ፡ አስረኞች ፡ ሸሞኑን ፡ ተጎድተው ።
በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ምግብ ፡ ዛሬ ፡ አግኝተው ፡
ይገርማል ፡ ይደንቃል ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ እህል ፡ ጐርሰው ፡
ሲበሉ ፡ አየኋቸው ፡ ጥቁሮችም ፡ እንደ ፡ ሰው ።

የበረሃ ፡ መንገደኛ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ በበረሃ ፡ ሲጓዝ ፡
ድንገት ፡ አውሬ ፡ ገጠመውና ፡ ሊበላው ፡ አባረረው ፡ መንገደኛውም ፡
ነፍሱን ፡ ለማዳን ፡ የድንጋጤው ፡ ብዛት ፡ ከልማዱ ፡ በላይ ፡ ጉልበት ፡
ስለሰጠው ፡ በሚያስደንቅ ፡ ፍጥነት ፡ እየሮጠ ፡ መጠጊያና ፡ መደበቂያ ፡
በሌለው ፡ በዚያ ፡ ሜዳ ፡ ብለው ፡ ብአሸዋ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሲሯሯጥ ፡ አንድ ፡
ጉድጓድ ፡ አይቶ ፡ ከውስጡ ፡ ዘሎ ፡ ሊገባ ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አድርጎ ፡
ደረሰና ፡ ጉንበስ ፡ ብሎ ፡ ቢያስተውል ፡ አንድ ፡ ዘንዶ ፡ ከዚያ ፡ ጉድ
ጓድ ፡ ውስጥ ፡ ኖሮ ፡ ተንቀሳቀሰና ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ሊውጠው ፡ አሰፈ
ሰፈ ። ድንጋጤው ፡ ከቀድሞው ፡ የባሰ ፡ ሆኖበት ፡ ተመለሰና ፡ የሚደርስበት ፡
በታ ፡ አጥቶ ፡ ሲርበደበድ ፡ ከጉድጓዱ ፡ አጠገብ ፡ የበረሃ ፡ ቁጥቋጦ ፡
በቅሎ ፡ ከጉድጓዱ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ሲወዛወዝ ፡ አየ ፤ ፈጥኖም ፡ ቍጥቋጦውን ፡
ጨብጠ ፡ ከጉድጓዱ ፡ ላይ ፡ ተንጠለጠለ ። ወዲያው ፡ አውሬው ፡ ደርሶበት ፡

Scanned with CamScanner

ከጉድጓዱ ፡ አፍ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ተርቦ ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ ሲያሳየው ፡ አፋን ፡ እያዛጋ ፡ ቁልቁል ፡ ይመለከተው ፡ ጀመር:: መንገደኛው ፡ መጨረሻዬ ፡ ምን ፡ ይሆን ብሎ ፡ በመጨነቅ ፡ ፈንታ ፡ ለጊዜው ፡ በመትረፋ ፡ ብቻ ፡ ደስ፡ ብሎት ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ አይጥ፡ አንድ ፡ ጥቁር ፡ አይጥ ፡ እሱ ፡ የተንጠለጠለበትን ፡ ቁጥቋጦ ፡ ከሥሩ ፡ በጥርሳቸው ፡ ይቀረጣጥፋት ፡ ጀመር ፡፡ አያያዛቸውም ፡ ቡቱሎ ፡ ቆርጠው ፡ ለመጣል፡ እንደ ፡ ተጣደፉ ፡ ያሰረዳ ፡ ነበር::

መንገደኛው ፡ ይህን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ደንግጠ ፡ ጮኅ በስ ፡ በሉ ፡ ዳግም ፡ ቁልቁል ፡ ቢመለከት ፡ የተንጠለጠለበት ፡ ቁጥቋጦ ፡ በተበጠሰ ፡ ጊዜ ፡ ከጉድጓዱ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ ተከፍቶ ፡ ከሚጠብቀው ፡ ከዘንዶው ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚወድቅ ፡ ተረዳው ፡፡ ቀኖ፡ ብሎ ፡ ደግሞ አይጦቹን ፡ ቢመለከታቸው ፡ ቁጥቋጦውን ፡ በጥርሳቸው ፡ የመመድመዳ ቸውን ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ተገበት ፡ አየ ፡፡ የሚጠብቀውን ፡ ክፋ ፡ እሚ ሚት ፡ ዐውቆት ፡ መጠን ፡ በሌለው ፡ ኀዘን ፡ ሲጨነቅ ፡ ከቁጥቋጦው ፡ ቅጠሎች ፡ ላይ ፡ ወለላ ፡ ማር አገኛና ፡ መከራውን ፡ አሁን ፡ ባሁን ፡ ረሱቶት ፡ ይሆን? ወይስ ፡ ደግሞ ፡ እንግዲህ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ይድረስ፡ ለማ ለት ፡ ይሆን? ፡ እንጃ ፡ ምክንያቱን ፡ የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ከቅጠሎቹ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ማር ፡ እየተንጠራራ ፡ ይልስ ፡ ጀመር ::

ይህ ፡ ክምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ የተገኘ ፡ ተረት ፡ ከባድ ፡ መከራ ፡ ወይም ፡ ብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ እንዳለበት ፡ ልቡ ሲያውቀው በማይ ረባ ጨዋታ፡ ጊዜውን የሚያሳልፈውን፡ አሳብ ፡ የለሽ ፡ የሆነ ውን ፡ አንዳንድ ፡ ሰው፡ ለመንቀፍ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲተረት ፡ የሚ ኖር ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ምሳሌ ፡ ነው::

ሌዎን ፡ ቶልስቶኢ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ተረት ፡ አሳብ ፡ የለሽ ፡ ለለ ሆኑት፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ጠባይ ፡ ምሳሌ ፡ በመሆን ፡ ብቻ ፡ ሊወ ሰን ፡ አይገባውም ፡ በጠቅላላው ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ለሆነው ፡ ስዎች፡ ሁሉ ፡ የሕይወታችን ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ ነው ፡ ይለናል ፡፡ ምክንያ ቱንም፡ እንደሀ ፡ ሲል ፡ ይቀጥላል ፡ ሞትን ፡ የሚያህል ፡፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ ተሸክመን ፡ የዘንዶውንም ፡ አፍ ፡ የመ ለለ ፡ የመቃብር ፡ ዋሻ ፡ ተከፍቶ ፡ ሲጠብቀን ፡ ይህንንም ፡ ልቡና ችን ፡ እያወቀው ፡ ግማሻችን ፡ በንግድ ፡ ግማሻችን ፡ በእርሻ ፡ ግማሻ

ችንም ፡ ጥበብን ፡ ልንመረምር ፡ መጻሕፍት ፡ በማገላበጥ ፡ የቀሩትም ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ትተነው ፡ ለም ንሄደው ፡ ምድራዊ ፡ ኑሮ ፡ ዘላለም ፡ እንኖርበት ፡ ይመስል ፡ ስንጪ ነቅለት ፡ መታየታችን ፡ መንገደኛው ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ከዘንዶ ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡ መውደቁን ፡ እያወቀው ፡ ማሩን ፡ እንደመላሱ ፡ ያህል ፡ ሊቋጠርብን ፡ ይብቃው ። የሴዎን ፡ ቶልስቶኢን ፡ ምሳሌ ፡ ሳንክድ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ በቅጽበት ፡ የሚያልፋትን ፡ የሞት ፡ መከራ ፡ እያ ስታወሰ ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ ሲጨነቅ ፡ እንዳይኖር ፡ አዝናለት ፡ ልበ ፡ ደንዳናነትን ፡ ለሰጠው ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ይገባናል ። ሰው ፡ ሞትን ፡ ድል ፡ የሚያደርገው ፡ መልክም ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ሕይወቱን ፡ በማሳለፍ ፡ እንጂ ፡ ሞትን ፡ በመፍራትና ፡ በመሸሽ ፡ አይ ዶለምና ።

የአዚናራ ፡ እስረኛ ።

ቀና ፡ ቢሉ ፡ ሰማይ ፡ ጐንበስ ፡ ቢሉ ፡ ምድር ፡ ቀኝ ፡ ቢያዩ ፡ ጋራ ፤ ግራ ፡ ቢያዩ ፡ ባሕር ፡ በታው ፡ የትካዜ ፡ የቁንቅ ፡ የመከራ ፡ መሬቱ ፡ ኰረኰንች ፡ አወይ ፡ አዚናራ ።

ዋንትም ፡ ለካ ፡ ኖርዋል ፡ በታው ፡ ልማደኛ ፡ ብለም ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ገብቶበት ፡ እስረኛ ፡ መቃብር ፡ ሆኖታል ፡ ለጀርመን ፡ ምርከኛ ።

ባንድ ፡ ወገን ፡ ባሕር ፡ ነው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ተራራ ፡ አዚያ ፡ መካከል ፡ ነው ፡ የአስረኞቹ ፡ ስፍራ ።

ባፈሳ ፡ ተይዘው ፡ እየተጐተቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወጥተው ፡ እየተንገላቱ ፡ ብዱር ፡ በበረሃ ፡ ታመው ፡ እየሞቱ ፡ ካለቁት ፡ መካከል ፡ በጣሊያኖች ፡ ቀንበር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ አንድ ፡ አስረኛ ፡ ነበር ። የተቸገረ ፡ ልው ፡ የሚያጽናናው ፡ ያጣ ፡ ያማውታል ፡ አሉ ፡ ዋንቁን ፡ ለባላንጣ ። እሱም ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ጣልያኑን ፡ ጠየቀው ፡

Scanned with CamScanner

የአገርህን ፡ ፖሊቲክ ፡ በጣም ፡ የምታውቀው ፡
እስቲ ፡ አንተ ፡ ንገረኝ ፡ ምሥጢሩን ፡ ልረዳ ፡
እግኙቶኛልና ፡ የነገር ፡ እንግዳ ።።
ለምን ፡ ወደቀብኝ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ፍዳ ?
አባቱ ፡ ማይጨው ፡ ላይ ፡ ተሠዋ ፡ ሕይወቱ ፡
ሦስቱ ፡ ወንድሞቼ ፡ ተይዘው ፡ በከንቱ ፡
በጣሊያን ፡ መትረየስ ፡ ተደብድበው ፡ ሞቱ ።።
አንደኛው ፡ ወንድሜም ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡
ሄዶ ፡ ይቀበላል ፡ የስደት ፡ መከራ ።።
በግራሲያኒ ፡ አደጋ ፡ ሰበብ ፡ የተነሣ ፡
እናቴ ፡ እስክ ፡ ቤቷ ፡ ነደደች ፡ ተጠብሳ ።።
ታስሬ ፡ አዚናራ ፡ ይኸው ፡ መጣሁ ፡ እኔ ፡
ሚስቱም ፡ እንደዚሁ ፡ ታስራለች ፡ ደናኔ ።።
ጣሊያኖች ፡ እነደ ፡ እኛ ፡ በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡
በወንጌል ፡ ተጠምቀው ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑ ፡
በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ የእኛ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡
አሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ነው ፡ የእነሱም ፡ ሕጋቸው ።።
በኢትዮጵያ ፡ ገብተው ፡ ሠራዊት ፡ ሲፈጁ ፡
የግፍና ፡ የቂም ፡ ጥቃት ፡ ሲያዘጋጁ ፡
እንዲህ ፡ በጭካኔ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ሲያፈሱ ፡
አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አቃጥለው ፡ ሲያፈርሱ ፡
በክርሲቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ሲጨክኑ ፡
ምነው ፡ በእግዜር ፡ መንገድ ፡ አያመዛዝኑ ?
ለክርስቲያን ፡ ሕዘብ ፡ ደም ፡ ጥቂትም ፡ አያገዘኑ?
የአረመኔ ፡ ሥራ ፡ እንዲህ ፡ እየሠሩ ፡
እሑድ ፡ ተሰብስበው ፡ ሰንበትን ፡ ሊያከብሩ ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉም ፡ ይሄዳሉ ፡
ካህናቶቻቸው ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ይላሉ ?
ያረመኔ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ እያዩዋቸው ፡
በሃይማኖት ፡ ሥልጣን ፡ አለማገዳቸው ።።
አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በእሳት ፡ ከማቃጠል ።።
ማላ ፡ እያፈረሰ ፡ ምርኩኖ ፡ ከመግደል ፡

ከመፍጀት ፡ በቀር ፡ ሕዝብ ፡ አርዶ ፡ ከመጣል ፡
አረመኔ ፡ ቢሆን ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ያመጣል
ጣልያኑ ፡ ፖሊቲክ ፡ በጣም ፡ ስላወቀ ፡
ገልጦ ፡ ተናገረ ፡ ምንም ፡ አልደበቀ ።።
እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፡ ለአገሬ ፡ አስረኛ ፡
ያውሮፓ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ባሁን ፡ ዘመን ፡ እኛ ፡
ልዩ ፡ ነው ፡ ግብራችን ፡ መች ፡ እንደ ፡ ጥንቶቹ ፡
ዱሮ ፡ በአውሮፓ ፡ አገር ፡ ጉበዝ ፡ ጉበዘቹ ፡
በሃይማኖት ፡ ፍቅር ፡ እየተቃጠሉ ፡
ለክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ሲሉ ፡
ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ ተራራ ፡ እያለፉ።።
ይሞቱ ፡ ነበረ ፡ እየተሰለፉ ።።
የመስቀል ፡ መለዮ ፡ ለብሶ ፡ እየዘመተ ፡
ከልዑላን ፡ ጋራ ፡ ንጉሥ ፡ እየሞተ ፡
ለክርስቶስ ፡ መቃብር ፡ ረግፎ ፡ እየወደቀ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ሰው ፡ አለቀ ።።
ዛሬ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተረስቷል ፡ ጨርሶ ፡
ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ በልቶ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ሰብሶ ፡
ያውሮፓ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መኖርን ፡ ወደደ ፡
የምኞትም ፡ ነገር ፡ እየባሰ ፡ ሄደ ።።
የቅምጥል ፡ ኑሮ ፡ ባውሮፓ ፡ ላይ ፡ መጣ ፡
ፈረሱ ፡ መኪና ፡ ቤንዚን ፡ የሚጠጣ ፡
አራት ፡ እግሩ ፡ ላስቲክ ፡ የሚጋልብበት ፡
ባቡር ፡ አሌውሮፕላን ፡ መሣሪያችን ፡ ብረት ፡
ብረትና ፡ ላስቲክ ፡ ቤንዚንና ፡ ጥጥ ፡
ባለመገኘቱ ፡ በአገራችን፡ ውስጥ፡
ሌላም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡
ባውሮፓ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ሞራሽ፡ ስለሌለ ፡
በድሎት ፡ በተድላ ፡ ለመኖር ፡ ዘንድሮ ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያሻናል ፡ ላሁን ፡ ዘመን ፡ ኑሮ ።።
ስለዚህ ፡ ግፍ ፡ በደል ፡ ተንኰል ፡ እያስፋፉን ፡
የሌላውን ፡ መንግሥት ፡ ወሰን ፡ እየገፉን ።።

Scanned with CamScanner

በእጥቂነትም ፡ ገብተን ፡ ሕዝቡን ፡ እያጠፋን ፡
ኃጢአቱ ፡ ክፉቱ ፡ በብዙ ፡ ተጽፎ ፡
ባለም ፡ መንግሥታት ፡ ፊት ፡ መንግሥቱ ፡ ተነቅፎ ፡
ራሱን ፡ አይችልም ፡ ተብሎ ፡ እንዲወረ ፡
ነውሩን ፡ እያበዛን ፡ ባሰት ፡ በፈጠራ ፡
የመጣን ፡ ነን ፡ አያልን ፡ ለሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡
ለሰው ፡ ሳንራራ ፡ ለቅሶ ፡ ሳንሰማ ፡
የሚያስፈልገን ፡ ነው ፡ ሀብቱን ፡ ልንቀማ ፡
የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ቀልድ ፡ ነው ፡ ጨዋታ ፡
ሕዝብ ፡ ከተገዛ ፡ እኛን ፡ አርጎ ፡ ጌታ ፡
አረመኔም ፡ ቢሆን ፡ ለደንጊያ ፡ የሚሰግድ ፡
ለጥቅማችን ፡ ስንል ፡ ይገባናል ፡ መወደድ ።
ቢያሻም ፡ እንሠራለን ፡ ለጣዖቱ ፡ መቅደስ ፡
ኃይለኛ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ ሕዝቡን ፡ ለመጨረስ ።
ክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ደም ፡ ሳናዝን ፡ ብናፈስ ፡
አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብናፈርስ ።
የባሰም ፡ ብንሠራ ፡ አይግረምህ ፡ ደግሞ ፡
የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ተረስቷል ፡ ፈጽሞ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ሰዎች ፡ ወዲያ ፡ ትተው ።
ለጥቅሙ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሕዝብ ፡ የሚራኮተው ፡
ዘዚህ ፡ ባሁን ፡ ዘመን ፡ የተፈጠራችሁ ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የደረሰባችሁ ፡
ግማሹ ፡ ተሰዶ ፡ ግማሹ ፡ ሽፍቶ ፡
ግማሹም ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ጋስሮ ፡ ተንገላቶ ፡
ምንም ፡ ሳያጠፋ ፡ ሰው ፡ በገዛ ፡ አገሩ ፡
በግፍ ፡ መገደሉ ፡ ቢግፍ ፡ መታሰሩ ፡
ለዚህ ፡ ነው ፡ እነሆ ፡ አሜር ፡ ነው ፡ ምሥጢሩ ።
እኛን ፡ ያደረገን ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ አረመኔ ፡
ይህም ፡ አዲስ ፡ ክፋት ፡ ይህ ፡ አዲስ ፡ ጭካኔ ፡
ያሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ይበላል ፡ ሥልጣኔ ።

የ ፀ ሐ ይ ፡ ባ ሕ ሪ ።

ይች ፡ የምንኖርባት ፡ መሬት ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀትን ፡ የምትቀበ
ለው ፡ ከፀሐይ ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደሚናገሩት ፡
የሌሎቹ ፡ ዓለሞችና ፡ እኛ ፡ የምንኖርባት ፡ መሬት ፡ አዘዟቸው ፡
በሥርዐት ፡ እንዲከናወንና ፡ እንዲካሄድ ፡ የምታደርገው ፡ ፀሐይ ፡ ናት ።
የከዋክብትን ፡ ትምህርት ፡ (አስትሮኖሚ ፡) የሚመረምሩ ፡ ሊቃው
ንት ፡ ፀሐይ ፡ አክሷ ፡ ጠንካራ ፡ ሆኖ ፡ የሚያብረቀርቅ ፡ ዙሪያ ፡ ክበ
ቧም ፡ በሚያንጸባርቅ ፡ አየር ፡ የተከበበ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። በመሬትና ፡
በፀሐይ ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ መቶ ፡ ጎምሳ ፡ ሚሊዮን ፡ ኪሎ ፡
ሜትር ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተገምቷል ። ለምሳሌ ፡ በአንድ ፡ ሰዓት ፡ ስድሳ ፡
ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የሚሄድ ፡ ባቡር ፡ ቢገሠግሥ ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡ ሰማ
ኒያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ፀሐይ ፡ ከለችበት ፡ ቦታ ፡ ይደርሳል ፡ እንደዚ
ሁም ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ፍጥነቱን ፡ ሳያጓድል ፡ ቢወረወር ፡ በሐያ ፡
ዓመት ፡ ይደርሰል ምንም ፡ እንኳ ፡ ለዓይናችን ፡ ክብ ፡ የሆነች ፡ ቅር
ጿ ፡ እንደ ፡ ሰፈድ ፡ የተዘረጋ ፡ መስሎ ፡ ቢታየን ፡ ይህ ፡ ከርቀት ፡
የተነሣ ፡ እየመሰለን ፡ የምናደርገው ፡ ያስተያየት ፡ ስሕተት ፡ ነው ።
ፀሐይ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ኳስ ፡ ድብልብል ፡ ነች ። ትልቅነቷም ፡ ከመሬት ፡
አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ሥስት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ። በቀድሞ ፡
ጊዜ ፡ ፀሐይ ፡ በመሬት ፡ ዙሪያ ፡ ትዞራለች ፡ ተብሎ ፡ ይታሰብና ፡ ይታ
መንበት ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ይልቁንም ፡ ኩፔርኒከ ፡ የሚበለው ፡
ሊቅ ፡ መርምሮ ፡ ያገኘውን ፡ ዕውቀት ፡ ማስረጃ ፡ እየሰጠ ፡ ከገለጸ ፡
ጀምሮ ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ የምትዞር ፡ መሬት ፡ መሆኗን ፡ የዓ
ለም ፡ ሊቃውንት ፡ ተቀብለውታል ። ፀሐይ ፡ መቀዝና ፡ ብርሃኗ ፡ ሳይ
ደክምና ፡ ሳይጓደል ፡ ይኖራል ። መቀዝም ፡ በውኃዎች ፡ ላይ ፡ ሲያ
ርፍ ፡ ወደ ፡ እንፋሎትነት ፡ እየለወጣቸው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡
በአየር ፡ ላይ ፡ እየተበታተኑ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ደመናነትና ፡ ወደ ፡ ዝና
ምነት ፡ እየተለወጡ ፡ ጤዛ ፡ ሆነው ፡ መሬትን ፡ እንዲያርጥቡ ፡ ዘንበ
ውም ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ እንዲያርሱ ፡ ያደርጋቸዋል ።

Scanned with CamScanner

የልቦና ፡ ሥልጣኔ ።

በባሕር ፡ ተንዝ ፡ በሰማይ ፡ በረረ ፡
መብረቅን ፡ ጠበጠ ፡ በአየር ፡ ተናገረ ፡
ነፋስና ፡ ውኃን ፡ ብረትና ፡ እንጨትን ፡
እንድም ፡ ሳይቀር ፡ ሁሉን ፡ ያለም ፡ ጠባያትን ፡
የሰው ፡ ልጅ ፡ ገዝቸው ፡ አገልጋይ ፡ አድርጎ ፡
ያሠራቸው ፡ ጅመር ፡ በጥበብ ፡ ስንጎ ።
ከፍ ፡ ከፍ ፡ አረገ ፡ የሀብቱን ፡ ደረጃ ፡
ክፉኛ ፡ ዘለቀ ፡ የጥበቡ ፡ እርምጃ ።
ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ለፍቶ ፡
ዋና ፡ ነገር ፡ ቀረው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡
አልቻለም ፡ ራሱን ፡ ሊያሻሽለው ፡ ከቶ ።
ከጥንቶቹ ፡ ሰዎች ፡ በባሕሪ ፡ አልበለጠም ፡
ልቡ ፡ ተሻሽሎ ፡ ገና ፡ አልተለወጠም ።
እንደ ፡ ብረት ፡ አርጎ ፡ እንዲ ፡ እንጨቱ ፡ መጠን ፡
የሰው ፡ ልጅ ፡ አልቻለም ፡ ራሱን ፡ ማሠልጠን ።
ወንድሙን ፡ ሊበድል ፡ ወንድሙን ፡ ሊቀማ ፡
ያዳም ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ተጠማ ።
ስለዚህ ፡ ሥልጣኔው ፡ እጅግ ፡ ቢበረታ ፡
የድካሙ ፡ ፍሬ ፡ የለውም ፡ ደስታ ።
ትቅበዘበዛለች ፡ አትረጋም ፡ ነፍሱ ፡
የቃሌል ፡ እርግማን ፡ ስላለ ፡ በራሱ ፡
ስንት ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ከተፈጠረ ፡
ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እየመረመረ ፡
ወደ ፡ ፍጹምነት ፡ ልቡን ፡ እየመራ ፡
ለምን ፡ ነው ፡ ራሱን ፡ በጥበብ ፡ ያልመራ ?
አይበቃም ፡ መታገል ፡ ከእንጨት ፡ ከብረቱ ፡
የሰው ፡ ልጅ ፡ ስለምን ፡ ይደክማል ፡ በከንቱ ?
መዶሻና ፡ ሞረድ ፡ ይፈልጋል ፡ ገና ፡
ድንጋይ ፡ ነው ፡ ብረት ፡ ነው ፡ የሰዎች ፡ ልቦና ።
በጣም ፡ ተቀጥቅጠ ፡ እየለሰለሰ ፡

ከጦድፍ ፡ ከልጠራ ፡ በጣም ፡ ከልታደሰ ፡
ወደ ፡ ሰው ፡ ልቦና ፡ ቢመጣም ፡ ደስታ ፡
የሚቀመጥበት ፡ ስለ ፡ ሴለ ፡ ቦታ ፡
ቶሎ ፡ እንደ ፡ ኖኅ ፡ ርግብ ፡ በሮ ፡ ይመለሳል ፡
በደስታም ፡ ፋንታ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ያለቅሳል ።
መዶሻው ፡ ተግማጽ ፡ ነው ፡ ሞረዱም ፡ መመከር ፡
የሚመራቢቸው ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ መፋቅር ፡
ሰው ፡ ወዲህ ፡ ትልቅ ፡ ነው ፤ ወዲህ ፡ ለከስካሳ ፡
በንድ ፡ ወገን ፡ መልአክ ፡ ነው ፤ በንድ ፡ ወገን ፡ እንስሳ ፡
ክልተመገደለት ፡ የእንስሳነቱ ፡ ዐመል ፡
ድከመ ፡ ጠከን ፡ ነው ፡ ለኑሮው ፡ ቢታገል ፡
አሳቡ ፡ ተቃንቶ ፡ ሥራው ፡ አይሳከም ፡
እንዲያው ፡ መጨመር ፡ ነው ፡ በድከም ፡ ላይ ፡ ድከም ፡
ክፋት ፡ ምቀኝነት ፡ ትዕቢትና ፡ ንፍገት ፡
ሞከኔና ፡ ሐሰት ፡ ተንኰልና ፡ ንቀት ፡
የጠባይ ፡ ወሰኮች ፡ የመንፈስ ፡ ቁሽሽ ፡
የልቡናን ፡ ሰላም ፡ አሳጡት ፡ መድረሻ ።
ሕዝብ ፡ እንዳያገኛት ፡ ጸጥታን ፡ ፈልጎ ፡
ዓለምን ፡ አረጓት ፡ የወዮታ ፡ ሽንጎ ፡
ሰውም ፡ ስንቱን ፡ ጎዘን ፡ በልቡ ፡ ሸሽጎ ።
ደስ ፡ አለው ፡ እንዲባል ፡ በሐሰት ፡ ይስቃል ፡
ጎዘንህ ፡ ይገለጥ ፡ ማታለል ፡ ይበቃል ፡
በጎዘን ፡ ከምትኖር ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡
ይልቅ ፡ ይሻልሃል ፡ መድኃኒት ፡ ብትሻ ፡
ሀብትህ ፡ ተከማችቶ ፡ ክብርህም ፡ ቢጋንን ፡
እንደ ፡ ናፖሊዮን ፡ ብታድግ ፡ አለመጠን ፡
ትልቅ ፡ ስም ፡ ባይገኝ ፡ ያንተን ፡ የመሰለ ፡
በልብህ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ደስታ ፡ እንደሌለ ፡
ሐሰት ፡ የሌለበት ፡ የሸፍጥ ፡ ክርክር ፡
ሴላም ፡ ሰው ፡ አይደለ ፡ ልቦናህ ፡ ይመስክር ።
መንፈስህ ፡ ይንጃበብ ፡ በፍቅር ፡ ደመና ፡
ሕሊናህ ፡ ይንፋሰስ ፡ በባሕረ ፡ ትሕትና ፡

Scanned with CamScanner

በዓ ብየዘራሙሰ ሥርና ፡ በየአቀበት ፡ ላይ ፡ የምንመለከታቸው ፣ አልፎአቸው የሚቀጥሉንጋጋቢዎች ፡ አጥንቶቻችን ፡ ሥጋችንን ፡ ለሸቅ ለወጥ ፡ ልንደርሚይዙት ፡ ሀሳቡ ፡ እነሱም ፡ የዳኑቱን ፡ ሸልር ፡ ደማሪው ፣ የሚይዙት ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ ሴሳ ፡ ለሰውና ፡ ለእንስሳ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፣ ጥቅም ፡ ይሰጣሉ ።

እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ተቋጥሮ ፡ የሚያልቀውን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ የፍጥረት ፡ ሠሉ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ፈጥሮ ፡ የያዘውና ፣ ንጉሥ ። ጌጅርሳ ፡ ንግሥ ፡ ሠሙ ፡ ሰጠው ፡ ልጅ ። እንዲጠቅመውና ፡ እንጂ ጀንሎገለውም ፡ ሳይሰጠው ። እንደሚታወቀው ፡ ሰው ። መሬት ፡ ብጣም ፡ ይጠንከሬ ፡ ብትሆን ፣ ዕፅ ፡ ለማረስ ፡ ታስቸግር ፡ ነበር ። ዶሮም ፣ በጣም ፡ ብልሃተኛ ፡ ብትሆን ፡ ፍሮ ፡ አጼ ፡ አሸዋ ፡ አያሰመጠች ፡ ለመሸሸም ። የማትችል ፡ ቅሆነች ፡ ነበር ። የእግዚአብሔርን ፡ ጥበብ ፡ በሁሉ ፡ በታ ፡ እናበሃያሉንነቱን ፡ ሠራ ፡ ሁሉ ፡ ሰንፍ ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ ከለሚታይ ፡ የተሰጠንን ፡ የተመልከትነት ፡ ዕውቀት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አንሠራበትም ። የእግዚአብሔርንም ፡ ሥዋበጡ ፡ አናደንቅበትም ፡ ለምሳሌ ፡ ዓይኖቻችን ፡ በአጅቻችን ፡ ሙስጥ ፡ ወደም ፡ በአ ግርቻችን ፡ ውስዋ ፡ ሆነው ፡ ቢፈጠሩ ፡ ኖሮ ፡ ምንይበጀን ፡ ፍርዋልንእን ጂት ፡ አድርገን ፡ እንሠራለን ፡ አንዴ ፡ ስ ፡ አድርገን ፡ እንሠራ ፡ ሳሙራችን ፡ ለኑሮአችንና ፡ ለደስታችን ፡ የሚያስፈልገንን ፡ ሁሉ ፡ ከምንመገበው ፡ ከእህልና ፡ ከውኃ ፡ ጀምሮ ፡ እስከምናገኘበት ፡ መር ቅ ፡ አልግዝ ፡ ድረስ ፡ በሚሔዩና ፡ ተሸክሚ ፡ በረከበት ፡ ታቋፍብልና ለችዘረከቲ ፡ ከምስጦት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ አያልቅም ፡ ከስንት ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ሰዎች ፡ ያርሱታል ፡ ይቆፍሩታል ፡ ዛግቋሳሉ ! ፍሬዋን ፡ ከመዝረፍ ፡ ሰላቋረጥም ፡ እስከ ፡ ለሰጠው ፡ ስዘታ ዋን ፡ አየዉመረችለት ፡ ቸሮዳለች ፡ እኔ ፡ ሳትቀንስም ። ተበላሠምሰሰ ሚልሩት ፡ ሰይ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሠሉ ፡ እያደረጉ ፡ እየወደቁ ፡ ልየራ ረሰ ፡ ይጠፍል ። መሬት ፡ ግን ፡ እስ ፡ ራሷ ፡ ዘመንዋ ፡ ሳሚቹ ፡ መጸው ፡ በገባ ፡ ቅጥር ፡ እያበበች ፡ እየለመለመች ፡ ስትታደስ ፡ ትና ራለች ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ መሬት ፡ የምትሰጠው ፡ እንደተደከመ ባት ፡ መጠን ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ሰ ፡ ሄክታር ፡ ብልሃተኛ ፡ ገበሬ ፡ ዘንድ ፡ አደራት ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ከሬ ፡ መሬት ፡ የሚሰጠውሰ ፡ ሩቤሳ ፣ ሳይሰጠው ፡ ኑሮ ፡ የበቃ ፡ ሲሆን ፡ በዘልሰው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ዘጠኙ ፡ ሄክታሩ ፡

የሥልጣኔው ፡ ታና ፡ የቸበከሰ ለዘንጦበ ፡ ሰጠሰለ ፡ ቅኋኖበ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያገኛል ፡ የጠፈጠሞ ፡ ዓዛ ፡ ንበል ፡ ጠሰ ፡ ጀመ ዛሬ ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቅንጣት ፡ ሰ ፡ ሰላሳ ፡ ቸበጥመቅ ፡ ጥበቡ ፡ ጉዶል ፡ ሰ ፡ ሰ ፡ ሰ ፡ ከሚጠጣ ፡ ዕን ፡ ጀኖ ፡ ። ለሰኑሰ ፡ ጥጦን ፡ ጠበ ፡ ሚኖች ፡ ሚኖሰበ ፡ ። ጋበ ፡ ሰ ፡ ሰ ፡ ሰ

በሚገባ፡ ከሠሩት ፡ ላንድ ፡ ሺህ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ኑሮ ፡ ደበ
ቃል ፡ ሲሉ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ፖለቲካ ፡ ኤክስፔርቶች ፡ ገምተውታል።
ይህም፡ መሬት ፡ ለሠራባት ፡ ሰው፡ ሀብት ፡ የሞላባት፡ መሆንዋን ፡
ያስረዳል።

የሐር ፡ ትል ::

ሐርን ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ ትል ፡ ነው ፤ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡
የሐር ፡ ትል ፡ ተብሎ፡ ይጠራል። የተገኘው፡ ክቺና ፡ አገር ፡ ነው፡
ይባላል፤ ኋላም ሚሲዮናውያን፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ወሰዱት። የሐር፡
ትል ፡ እንቁላሉ ፡ በግራም ፡ እየተሰፈረ፡ ይሸጣል፤ ሥራውን ፡ የሚ
ያውቁ፡ ሰዎች፡ እንቁላሉን ፡ የሚስማማውን ፡ ያየር፡ ሙቀት ፡ በመ
ጠን፡ ለጥተው፡ ሲያስቀምጡት፡ ትሎቹ፡ ይፈለፈላሉ፤ መልካቸውም ፡
መጀመሪያ፡ ጥቁር፤ ቀጥሎ ፡ ብጫ፡ ይሆንና፡ በመጨረሻ፡ ወደ፡ ነጭ ፡
ይለወጣል።

የጮመን፡ ትል፡ ሲመስል ፡ በተለይ ፡ ለእሱ ፡ ምግብ ፡ የሆነውን፡
ቅጠል፡ ይመገባል። ሰውነቱም ፡ ሲጠና ፡ በአፉ ፡ ሐሩን ፡ እየፈተለ፡
በሰውነቱ ፡ ዙሪያ ፡ አድርቶ ፡ ይጠቀለልበታል። ኋላም የሐሩ ፡ ልቃ
ቂት ፡ ሲሞላ ፡ የርግብ ፡ እንቁላል ፡ ያህላል። ከዚህ በኋላ ፡ ትሉ ፡
ወደ፡ ቢራቢሮነት ፡ ተለውጦ ፡ ይወጣል። ላላወቀ፡ ሰው፡ ግን የሞተ ፡
ይመስለል፤ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የተገኘው ፡ ሐር ፡ ሁላችሁም ፡ እንደ
ምታውቁት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨርቅና ፡ ለጥልፍ ፡ ሥራ ፡ ለብዙ ፡
ዓይነት ፡ ጌጥም ፡ እየሆነ ፡ ያገለግላል። ከሚሰጠውም፡ አገልግሎት ፡
ሁሉ፡ የሚበልጠው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመቅደስ፡ ጌጥ ፡ እየሆነ ፡
ስለሚሠራበት ፡ ነው፤ ላንድ ትል ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዕድል ፡ ሲሰ
ጠው፡ ይደንቃል። እግዚአብሔርን፡ በማክበርና ፡ በማመስገን ፡ ከመሥ
ራት ፡ የሚበልጥ ፡ ላንድ ፡ ፍጡር ፡ ምን ፡ አገልግሎት ፡ ይገኛል።

ዛሬና ፡ ነገ ::

ዛሬ ፡ ጊዜያችን ፡ ነው፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አለን ፡
ያለኘንን ፡ ሁሉ ፡ እናዝበታለን።
ብንጥርን ፡ ብናሾፍ ፡ ብንሠራ ፡ ብናብድ ፡

ቀኖችንን ፡ ትተን ፡ በግራ ፡ ብንሄድ ፡
እጅግ ፡ ብናበዛ ፡ ክፋትና ፡ ቧልታ ፡
ሁሉን ፡ ብንይዘው ፡ በሰፊ ፡ ቸልታ ፡
እሾሁን ፡ አበባ ፡ ጥፋትን ፡ ሙያ ፡ አርነ ፡
ልብ ፡ ቢተረጉም ፡ ሁሉን ፡ ወደ ፡ በጎ ፡
ሳንሸ ፡ ሳንወደው ፡ በግድ ፡ የሚመጣ ፡
ነገ ፡ የሚባለው ፡ አለብን ፡ ባላንጣ ።
ዛሬ ፡ ሰው ፡ አለሁ ፡ ቢል ፡ ነገ ፡ ግን ፡ ይሞታል ፡
ምንም ፡ ጉበዝ ፡ ቢሆን ፡ አይቀርም ፡ ይረታል ፡
ለተከታይ ፡ ትውልድ ፡ ለመሆን ፡ ሐተታ ፡
ሥራው ፡ ግን ፡ ይቅራል ፡ በታሪክ ፡ ገበታ ።
ነገ ፡ የጠቆረ ፡ ሥዉር ፡ ነው ፡ ምሥጢሩ ፡
ሊታወቅ ፡ አይችልም ፡ ተሸፍኗል ፡ ግብሩ ።
ነገ ፡ እንቆቅልሽ ፡ ነው ፡ ፍችውን ፡ ግን ፡ ያውቃል ፡
ትርጕሙን ፡ ለማግኘት ፡ ዓለም ፡ ይጨነቃል ።
ነገ ፡ ጉም ፡ ጭጋግ ፡ ነው ፡ ጥቅጥቅ ፡ ነው ፡ ጨለማ ፡
ሞው ፡ ያለ ፡ ዝምታ ፡ ድምፁ ፡ እማይሰማ ።
ምሥጢር ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያኖረው ፡ ሠዉሮ ፡
ሊዘልቀው ፡ የማይችል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አእምሮ ።
ነገ ፡ ጌታችን ፡ ነው ፡ ሰንጎ ፡ እሚገዛን ፡
ተቂጣጣሪ ፡ ነው ፡ የግብራችን ፡ ሚዛን ።
ነገ ፡ የማይሻር ፡ አዋጅ ፡ ነው ፡ ውሳኔ ፡
ፍርዱ ፡ እማይዛነፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስለኔ ።
ነገ ፡ ትልቅ ፡ ነሲብ ፡ የተሰወረ ፡ ዕጣ ፡
ሊያስቅ ፡ ወይ ፡ ሊያስለቅስ ፡ ድንገት ፡ የሚመጣ ።
ነገ ፡ ከባድ ፡ ጥላ ፡ ከትከሻ ፡ አንሥተው ፡
ቢጥሉት ፡ ቢሸሹት ፡ መከተል ፡ የማይተው ።
የፀሓይዋ ፡ ብርሃን ፡ ነገ ፡ ይታደሳል ፡
ቢጋና ፡ ክረምትም ፡ በመት ፡ ይመለሳል ፡
አንዱ ፡ ዓመት ፡ ያልፍና ፡ አንዱ ፡ ዓመት ፡ ይተክል ፡
ሰዓቱ ፡ መች ፡ አልቆ ፡ ጊዜ ፡ መች ፡ ይነክል ።

Scanned with CamScanner

ይሄዳል ፣ ይመጣል ፣ ዘመን ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ፣ ያዕቆብ ፣ ኖኅ ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ከሞተ ፣ ሰው ፣ ነው ፣ የማይመጣ ፣ ለዘላለም ፣ ሲኖር ፣ የሚፈጽን ፣ ፍፁ ፣ መከራ ፣ ከነገ ፣ በተቀር ፣ ጊዜያችን ፣ ነው ፣ ዘሬ ፣ በል ፣ ግብራችንም ፣ ደግሞ ፣ እሷ ፣ ምክርና ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ከሰሩት ፣ ሰውን ፣ ከጊዜ ፣ ጋር ፣ ሰዎች ፣ አዲስ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ መሰሉ ፣ እንደሚያየው ፣ ዛሬ ፣ ከነገ ፣ ሳምንቱ ፣ በወር ፣ ዓመት ፣ ሁለት ፣ ጊዜው ፣ በዘመን ፣ ግሥገሣ ፣ ያለፍንው ፣

ሲ ፣ ሊንግ ፣ ሽ ፣ የምትባለው ፣

ሆአንግ ፣ ሊንግ ፣ ሺ ፣ የምትባለው ፣ መታሰቢያዋ ፣ ሐውር ፣ ድረግ ፣ አንድ ፣ ዘጺ ፣ ሐር ፣ የሚፈትለውን ፣ ጠውን ፣ አስተውጹ ፣ ቢሆን ፣

ከዚህም ፣ የተነሣ ፣ ሲ ፣ ሊንግ ፣ ሺ ፣ ሐር ፣ ልብ ፣ አድርጋ ፣ ደሚሞቱ ፣ ነጠኝች ፣

ቀሞም ፣ ሰመሰርመርዋ ፣ የሐር ፣ ትሎች ፣ አንድ ፣ መሙ ፣ እያደቆች ፣ ለሽ ፣ ይህን ፣ አልፈዋል ፣ ለፀሐይ ፣ ከተደረገ ፣ ፈልቅቅ ፣ ፈለቀች ፣ ከቤቶቿን ፣ ከሾፕን ፣ መዓዛ ፣ ረቂቋ ፣ ንጹሕ ፣ የዉጠታች ፣ የመንፈስ ፣ አገርሽ ፣ በሰማንች ፣ ታማውቺናለሽ ፣ ነፍሱ ፣ ትሽቆጠቆጣለች ፣ ጠባይሽ ፣ ከገነት ፣ ጣዕሙ ፣ የትካዜ ፣

ለበያሞመልእክት ፣ ሁሉንም ፣ ሙሉ ፣ ከሆኑ ፣ ሁሉም ፣ ሁሉ ፣ ሁሉ ፣ ሁሉ

በሕሪሽን ፡ እንዲያውቀው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አእምሮ ፡
መመርመር ፡ አለበት ፡ የነፍስን ፡ ተፈጥሮ ።
ነፍስና ፡ ሙዚቃ ፡ ተመሳሳይ ፡ መንታ ፡
በሕፃያቸው ፡ ረቂቅ ፡ የምሥጢር ፡ ሁኔታ ፡
ቢሹት ፡ ያልተገኘ ፡ የመጡበት ፡ ቦታ ።
ያምላክ ፡ ጠባይ ፡ ናችሁ ፡ ሰማያዊ ፡ ጸጋ ፡
ምናችሁም ፡ አይደል ፡ ይህ ፡ ምድራዊ ፡ ሥጋ ።
ግዙት ፡ ነው ፡ ሰንሰለት ፡ ለናንተ ፡ ሥጋችሁ ፡
የምትቀጡበት ፡ ጥፋት ፡ አጥፍታችሁ ።
እግዜር ፡ የራሱ ፡ ዕለት ፡ ፈጣሪ ፡ ጌታችሁ ፡
ሥጋ ፡ ከሚባለው ፡ ከዚህ ፡ መጥፎ ፡ ዉታ ፡
ይለያያችኋል ፡ ቅጣቱን ፡ ሲል ፡ በታ ።
ለእናንተ ፡ ግዙት ፡ ነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡
ሞት ፡ ግን ፡ ይቅርታ ፡ ነው ፡ የሕይወት ፡ ፍጻሜ ።
የተፈረደባት ፡ ዋና ፡ ጥፋተኛ ፡
ነፍስ ፡ ነች ፡ ባለዕዳ ፡ የመሬት ፡ እስረኛ ።
ሙዚቃ ፡ እኅቷ ፡ ነች ፡ በመንፈሷ ፡ ቃና ፡
የተከተለቻት ፡ ልቢን ፡ ልታጥናና ።
ከሰማይ ፡ ተነሥተሽ ፡ እመሬት ፡ ድረስ ፡
ዘላለም ፡ ያለሽው ፡ በመመላለስ ፡
ድምፅሽ ፡ የሚያጽናናን ፡ ተልከ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡
እንዲነሽ ፡ ሙዚቃ ፡ የነፍሴ ፡ ንጀኛ ።
በመሄድ ፡ በመምጣት ፡ ምድርን ፡ ስትገ-በኚ ፡
ሰውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ የምታገናኚ ።

የ ሥራ ፡ ጥቅም ።

አንድ ፡ መምህር ፡ ከተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ አበበ ፡ የሚባለ
ውን ፡ ልጅ ፡ ለምሳሌ ፡ ሎተሪ ፡ ገዝተህ ፡ ዕጣ ፡ ወጥቶልህ ፡ ብዙ ፡
ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ብታገኝ ፡ ምን ፡ ታደርገዋለህ ? ብሎ ፡ ጠየቀው ።
አበበም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ አግኝቼ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ቸርነት ፡ ዕጣ ፡ ቢወጣልኝና ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ በገኝ ፡ ጥሩ ፡

ቤት ፡ ሠርቼ ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ ገዝቼ ፡ ጥሩ ፡ አቶሞቢል ፡ አስመ
ጥቼ ፡ እየተንሸረሸርኩ ፡ ዕድሜዬን ፡ ሙሉ ፡ ያለ ፡ አሳብና ፡ ያለ ፡
ድካም ፡ በደስታ ፡ እኖራለሁ ፡ ደግሞም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲያሸንፃ ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየሄድሁ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ሕዝቦችና ፡ ሥልጣኔዎች ፡ እየዞርሁ ፡ እገ-በኛለሁ ። ዘመዶቼንና ፡ ወዳ
ጆቼንም ፡ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ ደስ ፡ አሰኛቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

መምህሩም ፡ አገር ፡ ለመገ-ብኘትና ፡ ዘመዶችህን ፡ ወዳጆችህ
ንም ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ያለህ ፡ ምኞት ፡ መልካም ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡
ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚመኙትና ፡ እንደሚያደርጉትም ፡ ገንዘብ ፡ ማግ
ኘት ፡ የሚጠቅመው ፡ ሳይሠሩ ፡ ለመኖር ፡ መስለው ፡ የታየህን ፡ ሐሳብ ፡
አልወደድኩልህም ።

ሰው ፡ መሥራት ፡ የሚገባው ፡ ለገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ሲል ፡ አይምሰ
ልህ ። እግዚአብሔር ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ፍጥ
ረት ፡ ሲፈጥረው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ነው ። ነፍስን ፡ ተመ
ልከት ፡ ይነፍሳል ። ደመናን ፡ ተመልከት ፡ ይገሠግሣል ፡ የጅረት ፡
ውኃን ፡ ተመልከት ፡ ይፈሳል ። መሬትም ፡ ራሷ ፡ ትዘራሊች ። ነፋስ ፡
ባይነፍስ ፡ በሽታ ፡ ይመጣል ። ደመና ፡ ቢቀር ፡ ዝናም ፡ ይጠፋል ።
በዚህ ፡ ምክንያትም ፡ ራብና ፡ በሽታ ፡ ይመጣል ። የጅረት ፡ ውኃ ፡
ባይፈስ ፡ አገር ፡ ይጠማል ። መሬት ፡ በትዘር ፡ የፍጥረት ፡ ዓለሙ ፡
ሥርዐት ፡ ይቃወሳል ። ሰው ፡ ደግሞ ፡ ከእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠና ፡
የተከበረ ፡ በአርአያ ፡ ሥላሴ ፡ የተፈጠረ ፡ ፍጡር ፡ ስለሆነ ፡ ለክብ
ሩና ፡ ለማዕርጉ ፡ የተገባ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አለበት ። በመሬት ፡
ላይ ፡ በዓይኑ ፡ የሚያየውና ፡ በጆሮው ፡ የሚሰማው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ሥራን ፡ ያሳስበዋል ። በገዛ ፡ ሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የሕዋሳ
ቶችን ፡ ተግባር ፡ ቢያጸምጥ ፡ ሳንባው ፡ ሲታጠፍና ፡ ሲዘረጋ ፡
ልቡም ፡ ሲመታ ፡ ይሰማል ። ይህ ፡ የልቡና ፡ የሳንባው ፡ መንቀሳ
ቀስ ፡ ሲቆም ፡ ግን ፡ ይሞታል ። እንዲሁም ፡ ሰው ፡ ሥራን ፡ ጠልቶ ፡
በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይቆሞል ፡
(ይሞታል) እንስሳት ፡ ድንጋዮች ፡ እንጨቶች ፡ ይተኛሉ ፡ ያንቀላ
ፋሉ ። በዙሪያው ፡ ባለው ፡ መሬት ፡ ላይም ፡ ችግርና ፡ መከራ ፡
ረኃብና ፡ ብስጭት ፡ ይሠለጥኑበታል ። ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ ሲሠራ ፡ ግን ፡
እንስሳት ፡ ይነቃሉ ፡ እንጨትና ፡ ድንጋይም ፡ ይንቀሳቀሳሉ ። ማኅ

Scanned with CamScanner

ሙሉ ፡ ነቋጠ ፡ ሰጠ ፡ ሰጣ ፡ ሰፈረ ፡ ሰፈሰ ፡ ሰፋ ፡ ሰፍሰፈ ፡ ሰፍሰፍ ፡ ሰፍ ፡ ሰፍ ፡

ብቻ ፡ ይጉድለዋል ። ይሽውም ፡ የሐር ፡ ፈትል ፡ ስለሆነ ፡ እንደልግ
ድሽ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ እየለበሰሽ ፡ ለመናር ፡ ብትፈልጊ ፡ ልግ
ንም ፡ ሰው ፡ ሓትናፃሪ ፡ የሐር ፡ ትል ፡ ዘርና ፡ ለትሉም ፡ ምግብ ፡ የሆ
ነውን ፡ የፃፉን ፡ ዘር ፡ ይዘሽ ፡ እንድትመጭ ፡ ብለህ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገ
ሥቱ ፡ ልጅ ፡ እንድትነግራት ፡ ብሎ ፡ መልክተኛውን ፡ አዘዘው ።

ለዕልቲቱ ፡ የትሉንና ፡ የዛፉን ፡ ዘር ፡ በባርኔጣዋ ፡ ውስጥ ፡ ደብቃ ፡
መሰየችለት ። ያገሯን ፡ ጠረፍ ፡ ስታልፍ ፡ የተከለከለ ፡ ነገር ፡ ይዛ ፡
እንደሆነ ፡ በማለት ፡ ኬለኞች ፡ ፈተ኿ት ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ባርኔጣዋን ፡
ለማስወለቅ ፡ የደረረ ፡ ሰው ፡ አልተገኘም ። እነሆ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡
አኳሃን ፡ የቡክሐራ ፡ አገር ፡ ሰምቶ ፡ ሐር ፡ የሚፈትልውን ፡ ትል ፡
ዘርና ፡ ትሉም ፡ የሚበላውን ፡ የዛፍ ፡ ፍሬ ፡ በአገራቸው ፡ ውስጥ ፡
አንፀተው ፡ ሲያረቡና ፡ ሊተክሉ ፡ ቻሉ ። ልዕልቲቱም ፡ ይህን ፡
ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ የሚቻልበትን ፡ ብልሃት ፡ አስተማረቻቸው ።

ከከቦች ፡ ፕላኔቶችና ፡ ጅራታም ፡ ኮከቦች ።

ከዋክብት ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፈርጥ ፡ ፈሰው ፡ ሲያብረቀርቁ ፡
እናያለን ፡ በዓይናችን ፡ የምንመለከታቸው ፡ ከዋክብት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤
ተመልካቾች ፡ የሆኑ ፡ ሊቃውንት ፡ ሲናገሩ ፡ ከዋክብት ፡ በዓይናችን ፡
የምናያቸው ፡ ብቻ ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ ልንቈጥራቸውና ፡ ብዛታቸውንም ፡
ቈጥረን ፡ ልንደርስበት ፡ ዘንድ ፡ በልተሰነን ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የከ
ዋክብት ፡ ብዛት ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ የምንረዳው ፡
(ቴሌስኮፕ ፡) በሚባለው ፡ መነጽር ፡ ስንመለከታቸው ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

ከዋክብት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ብርሃንን ፡ ከራሳቸው ፡ እንደ ፀሐይ ፡
እያመነጩ ፡ የሚያበሩ ፡ ናቸው ፡ እነሱ ፡ ፀሓዮች ፡ ሆነውላቸው ፡
ብርሃንን ፡ የሚሰጡዋቸው ፡ ሌሎች ፡ ዓለሞች ፡ አሉ ፡ ለማለት ፡ ያስ
ደፍራል ። ለዓይናችን ፡ ያነሱ ፡ መስለው ፡ ቢታዩ ፡ ምክንያቱ ፡ በኛና ፡
በእሱ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ እያሌ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ እነሱስ ፡ ከፀሓይ ፡ የሚያንሱ ፡ ሆነው ፡ አይደለም ።

ከከዋክብት ፡ ሁሉ ፡ ለመሬት ፡ ቅርብ ፡ የሆነች ፡ ከከብ ፡ የመ
ድፍ ፡ ጥይት ፡ ፍጥነቱን ፡ ሳይቀንስ ፡ ወደ ፡ እሷ ፡ ቢወረወር ፡ እሷ ፡
ዘንድ ፡ ለመድረስ ፡ ሰባት ፡ ሽህ ፡ ዓመታት ፡ ያስፈልገዋል ፡ ብለው ፡

ሊቃውንት ፡ ገምተውታል ። ለፀሓይ ፡ ግን ፡ የገመቱት ፡ በሐያ ፡
ጎመት ፡ መሆኑን ፡ ስናስታውሰው ፡ በኛና ፡ በኩከቧ ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡
የርቀት ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ ያስረዳናል ።

የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ በሚያስደንቅ ፡ ፍጥነት ፡ ይፈነጠቃል ፤ በዚ
ህም ፡ አከፄድ ፡ ከፀሐይ ፡ ተነሥቶ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ በስምንት ፡ ደቂቃ ፡
ይደርሰል ፤ እንደዚሁም ፡ በአንድ ፡ ሰከንድ ፡ ውስጥ ፡ ስምንት ፡ ጊዜ ፡
መሬትን ፡ ይሙሉ ፡ ይዞራል ። የብርሃን ፡ ፍጥነት ፡ በዚህ ፡ ሲወሰን ፡
ከዕሎች ፡ ሁሉ ፡ ለኛ ፡ ቅርብ ፡ የሆነችው ፡ ከከብ ፡ ብርሃኗ ፡ ተነሥቶ ፡
እኛ ፡ ዘንድ ፡ ለመድረስ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያስፈልገዋል ፤ የሰሜን ፡
ኮከብ ፡ የምትባለው ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ከበስተ ፡ ሰሜን ፡ በኩል ፡ ሁል
ጊዜ ፡ በንድ ፡ ቦታ ፡ ረግታ ፡ የምትታየው ፡ ኮከብ ፡ ብርሃኗ ፡ እኛ ፡
ዘንድ ፡ እስኪደርስ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ይጓዛል ፤ በሷና ፡ በኛ ፡ መካከል ፡
ያለው ፡ ርቀት ፡ ከፀሓይ ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ።

ከንድ ፡ ቦታ ፡ ረግተው ፡ የቆሙ ፡ መስለው ፡ የሚታዩን ፡ ከዋክ
ብት ፡ ሁሉ ፡ እውነትም ፡ ከቦታቸው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡
እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ይታመን ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የሚዘ
ዋወሩ ፡ መሆናቸው ፡ አሁን ፡ በእርግጥ ፡ ታውቋል ። የሚዘዋወሩትም ፡
በሚያስደንቅና ፡ በሚያስፈራ ፡ ብርቱ ፡ ጠሆን ፡ ፍጥነት ፡ ነው ። ነገር ፡
ግን ፡ በጣም ፡ ሩቅ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ለኛ ፡ አይታወቁንም ።

ለመዘዋወሪያ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሥፍራ ፡ አለመጠን ፡ ሰፊ ፡ ከመ
ሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሥፍራ ፡ መለወጣቸውን ፡ ሰዎች ፡ ተመልክተው ፡ ለመ
ረዳት ፡ የሚችሉት ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ነው ። የከዋክብትን ፡
ሠራዊት ፡ ከመመልከት ፡ የተነሣ ፡ የሰው ፡ ነፍስ ፡ ብርቱ ፡ የሆነ ፡
የመደነቅ ፡ ስሜት ፡ ያድርባታል ፤ ይህንን ፡ ሰፊና ፡ ተቈጥሮ ፡ የማያ
ልቅ ፡ ዓለም ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ የሚያስደንቅ ፡
ኃይልና ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። እንደ ዋዛ ፡ ሁሉ ፡ "ሁኑ ፡" ሲላቸው ፡
ዓእዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከዋክብት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ውበትና ፡ ጥልቅነት ፡
ይዘው ፡ ከኢ ፡ ምንት ፡ ከለመኖር ፡ ወጥተው ፡ ተፈጠሩ ፤ በዚህም ፡
በሚያስደንቀው ፡ ፍጥነት ፡ በሚያደርጉት ፡ መዘዋወር ፡ የሚሄዱበ
ትን ፡ ቦታ ፡ እያመለከተ ፡ የሚመራቸው ፡ የአግዚአብሔር ፡ ሣት ፡
ነው ። በመዘዋወራቸው ፡ የሚሠሩትንም ፡ ሥራ ፡ የሚያውቀው ፡ እሱ ፡
ራሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ሙቅቅኝ ፡ ለመፈለግ ፡ ከሰማይ ፡ ተወር
ወረሙ ፡ ወደማገፀፍሮ ፡ ኢቅራቢይ ፡ ኢየደረሰ ፡ የሚሆዱ ተጅሐሰታም ፡
ከበሰች ፡ "የሚከለሱ ፡ አለ ፡ ከነሱም ፡ እንዳንዶቹ ፡ በፀሐይ ፡ ሙቃት
ሥርየሚያሰኝ" ፡ ነሙሰር ፡ "በሥርዐት ፡ መከናወኑን ፡ ሲቀትል ፡ ሌሎቹ
ሳጥዎወይሌሻ ፡ ከጠብ ፡ ዘንድ ፡ መ·ቀትን ፡ ለማግኘት ፡ ርቀው ፡ ይሄ
አቶ ፡ አይመለሱ ፡ ምም ። ፡ ቀበ ፡ ሚ ፡ ተ·ዘ ፡ ተመ ። ጋበ ፡ ሂወ
ሩጅሚ ፡ ለሆኑ ፡ የብርሃን ፡ ው·ጋጋን ፡ ስለሚያስከትሉ ፡ ከ ፡ እው ፡ ። ብሎ
መሰለ ። ፡ ይታየናል ፡ እንጂ ፡ ያንጸንዶቹም ፡ ርዝመቱን ፡ በመሬቶፍ ፡
በፎጴ ፡ መከከል ፡ ከለው ፡ ርቀት ፡ ይበልጣል ፡ ሲሉ ፡ ሊያውጁት ፡
ኮኛሉ ፡ ብሃ ፡ ዲ·መለበ ። ፡ ኮበባ ፡ ቲ·ሙ·ሙ ፡ ብሰ ፡ ዘሰ ፡ ዘሰ ፡
ድራም ፡ ከክብ ፡ በታየቱ ፡ ጊዜ ፡ መቀር ፡ ምልክት ፡ ነው ፡
አያሉ ፡ አንጻንጅ ፡ ለም ፡ ይናገራሉ ፡ ጸሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የማ
ይገባ ፡ ሐምልክት ፡ ነው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ለመለስ ፡ አምልክ
ቋዊ ፡ አስፈላጊ ፡ ኮንጅ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ እነዚህ ፡ ክቡቦች ፡ የሚዘዋወ
ፍሰ ፡ ብሚጪለብሱር ፡ ለፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ በወሰነው ፡ ሥርዐት ፡ ሙስዋ
አንኪፈጅመሳ ፡ ክዘዛቸው ፡ ሥረ ፡ ቋድኖ ፡ ልህእንጂና ፡ በዘንቱ ፡ ሉቋደ
ለምንሰማለት ፡ ጅዕፅኑ ፡ ምሥጢር ፡ ይለማግኘትሊ ፡ ሊቃመጣት ፡ ይሕ
ሸጪሉ ፡ ኖ ፡ ማ ፡ ዋ ፡ ሉ ፡ ። ፡ ኖ ፡ ሙ ፡ ሊ ፡ ። ፡ ማ ፡ ሚ ፡ ለ ፡ ። ፡ ኖ ፡ ሊ ፡ ኳ ፡ ኒ ፡ ሊ ፡ ። ፡ ጋ ፡ ኮ ፡
የዚዋክ ፡ ብሉት ፡ ብሉት ፡ በሣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ። ኡ ፡ ይሰ ፡
የሚሰው ፡ ፡ ፕላኔት ፡ ከነተከታዮቹ ፡ (ሳቴሊቶች ፡) ጋር ፡ መኖሩን ፡
ለዓለም ፡ ተገልጠ ፡ ያስታወቁ ፡ ሄርሺል ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሊቀ
ከዋክብት ፡ ተመራማሪ ፡ ባንደ ፡ ተርታ ፡ ቲከማች ፡ ። ፡ ያሚገኙት ፡ ከዋ
ክብ ፡ ብዛታቸውን ፡ ለሚወቁ ፡ ብዙ ፡ ረገው ፡ ሮሞርሞሩስ ፡ ከአሜሽ
ሚለውስ ። በለይ ፡ ከእንደ ፡ ቁጠሩ ፡ ተናገርዋል ፡ በዓጀዉ ፡ ብቻ ፡
ዎች ። ከከዋክብት ፡ ብዛት ፡ ጋር ፡ ሲነጻጸር ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ።
ሰው ፡ ሲ·ሙ ፡ ሳ ፡ ። ፡ ሙ ፡ ሰ ፡ ሰ ፡ ሰ

ፈ ፡ ኪያንግ ።

በጥንት ፡ ዘመን ፡ በቺና ፡ አገር ፡ ፈ ፡ ኪያንግ ፡ የሚባል ፡ ግርማ ፡ ባለው ፡ ክብርና ፡ በብዙ ፡ ደስታ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። እሱም ፡ በያይነቱ ፡ ሽቶ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፤ ለጆሮ ፡ ደስ ፡ የሚ ያሰኝ ፡ በያይነቱ ፡ ዘፈን ፤ ጊዜ ፡ የሚያሳልፍ ፡ በያይነቱ ፡ የሚ ይወድ ፡ ነበር ። የወጥ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓይነት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምግብ ፡ ያዘጋጃል ። የድግ ፡ መምህራንም ፡ ንጉሡ ፡ ሰምቶ ፡ የሚያውቀውን ፡ ዘፈን ፡ ለማሰማት ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ አዲስ ፡ አዲስ ፡ ዜማ ፡ ይፈጥራሉ ። ፈ ፡ ኪያንግ ፡ ከልጅነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ደስታ ፡ ይኖራል ። ኋላ ፡ ግን ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ደስታ ፡ በጣም ፡ አታከተው ። ለጆሮ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ አድርገው ፡ ሊቃውንት ፡ የደከሙበት ። ዘፈን ፡ ለዛ ፡ የሌለው ፡ ጫጫታ ፡ ሆነበት ። ባለሙያ ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ የለቆበትም ፡ ወጥ ፡ ሁሉ ፡ ጨው ፡ እንደሌለው ፡ አልጫ ፡ ሲቀምሰው ፡ ጣም ፡ የማያገኝበት ፡ ሆነ ። በዘንዶ ፡ እምሳል ፡ ተጌጠ ፡ የተ ሠራውን ፡ የሚተኛበትን ፡ የወርቅ ፡ አልጋ ፡ ሁልጊዜ ፡ ማየት ፡ ሰለቸው ። ለኑሮው ፡ ደስታ ፡ የሚያገኝበትን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ በመፈለግ ፡ ታላላቅ ፡ ሶርኔት ፡ አድርጎ ፡ ብዙ ፡ ከተማዎች ፡ አፍርሶ ፡ ዘረፈ ፤ የጠ ላቱም ፡ አገሮች ፡ ሲቃጠሉ ፡ ወደሰማይ ፡ የሚነሣውን ፡ የእሳት ፡ ነበ ልባል ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኝ ፡ አበበ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መሰልቸት ፡ ሊያስወግድለ ትና ፡ ሊያስታግሥለት ፡ አልቻለም ። ሊቃውንት ፡ የጻፉዋቸውን ፡ መጻ ሕፍት ፡ እያስፈለገ ፡ አነበበ ፡ በውስጣቸውም ፡ ብዙ ፡ ምክር ፡ ሲያ ገኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ላልቡ ፡ ማረጋጊያ ፡ የሚሆን ፡ ለሱ ፡ የሚስማ ውን ፡ ነገር ፡ አላገኘባቸውም ።

ለሕይወቱ ፡ ሸክም ፡ ሆኖ ፡ የተጫነው ፡ ይህ ፡ የታከተው ፡ መ ፈስ ፡ እየበረታ ፡ ሲሄድ ፡ መራራ ፡ ስሜት ፡ በልቡ ፡ እደረበት ። ሰው በዚህ ፡ ዓለም ፡ ደስታን ፡ ሊያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚ ገባው ፡ ለማወቅ ፡ በጣም ፡ ደከመ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ መሞትንና ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ መገላገልን ፡ መርጠ ፡ ቁርጠኛ ፡ ፈቃድ ፡ አደረገ ። መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሊሞት ፡ አሰበ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሞከረው ፡ ጊዜ ፡ ሊደፍር ፡ አልቻለም ።

ፈ ፡ ኪያንግ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ጭት ፡ ሲሆን ፡ ከመኝታ ፡ ቤቱ ፡ አየገባ ፡ ጨውን ፡ የሚላጨው ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ ጨ ፡ ላጪው ፡ የዕለት ፡ ተግባሩን ፡ ሊፈጽም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ገባ ። ንጉሡም ፡ ጨውን ፡ ሲላጭ ፡ ምላጭ ፡ በጉንጭ ፡ ላይ ፡ ሲሄድ ፡ ጨ ፡ ላጪው ፡ ካንገቱ ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ምላጩን ፡ ጥቂት ፡ ወደታች ፡ ገፋ ፡ ቢያደርገው ፡ አታካች ፡ ከሆ ነው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ እንደሚገላግለው ፡ በልቡ ፡ አሰበ ። ስለዚህ ፡ ባጠገቡ ፡ የነበሩትን ፡ የልፍኝ ፡ አሽከሮቹን ፡ እንዲወጡ ፡ አዘዘና ፡ ጨ ፡ ላጪውን ፡ እንዲህ ፡ አለው ። የዓለም ፡ ኑሮ ፡ ሰል ችቶኝ ፡ ለመሞት ፡ ፈቅጃለሁና ፡ ይህን ፡ እንድትፈጽም ፡ አንተን ፡ አዝዣሃለሁ ። ጨ ፡ ላጪውም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በድ ንጋጤ ፡ ወድቆ ፡ ተንበረከከ ። ንጉሡም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ የትእዛዙን ፡ ቃል ፡ ቀጠለ ።

“ አዲሷ ፡ ጨረቃ ፡ ከመወለዷ ፡ በፊት ፡ አንተው ፡ በፈቀድከው ፡ ቀን ፡ ለኔ ፡ ሳታመለክተኝ ፡ ጨሜን ፡ ስትላጭ ፡ እንድታርደኝ ፡ አዝ ዣሃለሁ ። ” ሽማግሌው ፡ በፍርሃት ፡ ተንቀጠቀጠ ። ይህ ፡ የማይደረግ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሊመልስ ፡ ሲቃጣ ፡ ንጉሡ ፡ ባይኑ ፡ ነስገሠጻው ፡ አፉን ፡ ዘግቶ ፡ ግንባሩን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ደፍቶ ፡ “ የሰማይ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፤ ፈቃድህ ፡ የተፈጸመ ፡ ይሁን ፡ ” ሲል ፡ በመንተባተብ ፡ መለሰ ። ምላጩንም ፡ አጥሮ ፡ የኋሊት ፡ እየተራመደ ፡ ከጌ ፡ ኪያንግ ፡ የመኝታ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ።

ማንኛውንም ፡ ትእዛዝ ፡ ቢሰጥ ፡ ሰምቶ ፡ ከመፈጸም ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡ ሊታወመው ፡ ዘንድ ፡ ስማናቸውም ፡ ለምድራዊ ፡ ፍጡር ፡ ያልተፈቀደለት ፡ በመሆኑ ፡ ንጉሡ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በጠረጴዜቱ ፡ ላይ ፡ የፈሰሱትን ፡ የወርቅና ፡ ያልማዝ ፡ ጌጦች ፡ እየተ መለከተ ፡ ዕድሉን ፡ በማመስገን ፡ ጊዜውን ፡ አሳልፎ ፡ ዋለ ፡ በማግ ሥቱ ፡ እንደተለመደው ፡ ጨ ፡ ላጪው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ የመኝታ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ ፈ ፡ ኪያንግ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ትላንት ፡ የሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ዛሬ ፡ እንደማይፈጸም ፡ ቢያውቀው ፡ ከእ ንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ሕይወቱ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ ዓይኑ ፡ ከምላጩ ፡ ጋር ፡ ይንከራተት ፡ ነበር ።

Scanned with CamScanner

አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ጸም ፡ ላጭው ፡ ለሥራው ፡ ጢት ፡ ጢት ፡ በመጣ ፡ ቁጥር ፡ ፤ ኪያንግ ፡ ጊዜውን ፡ በሚንቅና ፡ በሥጋት ፡ አሰለፈ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ የንጉሡ ፡ ትክዜ ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ፡ ምት ፡ እንዳንገበበት ፡ ያስብ ፡ ነበርና ።

በቀን ፡ በቀኑ ፡ ንጉሡ ፡ ጠልቶት ፡ የነበረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እየወደደ ፡ መሄድ ፡ ጀመረ ። ባጠገቡ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሊያያቸው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የተለያቸው ፡ ያህል ፡ በናፍቆ ፡ ትና ፡ በመውደድ ፡ ዓይን ፡ ይመለከታቸው ፡ ነበር ። በዙሪያውም ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አዲስ ፡ ሆነበት ።

በቀን ፡ በቀኑ ፡ የሚያዘጋጁለት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምግብ ፡ ተበልቶ ፡ ዘፈኑም ፡ ተሰምቶ ፡ የማይጠገብ ፡ ሆነለት ። የቀረው ፡ ቀርቶ ፡ ከውሜ ፡ ሲመሡ ፡ የሚሰማው ፡ የወሮች ፡ ጫጫታ ፡ እንኳ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ዜማ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። የፀሓይም ፡ ብርሃን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የተሰጠ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ የሚገኝበት ፡ ጸጋ ፡ እንደሆነ ፡ ታወቀው ። ስለዚህ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በሚያየውና ፡ በሚሰማው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ሲውል ፡ ሕይወቱን ፡ የጠላትን ፡ ያህል ፡ ወደጻት ፤ ጻሩ ፡ ግን ፡ በመሸ ፡ ቁጥር ፡ ሲኦጋ ፡ ጸም ፡ ላጭው ፡ መምጣ ቱን ፡ ማሰብ ፡ የቀኑን ፡ ደስታ ፡ ሁሉ ፡ የሚያደፈርስበት ፡ ሥጋት ፡ ሆነበት ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ጢት ፡ ጸም ፡ ላጭው ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ ከንጉሡ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ትልቁኑን ፡ ለመፈጸም ፡ ምላውን ፡ ግን ፡ ሊለው ፡ የታሳ ፡ መሰለ ። ንጉሡም ፡ „ተው ፡ "ለግለት ፡ ሊመህ ፡ ሲል ፡ ጸም ፡ ላጭው ፡ ሳያደርገው ፡ ስላሰፈ ፡ ንጉሡም ፡ ሊናገረው ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ መለሰው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዚያች ፡ ደቂቃ ፡ መራራነት ፡ ከፒ ፡ ኪያንግ ፡ መንፈስ ፡ ሳትለይ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ስታስጨንቀው ፡ ዋለች ። የዚያን ፡ ቀንም ፡ ጸሙን ፡ ተላ ጭቶ ፡ በደኅና ፡ በተኙ ፡ ጊዜ ፡ ከጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ እድ ርጎ ፡ ከተመለሰበት ፡ ቀን ፡ የበለጠ ፡ ደስታና ፡ ኩራት ፡ ተሰማው ። ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ለመሞት ፡ የነበረውን ፡ ፈቃድ ፡ ከመገለሉ ፡ ጨርሶ ፡ አስወገደ ። የሰጠውንም ፡ ትእዛዝ ፡ መልሶ ፡ መሻር ፡ ነውሩ ፡ ስለሆነበት ፡ ጸም ፡ ላጭው ፡ የዚያኑ ፡ ዕለት ፡ እንዲገደል ፡ አዘ ፡

ቡ ሶ ል ።

በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ መርከቦች ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሲጓዙ ፡ መን ገድ ፡ እንዳይጠፋቸው ፡ ከመሬት ፡ ጠረፍ ፡ በጣም ፡ ሳይርቁ ፡ መጓዝ ፡ ነበረባቸው ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በአሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የቡሶል ፡ ዘዴ ፡ ተገኘ ። ቡሶል ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ሰዓት ፡ ያለ ፡ መሣ ሪያ ፡ ሆኖ ፡ መርፌው ፡ ሁልጊዜ ፡ ሰሜንን ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሰዎች ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያሉ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሩቅ ፡ መንገድ ፡ ለመሄድ ፡ ቻሉ ። ይህን ፡ መሣሪያ ፡ ሲያገኙ ፡ መርከባቸው ፡ በማናቸውም ፡ ሰፈ ፡ ውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ ቢጓዝ ፡ መንገዳቸውን ፡ ለመ ክተልና ፡ ያሉበትን ፡ ቦታ ፡ ለማወቅ ፡ የሚቻላቸው ፡ ሆነ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመርከብ ፡ ተጉዞ ፡ ከአንዱ ፡ ዓለም ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ለመዘዋወርና ፡ ውቅያኖሶችን ፡ ወንጥቆ ፡ ለማለፍ ፡ ያልታወቁትንም ፡ አገሮች ፡ ለማግኘት ፡ የተቻለው ፡ በአሥራ ፡ አም ስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ነው ። የፖርቱጋል ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ተጉዘው ፡ የመልካም ፡ ተስፋ ፡ ክፕ ፡ የተባለውን ፡ አልፈው ፡ የሕንድ ፡ ባሕሮችን ፡ ተሻገሩ ። የእስፓኛ ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ ክርስቶፍ ፡ ክሎምብ ፡ በሚ ባለው ፡ ሰው ፡ መሪነት ፡ መጀመሪያ ፡ ፈጊዜ ፡ ተጉዘው ፡ የአሜሪካንን ፡ አገር ፡ አገኙ ። በዚያም ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ለብዙ ፡ ሰፊ ፡ አገሮች ፡ ገዢዎች ፡ ለመሆን ፡ ቻሉ ።

በአሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ መርከብ ፡ በእ ንፋሱ ፡ ኃይል ፡ መሄድ ፡ ጀመረ ፡ ይህም ፡ ታላቅና ፡ አዲስ ፡ የሥ ልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ያጠ ። ክዚያም ፡ ከኋላ ፡ ብዙ ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ተቻለ ። የባሕር ፡ መንገድና ፡ የመንገድ ፡ ርቀት ፡ የሰ ዎችን ፡ እርምጃ ፡ ሲያሰናክሉ ፡ በመኖራቸው ፡ የነበረው ፡ ችግር ፡ ተወገደ ። አህጉሮችም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በጥቂት ፡ ጊዜና ፡ ድካም ፡ በሌለበት ፡ ሁኔታ ፡ ለመገናኘት ፡ ቻሉ ።

Scanned with CamScanner

እብነ ፣ አድግስ ።

የቡሶል ፣ መርፈ ፣ ሁልጊዜ ፣ ሰሚንን ፣ የምታመለክትበት ፣ ምክንያት ፣ እብነ ፣ አድግስ ፣ (ኤማንት) ስላለባት ፣ ነው ። እብነ ፣ አድግስ ፣ በፈረንሳዊ ፣ ቋንቋ ፣ ኤማንት ፣ በእንግሊዝ ፣ ቋንቋ ፣ ማኘት ፣ የሚባለውም ፣ ብረትን ፣ ለመሰብ ፣ ልዩ ፣ የኤሴክትሪክ ፣ ጠባይ ፣ ያለው ፣ „ማኜቲስም ፣" የሚባል ፣ ማዕድን ፣ ነው ። ማኜቲስም ፣ የተባለበትም ፣ ምክንያት ፣ ይህ ፣ ማዕድን ፣ መጀመሪያ ፣ የተገኘው ፣ በትንሹ ፣ እስያ ፣ አገር ፣ ክፍል ፣ ውስጥ ፣ በምትገኘው ፣ ጥንት ፣ ማኜዚ ፣ ዛሬ ፣ ማኒሳ ፣ በምትባለው ፣ ከተማ ፣ አጠገብ ፣ ስለሆነ ፣ ነው ።

አሱም ፣ ማዕድን ፣ በሚገኝባቸው ፣ ቦታዎች ፣ ብረታ ፣ ብረት ፣ አለ ፣ እንደሆነ ፣ ለማወቅ ፣ በጣም ፣ ይረዳል ። ሐኪሞችም ፣ የብረት ፣ ስንጣሪ ፣ በሰው ፣ ዓይን ፣ ውስጥ ፣ በገባ ፣ ጊዜ ፣ ያወጡበታል ።

ካ ሎ ሪ ክ ።

ካሎሪክ ፣ ማለት ፣ ሙቀትን ፣ የሚሰጥ ፣ በሚሠራው ፣ ሥራ ፣ ብቻ ፣ በመገለጡ ፣ የታወቀ ፣ ሥነ ፣ ፍጥረቱ ፣ ግን ፣ ተመርምሮ ፣ ያልታወቀ ፣ በጣም ፣ ረቂቅ ፣ የሆነ ፣ (ፍሉዊድ) ነው ። በዊሩ ፣ ካሎሪክ ፣ ማለት ፣ ሙቀት ፣ ማለት ፣ ነው ። ለምሳሌ ፣ ውኃ ፣ ከእሳት ፣ ላይ ፣ ሲጣድ ፣ እንዲሞቅና ፣ እንዲፈላ ፣ የሚያደርገው ፣ ካሎሪክ ፣ ነው ፣ እንዲሁም ፣ ደግሞ ፣ ካሎሪክ ፣ ማነኛውም ፣ አካል ፣ ጉን ፣ እንዲወጮር ፣ የሚድረግ ፣ ጠባይ ፣ አለው ። ለምሳሌ ፤ ብረት ፣ በጋለ ፣ ጊዜ ፣ ይረዝማል ፣ ይህን ፣ የሚያደርግ ፣ ካሎሪክ ፣ ነው ።

በውኃ ፣ ውስጥ ፣ ካሎሪክ ፣ ይገኛል ። ካሎሪክ ፣ ከሌለበት ፣ ግን ፣ ውኃ ፣ በረዶ ፣ ሆኖ ፣ ይጋገራል ። የካሎሪኩ ፣ መጠን ፣ ያነሰ ፣ ሲሆን ፣ ውኃው ፣ ይቀዝቅዛል ፤ ሲበዛ ፣ ግን ፣ ውኃው ፣ ወደ ፣ እንፋሎት ፣ እስኪ ለወጥ ፣ ድረስ ፣ እየሞቀና ፣ እየፈላ ፣ ይሄዳል ።

ካሎሪክ ፣ በየአንዳንዶቹ ፣ አካላት ፣ ላይ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ሥራ ፣ ይሠራል ። ለምሳሌ ፣ አሸዋን ፣ መስታውት ፣ ያደርገዋል ፤ አፈርን ፣ ሸክላ ፣ ያደርገዋል ።

ከዚህ ፣ ሌላ ፣ ደግሞ ፣ ልምላሴ ፣ አንዱን ፣ የጋለ ፣ ብረት ፣ በአንደኛው ፣ ቀዝቃዛ ፣ ብረት ፣ ላይ ፣ ቢያስቀምጡት ፣ የሁለቱ ፣ ብረቶች ፣ ሳለት ፣ እኩል ፣ እስኪሆን ፣ ድረስ ፣ በጋለው ፣ ብረት ፣ ውስጥ ፣ የሚገኘው ፣ ካሎሪክ ፣ ወደ ፣ ቀዝቃዛው ፣ ብረት ፣ ይተላለፋል ። ይህም ፣ አንድ ፣ ልዩ ፣ ጠባይ ፣ ነው ።

ነገር ፣ ግን ፣ አካሎች ፣ ሁሉ ፣ ሙቀትን ፣ እኩል ፣ ስለማይቀበሉ ፣ ይህ ፣ ጠባይ ፣ በሁሉም ፣ ላይ ፣ ትክክል ፣ ሊፈጸምባቸው ፣ አይችልም ። ለምሳሌ ፣ ብረትን ፣ እሳት ፣ ውስጥ ፣ ቢጨምሩት ፣ ይግላል ፣ እንጨትን ፣ ግን ፣ ሲጨምሩት ፣ ይነዳል ፣ እንጂ ፣ አይግልም ። ስለዚህ ፣ ሙቀትን ፣ የሚቀበሉና ፣ የማይቀበሉ ፣ አካሎች ፣ አሉ ።

እንደዚሁ ፣ ሁሉ ፣ እብነ ፣ በረድን ፣ በእጅ ፣ ቢነኩት ፣ ይቀዘቅዛል ፤ ጨርቅን ፣ ግን ፣ ቢነኩት ፣ አይቀዘቅዝም በሁለቱ ፣ ውስጥ ፣ ያለው ፣ የቅዝቃዜ ፣ መጠን ፣ ግን ፣ ሲመዘን ፣ እኩል ፣ ነው ። እብነ ፣ በረድ ፣ መቀዝቀዙ ፣ በእጃችን ፣ ስንነካው ፣ በኛ ፣ ውስጥ ፣ የሚገኘውን ፣ ካሎሪክ ፣ ስለሚወስድ ፣ ስለሚቀበል ፣ ነው ። ጨርቅ ፣ ግን ፣ ካሎሪክ ፣ አይቀበልም ።

ቴርሞሜትር ።

ቴርሞሜትር ፣ ማለት ፣ የሙቀት ፣ መጠን ፣ የሚለካበት ፣ ትንሽ ፣ መሣሪያ ፣ ነው ፤ ወይኑቱም ፣ ከታች ፣ ድብልብል ፣ ሆኖ ፣ በውስጡ ፣ ባዚቃ ፣ ወይም ፣ አልኮል ፣ የሚገኝበት ፣ የብርጭቆ ፣ አገዳ ፣ ነው ።

ባዚቃ ፣ ወይም ፣ አልኮል ፣ ሙቀት ፣ ሲያገኛቸው ፣ ይቀልጣሉ ፣ እንዲሁም ፣ ብርድ ፣ ሲሆን ፣ ይጨበጣሉ ፣ ከዚህም ፣ የተነሣ ፣ ለመቀት ፣ ታዛዦች ፣ በመሆናቸው ፣ ለቴርሞሜትር ፣ መሣሪያ ፣ ያገለግላሉ ። የቴርሞሜትር ፣ ሚዛን ፣ በመቶ ፣ ደረጃ ፣ (ደግሬ ፣) ተከፍሏል ። ከታች ፣ የመነሻው ፣ ዜሮ ፣ (0) የበረዶን ፣ ቅዝቃዜ ፣ ሲያስረዳ ፣ የላይኛው ፣ የመጨረሻው ፣ መቶ ፣ (100) የፈላ ፣ ውኃን ፣ ሙቀት ፣ ልክ ፣ ያመለክታል ። የቴርሞሜትር ፣ መሣሪያ ፣ ሰው ፣ በታመመ ፣ ጊዜ ፣ የሙቀቱ ፣ (የትኩሳቱ) መጠን ፣ መውጣቱንና ፣ መውረዱን ፣ ለመረዳት ፣ ስለሚጠቅልበት ፣ ለሕክምና ፣ ሥራ ፣ በጣም ፣ ይረዳል ።

Scanned with CamScanner

ሺ ሚ ።

ሺሚ ፡ ማለት ፡ ማነኛውንም ፡ አካል ፡ እየመረመረ ፡ በውስጡ ፡ የሚገኙትን ፡ ጠባያት ፡ በየመልካቸው ፡ የሚለይና ፡ የሚያጠና ፡ ትምህርት ፡ ነው ። ይህም ፡ ትምህርት ፡ እነዚህን ፡ ጠባያት ፡ እየመረመረና ፡ እያጠና ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚቀላቀሉበትንና ፡ የሚቀመሙበትን ፡ ወይም ፡ የሚለያዩበትንና ፡ የሚነጣጠሉበትን ፡ መንገድ ፡ መለማና ፡ ግኝት ፡ ዓይነተኛ ፡ ሥራው ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ተማሪዎች ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ በጥቁር ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ የሚጽፉበት ፡ የኖራ ፡ እርሳስ ፡ (ቾክ) በሺሚ ፡ ትምህርት ፡ ሊመረመር ፡ በኖራና ፡ በአሲድ ፡ ካርቦኒክ ፡ የተቀመመ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል። አሲድ ፡ ካርቦኒክ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ በአክሲጊንና ፡ በካርቦን ፡ የተቀመመ ፡ አካል ፡ ነው ። ኖራ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ በአክሲጊንና-በካልሲዩ የተቀመመ ፡ አካል ፡ ነው ። በድምሩም ፡ የኖራ ፡ እርሳስ ፡ (ቾክ)የተቀመመው ፡ በአክሲጊን ፡ በካርቦንና ፡ በካልሲዮ ፡ ነው ።

ሺሚና ፡ ፊዚክ ፡ የአካላትን ፡ ጠባያት ፡ መመርመር ፡ ልውለቱም ፡ ሥራቸው ፡ በመሆኑ ፡ በዚህ ፡ ይመሳሰላሉ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የፊዚክ ፡ ሥራ ፡ የአካላትን ፡ ጠባይ ፡ ከሚለውጠው ፡ ምክንያት ፡ ኤልፎ ፡ አይሄድም ፤ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይቆማል ። ሺሚ ፡ ግን ፡ አክላትን ፡ የሚለዋወጧቸውን ፡ ምክንያቶች ፡ እየመረመረ ፡ ጠባያቸውን ፡ ከለወጠ ፡ በኋላም ፡ አዋጅ ፡ ይሰጣቸዋል ።

ምሳሌ ፤ ብረት ፡ በጋለ ፡ ጊዜ ፡ ካሎሪክ ፡ ይይዛል ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አክል ፡ ይጨምራል ። . . . . ይህ ፡ ማስተዋል ፡ የፊዚክ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ሙቀት ፡ ብረትን ፡ ሲያግለው ፡ አያበላሸውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ብረትን ፡ ውርጭ ፡ ላይ ፡ ቢጥሉት ፡ ይዝጋል ፤ ዝገቱም ፡ ለብረቱ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ስለሚሰጠውና ፡ ስለሚያበላሸው ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ የሺሚን ፡ ጉዳይ ፡ የሚነክ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ዝገት ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ከአክሲጊንና ፡ ከብረት ፡ የተቀመመ ፡ አክል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ ጨው ፡ ቢጨምሩበት ፡ ይሟሟል ፤ ከውኃውም ፡ ጋር ፡ ሲዋሐድ ፡ ላይን ፡ አይታይም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡

ጨው ፡ በውኃው ፡ ውስጥ ፡ መኖሩ ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ። ጨው ፡ ለማግኘት ፡ ውኃውን ፡ አፍልቶ ፡ ወደ ፡ እንፋሎትነት ፡ መለወጥ ፡ ያስፈልጋል ። ውኃው ፡ እንፋሎት ፡ ሆኖ ፡ ሲሄድ ፡ ጨው ፡ ብቻ ፡ ይቀራል ። ይህም ፡ አስተያየት ፡ የፊዚክ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። የኖራ ፡ እርሳስን ፡ (ቾክ) ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ ቢጨምሩት ፡ አሲድ ፡ ካርቦኒኩ ፡ ይበናል ። የሚቀረውም ፡ የኖራ ፡ እራሪ ፡ ነው ። እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ የቀረው ፡ እራሪ ፡ ጠባዩ ፡ በፍጹም ፡ የተለወጠ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ የሺሚ ፡ ምርመራ ፡ ይባላል ።

ፊዚክ ፡ የበራ ፡ ፋኖስ ፡ ሲያገኝ ፡ የብርሃኑን ፡ ውጋጋን ፡ በነበልባሉ ፡ ዙሪያ ፡ በሚገኘው ፡ አየርና ፡ በፋኖሱም ፡ ብርጭቆ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ሙቀት ፡ በመፋጀትና ፡ በማጋል ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ያስተውላል ። ሺሚ ፡ ግን ፡ በፋኖስ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ዘይት ፡ ወይም ፡ ጋዝ ፡ (ላምባ)ሲበራና ፡ ሲነድ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ የሚሰጠውስ ፡ ጠባይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ መርምሮ ፡ በአየር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ አክሲጊን ፡ በዘይት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ነገሮች ፡ አንደኛው ፡ ከሆነው ፡ ከካርቦን ፡ ጋር ፡ ሲቀላቀል ፡ አሲድ ፡ ካርቦኒክን ፡ እንደሚፈጥር ፡ ይናገራል ። በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ አካሎች ፡ ተቀላቅለው ፡ ሲዋሐዱ ፡ የየራሳቸውን ፡ የግል ፡ ጠባይ ፡ ትተው ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ጠባይ ፡ የማምጣታቸው ፡ ሁኔታ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ አየር ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ከአክሲጊንና ፡ ከአዘት ፡ የተቀመመ ፡ ነገር ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ሁለት ፡ ቅመሞች ፡ አክሲጊን ፡ የሚቃጠል ፡ ጠባዩን ፡ አዘትም ፡ የሱን ፡ ጠባይ ፡ የማስታገሥ ፡ ጠባዩን ፡ ይዘው ፡ ሁለቱም ፡ በየጠባያቸው ፡ ስለሚረጉ ፡ ይህ ፡ የአየር ፡ ሁኔታ ፡ ተቀመመ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ተዋሐደ ፡ አይባልም ። ውኃ ፡ ግን ፡ ከአክሲጊንና ፡ ከሂድሮጊን ፡ መዋሐድ ፡ የተገኘ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ እንዲቃጠል ፡ የግድረግ ፡ ወይም ፡ የመቃጠል ፡ ጠባይ ፡ የለውም ። የሺሚ ፡ ትምህርት ፡ ለእርሻ ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ ለቤተ ፡ ሰብ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ጉዳይና ፡ ለሕክምና ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner



አፄ ፡ ቴዎድሮስና ፡ ሁለት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ።

በአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡
ሁለት ፡ ፈረንጆች ፡ መጥተው ፡ አንድነት ፡

በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ አውሬ ፡ እንዲያድኑ ፡
አፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ፈቃድ ፡ ቢለምኑ ፡
እሺ ፡ አሉዋቸውና ፡ እያመሰገኑ ፡
ለማደን ፡ ሲሄዱ ፡ ፈቃዱን ፡ አግኝተው ፡
በረገጡት ፡ አገር ፡ ሁሉን ፡ ተመልክተው ፡
ለይተው ፡ ለማወቅ ፡ እያንዳንዱን ፡ ቦታ ፡
ጽፈው ፡ እያነሡ ፡ የመንገዶች ፡ ካርታ ፡
ሲሠሩ ፡ ከረሙ ፡ የስለላ ፡ ሥራ ።
አብሮዋቸው ፡ የሚዘር ፡ መንገድ ፡ እየመራ ፡
የማይለያቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡
እሱም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ቂየና ፡ እየዘረ ፡
ሁለቱ ፡ ፈረንጆች ፡ አደኑን ፡ ጨርሰው ፡
ከተማ ፡ ሲገቡ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰው ፡
መሰለላቸውን ፡ ካርታም ፡ እንዳነሡ ፡
የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ ነገረ ፡ ለንጉሡ ፡
ሁሉን ፡ ነገራቸው ፡ ላፄ ፡ ገለጸና ፡
ተግቶ ፡ ሊጠባበቅ ፡ ጥንቱን ፡ ታዟልና ።
የመጡበት ፡ አሳብ ፡ ሴላ ፡ በመሆኑ ፡
ነገሩን ፡ ሲሰሙ ፡ ንጉሡም ፡ አዘኑ ።
ከዚያም ፡ ፈረንጆቹ ፡ ፈጥነው ፡ ሊመለሱ ፡
ሊሄዱ ፡ አገራቸው ፡ አስበው ፡ ሲነሡ ፡
ቀጠሮ ፡ ጠየቁ ፡ ፈቀደው ፡ መሰናበት ፡
አፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ወዲያው ፡ በደግነት ፡
ምሳ ፡ ጋበዙና ፡ በመልካም ፡ አብልተው ፡
አክብረው ፡ በብዙ ፡ ደስም ፡ አሸኝተው ፡
የተሠሩ ፡ ዋንጮች ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡
ጥሬ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ እንዲሁም ፡ ሱል ፡ ሚምር ፡
ቆጥተው ፡ ሲሸኙዋቸው ፡ ጠርተው ፡ አንዱን ፡ አሽከር ፡
እስከ ፡ መርከብ ፡ ድረስ ፡ ተለይቶ ፡ ሳይቀር ፡
ከሸኘ ፡ በኋላ ፡ ሲገቡ ፡ መርከብ ፡
የእግራቸውን ፡ ጫሞች ፡ አውልቆ ፡ እንዲያጥብ ፡
አዘዙት ፡ ንጉሡ ፡ እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡

Scanned with CamScanner

ሁለቱን ፡ ፈረንጆች ፡ ሄደ ፡ ተከትሎ ።
የታዘዘውን ፡ ቃል ፡ ገልጠ ፡ እያስታወቀ ፡
መርከብ ፡ ሲሳፈሩ ፡ ማሞቹን ፡ ጠየቀ ።
ሁለቱ ፡ ፈረንጆች ፡ ይህንን ፡ ሲሰሙ ፡
በንጉሡ ፡ ትዛዝ ፡ እጅግ ፡ ተገረሙ ።
ምክንያቱን ፡ ማወቅ ፡ ስለናፈቃቸው ፡
እንዲወርድ ፡ አድርገው ፡ ከመርከብ ፡ ዕቃቸው ፡
ጠይቀው ፡ ለማግኘት ፡ ነገሩን ፡ ከንጉሡ ፡
ፈጥነው ፡ ካሽከሩ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ተመለሱ ።
እሷ ፡ ዘንድ ፡ ሲደርሱ ፡ ነገሩን ፡ አውርተው ፡
መጀነቃቸውን ፡ ለንጉሡ ፡ አመልክተው ፡
የዚህን ፡ ምክንያት ፡ ሳይሄዱ ፡ እንዲያውቁ ፡
እንዲገልጡላቸው ፡ ለምነው ፡ ጠየቁ ።
ንጉሡም ፡ መለሱ ፤ አገሬ ፡ ገብታችሁ ፡
የኢትዮጵያን ፡ አፈር ፡ በይናችሁ ፡ አይታችሁ ፡
ከሁሉም ፡ መብለጡን ፡ ስለተረዳችሁ ፡
እኔም ፡ አገራችን ፡ ብትሉ ፡ እንመለስ ፡
ከወርቅም ፡ ከሉልም ፡ ሰጠሁ ፡ በመለገሥ ።
የኢትዮጵያ ፡ አፈር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የነጠረ ።
ከወርቅም ፡ ከሉልም ፡ ይበልጥ ፡ የከበረ ፡
ውድ ፡ በመሆኑ ፡ አልችልም ፡ ለመስጠት ፡
አሁንም ፡ እነሆ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡
እናንት ፡ አገራችሁ ፡ ከዚህ ፡ ስትሄዱ ፡
ከገሬ ፡ ውብ ፡ አፈር ፡ ከጠራው ፡ ከውዱ ፡
ሣማ ፡ ያነሣውን ፡ እንኳ ፡ እንዳትወስዱ ፡
በጣም ፡ ነፍጌ ፡ ነው ፡ በሄዳችሁ ፡ ጊዜ ፡
ይህን ፡ እንዳያጽም ፡ አሽከሬን ፡ ማዘዜ ።

ንጹሕ ፡ አካሎችና ፡ ቅልቅል ፡ አካሎች ።

ንጹሕ ፡ አካሎች ፡ የሚባሉት ፡ በውስጣቸው ፡ ከንድ ፡ ነገር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሌለባቸው ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡ ወርቅ ፡ በውስጡ ፡ ሌላ ፡ የተቀላቀለው ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ንጹሕ ፡ አካል ፡ ይባላል ። ብቻውን ፡ የሆነ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ግለት ፡ ነው ።

የተቀላቀሉ ፡ አካሎች ፡ የሚባሉት ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ተቀላቅለው ፡ የየግል ፡ ጠባያቸውን ፡ ትተው ፡ የተዋሐዱ ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡ ገሠጥ ፡ የአክሲገርንና ፡ የብረት ፡ ቅይጥ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወይም ፡ የአክሲገርን ፡ ወይም ፡ የብረት ፡ ጠባይ ፡ በውስጡ ፡ አይንጸባረቅም ።

በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ በብዙ ፡ ተሰራጭቶ ፡ የሚገኘው ፡ ንጹሕ ፡ ወይም ፡ ብቻኛ ፡ የሆነ ፡ አካል ፡ አክሲገርን ፡ ወይም ፡ የሕይወት ፡ አየር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ነው ። እሱም ፡ እሱን ፡ ከመሰለው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በብዙ ፡ ተሰራጭቶ ፡ ከሚገኘው ፡ ንጹሕ ፡ አካል ፡ ከሆነው ፡ አዘት ፡ ከሚባለው ፡ ጋር ፡ ከአምስት ፡ በአንድ ፡ እጅ ፡ መጠን ፡ ተቀላቅሎ ፡ ይገኛል ። ከሂድሮጊን ፡ ጋር ፡ ሲቀላቀል ፡ ደግሞ ፡ ውኃን ፡ ይፈጥራል ።

አክሲገርን ፡ ብቻውን ፡ ሲሆን ፡ የሚያቃጥል ፡ አካል ፡ ነው ። የእሳት ፡ ምድጃ ፡ እንዲፋፋም ፡ የሚያደርግ ፡ እሱ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የእሳት ፡ ምድጃን ፡ ከሥሩ ፡ የአክሲገርን ፡ አየር ፡ እንዳይገባ ፡ አድርገው ፡ ቢዘጉት ፡ እሳቱ ፡ ይጠፋል ፤ የሚያቀጣጥለው ፡ አየር ፡ አክሲጊርን ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ብረትነት ፡ የሌላቸው ፡ ንጹሕ ፡ አካሎች ፡ የሚባሉት ፤ አዘት ፤ ሂድሮጊን ፤ ክርበን ፤ ድኝ ፤ ፎስፎር ፤ ክሎር ፡ ናቸው ።

ብረትነት ፡ ያላቸው ፡ ንጹሕ ፡ አካሎች ፡ ዋና ፡ ዋኖቹ ፡ ብረት ፤ ናስ ፤ እርሳስ ፤ ቆርቆሮ ፤ ወርቅ ፡ ብር ፤ ባዜቃ ፡ ፕላቲን ፡ ናቸው ።

የውኃ ፡ ሁኔታ ።

ውኃን ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ቢያፈሱት ፡ ይፈላና ፡ ከላዩም ፡ እንፋሎት ፡ ይነሣል ፤ ውኃውም ፡ እየፈላ ፡ ይድበለበልና ፡ ተንተክትክ ፡ ሁሉም ፡ እንፋሎት ፡ ሆኖ ፡ ይጠፋል ፤ ይህ ፡ አስተያየት ፡ የፊዚክ ፡ ሥራ ፡ ነው ። የእሳትና ፡ የውኃን ፡ ጠባያት ፡ ለየብቻቸው ፡ እየመረመረ ፡ አንዱም ፡ በንደኛው ፡ ላይ ፡ የሚፈጽመውን ፡ አድራጎት ፡ አስተውሎ ፡ ያጠናል ።

ይህ ፡ አደራረግ ፡ የውኃና ፡ የእሳትን ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባያቸውን ፡ አይለውጠውም ። ውኃው ፡ ሲሞቅና ፡ ሲፈላ ፡ ጠባዩን ፡ አይለውጥም ፡ ከእሳቱ ፡ ምድጃ ፡ ሲያርቁት ፡ ተመልሶ ፡ እንደቀድሞው ፡ ይሆ

Scanned with CamScanner

ናል ፤ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ሙቀት ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ይሄዳልና ። እንዲ
ሁም ፡ እንፋሎት ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ የውኃነቱ ፡ ባሕሪ ፡ አልተለወጠም ፤
በቀዘቀዘ ፡ ጊዜ ፡ ይረጋና ፡ ተመልሶ ፡ ውኃ ፡ ይሆናል ። ውኃ ፡ በጣም ፡
ሲቀዘቅዝ ፡ ይረጋና ፡ በረዶ ፡ ይሆናል ። በጣም ፡ ሲፈላና ፡ ሲሞቅ ፡
ደግሞ ፡ እንፋሎት ፡ ይሆናል ። በረዶና ፡ እንፋሎት ፡ ስማቸው ፡ ይለ
ወጥ ፡ እንጂ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ያው ፡ ውኃ ፡ ናቸው ። ጨጋግ ፤ ጉም ፡
ደመና ፡ ቢባል ፤ በረዶ ፤ ዝናም ፤ ጤዛ ፤ አመዳይ ፡ እንደማለት ፡ ያህል ፡
ነው ። ሁሉም ፡ ውኃ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ የውኃ ፡ ሁኔታ ፡ ሦስት ፡
ነው ። እንደኛ ፡ ውኃ ፡ ራሱ ፡ በፈሳሽነት ፡ ባሕሪ ፡ ሳለ ፤ ሁለተኛ ፡
ይረጋና ፡ በረዶ ፡ ሲሆን ፡ በጠጣርነት ፡ ባሕሪ ፤ ሦስተኛ ፡ እንፋሎት ፡
ሲሆን ፡ በጢስነት ፡ (ጋዝነት ፡) ባሕሪ ።

የአየር ፡ ባሕሪ ።

ሰው ፡ በባቡር ፡ ወይም ፡ በአቶሞቢል ፡ እንደሚመላለስ ፡ ድም
ፅን ፡ ደግሞ ፡ የሚያመላልሰው ፡ አየር ፡ ነው ። ያመላላሽነት ፡ ሥራ
ውን ፡ ሲሠራ ፡ ድምፅ ፡ ባንድ ፡ ሰንንድ ፡ 340 ሜትር ይሮጣል ።

ይህንንም ፡ ለመረዳት ፡ ብልሃቱ ፡ አዎር ፡ ነው ። አንድ ፡ አጻኛ ፡
ሰው ፡ እኛ ፡ ከለንበት ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የሚሆን ፡
ርቆ ፡ ጠበንጃውን ፡ ደግኖ ፡ ከነጣጠረ ፡ በኋላ ፡ ባንድ ፡ አውሬ ፡ ላይ ፡
ሲተኩስ ፡ ብናየው ፡ መጀመሪያ ፡ የምናየው ፡ የጠበንጃውን ፡ ጢስ ፡
ነው ። ሦስት ፡ ሰንንድ ፡ የሚሆን ፡ ቄይቶ ፡ ግን ፡ የጠበንጃውን ፡
ድምፅ ፡ እንሰማለን ።

እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ መድፍ ፡ ከሩቅ ፡ ተጠምዶ ፡ ብናይ ፡
ኋላም ፡ እሳቱን ፡ ወይም ፡ ጢሱን ፡ ብንመለከት ፡ ቀጥሎም ፡ አሥር ፡
ሰንንድ ፡ ቄይቶ ፡ ድምፁን ፡ ብንሰማ ፡ ይህ ፡ መድፍ ፡ እኛ ፡ ከለን
በት ፡ ቦታ ፡ 3,400 (ሦስት ፡ ሽህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡) ሜትር ፡ ርቆ ፡
እንደሚገኝ ፡ በሒሳብ ፡ መንገድ ፡ እናውቀዋለን ።

አ ቶ ም ።

በተቀደሰ ፡ ድምፅ ፡ በግርማዊ ፡ ቃሉ ፡
ዓለምን ፡ እንፍጠር ፡ እንሥራ ፡ በሙሉ ።
አለና ፡ መለኮት ፡ በሞገስ ፡ ተነሥቶ

ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ያለአውታር ፡ ዝርንቶ ፡
ከዉለማ ፡ በዶ ፡ አውጥቶ ፡ ቀምሞ ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ፍጡር ፡ በጥበብ ፡ ሸልሞ ፡
በብዙ ፡ መራቀቅ ፡ ግብሩን ፡ አከናውኖ ፡
ሁሉን ፡ ነገር ፡ ሠርቶ ፡ ሲጨርስ ፡ ወስና ፡
በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ መከራን ፡ ሲመራ ፡
የሚያስቀምጥበት ፡ ተቸገረ ፡ ሥፍራ ።
ውቅያኖስ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ወስዶ ፡ ቢያስቀምው ፡
የመከራ ፡ ሸክም ፡ ባሕሩን ፡ በጠበጠው ።
የማይችለው ፡ ሆነ ፡ ክፉኛ ፡ ተናጠ ።
ወስዶም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ፈጣሪ ፡ አስቀመጠ ።
ተንዶ ፡ ፈረሰ ፡ ወደቀ ፡ ተራራ ፡
ጫንቃው ፡ ባይችልለት ፡ ቢከብደው ፡ መከራ ።
ተራራው ፡ ሲፈርስም ፡ ሆነ ፡ ትልቅ ፡ መዓት ፡
መሬት ፡ ተናወጠች ፡ መከራ ፡ ሲሰማት ።
አምላክ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በብዙ ፡ ተገርሞ ፡
ከዝሆን ፡ ትከሻ ፡ አስቀመጠ ፡ ደግሞ ።
አቶ ፡ ገዝሆን ፡ ጥቂት ፡ አፍታም ፡ አልበረቱ ፡
ተንገዳገዱና ፡ ተንከባለው ፡ ሞቱ ።
አሁንም ፡ መልሶ ፡ ደግሞ ፡ መጨረሻ ፡
አንሥቶ ፡ አስቀመጠው ፡ ከንበሳ ፡ ትከሻ ።
ክብሩን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲገደረደር ፡ ደርሶ ፡
አንድ ፡ ሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ቆመ ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ።
ሊራመድ ፡ ሲሞክር ፡ ክርብት ፡ አለ ፡ አንበሳ ፡
መከራ ፡ ዳመጠው ፡ ወድቆም ፡ አልተነሣ ።
እንግዲህ ፡ ከጠፋ ፡ ለመከራ ፡ ቦታ ፡
መልሲ ፡ ልፋቀው ፡ ብሎ ፡ ሲያመነታ ፤
እንኳ ፡ ከምን ፡ ቦታ ፡ ከየት ፡ እንደወጣ ፡
ያጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ድንገት ፡ አዳም ፡ መጣ ።
ሲጥለው ፡ ለማየት ፡ ሸነጐ ፡ ሲያናውጠው ፡
ከዳም ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ አስቀመጠው ።

Scanned with CamScanner

አጻም ፡ ግን ፡ ይደንቃል ፡ ከሁሉም ፡ በሊጠ ፡
ዘር ፡ ብሉም ፡ አላየ ፡ አልተገላመጠ ፡
ምንም ፡ ሳይሰማው ፡ ነጐደ ፡ እየሮጠ ።
በውነተኛው ፡ ነገር ፡ ይቅርና ፡ ተረቱ ፡
ጠልቃችሁ ፡ በግሰብ ፡ ስትመለከቱ ፡
የመዘራን ፡ ከሰ ፡ ያሳርን ፡ አተሳ ፡
ማን ፡ ይችለው ፡ ናሯል ፡ እስቲ ፡ ከሰው ፡ ሌላ ።
ጌታችን ፡ ሲሰቀል ፡ ፀርብ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡
የሰዎችን ፡ ድፍረት ፡ መሬት ፡ ተመልከታ ፡
እጅግ ፡ ተናወጠች ፡ ከፋኖ ፡ ደንግጣ ፡
ፀሓይም ፡ ጠቆረች ፡ ውቢቲ ፡ ገረጣ ።
የሰግይ ፡ የመሬት ፡ ጌታን ፡ አሰቅሎ ፡
በሰላም ፡ እምሽቶ ፡ በጸጥታ ፡ ውሎ ፡
ጥቂት ፡ ሳይሰማው ፡ የዕለቱ ፡ መከራ ፡
ስሕተቱን ፡ ዘንግቶ ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡
ምን ፡ ብታስፈራራው ፡ ሚስቱ ፡ ሕልሟን ፡ ነግራ ፡
ሁሉን ፡ ነገር ፡ ረስቶ ፡ ተቀምጦ ፡ ከቤቱ ፡
ይጫወት ፡ ነበረ ፡ ጲላጦስ ፡ ከሚስቱ ።
ዛሬም ፡ አልተሻለው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ድፍረቱ ፡
አልተገንምና ፡ ከጲላጦስ ፡ በልጦ ፡
ተኝቶ ፡ ማደሩ ፡ አቶምን ፡ አስቀምጦ ።
የዘመናችን ፡ ጉድ ፡ እዩት ፡ የኛን ፡ ነገር ፡
ፍቅር ፡ ስለጠፋች ፡ በጉልበት ፡ ለማደር ፡
እንዱ ፡ እንዱን ፡ ሊበልጠው ፡ በዕውቀት ፡ ሲወዳደር ፡
በበቀል ፡ ሠለማ ፡ ገብቶ ፡ ሲደናበር ፡
ደም ፡ ስላልጠገበ ፡ እየተበሳጨ ፡
ልቡ ፡ ጥበብ ፡ ሲሻ ፡ ቂም ፡ እያመነጨ ፡
ከጥፋቱ ፡ ጋራ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተጋጨ ።
አቶም ፡ ትልቅ ፡ ጥፋት ፡ የሥልጣኔ ፡ እዳ ፡
ለፍጥረት ፡ ዓለሙ ፡ እጅግ ፡ የሚያሠጋ ።
እሜቲቱ ፡ ጥበብ ፡ ያንች ፡ ልጆች ፡ መንታ ፡
አንዱ ፡ መከራ ፡ ነው ፡ እንደኛው ፡ ደስታ ።

መከራ ፡ እግይከብደው ፡ ያጻም ፡ ልጅ ፡ ደፋሩ ፡
እየተራራቀ ፡ በመመራመሩ ፡
በግብረ ፡ ጥበቡ ፡ ሲሠራ ፡ ሲያፈርሰን ፡
ከነ ፡ ቦምብ ፡ አቶሚክ ፡ ዘንድሮ ፡ አደረሰን ።
አቶም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታ ፡ ያድናል ፡
ይላሉ ፡ ለብዙ ፡ ጥበብ ፡ ይጠቅመናል ፡
ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢቻል ፡ አፍርሶ ፡ መጠገን ፡
መከራው ፡ ከባድ ፡ ነው ፡ የጥፋቱ ፡ ወገን ።
እንዳይሆን ፡ ያሠጋል ፡ የሌለው ፡ ማደሻ ፡
ያደጋ ፡ ፍጻሜ ፡ የሰው ፡ መጪረሻ ።
ሺሚ ፡ እየቀመመ ፡ ፀአደራጀው ፡ ፊዚክ ፡
ከባሩድ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ቦምብ ፡ አቶሚክ ፡
ራዳር ፡ ተጨምሮ ፡ ፊዚ ፡ ስትራቶስ ፡ ፈሪክ ፡
ከነቁፍሮቻቸው ፡ እነ ፡ ሬዮን ፡ ኩስሚክ ፡
ግሩም ፡ ነው ፡ ሰማነው ፡ ደረሰ ፡ በእኛ ፡ ዕድሜ ፡
ትልቅ ፡ እርምጃ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ።

አ ኒ ባ ል ።

ከሰሜን ፡ አፍሪካ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ከርታጎን ፡ የምትባል ፡ መን
ግሥት ፡ ከአውሮፓ ፡ ደቡብ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ሮማ ፡ የምትባል ፡ መንግ
ሥት ፡ በጥንታዊ ፡ ዘመን ፡ ተመሥርተው ፡ የሁለቱ ፡ መንግሥ
ታት ፡ በሀብትና ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ መደርጀት ፡ የተፈጸመው ፡ በንድ ፡
ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረ ፡ ጥቅማቸውና ፡ ክብራቸው ፡ እንዲጋጭ ፡
ያደረገው ፡ ከሴላው ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡
የጆግራፊ ፡ አቀማመጥ ፡ መስሎ ፡ ለታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ይታያል ።
ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በጦርም ፡ ሆነ ፡ በሀብት ፡ ረገድ ፡ ያንዱ ፡
መንግሥት ፡ ማደግ ፡ ያንደኛውን ፡ ጥቅም ፡ የሚጎዳ ፡ መስሎ ፡
በእያንዳንዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለተገመተ ፡ ከዚህ ፡ ሐሳብ ፡ የተፀነሰው ፡
ጠብ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዳቸው ፡ ወርሶ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በመከከሳ
ቸው ፡ ሳይበርድ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደ ፡ ነደደ ፡ ናር ዋል ። አስደናቂው ፡
የአኒባል ፡ ጀግንነት ፡ የተፈጠረው ፡ ከዚህ ፡ ከጋለው ፡ የጠብ ፡

መንፈስ ፡ ነው ። አስፓኛ ፡ የክርታጎን ፡ ግዛት ፡ በነበረች ፡ የአኒባል ፡ አባት ፡ አሚልካር ፡ ባርካ ፡ የአስፓኛ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡



አኒባል ።

ነበር ። አሱም ፡ ከሮማውያን ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተዋጋ ፡ የክርታጎን ፡ የጦር ፡ አበጋዝ ፡ ስለነበር ፡ ስለሮማውያን ፡ የነበረው ፡ ቂም ፡ ጽኑ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ልጁ ፡ አኒባል ፡ ገና ፡ የዘጠኝ ፡ ዓመት ፡

ልጅ ፡ ሳለ ፡ በሮማውያን ፡ ላይ ፡ ዘላለም ፡ የማይብርድ ፡ ቂም ፡ በልቤ ፡ አሳድራለሁ ፡ እሰኝቶ ፡ አስምሎታል ። ይህንንም ፡ ማላ ፡ አኒባል ፡ አስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቴ ፡ ድረስ ፡ ጠብቅታል ።

አሚልካር ፡ ባርካ ፡ ሞቶ ፡ አኒባል ፡ ባባቱ ፡ ቦታ ፡ ሲተካ ፡ ለዋቂት ፡ ጊዜ ፡ በርዶ ፡ የነበረውን ፡ የሁለቱን ፡ መንግሥታት ፡ ጠብ ፡ የሚያነሣሣ ፡ ምክንያት ፡ መፍጠር ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተው ። ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ በሰላም ፡ ሊኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ የሌለው ፡ ከሆነና ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ እንዲጠፋ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ ከተሰማቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠላትን ፡ ሳይቀድም ፡ ከመ ቅደም ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ አለመኖሩን ፡ አኒባል ፡ በቶሎ ፡ ተረዳው ። ስለዚህ ፡ የአገሩ ፡ ጠላት ፡ የሆነችውን ፡ ሮማን ፡ ለማጥፋት ፡ አኒባል ፡ የበታ ፡ የጦር ፡ ሥያ ፡ አለኝ ፡ ሲል ፡ ራሱን ፡ ገመተ ። አምሳ ፡ ሺህ ፡ አግረኛ ፡ ጦር ፡ ዘጠኝ ፡ ሺህ ፡ ፈረሰኛና ፡ ለጦርነት ፡ ሥራ ፡ የሠለጠኑ ፡ ዘሆኖች ፡ ጨምሮ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሊሄድ ፡ ተነሣ ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ በጠላት ፡ ተከላካይነት ፡ ከሚጠብቀው ፡ ችግር ፡ ይልቅ ፡ አዚያ ፡ አስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ከመንገዱ ፡ ርቀትና ፡ አስቸጋሪነት ፡ የተነሣ ፡ የሚያገኘው ፡ መከራ ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋው ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አኒባል ፡ ሰውነቱ ፡ ለድካም ፤ መንፈሱ ፡ ለችግር ፡ የማይበገር ፡ ደፋር ፤ ዘዴኛ ፡ ብርቱና ፡ ጨካኝ ፡ ቦረኛ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እንቅፋት ፡ ክጉዳይ ፡ አልጣፈውም ።

ቡርፊኔና ፡ በአልፕ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ሙሉ ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፡ ከሮማ ፡ ግዛት ፡ ሲገባ ፡ በየመንገዱ ፡ አገራቸውን ፡ ከረገጠባቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ በመዋጋት ፡ ከመንገዱ ፡ ርቀት ፡ የተነሣ ፡ ወታደሮቹ ፡ በመራባቸውና ፡ በሽታም ፡ ስለፈጃቸው ፤ ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ በአልፕ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ብዙዎቹ ፡ ገደል ፡ እየገቡ ፡ ስላለቁ ፡ አኒባል ፡ ከሮማ ፡ ግዛት ፡ ሲገባ ፡ የቀረው ፡ የጦሩ ፡ ግማሽ ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሮማውያን ፡ በጦር ፡ ሚዳ ፡ ላይ ፡ በገጠሙት ፡ ጊዜ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ ገድሉባቸው ፡ ስድስት ፡ ሺ ፡ ማርከባቸው ፡ ድል ፡ ሲያደርጋቸው ፡ ከጠላቶቹ ፡ ሥሬር ፡ ላይ ፡ ያገኘውን ፡ ምግብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ከብት ፡ ብዙ ፡ ወርቅም ፡ ደክመው ፡ የነበሩትን ፡ ወታደሮቹን ፡ ማዳበሪያ ፡ አድርጎ ፡ ታል ።

Scanned with CamScanner

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አኒባል ፡ ከሮማ ፡ አገር ፡ ከንዱ ፡ አውራጃ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ እየተዘዋወረ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ ሲ
ጋቸው ፡ ኖሮዋል ። ይልቁንም ፡ ከን ፡ ከሚባለው ፡ አገር ፡ አጣጥፎ ፡
በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ በውጊያው ፡ ሰዓት ፡ ትልቅ ፡ ንፋስ ፡ ስለ
ተነሣ ፡ አኒባል ፡ ነገሩን ፡ አስቀድሞ ፡ በማስተዋሉ ፡ ንፋሱን ፡ ከጀ
ርባው ፡ አድርጎ ፡ ውጊያ ፡ ገጠመ ። ሮማውያን ፡ ግን ፡ ባለማስተዋል ፡
ንፋሱን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አድርገው ፡ ስለገጠሙት ፡ ንፋሱ ፡ ያስነሣው ፡
አቧራ ፡ ዓይናቸውን ፡ ይመታው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የሮ
ማውያን ፡ ፈረሰኞች ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ተደናግጠው ፡ ከፈረሰኞ
ቸው ፡ ላይ ፡ ስለወረዱ ፡ ትልቅ ፡ ስሕተት ፡ አደረጉ ። በዚህ ፡ ውጊያ ፡
ላይ ፡ የሞቱት ፡ ሮማውያን ፡ ከአምሳ ፡ ሺ ፡ አስከ ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡
ናቸው ። አኒባል ፡ ስለዚህ ፡ ውጊያ ፡ ሲናገር ፡ ሮማዊው ፡ የጦር ፡ አበ
ጋዝ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የተበላሸ ፡ የጦር ፡ አቅድ ፡ ተከትሎ ፡ መቼ
ጋቱ ፡ ወታደሮቹን ፡ እግራቸውንና ፡ እጃቸውን ፡ አስሮ ፡ እንደ ፡ ሰጠኝ ፡
ያህል ፡ እቈጥረዋለሁ ፡ አለ ፡ ይባላል ።

ናፖሌዎን ፡ ስለ ፡ አኒባል ፡ ሲናገር ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡
ውስጥ ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ እንደኛ ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ሥራው ፡
ያስረዳል ፡ ብሏል ። ሮማውያን ፡ የጦር ፡ መሪያቸው ፡ ከአኒባል ፡ ጋር ፡
ተዋግቶ ፡ ተሸንፎ ፡ ሲመለስ ፡ ልብሀ ፡ ተስፋ ፡ ስላልቈረጠ ፡ እናመሰ
ግንለን ፡ ብለው ፡ ሽልመው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገንዘብና ፡ ጦር ፡
ሰጥተው ፡ ሲያበረታቱት ፡ የከርታጎን ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ መሠረታቸው ፡
ንግድና ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ስለሆነ ፡ አኒባል ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡
ያህል ፡ በጠላት ፡ አገር ፡ ተቀምጦ ፡ አሳቡን ፡ ከናጻሜ ፡ ለማድረስ ፡
በሚያደርገው ፡ ተጋድሎ ፡ እርዳታ ፡ የሚሆን ፡ መታደርና ፡ ገንዘብ ፡
እንዲልኩለት ፡ ሲትተጉታቸው ፡ እነሱ ፡ ግን ፡ አኒባል ፡ ድል ፡ እሮ
ራጊ ፡ ከሆነ ፡ እየዘረፈ ፡ ወርቅ ፡ ለኛ ፡ ይላክልን ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ በምን ፡
ምክንያት ፡ እንልክለታለን ። ድል ፡ ተደራጊ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ የምንልክ
ለት ፡ እርዳታ ፡ ትርፍ ፡ የሌለው ፡ ከሣራ ፡ ነውና ፡ ለምን ፡ ይጠቅመ
ናል ፡ እያሉ ፡ በመንግሥቱ ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ እሳብ ፡ ከፍተኛ ፡
የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ እስተያየት ፡ እድርገው ፡ ይከተሉት ፡ ነበር ፡

ዳሩ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አገር ፡ ከፍተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ እንድ ፡ መ
ግሥት ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ ከሣራ ፡ ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ ሰ
ቀጥር ፡ መቅር ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ የከርታጎን ፡ ሰዎች ፡ ተረድ

ታት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እርዳታ ፡ ለአኒባል ፡ ልከውለት ፡ ቢሆን ፡
ናር ፡ አኒባል ፡ ሮማን ፡ ምናልባት ፡ ያጠፉት ፡ ነበር ፡ ሮማም ፡
ይአኒባል ፡ እጅ ፡ ብትጠፋ ፡ ናሮ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የክ
ርታ ፡ አቀማመጥና ፡ የሕዝቦችም ፡ የሥልጣኔ ፡ ውኔታ ፡ የሚናረው ፡
ፅልክ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ነበር ፡ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የሕዝቦች ፡ ዕድል ፡ የሚ
ወሰነው ፡ ጥልቅ ፡ በሆኑ ፡ ሊታሪክ ፡ ተመራማሪ ፡ በሚያስቸግሩ ፡ በተ
ሰሱ ፡ የነገር ፡ አመጣጠች ፡ እንጂ ፡ አኒባልን ፡ የመሰሉ ፡ ዋጋቸው ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ የጦር ፡ ሰዎች ፡ ሰይፍ ፡ ሠብጠው ፡ በሰነዘሩት ፡ ክንዳ
ቸው ፡ ስላልሆነ ፡ የአኒባል ፡ ስም ፡ ሳንድ ፡ አፍታ ፡ ታይታ ፡ እንደ
ምትጠፋ ፡ ውብ ፡ የሆነች ፡ በራሪ ፡ ክክብ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አንጸባ
ርቆ ፡ ሳይጠገብ ፡ ስላለፈ ፡ ዋንቱንም ፡ የመጣው ፡ ለሴላ ፡ ጉዳይ ፡
መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ በለቅኔዎች ፡ የሥራቸው ፡ አር
አስት ፡ አድርገው ፡ የሐሳብ ፡ ስሚታቸውን ፡ የሚቀዱበት ፡ ምንጭ ፡
እንዲሆናቸው ፡ ይመስላል ።

ሮማን ፡ ለመውጋት ፡ አፍሪክ ፡ ተመኝ ፡
ወንድ ፡ ይፈለግ ፡ ቢባል ፡ አኒባል ፡ ተገኘ ።
ወንዱ ፡ ልጅ ፡ ጨከነ ፡ ያልገን ፡ መንገድ ፡ ያዘ ፡
አሚልክር ፡ ባቀደው ፡ አኒባል ፡ ተጓዘ ።
ለመፍጀት ፡ ሲነሣ ፡ የጠላቶቹን ፡ ዘር ፡
ተራራ ፡ እይመልሰው ፡ ጠሩ ፡ ሲመረመር ።
የወንድኑቱን ፡ ልክ ፡ ሁሉም ፡ ስላወቀ ፡
እንኳንስ ፡ መታደር ፡ ገዘቡ ፡ ታጠቀ ።
የሮማን ፡ አውራጃ ፡ ሰንጥቆ ፡ እያለፈው ፡
አኒባል ፡ ነውከ ፡ በእሳት ፡ የሚገርፈው ።
ቢመክር ፡ ቢዘክር ፡ አልተገኘም ፡ ዘጁ ፡
አንገት ፡ ሠፈሠፈ ፡ ያኒባል ፡ ጉራጁ ።
የሮማን ፡ ወታደር ፡ አኒባል ፡ አረደው ፡
ቤት ፡ ለቤት ፡ አሳዶ ፡ አያርበደበደው ።
አኒባል ፡ ባገሩ ፡ መጠታቱ ፡ ቀርቶ ፡
አሸፈረኝ ፡ አለ ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ገብቶ ።
ከርግ ፡ ጉበዞች ፡ እንደምን ፡ ሰው ፡ ታጣ ፡
አኒባልን ፡ ገጥሞ ፡ ከገር ፡ የሚያበጣ ።

Scanned with CamScanner

እያንበረከከ ፡ ሲያርደው ፡ እንደ ፡ ጭዳ ፡
አቢራም ፡ አገዘው ፡ ነፋሱም ፡ ረዳ ፡
አኒበል ፡ ጨክኖ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ጋለበ ፡
የመታውን ፡ አገር ፡ በደም ፡ እያጠበ ።።
ድንኳኑን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተክሎ ፡ ሲቀመጥ ፡
አኒበል ፡ ይሰጣል ፡ ወንዱን ፡ ልጅ ፡ ለምጥ ፡
አፋፉ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ሮማን ፡ እያየ ፡
ምነው ፡ አይወርድም ፡ ወይ ፡ አኒበል ፡ ዘገየ ?
አኒበል ፡ ሲሏቸው ፡ ፈርተው ፡ እየራዱ ፡
እርገጣ ፡ የነበሩት ፡ ሴቶች ፡ አስወረዱ ።።
ሰይፉን ፡ ሲሰንዘር ፡ ባንዳንድ ፡ ቀን ፡ ውሎ ፡
አኒበል ፡ ይገባል ፡ አምላ ፡ ሽውን ፡ ገድሎ ፡
ወይስ ፡ የጊጤ ፡ ሩር ፡ የዱር ፡ ኪስ ፡ መስሎታል ፡
አኒበል ፡ ጉራዴህ ፡ ባንገት ፡ ይጫወታል ።።

አስትሮኖሚ።።

ከዋክብትን ፡ ማታ ፡ ቱሌስኮፕ ፡ በሚባለው ፡ መነጽር ፡መመልከትን፡ ያህል፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው፡ ዓለም፡ ወሰን፡ የሌለው፡ መሆኑን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ አይነኝም። ይህ ፡ ነገር ፡ በኒውተን ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ስሜት፡ እንዳሳደረበት ፡ "ኢትዮጵያና ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡" በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተነዋል ።።

የእግዚአብሔርን ፡ ሥልጣንና ፡ ጥበብ ፡ ለማድነቂያ ፡ከመሆኑ፡ በቀር ፡ በማንኛውም ፡ በለው ፡ እጅ ፡ በተሠራ ፡ መነጽር፡ የሰማይን ፡መጨረሻ ፡ ዘልቶ ፡ ለማየት ፡ ከቶ ፡ የሚሞከር ፡ ነገር ፡ አለመሆኑን ፡ሊታውንት ፡ ይናገራሉ ።።

ዐሓይ ፡ ከመሬት ፡ በጣም ፡ ትበልጣለች ።። ዳሩ ፡ ግን ፡በሰማይ ፡በፊ ነት ፡ ውስጥ ፡ የምትይዘው ፡ ስፍራ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ከመሆኑ የተነሣ ፡ እኛ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለን ፡ ሰዎች ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡የምናያቸውን ፡ ታናናሾች ፡ ከዋክብት ፡ ነው ፡ የምታህለው ።። በዚህ ፡

አመዛዝኑን ፡ የመሬትን ፡ ትንሽነት ፡ ስንገምተው ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

በመሬትና ፡ በፀሓይ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ወደ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሚሊዮን ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ይጠጋል ። ፀሓይ ፡ በትልቅነት ፡ ከመሬት ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ጊዜ ፡ ትበልጣለች ። በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ የሚገኙት ፡ ፕላኔቶች ፡ ሜርኩር ፤ ቬኑስ ፤ መሬት ፤ ማርስ ፤ ጁፒቴር ፤ ሳቱርን ፤ ኡራኑስና ፡ ኔፕቱን ፡ ናቸው ። ከእነዚህም ፡ በቀር ፡ ባያን ፡ የማይታዩ ፡ ቬስታ ፤ ጁኖን ፡ ሴሬስ ፤ ፓላስ ፡ የሚባሉትና ፡ እነሱንም ፡ የመሰሉ ፡ ሌሎች ፡ ታናናሽ ፡ ፕላኔቶች ፡ አሉ ።

እኛ ፡ ከዋክብት ፡ የምንላቸው ፡ ብዙዎቹ ፡ ፀሓዮች ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ዕሩቅ ፡ ስለሆኑ ፡ ትንሾች ፡ መስለው ፡ ይታየናል ። በቴሌስኮፕ ፡ ሲመለከቷቸው ፡ ግን ፡ ቀጭራቸው ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የብርሃን ፡ ቀለሞች ፡ ያሏቸው ፡ ውበታቸውም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ስሜት ፡ የሚሰጥ ፡ ሆነው ፡ ይታያሉ ።

ጠረቅ ፡ በሌለችበት ፡ ጊዜ ፡ በከዋክብት ፡ ተሸልሞ ፡ ሰማይ ፡ ውብ ፡ ሆኖ ፡ ብሚታይበት ፡ ልሊት ፡ ሰው ፡ ባይኑ ፡ ከሦስት ፡ ሺህ ፡ ከዋክብት ፡ በላይ ፡ ለማየት ፡ አይችልም። ዳሩ ፡ ግን ፡ በአስትሮኖሚ ፡ መነጽር ፡ ሲያስተውል ፡ በብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚቁጠሩ ፡ እነዚህን ፡ ከዋክብት ፡ የምንላቸውን ፡ ፀሓዮች ፡ ሰው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ውበታቸውን ፡ አስተውሎ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የማይነገር ፡ ቃል ፡ የማይገኝለት ፡ የመደነቅ ፡ ስሜት ፡ ያድርበታል ።

ብርሃናቸውን ፡ በሰፊው ፡ እየዘረጉ ፡ ተራርቀው ፡ በሚገኙት ፡ በእዚህ ፡ ፀሓዮች ፡ መካከል ፡ የብርሃናቸው ፡ ቀለም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ከዋክብት ፡ አልር ፡ አልር ፡ በብዙ ፡ ተዘማችተው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የብርሃናቸውም ፡ ቀለም ፡ የተለዋወጠ ፡ የውበት ፡ መልክ ፡ እየሰጣቸው ፡ ሲታዩ ፡ ተመልካች ፡ የደስታና ፡ የመደነቅ ፡ አሳብ ፡ ያድርበታል ።

Scanned with CamScanner

እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ከያንዳንዱ ፡ የሰማይ ፡ ቦታ ፡ ኮከብ ፡ ፀሓይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡ ፕላኔቶች ፡ ሳተላይቶች ፡ ተከማችተው ፡ ይታያሉ ፤ ቀለማቸውም ፡ ሩቢ ፤ ቶጳዝዮንና ፡ ሰንፔር ፡ እየመሰለ ፡ ስለሚታይ ፡ በተበታተኑ ፡ አልማዞች ፡ ሊመሰሉ ፡ ይቻላል ።

በሰማይ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ውበት ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ። የእኛ ፡ ፀሓይ ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ሦስት ፡ ፕላኔቶች ፡ ታጅባ ፡ ከእነሱም ፡ ብዙዎቹ ፡ ሳቴሊቶቻቸውን ፡ (ጨረቮቻቸውን ፡) አስከትለው ፡ ሳቱርንም ፡ ከቀለበቱና ፡ ከስምንት ፡ ጨረቃዎች ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ ይህን ፡ ትንግርት ፡ የሆነ ፡ ውበት ፡ ተመልክቶ ፡ ሊጠ ግበው ፡ አይችልም ።

ፀሓዮቹም ፡ ፕላኔቶቹም ፡ ሳቴሊቶቹም ፡ ከሚቶቹም ፡ (ጅራታም ፡ ከከቦች ፡) ሁሉም ፡ ይንቀሳቀሳሉ ። እነዚህ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚ ታዩት ፡ ቀጥራቸው ፡ ሊጠሰን ፡ የማይቻል ፡ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ የሆኑ ፡ ፀሓዮች ፡ የብዛታቸው ፡ ልክ ፡ እንኳንስ ፡ ተቈጥሮ ፡ ሊደረስበት ፡ ይቅ ርና ፡ ለሊቀውንት ፡ ታይቶ ፡ የማያልቅ ፡ ነገር ፡ ሆኖባቸዋል ፤ የመ ንጽሩን ፡ አሠራርና ፡ የማስተዋሉንም ፡ አኳኋን ፡ እያሻሻሉ ፡ በሂዱ በት ፡ መጠን ፡ ቀድሞ ፡ ያልታዩ ፡ ሌሎች ፡ አዲሶች ፡ ፀሓዮችና ፡ ከዋክብት ፡ ይገኛሉ ። ይህም ፡ ነገር ፡ ሰማያዊው ፡ ዓለም ፡ ርቀቱ ፡ የማይደረስበት ፤ ወሰን ፡ የሌለው ፤ ሠለማ ፡ የማይነካው ፤ በሰው ፡ ዓይን ፡ የማይመረመር ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል ።

ስለዚህ ፡ የአስትሮኖሚ ፡ ሊቃውንት ፡ ሲናገሩ ፡ መነጽሮቻችንን ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ብናሻሽላቸው ፡ ከዋክብትን ፡ ጨርሰን ፡ በሙሉ ፡ ልናያቸው ፡ አንችልም ። በጣም ፡ ዘልቀን ፡ ለማየት ፡ በቻልንበት ፡ መጠን ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ሌሎች ፡ አዲሶች ፡ ከዋክብት ፡ ይወጣሉ ፡ የእኛ ፡ ዕውቀት ፡ ከቶ ፡ ሊዘልቀው ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

እንግዲህ ፡ የዚህ ፡ መጨረሻ ፡ ወዴት ፡ ይሆን ፡ ? ማንም ፡ እያ ውቀውም ፡ ሊያውቀውም ፡ የሚችል ፡ ወደፊት ፡ አይገኝም ።

ሊቀውንት ፡ መርምረው ፡ የደረሱበት ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ከዋክብት ፡ ወይም ፡ ፀሐ ዮች ፡ ሥነ ፡ ዅጥረታቸው ፡ እኛ ፡ ከለንበት ፡ መሬት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡

ዓይነት ፡ መሆኑንና ፡ የተወሰነ ፡ ዕድሜ ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ። ሁሉም ፡ መኖር ፡ የሚጀምሩበት ፤ ሥራቸውን ፡ የሚያከናው ኑበት ፤ የሚይከሙበጥና ፡ ጨርሰው ፡ የሚጠፉበትም ፡ ጊዜ ፡ አለ ። በመጀመሪያ ፡ የብርሃን ፡ ምንጭ ፡ ሆነው ፡ ይፈጠራሉ ፤ ኋላም ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ እየተለዋወጡ ፡ ኖረው ፡ ይቀዘቅዙና ፡ ፕላኔቶች ፡ ወይም ፡ ሳቴሊቶች ፡ ሆነው ፡ በመጨረሻ ፡ ይፈርሳሉ ፤ ይጠፋሉ ።

ሉዊ ፡ ቡህነር ፡ የተባለው ፡ የጀርመን ፡ ሊቅ ፡ በጻፈው ፡ (ኃይ ልና ፡ ጥንተ ፡ ፍጡር ፡) በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ አስትሮኖሚ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

በቦዶ ፡ ዓይን ፡ ሲመለከቱት ፡ የተነደፈ ፡ ጥጥ ፡ መስሎ ፡ ንጹሕ ፡ በሆነ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ የከዋክብት ፡ ሠፈር ፡ በቴሌስኮፕ ፡ መነጽር ፡ ሲመለከቱት ፡ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ ከዋክብት ፤ ዓለሞች ፤ ፀሓ ዮች ፤ የፕላኔት ፡ ሠራዊት ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በላይዋ ፡ ከሚኖሩት ፡ ፍጡሮች ፡ ጋራ ፡ የፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ አክሊ ልና ፡ እምብርት ፡ ናት ፡ ተብላ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ትታሰብ ፡ የነበረ ችው ፡ ይህች ፡ የኛ ፡ መሬት ፡ ባሳብ ፡ ልማድ ። ተሰቅላ ፡ ትኖር ፡ ከነበረችበት ፡ ከፍ ፡ ከለው ፡ አስተያየት ፡ ወርዳ ፡ ሰፊ ፡ በሆነው ፡ የፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ የምትንሳፈፍ ፡ አንዲት ፡ ተራ ፡ አቶም ፡ ሆና ፡ ከመቈጠር ፡ ወደቀች ።

የአስትሮኖሚ ፡ ሊቃውንት ፡ (አስትሮኖሞች ፡) ስለፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ጕዳይ ፡ (UNIVERS) የሚሰጡት ፡ የቀኖር ፡ አሳብ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ለሰው ፡ ዕውቀት ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ እየተ ገኘ ፡ አስቸግሯል ። የሰው ፡ አሳብ ሊከታተለውና ፡ ሊደርስበት ፡ ዘንድ ፡ የሚያውክ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ የጥንት ፡ ሰዎች ፡ የውሻ ፡ ኮከብ ፡ ብለው ፡ የሚጠ ሩዋት ፡ (SIRIUS) የምትባለው ፡ በጣም ፡ ብርሃናዊት ፡ የሆነች ፡ አን ዲት ፡ ኮከብ ፡ አለች ። የእሷም ፡ ብርሃን ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ለመድረስ ፡ ወሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ያስፈልገዋል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ርቀቷ ፡ በመሬትና ፡ በፀሓይ ፡ መካከል ፡ ከሚገኘው ፡ ርቀት ፡ አንድ ፡ ሚሊ ዮን ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ብርሃን ፡ በአንድ ፡ ሴኮንድ ፡ 300. 000 ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ስለሚሄድ ፡ በዚሁ ፡ ፍጥነት ፡ ልክ ፡ ልን

Scanned with CamScanner

ስለራት ፣ ወይም ፣ ከአምስት ፣ ሰዓት ፣ በኋላ ፣ ነው ። በኛና ፣ በሷ ፣ መከከል ፣ ያለውን ፣ ርቀት ፣ ለመገለልቅ ፣ ብርሃን ፣ ይህን ፣ የተባለውን ፣ የሚያህል ፣ ጊዜ ፣ ያስፈልገዋልና ።

Lyre ሊር ፣ በሚባለው ፣ የክዋክብት ፣ ሠራዊት ፣ ክፍል ፣ የም ትገኘው ፣ Vega ቬጋ ፣ የምትባለው ፣ ውብ ፣ የሆነች ፣ ከከብ ፣ ለም ሰሉ ፣ በንድ ፣ ነገር ፣ ምክንያት ፣ ብትጠፋ ከጠፋች ፣ በኋላ ፣ እስከ ፣ ፀሥ ፣ ሰባት ፣ ዓመት ፣ በሰማይ ፣ ላይ ፣ ስታበራ ፣ እኛ ፣ በይናችን ፣ እናያታለን ። ምነው ፣ ቢሉ ፣ ጠናርዋን ፣ የሚነግረን ፣ የብርሃን ፣ ፍጥ ነዚህ ፣ ጊዜ ፣ በፊት ፣ ወደ ፣ እኛ ፣ ለመድረስ ፣ ተነሥተዋልና ።

ብርሃናቸው ፣ በቴሌስኮፕ ፣ መነጽር ፣ ከለሆነ ፣ በቀር ፣ ላይን ፣ የማይታዩ ፣ ከዋክብት ፣ አሉ ። እነሱ ፣ ግን ፣ ብርሃናቸው ፣ ከኛ ፣ ዘንድ ፣ ለመድረስ ፣ ከሁለት ፣ እስከ ፣ ሦስት ፣ ሺህ ፣ ዓመታት ፣ ያስ ፈልገዋል ። ወይም ፣ ደግሞ ፣ ብርሃናቸው ፣ ወደ ፣ እኛ ፣ ለመምጣት ፣ የተነሣው ፣ ከርስቶስ ፣ በተወለደበት ፣ ወይም ፣ ደግሞ ፣ ራቅ ፣ ብሎ ፣ ሆሜር ፣ ቅኔውን ፣ በተቀኘበት ፣ ንግሥተ ፣ ሳባ ፣ ወደ ፣ ሰሎሞን ፣ ዘንድ ፣ በሄደችበትና ፣ የግሪክ ፣ ፈላስፎች ፣ ጥበብን ፣ ያስተምሩ ፣ በነ በረበት ፣ ዘመን ፣ መሆኑ ፣ ነው ።

እንግዲህ ፣ ከዚህ ፣ የተነሣ ፣ ባይናችን ፣ የማናያቸው ፣ ብዙ ፣ ከዋክብት አሉ ። ምክንያቱም ፣ ብርሃናቸው ፣ ከኛ ፣ ዘንድ ፣ ገና ፣ አልደረሰም ። አንዳንዶቹ ፣ ከዋክብት ፣ ደግሞ ፣ የሚገኙበት ፣ ሥፍራ ፣ አለመጠን ፣ የራቀ ፣ ስለሆነ ፣ ጨርሶ ፣ ስለጠፋ ፣ ይሆን ፣ ወይም ፣ ደግሞ ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ ረጅም ፣ የሆነ ፣ ጉዞ ፣ ለመገለቅ ፣ የበቃ ፣ ኃይል ፣ ሳይኖራቸው ፣ እየቀረ ፣ ይሆን ፤ ብርሃናቸው ፣ ከኛ ፣ ዘንድ ፣ መቼም ፣ ቢሆን ፣ ሊደርስ ፣ አይችልም ።

እኛ ፣ ያለንበት ፣ መሬትና ፣ የቀሩትም ፣ ፕላኔቶች ፣ ፀሓዮችና ፣ ከዋክብት ፣ በራሪ ፣ ከከቦችም ፣ ሁሉም ፣ አንድነት ፣ ሆነው ፣ ወደ ፣ ሰማይ ፣ የተወረወሩ ፣ ትልልቆች ፣ ኳሶች ፣ መስለው ፣ በአየር ፣ ላይ ፣ እየተንሳፈፉ ፣ ይኖራሉ ።

የሊቃውንት ፣ ምርመራ ፣ ሁልጊዜ ፣ ሳያቋርጥ ፣ እየቀጠለ ፣ በመሄዱ ፣ አሁንም ፣ በየጊዜው ፣ በጣም ፣ የሚያስደንቁ ፣ ብዙ ፣ አዲስ ፣ ነገሮች ፣ ይገኛሉ ። ሙሴ ፣ ሞኖድ ፣ ሄርዜን ፣ የሚባሉ ፣ የፈረንሳይ ፣ ተወላጅ ፣ የሆኑ ፣ „የኅልም ፣ ሥዕል ፣" በሚል ፣ አርእስት ፣ በጸፉት ፣

ጓዝ ፣ ችለን ፣ ለመሬት ፣ በጣም ፣ ቅርብ ፣ ከሆነችው ፣ ረግፉ ፣ ከም ትገኝ ፣ ከከብ ፣ ዘንድ ፣ ለመድረስ ፣ ብናስብ ፣ ይህችም ፣ ከከብ ፣ ቦታ ፣ ሳትለውጥ ፣ ብትጠብቀን ፣ ናሮ ፣ ሠላሳ ፣ ሺህ ፣ ዓመታት ፣ ያስፈልገናል ።

ይህ ፣ ለኛ ፣ ቅርብ ፣ ለሆነችው ፣ ከከብ ፣ የተገመተ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ በጣም ፣ ሩቅ ፣ የሆኑ ፣ በቦታቸው ፣ ረግተው ፣ የሚገኙ ፣ ሌሎች ፣ ከዋክብት ፣ አሉ ። እነሱም ፣ ብርሃናቸው ፣ እኛ ፣ ዘንድ ፣ ለመድረስ ፣ ብዙ ፣ መቶና ፣ ብዙ ፣ ሚሊዮን ፣ ዓመታት ፣ ያስፈልጋል ።

አሁን ፣ በመወረሻው ፣ ጊዜ ፣ በተሠሩ ፣ ግዙፍ ፣ በሆኑት ፣ የቴ ሌስኮፕ ፣ መነጥሮች ፣ ተመርምሮ ፣ እንደተገኘው ፣ ከኛ ፣ ፀሓይ ፣ አካ ባቢ ፣ ውጭ ፣ የሚገኙት ፣ ከዋክብት ፣ ወይም ፣ ፀሓዮች ፣ ቁጥራቸው ፣ እስከ ፣ ሐያ ፣ ሚሊዮን ፣ ይጠጋል ። በባዶ ፣ ዓይን ፣ ሲመለከቷቸው ፣ ግን ፣ ከእነዚሁ ፣ የሚታዩት ፣ አሉት ፤ ወይም ፣ ቢበዛ ፣ አምስት ፣ ሺህ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ ሊሉ ፣ ሊቃውንት ፣ ይናገራሉ ። እነዚህ ፣ ቁጥራ ቸው ፣ አያሌ ፣ የሆነ ፣ ከዋክብት ፣ ሁሉ ፣ እያንዳንዳቸው ፣ ተከታዮች ፣ የሆኑ ፣ ሞፍሮችና ፣ (ሳቴሊቶች ፣) ምክትል ፣ ሞፍሮች ፣ (ምክትል ፣ ሳቴሌቶች ፣) አሏቸው ። በእነሱም ፣ መካከል ፣ ከፍ ፣ ብሎ ፣ በላይ ኛቹ ፣ መስመሮች ፣ ያመለከትነውን ፣ የመሰል ፣ መራራቅ ፣ ይገኛል ።

ይህ ፣ ደግሞ ፣ እነዚህ ፣ ሁሉ ፣ ከዋክብት ፣ አንድነት ፣ ሆነው ፣ ፍጥረተ ፣ ዓለም ፣ አይደሉም ። ነገር ፣ ግን ፣ አንድነት ፣ ሆነውም ፣ ሆነ ፣ ወይም ፣ በየከፍላቸው ፣ ተመድበውም ፣ ሆነ ፣ የተወሰነ ፣ ቦታ ፣ ያላ ቸው ፤ በፍጥረተ ፣ ዓለምም ፣ አንጻር ፣ ጠባብ ፣ ሥፍራ ፣ የያዙ ፣ ሆነው ፣ የሚቋጠሩ ፣ ናቸው ። በእነሱም ፣ አጠገብ ፣ ሌሎች ፣ ብዙ ዎች ፣ ከእነዚሁም ፣ ቀጥራቸው ፣ ከእነሱም ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ የበለጠ ፣ የከዋክብት ፣ ወሬዊት ፣ ይገኛሉ ።

በፀሓይ ፣ ላይ ፣ አንድ ፣ የመለዋወጥ ፣ ነገር ፣ ሲፈጸም ፣ በየን ፣ ጊዜ ፣ ይህ ፣ መለዋወጥ ፣ የተፈጸመው ፣ ከሰባት ፣ ደቂቅ ፣ ተኩል ፣ በፊት ፣ ነው ፣ ብለን ፣ ማሰብ ፣ አለብን ፤ የፀሓይ ፣ ብርሃን ፣ ወደ ፣ እኛ ፣ ዘንድ ፣ ለመድረስ ፣ ይህ ፣ የጠራነው ፣ የጊዜ ፣ መጠን ፣ ያስ ፈልገዋልና ። ከኛ ፣ የፀሓይ ፣ አካባቢ ፣ ውስጥ ፣ ከሚገኙት ፣ ፕላኔቶች ፣ ውሱ ፣ የራቀችው ፣ ኔፕቱን ፣ የምትባለው ፣ ፕላኔት ፣ ለምሳሌ ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ አደጋ ፣ አግኝቷት ፣ ብትጠፋ ፣ ላይናችን ፣ የምትመወረው ፣

Scanned with CamScanner

መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የሚገኙትን ፡ አሁን ፡ በመጪ ረሽ ፡ ጊዜ ፡ የዓለም ፡ ሊቃውንት ፡ በአስትሮኖሚ ፡ ምርመራ ፡ የገለ ጧቸውን ፡ ነገሮች ፡ ይናገራሉ ።

ለኛ ፡ የሚታዩን ፡ አንዳንድ ፡ ከዋክብቶች ፡ ብርሃናቸው ፡ በአ ስትሮኖሚ ፡ መሣሪያዎች ፡ ሲመረመር ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ መድረስ ፡ የቻ ለው ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሚሊዮን ፡ ዓመታት ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

የዊልሰን ፡ ተራራ ፡ በሚባለው ፡ የከዋክብት ፡ መመርመሪያ ፡ (አብሴርቫቷር ፡) ወሚገኘው ፡ የቴሌስኮፕ ፡ መነጽር ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ከዋክብት ፡ ሊታዩ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰማዩ ፡ በቴሌስኮፕ ፡ ታይቶ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ሲነሣ ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚሆኑ ፡ ከዋክብት ፡ ይታዩበታል ። ፓል ፡ ኩዴርክ ፡ የሚባል ፡ ሊቅ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተነገረው ፡ በተወሰነ ፡ ጠባብ ፡ ሥፍራ ፡ ብቻ ፡ የሚታይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ትልቅ ፡ ቴሌስኮፕ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሚሊያርድ ፡ ከዋክብት ፡ ሊያሳየን ፡ ይገባዋል ፡ ሲል ፡ ተናግሯል ።

ያሳብ ፡ ጥልቅ ፡ አስተያየቶች ።

መርዝም ፡ መድኃኒት ፡ ነው ፡ ሲሆን ፡ በጠብታ ፡
እንዲሁም ፡ ለብንኩል ፡ አለው ፡ ቦታ ፡ ቦታ ።
ምን ፡ ቢመለጥኑ ፡ ቢራቀቁ ፡ በጣም ፡
ሁልጊዜ ፡ ደጋግሞ ፡ ብልጠት ፡ አያዋጣም ።
በእጅ ፡ የተበተቡት ፡ ተንከል ፡ ዘሮ ፡ ዘሮ ፡
ማጋለጡ ፡ አይቀርም ፡ እጅና ፡ እግር ፡ አስሮ ።
መጽሐፉም ፡ ይለናል ፡ ሲያስተምረን ፡ ጥበብ ፡
ብልጥ ፡ ሁን ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ የዋህ ፡ እንደ ፡ ርግብ ።
ስለዚህ ፡ በብልጠት ፡ ተንኩል ፡ ስትሠሩ ፡
በገዙት ፡ እንዳይገድላችሁ ፡ ግርኑት ፡ ሠምሩ ።

*

ሁለት ፡ ባልንጀሮች ፡ በጣም ፡ ሲዋደዱ ፡
አንደኛው ፡ በሐሰት ፡ አንደኛው ፡ ከሠዱ ።
ወስላታው ፡ በሥራው ፡ ሲጠፋ ፡ እየከዳ ፡
ሐቀኛው ፡ ግን ፡ ተርፎ ፡ ሁሉንም ፡ ሲረዳ ፡
ጅግና ፡ ክፉን ፡ ሰው ፡ እግዜር ፡ እየለየ ፡
ፍርዱን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ይባላል ፡ አሳየ ፡

*

የቅናት ፡ በሽታ ፡ ሕመሙ ፡ የከፋ ፡
የሕሊናን ፡ ዓይኖች ፡ ጨርሶ ፡ እሚያጠፋ ።
ያዘዘህ ፡ ክፉ ፡ ደዌ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሲለከፍ ፡
የተጣራው ፡ ነገር ፡ ይመስለዋል ፡ ሰፈፍ ።
ልቡም ፡ እያደላ ፡ ወዲ ፡ ክፋት ፡ ወገን ፡
መሞትን ፡ ይመርጣል ፡ ሰውን ፡ ከማመስገን ።

*

ሕይወት ፡ ጦርነት ፡ ነው ፡ ዋጋህን ፡ የሚያሳይ ፡
መታገል ፡ ግድ ፡ ነው ፡ ስትኖር ፡ ባለም ፡ ላይ ።
በገዛ ፡ እጁ ፡ ወድቆ ፡ በቁሙ ፡ እየሞተ ፡
መታገል ፡ ያልቻለ ፡ ልቡ ፡ እየታከተ ፡
የሚያኑሣው ፡ የለም ፡ በፍቅር ፡ በእርዳታ ፡
ባዚች ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ፍጡር ፡ ካልበረታ ፡
ጥንቱን ፡ አልተሠራም ፡ ለሰነፎች ፡ ቦታ ።

*

ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ የየሰዉን ፡ ዋጋ ፡
በጣም ፡ ያሻል ፡ መሆን ፡ እእምሮው ፡ የረጋ ።
ባስተዋይነትም ፡ መሆን ፡ ባለጸጋ ።

*

ሁሉን ፡ በማሻሻል ፡ መጨመር ፡ መቀነስ ፡
የሌለውን ፡ መፍጠር ፡ ያለውንም ፡ ማደስ ፡
መልከመኑን ፡ አስፋፍቶ ፡ መጥፎውን ፡ መደምሰስ ።
የሚጓዝበትን ፡ አቅድ ፡ እያሰመሩ ፡
ከጨለማ ፡ አውጥቶ ፡ ሕዝቡን ፡ እየጠሩ ፡
አሳብ ፡ እያቀዱ ፡ ሠርቶ ፡ በማሠራት ፡
ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆኖ ፡ ያስፈልጋል ፡ መምራት ።
የተማረ ፡ ሆኖ ፡ ዕውቀት ፡ እያበራ ፡
የቀሩትን ፡ ሰዎች ፡ በጥበብ ፡ ከልመራ ፡
ጥቅም ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ድከሙ ፡ ከማራ ።

Scanned with CamScanner

*

ፍጥረት ፡ ይስ ፡ ሲለው ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ተክዝ ፡
ሌሎቹ ፡ ሲመኩ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ፍዘዝ ።
ደግሞ ፡ ሲጊያጊያጡ ፡ መናኛውን ፡ መልበስ ፡
እንዲሁም ፡ ይሸላል ፡ ሲሰሳቱ ፡ ግልቂስ ፡
ሌላው ፡ ሲጠቃቀም ፡ ሌላው ፡ ሲረዳዳ ፡
አንተ ፡ ይሸልሃል ፡ ዐውቀህ ፡ ብትጎዳ ።
ቀኙ ፡ ግራ ፡ ሆኖ ፡ ፍጡር ፡ ሲደናበር ፡
ግለት ፡ ትችላለህ ፡ እኔ ፡ ዐውቄው ፡ ነበር ።

*

ብርሃንና ፡ ጽልመት ፡ መሬትና ፡ ባሕር ፡
ተራራና ፡ ሜዳ ፡ ጠፈርና ፡ ምድር ፡
ሰዎችና ፡ አራዊት ፡ ጠጠርና ፡ ከከብ ፡
ውበትና ፡ ጭቃ ፡ ጨለማና ፡ ጥበብ ፡
አብረው ፡ ተቀላቅለው ፡ ሆነው ፡ ትልቅ ፡ መዓት ፡
ሥራት ፡ የሚያጡበት ፡ የብጥብጥ ፡ ሰዓት ፡
መኖሩን ፡ ከመነ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በከንቱ ፡
ሥራት ፡ ልሥራ ፡ ብሎ ፡ በለም ፡ ላይ ፡ መልፋቱ ፡
ያስደንቃል ፡ በጣም ፡ አወይ ፡ ሞኝነቱ ፡

*

አንድ ፡ አዲስ ፡ ተገኝቶ ፡ ሌላው ፡ ግን ፡ ካረጀ ፡
የሚናደው ፡ ነገር ፡ ላዲሱ ፡ ከበጀ ፡
በዘመን ፡ መለወጥ ፡ እየተነወረ ፡
ይቅር ፡ ከተባለ ፡ ልማድ ፡ የነበረ ፡
ጠቃሚ ፡ ከሆነ ፡ ሲነቀል ፡ ሲጠፋ ፡
ማፍረስም ፡ መሥራት ፡ ነው ፡ ይለናል ፡ ፈላስፋ ።

*

ኀይን ፡ የለውም ፡ አሉ ፡ የሰነፍ ፡ ልመና ፡
ወደ ፡ እምላክ ፡ ሲጸልይ ፡ ግታ ፡ በልቡና ፡
መንገዱ ፡ ሳይመቻች ፡ ባቡዋራ ፡ በቄታ ፡

አድርገኝ ፡ ይለዋል ፡ ላገሬ ፡ እንድበታ ፡
አንጠጠ ፡ ተኝቼ ፡ ሀረር ፡ እንድነታ ።

*

እየተሸሸለ ፡ እየተለወጠ ፡
አንደኛው ፡ ካንደኛው ፡ አምሮ ፡ እየበለጠ ፡
ሁልጊዜ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሠርቶ ፡ በመሰብሰብ ፡
በኑሮ ፡ በሥራ ፡ በልማድ ፡ በጥበብ ፡
ከልተፈራረቁ ፡ ልቅሶና ፡ ደስታ ፡
ትክዜና ፡ ዘፈን ፡ ሳቅና ፡ ጨዋታ ፡
ቀይና ፡ አረንጓዴ ፡ ጥቁርና ፡ ብጫ ፡
ኑሮዋችን ፡ ጣዕም ፡ ያጣ ፡ ይሆናል ፡ አልጫ ።

*

ዓለምን ፡ ክልናቀ ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ አይሠራም ፡
ሞቱን ፡ ክላሰበ ፡ አምላኩን ፡ አይፈራም ።
ሲቀር ፡ እያየነው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሞቶ ፡
ልባችን ፡ ፀጎዘን ፡ ይኑር ፡ ተከራምቶ ።
ዘወትር ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በንዳንዲ ፡ ደቂቃ ፡
ይህንን ፡ ሊያስታውስ ፡ መንፈሳችን ፡ ይንቃ ።
ሀብቱም ፡ ብውነቱም ፡ አፈር ፡ ውስጥ ፡ ሲገቡ ፡
መሬት ፡ የማይበላው ፡ የማይሞት ፡ ጥበቡ ፡
እውነተኛነት ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ገንዘቡ ።

*

ሰው ፡ ሲበድላችሁ ፡ እስቲ ፡ አትናደዱ ፡
ጠላትን ፡ አትጥሉ ፡ ክፉን ፡ ሰው ፡ ውደዱ ።
የክፉ ፡ ሰው ፡ ክፉት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ትርፉ ፡
ያነቃቃችኋል ፡ እንዳታንቀላፉ ።
የልቦናው ፡ ስሜት ፡ እየተራቀቀ ፡
ሁልጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ እየላቀ ፡
በሥራ ፡ በጥበብ ፡ ግሎ ፡ ለመነሣት ፡
ቁስቋሽ ፡ ይፈልጋል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ እሳት ።

Scanned with CamScanner



ከበደ ሚካኤል በኢትዮጵያ ሥነፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ገናና ከሆኑት ደራሲያን አንዱ ናቸው። ጥቅምት 23፣ 1909 የተወለዱት ባለቅኔ የቤተክህነትን ትምህርት ካገባደዱ በኋላ በአሊያንስ ፍራንሲዝና በላዛሪስት ሚስዮን ዘመናዊ ትምህርትን ተከታትለዋል። የግሪክ ፣ የሮማውያን፣ የእንግሊዝ የፈረንሳይ፣ የጀርመን የሩስያና የጣሊያንን በርካታ መፃህፍት ከመረመሩም በኋላ ሃያ ስድስት መፃህፍትን ለወገኖቻቸው አበርክተዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዚሁ ተግባራቸው የክብር ዶክተርነት ግሪን በ1990 በሰጠበት ወቅትም፣ «በድርሰቶቻቸው ውስጥ የሚታዩት እኚህ ታላቅ ደራሲ የሃሳብ መግለጫዎች ፣ ቃላት ፣ ዘይቤ ሌሎች የአፃፃፍ ስልት ገፅታዎች በኋላ ለመጡ ደራሲዎች ያደረጉት አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም። በተለይ ከ1950ዎቹ ወዲህ የተነሱ በርካታ ደራሲዎች ያላቸውን አጣጥመው ደራሲ ሊሆኑ በቅተዋል» ብሏል።

1. ታሪክና ምሣሌ (፩ኛ መፅሐፍ)
2. ታሪክና ምሣሌ (፪ኛ መፅሐፍ)
3. የቅኔ ውበት
4. ሮሜዎና ዡልየት
5. የፅውቀት ብልጭታ
6. ጃፓን እንደምን ሠለጠነች?
7. ታላላቅ ሰዎች

ግራፊክ አታሚዎች

ዋጋ40.ፍዐብር

Scanned with CamScanner